# የአዲስ ወግ መድረኮች

ከ2011 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
2015 ዓ.ም

# የአዲስ ወግ መድረኮች

ከ2011 ዓ.ም እስከ 2015 ዓ.ም

የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
**2015 ዓ.ም**

ISBN 978-99990-50-59-3

9 789999 050593 >

ቅንብር፣ አርትዖትና ዝግጅት - የጠቅላዩ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
የዚህ መጽሐፍ ገቢ ለበጎ አድራጎት የሚውል ነው።

# ማውጫ


መቅድም I

## ክፍል አንድ፡ የ2011 ዓ.ም የአዲስ ወግ መድረኮች

1. የሥርዓት እና የተቋማት ግንባታ በኢትዮጵያ 1
1.1 የሕግ የበላይነት በዴሞክራሲ የሽግግር ወቅት 9
1.2 የሀገረ መንግሥት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት 17
1.2.1 ክፍል አንድ 17
1.2.2 ክፍል ሁለት 23
1.3 የምጣኔ ኃብት ሪፎርም መነሻና አቅጣጫ 29

## ክፍል ሁለት፡ የ2012 ዓ.ም የአዲስ ወግ መድረኮች

2.1 መደመር 39
2.2 የሚዲያ ሚና ሐሳቦችን ለማቀራረብ 49
2.2.1 ክፍል አንድ እና ሁለት 49
2.2.2 ክፍል ሦስት፣ ዲጂታል ሚዲያ 57
2.3 የግብርና ዘርፍ ቁልፍ የሪፎርም ርምጃዎች 61
2.4 የሎጅስቲክስ ዘርፍ ሪፎርም 73
2.5 "ዌቢናር" አንድ፣ ፈጠራ በቀውስ ጊዜ 83
2.6 "ዌቢናር" ሁለት ፣ ፈጠራ በቀውስ ወቅት፤ ከታሪክ ምን እንማር? በሥነ ልቦና እንዴት እንጠንክር? 91
2.7 ከሽገር ወደ ሀገር 97

## ክፍል ሦስት፡ የ2013 ዓ.ም የአዲስ ወግ መድረኮች

3.1 የቆላ አካባቢዎች እና የአርብቶ አደር ዜጎች የልማት ጉዞ 109
3.2 ሰላም እና ደኅንነት በምርጫ ወቅት (የሰላማዊ ምርጫ መገለጫዎች እና መስፈርቶች) 117
3.2.1 ክፍል አንድ 117
3.2.2 ክፍል ሁለት፣ በምርጫ ወቅት ሰላምን ለማስፈን ሰላም የሚያንጹ ሀገር በቀል እና ዘመናዊ ተቋማት ሚና 125
3.2.3 ክፍል ሦስት፣ ሐሰተኛ መረጃ በሰላማዊ ምርጫ ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መግታት 131
3.3 በዴሞክራሲ አንድ እርምጃ፣ የ6ኛው ብሔራዊ ምርጫ ምልከታዎች 137

## ክፍል አራት ፡ በ2014 ዓ.ም የአዲስ ወግ መድረኮች


4.1 በአዲስ መንፈስ አዲስ ውል 145

4.2 የጎልውና ጥሪ እና ሀገርን የማዳን ርብርብ 153

4.3 ጎልውናን መጠበቅ፤ ዕድገትን ማዝለቅ 161

4.4 የኑሮ ውድነት መንሥኤዎቹ እና የመፍትሔ ርምጃዎች 169

4.5 ሀገራዊ አምራችነት 175

4.6 ከጽንፎች መሐል ወርቃማውን አማካይ ፍለጋ 181

4.6.1 ክፍል አንድ 181

4.6.2 ክፍል ሁለት የጽንፈኝነት መገለጫዎችና አሉታዊ ውጤቶች 189

4.6.3 ክፍል ሦስት ጽንፈኝነትን የመከላከል ርምጃዎች 197

4.7 ፈተና፣ድል እና ተስፋ 203


## ክፍል አምስት ፡ በ2015 ዓ.ም የአዲስ ወግ መድረኮች


5.1 ሕዝባችን ዐቅማችን 211

5.2 የመደመር ትውልድን መቅረጽ፤ 219

5.3 የክረምት ትጋት የዓመት ልማት 227

# መቅድም

በ2010 ዓ.ም የመጣው የለውጡ መንግሥት የሐሳብ ብልጫ ለማንኛውም አወዛጋቢ የሆኑ ጉዳዮች ፍቱን እንደሆነ በተለያዩ ጊዜያት አመላክቷል። በፖለቲካ ምኅዳሩ ተለምዶ በማይታወቅ መልኩ ለውውይት እና ለሐሳብ ክፍት መሆኑን ያሳየው የለውጡ መንግሥት፤ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ጋር የውይይት መድረኮችን ለሕዝብ እይታ ክፍት በሆነ መንገድ አስተናግዷል። በአንድ ወቅትም፤ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "የኢትዮጵያ ሕዝብ ማስተዋል ያለበት ነገር፤ ወንድም ውንድሙን ገድሎ አያሸነፍም፤ ወንድም ወንድሙን ገፍቶ አያሸንፍም፤ ተቃቅፈን፤ ተባብረን፤ መሸናነፍ ካለም፤ በሐሳብ እና በሐሳብ ብቻ እንዲሆን የበኩሉን እንዲያደርግ ጥሪ ማቅረብ እፈልጋለሁ" ብለው ተናግረዋል።

በ2010ም በዓይነቱ የመጀመሪያ የሆነ 'አዲስ ወግ' የተባለ መድረክ ተፈጠረ። ይህም መድረክ በአንድ ዓመት የለውጥ ጉዞ ወስጥ በኢትዮጵያ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ታሪክ ዙሪያ የተካሄደውን የለውጥ ጉዞ አዎንታዊ እና አሉታዊ ጎኖች ፈትሿል። የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችን እንደ ተናጋሪ እና እንደ ተሳታፊ በመጋበዝ በሼራተን አዲስ ለመጀመሪያ ጊዜ ታልሞ ተካሄደ። በሁለት ቀን ቆይታውም አመርቂ ውጤቶችን አስገኘ። በመዝጊያው ላይ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተገኝተው "መድረኩ ሐሳባችንን ከአደባባይ ወደ አዳራሽ ለመሰብሰብ፤ ጉልበታችንን ከድንጋይና ዱላ ወደ ሐሳብ በማምጣት የተለያዩ ሸክሞቻችንን ጥለን ኢትዮጵያን በትብብር ወደፊት ለመውሰድ ዕድል የፈጠረ ነው" ብለው ተናግረው ነበር።

ይህ የመጀመሪያው መድረክ የአንድ ዓመት የለውጥ ጉዞውን ለመቃኘት ታልሞ የተዘጋጀ ነበር። እንደዚህ ዓይነት የውይይት መድረኮችን የማበራከት አስፈላጊነት በመታመኑ 'አዲስ ወግ - አንድ ጉዳይ' በሚል ወርኃዊ ዝግጅት እና 'አዲስ ወግ ዐቢይ ጉዳይ' በሚል የሩብ ዓመት ተለቅ ያለ መድረክ አዘጋጅቶ ለማስቀጠል የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፕሬስ ሴክረታሪያትም ይህንን ኃላፊነት ወስዶ ቀጠለበት።

የሚዘጋጁት የ"አዲስ ወግ" ውይይቶች፣ የውይይት ባህልንና የሐሳብ የበላይነትን ለማዳበር የታለሙ ናቸው። የሐሳብ ልዩነቶችን ወደ ተምሳሌታዊው ጠረጴዛና አዳራሽ በማምጣት "አዲስ ወግ" ተቃርኗዊ ዕሳቤዎችን ለማቀራረብ፣ የሐሳብ ብዝኃነትን

ለማዳበር እንዲሁም ለነበሩና አዲስ ለተፈጠሩ ችግሮች ፈጠራ የታከለባቸውን መፍትሔዎች ለማበረታታት ታስቦ የሚዘጋጅ ነው።

ይህንን እውን ለማድረግ የ “አዲስ ወግ” ቅርጽ በውይይት የማሳተፍን ተመራጭ መንገድ ይከተላል። ጥልቅ የመስማት እና የመነጋገር ክሂሎትን በተግባር ላይ ማዋልን ይጠይቃል። በተለምዶ እርስ በርስ የምንነጋገርበት እና የምንሰማበትን አካሄድና ልማድ በመተዉ፣ ዕሴቶችን ጨምረው ወደ ዘላቂ መፍትሔ የሚያደርሱንን ፍሬያማ ውይይቶች ማካሄድን ይሻል። በርግጥም እነዚህ ውይይቶች አዳጊ ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ሥርዓትን ለመገንባት አስፈላጊ ቅድመ ሁኔታዎች ናቸው።

በዚህ መጽሐፍ ታድያ የተካተቱት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት አዘጋጅነት ለአምስት ዓመታት ከ2011 እስከ 2015 ዓ.ም. የተካሄዱትን የአዲስ ወግ የሐሳብ ልውውጥ መድረኮችን ሰንዶ ለማስቀመጥ በማሰበ ነው። ውይይቶቹ ከተለያዩ የማኅበረሰብ ክፍሎች የመጡ የተወያዮችን ሐሳብ እና የመንግሥትን ፖሊሲ እና አቅጣጫ የሚያስቃኙ ናቸው። እነዚህ ውይይቶችም በዚህ መልኩ ተሰንደው መቀመጣቸው ለፖሊሲ ግብዓትና ለታሪክ ያግዛሉ ተብለው ይታሰባሉ።

**መልካም ንባብ!**



# ክፍል አንድ፤

## የአዲስ ወግ መድረኮች

## 2011 ዓ.ም

# 1. የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ የሥርዓት እና የተቋማት ግንባታ በኢትዮጵያ

ሚያዝያ 10 ቀን 2011 ዓ.ም




ይህ የመጀመሪያው የአዲስ ወግ የውይይት መድረክ በሚያዚያ ወር 2011 ዓ.ም "የሥርዓት እና የተቋማት ግንባታ በኢትዮጵያ" በሚል ርዕስ የተደረገውይይት ነበር። በውይይቱ የሥርዓት እና የተቋማት ግንባታ ታሪካዊ ዳራ እና አካሄድ በኢትዮጵያ ምን እንደሚመስል ተብራርቷል። ክፍተቶች ተለይተዋል፤ መፍትሔዎችም ተጠቁመዋል። ውይይቱን የመሩት (የቀድሞ) በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቢዝነስ እና የኢኮኖሚክስ ኮሌጅ ተባባሪ ፕሮፌሰር ዶ/ር ፋንታ ማንደፍሮ ናቸው። ዶ/ር ፋንታ በሥርዓትና የተቋማት ግንባታ ላይ ሰፊ የማስተማር፣ የጥናት እና የምርምር ልምድ ያላቸው ሲሆን ሌሎች አራት ባለሙያዎች ደግሞ ለውይይቱ የመነሻ ሐሳብ አቅርበዋል። እነርሱም፡-

1ኛ. ዶ/ር የራስ ወርቅ አድማሴ፣ የፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ (Forum for Social Studies) ዳይሬክተር እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከ36 ዓመት በላይ በምርምርና በማስተማር ያገለገሉ ሲሆን በሥርዓት እና በተቋማት ምንነት ላይ ብሎም በኢትዮጵያ ባለው ታሪካዊ ዳራ ላይ ሐሳብ አቅርበዋል።

2ኛ. ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው - በሞያቸው የኢንዱስትሪ መሀንዲስ (Industrial Engineer) ሲሆኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እና በሌሎች የውጭ ዩኒቨርሲቲዎች ለ39 ዓመታት በመመራመር እና በማስተማር የሠሩ ናቸው። የኢትዮጵያውያን ሥነ-ልቦናዊ ባሕሪይ ከሥርዓትና ተቋማት ግንባታ ጋር ያለው ትስስርአውስተው የተሻለ ሥርዓት እና ተቋም ለመገንባት ምን ዓይነት ባሕሪይ መገንባት እንደሚያስፈልግ ሐሳብ አጋርተዋል።

3ኛ. ወ/ሮ ሕይወት አለማየሁ - በአቅም ግንባታ እና በአመራር ልማት አማካሪ እና የ"ማይንድ ሴት ኮንሴፕት" የሚባል ተቋም ባልደረባ የነበሩ ሲሆኑ በሀገራችን የተቋማት ግንባታ እና የአመራሮች ሚና ላይ ያሉ ክፍተቶችና የመፍትሔ አቅጣጫዎች ላይ ሐሳብ አቅርበዋል።

4ኛ. አቶ በዛብህ ገብረየስ - የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር የነበሩ ሲሆኑ የ"ፓብሊክ ፖሊሲ" እና የ"ፐርፎርማንስ ማኔጅመንት" ባለሙያነታቸው በሙያቸው ከ20 ዓመታት በላይ አገልግለዋል፤ በመንግሥት ተቋማት የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ እየተሠሩ ባሉ ሥራዎች፣ ክፍተቶች እና መፍትሔዎች ላይ ሐሳብ አካፍለዋል ።

## ሥርዓትና ተቋማት በኢትዮጵያ

በውይይቱ መጀመሪያ ላይ የመወያያ ሐሳባቸውን ያቀረቡት ዶ/ር የራስ ወርቅ ሥርዓት ማለት ኅብረተሰቦች ማህበራዊ ሕይወትን ለማሳለጥ አባሎቻቸው ምን ማድረግ እንደሚፈቀድላቸው እና እንደማይፈቀድላቸው የሚደነግጉ ሕጎችን ያቀፈ ነው በማለት አስረድተዋል። እነዚህም ሕጎች አዋጆችን ወይም የታወጁ ደንቦችን ወይም ያልታወጁና ደርዝ የለሽ፣ በረጅም ጊዜ ከሕዝብ የፈለቁ እንደወግ፣ ነውር እና የመሳሰሉትን የሚያቅፉ ናቸው። ሁሉም ማህበረሰቦች የእነዚህ መሰል ሥርዓቶች ባለቤት መሆናቸውን፤ እነዚህ የተጻፉ ወይም ያልተጻፉ በባህል የሚወረሱ ሕጎች እና ወጎች እንደማህበረሰቡ ሁለንተናዊ እድገት የሚሻሻሉ፤ እልፍ ሲልም የሚቀየሩ እንደሆኑ ገልጸዋል ።

የቀድሞዋን ኢትዮጵያ ሁኔታ ሲያስረዱም፤ መንግሥታት በሚያስተዳድሯቸው የሀገሪቱ አካባቢዎች የተለያዩ አዋጆች ያወጡ እና ሥርዓት ያቆሙ ነበር። የዳግማዊ አጼ ምንሊክ ማዕከላዊ መንግሥት ከተቋቋመ በኋላ ግን ደንቦችና እና ሥርዓቶች በመደበኛ መንገድ መውጣት፤ የዘመናዊ ሥርዓት ሕጎች በአዋጅ መታወጅ ጀምረዋል። በዚህ ዘመን በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች የሚያገለግል ገንዘብ፣ የፖስታ አገልግሎት

ሲጀምርም የዘመናዊ ሥርዓት ጅማሬ እንደሆነ፤ በሂደትም የተለያዩ ደንቦች እና አዋጆች ሲወጡ ደንቦችን እና አዋጆችን እንዲያስፈጽሙ የተለያዩ ተቋማት መመሥረት ጀመሩ። ይህ የዘመናዊ ተቋማት ምሥረታ ጅምርም የጣሊያንን ወረራ እንደመልካም አጋጣሚ በመጠቀም ተጠናክሮ እንደቀጠለ አስረድተዋል ።

በኢትዮጵያ ለረጅም ዘመናት የዘለቁት ሃይማኖቶች በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል ስለሚኖር ግንኙነት የሰበኩ እና የሰውን አስተሳሰብ ሲቀርጹ የኖሩ መሆናቸው፤ በሕግ እና በሕዝብ መካከል የሚኖረውን ግንኙነት ያስተማሩ፤ እንዲሁም ለዘመናዊ ሥርዓት እና ተቋማት ግንባታ መልካም አጋጣሚዎች መሆናቸውን አንስተው፤ በሀገሪቱ የሕግ የበላይነት ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ መግባቱ ደግሞ ዋነኛው ተግዳሮት እንደሆነ አሳይተዋል። ሁለተኛው የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው፤ የሥርዓትና ደንብ መኖር ያስፈለገበት ቀዳሚ ምክንያት ሁላችንም በጥሩ ሁኔታ መኖር እንድንችል መሆኑን አንስተዋል። ኢትዮጵያውያን ዘርፈ ብዙ ሥርዓት ወለድ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ያሉብን ሕዝቦች ስንሆን ለእነዚህ ችግሮቻችን እንደአንድ መንስኤ ሆኖ የሚታየው የልቦና ውቅራችን መሆኑን አስረድተዋል። ስለዚህም አብዛኛውን የሀገራችንን ችግር ለመፍታት የብዙ ችግራችን ምንጭ የሆነውን የልቦናችንን ውቅር ማሻሻል ወይም መቀየር ዋነኛው መፍትሔ መሆን እንዳለበት አመልክተዋል። የልቦና ውቅር ሲባል፤ ሰዎች ከውልደት ጀምረው ከአካባቢያቸው የሚማሩትና የአስተሳሰብ ማንነታቸው የሚገነባበት ሂደት ውጤት የሆነው የአስተሳሰብ ሥርዓት ማለት መሆኑንም አስረድተዋል።

ሦስተኛዋ ሐሳብ አቅራቢ ወ/ሮ ሕይወት አለማየሁም ለሥርዓት እና ለተቋም መነሻ የሚሆነው በማህበረሰቡ ውስጥ ያለ ቅቡል ደንብ (norm) እንደሆነ፤ ይህም በተቋማት ላይ በተመሳሳይ የሚታይ ጉዳይ መሆኑን አንስተዋል። በየትኛውም የተቋም ግንባታ ወይም ለውጥ የአሠራር፣ የአደረጃጀት እና የሕግ ማዕቀፍ ለውጥ መደረግ እንዳለበት መታሰብ ያለበት ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በሀገራችን በተቋም ግንባታ ላይ የሚስተዋለው ችግር የተቋማት አደረጃጀት ሕጎች እና ሌሎች የተቋም መሠረተ ልማቶች መሻሻል ብቻ ለውጥ እንደሆኑ ተደርጎ እንደሚታሰብ፤ በዚህም ምክንያት በሰዎች አቅም ላይ የሚሠሩ የለውጥ ሥራዎች ወደኋላ እንደሚቀሩና ትኩረት እንደማያገኙ ገልጸዋል። ይህም ለተቋማት ግንባታ ውጤት አልባ መሆን አንዱ ምክንያት እንደሆነ አስረድተዋል ።

የተቋማት የለውጥ ሂደት በምዕራፍ ተከፍሎ የሚተገበር ስለሆነ ሁሉንም በአንድ ጊዜ

ማጠናቀቅ እንዳማይቻል በማወቅ በትንሽ ሥራና አቅም ተሠርተው ብዙ ውጤት ሊያመጡ ለሚችሉ ጉዳዮች ቅድሚያ መስጠት እንደሚገባ አስረድተዋል። በኢትዮጵያ ያሉ ተቋማት ተልዕኮን አለመወጣት፣ እሴቶችን አለመተግበር፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ ከእዝ ሰንሰለት ማፈንገጥ፣ የሕዝብ ቅቡልነት ማጣት፣ ቁርጠኛ እና የበቁ አመራሮች ያለመገኘት፣ በፖለቲካ ልሂቃን እና በባለሙያዎች መካከል የሚፈጠሩ ጥሩ ያልሆኑ ግንኙነቶች እና ለገጽታ ግንባታ ሲባል የሚቀርቡ ሐሰተኛ ሪፖርቶች፣ ሰዎች በብቃት ሳይሆን በፖለቲካ ውግንና የሚሾሙበት ሁኔታ በስፋት የሚታይባቸው ናቸው በማለት አብራርተዋል።

አራተኛው የውይይት ሐሳብ አቅራቢ ኮሚሽነር በዛብህ ገብረየስ፤ የመንግሥት ሥራ ልዩ ባሕሪይው ከትልቁ ሕገ-መንግሥት እና ከሌሎች ሕጎች የሚወለድ መሆኑና ሲፈጸምም በሕግ አግባብ መሆኑን አንስተው፤ በሥርዓት እና በተቋም ግንባታ ታሳቢ የሚደረገው በአንድ ሀገር ውስጥ የተለያየ ፍላጎት ያላቸው ማህበረሰቦች እንደመኖራቸው የመንግሥት ተቋማት እነዚህን ፍላጎቶች ለማርካት የሚመሠረቱ መሆናቸው እንደሆነ ገልጸዋል። "የመንግሥት የሥራ ውጤት በምን ይለካ?" በሚለው ሌላው የተቋማት ወይም የሥርዓት ግንባታ ወሳኝ ጥያቄ ላይ፤ በቅልጥፍናው፣ ዜጋው የሚፈልገውን አገልግሎት በመስጠት፣ በምቹነት፣ በተገቢ ጊዜ ምላሽ ሰጭነት እና በተልዕኮ ስኬት ወይም መንግሥት ሥራውን በሕግ ሲሠራ እንደሆነ አንስተዋል።

ኮሚሽነሩ ቀጥለውም ባለፉት 12 (ዐሥራ ሁለት ) ወራት ሲቪል ሰርቪሱ በተቋም ግንባታ ላይ የተስተዋሉ ክፍተቶችን፤ ማለትም የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ መዳከም፣ የመልካም አስተዳደር ጉድለት፣ ሌብነት እና የዜጎች የኑሮ ደረጃ መዳከም የፈጠረውን የሕዝብ ብሶት፣ ሕዝቦች ከመሠረታዊ ሰብዐዊ-መብቶች አንስቶ እስከ ሕገ-መንግሥታዊ መብቶች ገፈፋ ሰለባ መሆናቸውን መርምሮ፤ ጉድለቶች ለማረም እና ለውጥ ለማምጣት በተቋማት ግንባታ ሂደት ላይ ለውጦች መደረጋቸውን፣ የሕግ የበላይነትን ማስከበር እና ሰላምን ማረጋገጥ ቅድሚያ ተሰጥቶት የሰላም ሚኒስቴር መቋቋሙን፣ የኢኮኖሚን መዋቅራዊ ሽግግር ለማፋጠን አንዳንድ ኢኮኖሚያዊ ሥራ የሚያሳልጡ ሥርዓቶች እና ተቋማት በአዲስ መልክ የማደራጀት ሥራ መሠራቱን፤ የኢትዮጵያዊነት አስተሳሰብ እንዲያንሠራራ በተቋማት ደረጃም የተሠሩ ሥራዎች መኖራቸውን አሳይተዋል። በተቋማት ግንባታ ሥራ ላይ በተግዳሮትነት የሚታሰበው የመንግሥት ተቋማት ያላቸውን የሰው ኃብት ወደ ሙሉ ብቃቱ የማሳደግ እና ወደው ጤታማ አገልግሎት አሰጣጥ ደረጃ ላይ የማድረስ ሥራ ላይ ያለው ክፍተት ቀዳሚው መሆኑንም አንስተዋል።

# ከተሳታፊዎች የተነሱ ሐሳቦች እና ጥያቄዎች

ከውይይቱ ተሳታፊዎች በሀገራችን የሥርዓትና የተቋማት ግንባታ፣ በመንግሥት አስተዳደር እና በመንግሥት ሠራተኞች ነባራዊ ሁኔታ ላይ የሚታዩትን ጉድለቶች መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎች እና ሐሳቦች በስፋት ተነስተዋል። ከተሰነዘሩትም ሐሳቦች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው።

በኢትዮጵያ የሥርዓት እና የተቋማት ግንባታ የሐሳብ ልውውጦች ላይ ሥርዓት የሚለው ቃል የእንግሊዝኛውን [Institution (ሕጎችን እና ደንቦችን የሚያቀፈውን)] ሐሳብ የሚይዝልን እንደሆነ፤ በተደጋጋሚ (System) በሚል የምንጠቀመው ቃል ደግሞ ሥርዓት የሚለውን እንደማይተካ ተነስቷል። ከሥርዓት እና ከተቋማት ግንባታ ጋር የልቦና ውቅር በሀገሪቱ ለተስተዋሉ ችግሮች መከሰት ከፍተኛ ድርሻ ያለው እንደሆነ ተነስቶ፤ "ይህ ሁኔታ እንዴት ቢለወጥ ነው ለውጥ ማምጣት የሚቻለው?" በሚል በተደረገው ውይይት፤ በኢትዮጵያ ከቀድሞው ዘመን ጀምሮ ሲገነባ የኖረ ጠቃሚ የልቦና ውቅር ያለን ቢሆንም፤ በትምህርት እና በሥራ ባህላችን ውስጥ ያለንን አስተሳሰብ ለማስተካከል በአጭር ጊዜ የለውጥ ንቅናቄ መፍጠር እንደሚገባ፤ በረጂም ጊዜ ደግሞ የትምህርት ሥርዓታችን መመርመር እና መቀየር ይኖርበታል የሚሉ ሐሳቦች ተንጸባርቀዋል።

በሌላ በኩል፤ በተቋማት የለውጥ ሂደት ላይ አመራሩ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው እንዲታወቅና ለውጡን ለማሳካት ከፍተኛ ሥራ እንደሚጠበቅበት፤ ከሠራተኞች ጋር በተያያዘም ለለውጥ ብቁ የሆነ የሰው ኃይል ለመፍጠር መሥራት እንደሚገባ፤ ሠራተኞችን በየትኛውም ጊዜ ማብቃት የሚቻልበት እድል በመኖሩ እሱን መጠቀም ቀዳሚው የተቋማዊ ለውጥ ተግባር ሊሆን እንደሚገባው በውይይቱ ተነስቷል። በመንግሥት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ ክፍተቶች ላይ በተነሱ ጥያቄዎችም፤ ተቋማት የሚሰጧቸው አገልግሎቶች የሕዝብን ፍላጎት እንዳያረኩ ያደረጋቸው ዋነኛ ምክንያት የሠራተኛው የአቅም ውስንነት እንደሆነ ተጠቁሞ መንግሥት ሠራተኞችን ለውጥ ለማሳካት ብቁ እንዲሆኑ የሚያስችል የማብቃት ሥራ መሥራት እንዳለበት፤ በሀገራችን ያለውን የሐሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ሥርጭት እና የብቃት ማነስ ታሳቢ ያደረገ የሠራተኞች ምልመላ ሥርዓት ለመዘርጋት ተግባራት እየተከናወኑ እንደሆነ ተገልጿል።

በመጨረሻም፣ በመንግሥት ተቋማት ውስጥ በጥቅም ላይ በሚውሉ የለውጥ መሣሪያዎች እራሳቸውን እንደለውጥ መቁጠርና በአፈጻጸማቸውም ምክንያት ዝለት እየተከሰተ እንዳለ ተነስቶ የለውጥ መሣሪያዎቹ ለውጡን ሊያግዙ የሚችሉት ሠራተኛው ቅድሚያ ተረድቷቸው ተግባራዊ ሲያደርጋቸው እንደሆነ እና እዚህም ላይ ከፍተኛ ክፍተት እንደሚስተዋል ተገልጿል፡፡ የመንግሥትን ሥራ እና የፓርቲን ሥራ መደበላለቅን አስመልክቶም አሁን ላይ ባለው የለውጥ አስተደዳር ሁለቱን ለመለየት ጅማሬዎች እንዳሉ፤ ነገር ግን ፖለቲካው እና የመንግሥት ሥራ ፍጹማዊ በሆነ ደረጃ ሊለያይ እንደማይችል ታሳቢ ይደረግ የሚለው ሐሳብ በውይይቱ ወቅት ተነስቷል ፡፡

## ማጠቃለያ

በውይይቱ ላይ የሥርዓትን እና የተቋማትን ግንባታ ሂደት ለማሳካት የሚያስፈልጉ መሠረታዊ ሐሳቦች የተነሱ ሲሆን፤ በአሁኑ ወቅት በለውጡ አስተዳደር ለማሳካት እየተሠሩ ያሉት ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተቋማዊነት የተላበሰ አፈጻጸም እና ዘላቂ ውጤት እንዲኖራቸው ማድረግ፤ እንዲሁም የለውጡ ሕጋዊ የአሠራር ሂደቶች በተቋማት ብቸኛ የአሠራር መንገድ እንዲሆኑ ማስቻል ላይ ያተኮረ እንዲሆን የሚጠቁሙ ሐሳቦች የተነሱበት ነበር፡፡ በሁሉም የመንግሥት የአስተዳር እርከኖች ላይ የሚቀመጡ ሠራተኞች የሕዝቡን የአገልግሎት ጥያቄ ማርካት የሚያስችል አቅም ያላቸው እንዲሆኑ ለማብቃት፤ አገልግሎቶችም "ነጻነት፣ እኩልነት፣ ፍትሐዊነት እና የሕግ የበላይነት" የሚሉትን መርሆዎች የሚያረጋግጡ እንዲሆኑ፤ ሠራተኛው እና በየደረጃው ያሉት የመንግሥት አመራሮች ተፈላጊውን ክህሎት፣ የሥራ ተነሳሽነት እና ፍላጎት እንዲኖራቸው የአቅም ግንባታ ተግባራት መሠራት እንዳለባቸው ተገልጿል፡፡ እነዚህን የመንግሥት ተልዕኮዎች በአግባቡ መወጣት የሚችል አዲስ የሰው ኃይል ወደሥራው ዓለም ለማምጣት የሚስችሉ ተግባራትን የፖሊሲ እና የስትራቴጂ መሠረት ባለው መንገድ ተግባራዊ በማድረግ የመንግሥት አገልግሎቶችን የማሻሻል ሥራ መሥራት እንደሚስፈልግ፤ እንዲሁም የተጀመሩትን ሥራዎች ከግብ ማድረስ እንደሚገባ በውይይቱ ወቅት ተነስቷል፡፡

የለውጡ አስተዳደር የተሻሉ ተቋማትን ለመገንባት እያሳየው ካለው ፍላጎት እና ሙከራ አንጻር ወደፊት ሀገርን በበጎ የመቀየር፤ የሀገርን ሰላም እና ደኅንነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ተቋማትን ለመገንባት እየታየ ያለው ጅምር በበጎ የተነሱ ሐሳቦች ሲሆኑ፤ በቀደመው የአስተዳደር ሥርዓት በፓርቲ እና በመንግሥት ሥራ መካከል የነበረውን መደባላለቅ፤ እንዲሁም የፖለቲካ ውግንና ብቻ ሲሰጡ የነበሩትን የሥራ ምደባዎች በማስቀረት ብቃትን ያማከሉ ምደባዎች ይደረጉ የሚሉ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል፡፡ በፓርቲ

እና በመንግሥት ሥራ መካከል ያለው ግንኙነት ገደብ እንዲኖረው የሚያደርግ አሠራር በሁሉም የአስተዳደር ደረጃዎች በተገቢው መንገድ ተፈጻሚ እንዲሆን የሚስችል ስትራቴጅ መከተል እንደሚገባም ተገልጿል።











# 1.1 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ የሕግ የበላይነት በዴሞክራሲ የሽግግር ወቅት

ግንቦት 20 ቀን 2011 ዓ.ም




ይህ ሁለተኛው የአዲስ ወግ መድረክ "የሕግ የበላይነት በዴሞክራሲ የሽግግር ወቅት" በሚል ርዕስ ላይ አተኩሮ የተካሄደ ሲሆን በውይይቱም በመንግስት አስተዳደር እና የመንግስት ሃላፊነቶች ፣ የህግ የበላይነት እንዲሁም የሽግግር ጊዜ ፍትህን የተመለከቱ ከኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተያያዙ ጉዳዩች ላይ ውይይት የተደረገበት ነው። የዚህ መድረክ አወያይ ዶ/ር ዮናስ ተስፋ ናቸው። ዶ/ር ዮናስ የዓለም አቀፍ ሕግ እና እድገት ምሁር ሲሆኑ፤ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች ደግሞ፦

1. ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ - በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፍልስፍና መምህር፣
2. ዶ/ር ጌታቸው አሰፋ - በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ትምህርት ቤት መምህር፤
3. ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ - የጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፤ (የቀድሞ)
4. ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል - የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር (የቀድሞ) ናቸው።

በዚህ መድረክ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በተሳታፊነት ተገኝተው ሐሳብ ሰጥተዋል።

የሕግ የበላይነት ምንነት እና ፍልስፍናዊ አንድምታው

"በፖለቲካ አሳቤ መንግሥት እና የመንግሥት አስተዳደር ቀዳሚዎቹ ናቸው።" ያሉት የመጀመሪያው ጽሑፍ አቅራቢ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ፣ ዘመናዊ መንግሥታት የሚባሉት ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት ያላቸው እና በሉዓላዊ ግዛት ላይ ያረፈ አስተዳደር ያላቸው ናቸው። በዚህ መሠረት መንግሥታት አራት መሠረታዊ ኃላፊነት አለባቸው። እነዚህም፦ የማህበረሰቡን መሠረታዊ ፍላጎት ማሟላት፣ የሀገርን ሁለንተናዊ እድገት ማረጋገጥ፣ የእኩልነት አሠራር መዘርጋት እና የሕዝብን አጠቃላይ ደኅንነት ማረጋገጥ ናቸው። መንግሥት አራተኛውን ኃላፊነቱን ለመወጣት ኃይል የመጠቀም መብት ያለው ሲሆን፤ ይህም በሕግ የተገደበና በሕዝብ ተቀባይነት ያለው መሆን አለበት ሲሉ ማብራሪያ ሰጥተዋል።

ዶ/ር ዳኛቸው በሀገራችን የለውጥ ሁኔታ ላይ በሰጡት አስተያየትም፤ ሕዝቦች የሚያምጹት በበደል መብዛት ብቻም ሳይሆን በመንግሥት መዳከም ምክንያትም ሊሆን እንደሚችል አንስተዋል። የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ መንግሥት በታጠቁ አካላት ላይ ርምጃ ከመውሰድ ይልቅ የማባበልን አካሄድ እየተከተለ መሄዱ ትክክል አለመሆኑንና አስተዳደራቸው የዜጎችን መብት ማክበር ላይ ውጤታማ ሥራ እየሠራ ቢሆንም የሕግ የበላይነትን ሥርዓት በሚያደናቅፍ እና ወደኋላ እንዲመለስ በሚያደርግ መዋቅራዊ የክልሎች ሥርዓት ላይ ግን ትልቁ ችግር እንዳለበት ገልጸዋል።

ሁለተኛው ሐሳብ አቅራቢ ዶ/ር ጌታቸው አሰፋ፣ በ"የሕግ የበላይነት" ምንነት ላይ በሰጡት ሐሳብ "የዜጎችን እና የመንግሥትን ግንኙነት የሚወስን የሕግ ሥርዓት ወይም ተቋም ነው። ይህም ዜጎች እና መንግሥት እንቅስቃሴዎቻቸውን አስቀድሞ በወጣ ሕግ መሠረት ሲፈጸሙ እና ይበልጥ ደግሞ መንግሥት ለሥራው በሕግ ተገዥ መሆን እንዳለበት የሚጠቁም ጽንሰ ሐሳብ እንደሆነ አስረድተዋል። ስለሕግ የበላይነት ሲነሳ አንድን የዜጎችን መብት የማያከብር ሕግ ማክበር እንደሕግ የበላይነት ይቆጠራል? ወይስ ሕጎች የተለየ የይዘት መመዘኛ መስፈርቶች አሏቸው? በሚሉ ሐሳቦችም ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል። ከዚህ ጋር ተያይዞ ሁለት ዓይነት የሕግ አጠቃቀም እንዳለ ጠቁመዋል። የመጀመሪያው በሕግ መግዛት (Rule by Law) የሚባለው፤ መንግሥት ሕግን እንደመግዣ መሣሪያ የሚጠቀምበት (በየትኛውም ሕግ /መብትን የማያከበርም ሊሆን ይችላል) ሲሆን፤ ሁለተኛው የሕግ ገዥነት (Rule of Law) ነው። የሕግ ገዥነት ወይም የሕግ ልዕልና መንግሥት ለሕግ ተገዥ የሚሆንበት ሥርዓት ማለት መሆኑን አስረድተዋል። የሕግ የበላይነት ሥርዓት

አለ ለማለት የሚያስችሉ መስፈርቶች እንዳሉ አንስተው፤ ሂደታዊ የሕግ አወጣጥን የሚመለከቱ፣ ሥነ ሥርዓታዊ እና ይዘታዊ ወይንም ሕጎች ምን ዓይነት ይዘት ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን ያካተቱ ስምንት የተለዩ መስፈርቶች እንዳሉ ገልጸዋል።

የሕግ የበላይነትን በሁለት መልኩ ማየት እንደሚቻል የገለጹት ሦስተኛዋ የውይይት መነሻ ጽሑፍ አቅራቢ ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ፤ አንደኛ ከመንግሥት ኃላፊነት ማለትም የመንግሥት ተግባራት በሚታወቅ ሕግ የሚመሩ ናቸው ወይ? የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ከዜጎች መብት መከበር እና ግዴታ አንጻር ሊታዩ ይችላሉ። በማለት ኢትዮጵያ የሕግ የበላይነትን ከማስከበር አኳያ የት ትገኛለች? የሚለውን ለማሳየት ሞክረዋል። አሁን ያለው የኢትዮጵያ ሁኔታ ሚያመላክተው በሕግ ከመግዛት ወደየሕግ የበላይነት ለመሻገር እየተሞከረ እንደሆነና በዚህ ሂደት ውስጥ ብዙ ባለድርሻዎች ኃላፊነት ቢኖራውም፤ ፍ/ቤቶች ደግሞ የዚህ ሽግግር መሠረታዊ እና ማዕከላዊ ተቋማት መሆን አለባቸው ብለዋል። በዚህም ላይ እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል ። ሌላው የሽግግር ጊዜ ፍትህ ነው። የሽግግር ጊዜ ፍትህ አንድም ከግጭት (የመብት ጥሰት) በኋላ ወይም ደግሞ ከአፋኝ ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲ በሚደረግ ሽግግር ወቅት በመደበኛው የፍትህ ሥርዓት ሊፈቱ የማይችሉ ችግሮች የሚፈቱበት ሥርዓት እንደሆነ፤ አስፈላጊነቱ በጥናት መረጋገጥ እንደሚኖርበት፤ እንዲሁም በምን መንገድ ከሀገራችን ሁኔታ ጋር ታሳቢ ተደርጎ ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት መጠናት እንዳለበት አውስተው፤ ባጠቃላይ ግን የሽግግር ፍትህ ተጠያቂነት፣ ካሳ (ምልክታዊ ሊሆን ይችላል) እና የሕዝብ ተሳትፎ ሊኖሩት የሚገቡ ዋነኛ ጉዳዮች እንደሆኑ ገልጸዋል ።

የሰላም ሚኒስትሯ ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል በመንግሥት ኃላፊነት ላይ አተኩረው ባቀረቡት ሐሳብ መንግሥት ሽግግሩን በተገቢው ለማሳካት እና ኃላፊነቱን ለመወጣት ጥንካሬ ሊኖረው ይገባል። ይህም በተቋማቱ መፈጸም እና የማስፈጸም አቅም እንደሚገለጽ፤ እንደመንግሥት ባለፉት ጊዜያት ዴሞክራሲ ምን ያህል እደቀጨጨ እና ለዚህም ሲባል በዴሞክራሲ እና በመልካም አስተዳደር ላይ ለመሥራት ቅድሚያ እንደተሰጠው አመልክተዋል። የሕግ የበላይነትም ከነዚህ ሁለት ጉዳዮች ጋር ጥብቅ ቁርኝት እንዳለው አስረድተዋል። በዚህ እሳቤ መሠረት የሕግ አስከባሪ ተቋማቶቻችን የተቀረጹበት መንገድ ሚዛናዊነቱን የሳተ እና ወደአንደኛው ጽንፍ የተጠጋ እንደሆነ፤ ይህም ደግሞ የማህበረሰብ ሥነልቦና ውጤት እንደሆነ አስረድተዋል።

በዴሞክራሲና በመንግሥት ጠንካራነት መካከል መደበላለቅ እንዳለ፤ ተቋማት በአፈጻጸማቸው ብዙ ኢ-ዴሞክራሲያዊ የሆኑ ችግሮች እንዳሉባቸው፤ እነዚህን

ችግሮች መቀየር ደግሞ በአንድ ጀንበር የማያልቅ በመሆኑ ተቋማቱን ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ብዙ የሪፎርም ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ አስረድተዋል። ለማሳያነትም በህበረተሰብ እና በጸጥታ ኃይሉ መካከል ያለው ግንኙነት በጥርጣሬ የተሞላ መሆኑን እና ይህም የራሱ መንስኤ እንዳለው፤ ነገር ግን ለውጥ ለማምጣት ብዙ ጥረቶች እየተደረጉ እንደሆነ አንስተዋል።

አሁን ባለው የለውጥ ሂደት ዴሞክራሲያዊ አሠራሮችን ለመተግበር በተከናወኑ ሥራዎች ሳቢያ ብዙ የችግር ቧንቧዎች የተከፈቱ ሲሆን፤ እነዚህን የችግር ምንጮች ለመዝጋት ሕግ የማስከበር ተግባራት በሚሠሩበት ወቅት ችግሮች ሲፈጠሩ መስተዋሉንም አንስተው፤ ለውጡን ለማስተግበር ጊዜ የሚጠይቅ እንደሆነ አስረድተዋል። አክለውም ለውጡ በፖለቲካ፣ በኢኮኖሚ እና በሌሎች ዘርፎች እስኪረጋገጥ ድረስ የሚፈጠሩትን ሁኔታዎች እንዴት ማለፍ እንደሚገባ ህብረተሰቡንም፣ የሕግ አስፈጻሚውንም አካል የማዘጋጀት ሥራ በሚገባ ባለመሠራቱ ምክንያት መንግሥት እንደመንግሥት የሕግ የበላይነትን (ሕግን) በማስከበር ሥራ ላይ በሙሉ አቅም እንዳይሠራ እንዳደረገውም መረዳት እንደሚያስፈልግ ገለጸዋል።
ሰላምን ከማስጠበቅ አኳያ፤ በለውጡ አሉታዊውን ሰላም ወደ አዎንታዊ ሰላም ለማሸጋገር ጥረት እያደረግን ነው። በዚህ ረገድ፣ ግጭቶችን ለማስቆም የተቻለ ቢሆንም መዋቅራዊ የሆኑ ችግሮች ያልተፈቱ በመሆናቸው አልፎ አልፎ የሚከሰቱ ግጭቶች እንደሚስተዋሉ ገልጸዋል። ይህ ማለት ግን መንግሥት የዜጎችን ደኅንነት ማረጋገጥ አልቻለም ማለት እንዳልሆነ፤ ተቀራርቦ ለመሥራት የተደረገው ጥረት መንግሥትን እንደደካማ እና ማባበልን ያስቀደመ እንዳስመሰለው ገልጸው፤ አንድ መንግሥት ጠንካራ ሆኖ ሕግ እያስከበረ ይሄድ ማለት ግን ኃይል እየተጠቀመ አምባገነን ይሁን ማለት እንዳልሆነ አስረድተዋል።

## ከተሳታፊዎች የተነሱ ሐሳቦች አስተያቶች፤ እንዲሁም ምላሾች

ከተሳታፊዎች በተነሳ ሐሳብ ለውጡ እውን ያደረጋቸው ሁለት ነገሮች እንዳሉ ተገልጿል። አንደኛው የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ እና የዜጎችን ነጻነት ማስከበር ነው። በእዚህ ላይ ትልልቅ ስኬቶች አሉ። ሁለተኛው የፌደራሉን አስተዳደር እየተገዳደሩ ካሉ ክልሎች ጋር የሚደረግ ፍትጊያ ነው። በሁለተኛው ላይ መዋቅራዊ የሆነ የፖለቲካ ስሪት ለውጡን ሲገትተው የሚስተዋልበት ሁኔታዎች ዋነኞቹ እንደሆኑ ተነስቷል። በኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ አሉታዊ ትርክቶች እንደሚስተዋሉ ተገልጾ፤ ለዚህ ደግሞ በመንግሥት በኩል ማስተካከያ እውነቶች በተገቢው መንገድ እና ወቅት ሊቀርቡ

እንደሚገባ ተጠቁሟል። የሕግ የበላይነትን ለማረጋገጥ ከሚደረጉ ልዩ ልዩ ተግባራት መካከል ማህበረሰቡ ስለሕግ የበላይነት ያለውን ግንዛቤ እንዲያሳድግ እና በግለሰቦች እና በሕዝብ ደረጃ ሕጎች ሲጣሱ ምን መደረግ እንዳለበት ማስገንዘብ ላይ መሠራት እንዳለበት ሐሳቦች ቀርበዋል ።

ወ/ሮ መዓዛ አሸናፊ ሕግና ሥርዓት መከበር ባለመቻላቸው በዜጎች ላይ ጥቃቶች እየተፈጸሙ ነው በሚል ለቀረበው አስተያየት በሰጡት ምላሽ፤ በሕግ ማስከበር ሰበብ አልፈን ወደመጣነው የአፈና ሥርዓት እንዳንመለስ መንግሥት ርምጃዎቹን በጥንቃቄ ሊያደርግ ይገባል ሲሉ አስተያታቸውን ሰጥተዋል። ልዩነትን ከመፍታት አኳያ የኢትዮጵያውያን ባህል ልዩነትን የሚያስተናግድባቸው እሴቶች ያሉት ቢሆንም፤ በአሁኑ ዘመናዊ አኗኗራችን ግን መሰል እሴቶቻችን በጥቅም ላይ ሲውሉ እንደማይታይ አንስተዋል።

የሰላም ሚኒስትሯ ወ/ሮ ሙፈሪያት (የቀድሞ) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያውያን በታሪክ ያለፍንባቸው የፖለቲካ ሂደቶች በአሉታዊ ሁነቶች የተሞሉ ናቸው። በመሆኑም እነዚህን ክፍተቶች በአወንታዊ መንገድ አርመን ሀገራችንን መለወጥ ይጠበቅብናል። የኢትዮጵያዊነት፣ የብሔርተኝነት እና የዴሞክራሲ መርሆዎችን በጋራ ማስቀጠል እንዲቻል ጽንፈኛ አስተሳሰብን፣ ጽንፈኛ ብሔርተኝነትን ማስወገድ እንደሚጠበቅብን አሳስበዋል። እነዚህን ነገሮች ተግባራዊ ለማድረግም ማህበረሰቡ፣ ልሂቃኑ እና ማህበራት ለሕገ መንግሥታዊ ሥርዓት እና ለሕግ የበላይነት መከበር በጋራ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል ። ለውጡ የቆዩ ጠንካራ ነገሮችን ለማስቀጠልና መሻሻል ያለባቸውን ነገሮች እያሻሻሉ ለመሻገር እንደመሆኑ ለውጥ በሚያስፈልጋቸው የጸጥታ ተቋማት ላይ (ፖለስ፣ መከላከያ እና ደኅንነት) ተቋማት ላይ ተግባራዊ እየተደረገ እንደሆነ፤ በዚህም በሕዝቡ እና በጸጥታ ተቋማት መካከል መተማመን ለመፍጠር የዶክትሪን ማሻሻያ እየተሠራ እንዳለ ተናግረዋል።

በክልሎች እና በፌዴራል ፖሊስ መካከል ያለውን ግንኙነት ለማሻሻልም በትጥቅ፣ በዩኒፎርም እና በሥርዓት ሊኖር የሚገባውን ደረጃ ያገናዘበ ለውጥ በጥልቀት እየተዘጋጀ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በሂደት ወደተፈጻሚነት እንደሚገባ ጠቁመዋል። ሕግ የማስከበር ሥርዓቱን ለማሻሻልም የኃይል አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ሥራ ላይ መዋሉን ገልጸዋል። እነዚህ ሁሉ ተግባራት ባጠቃላይ የተዳከመውን የሰላም ባህል እያጠናከርን አንድም ዜጋ እንዳይሞት እና የመብት ጥሰት እንዳይደርስበት ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነ በመግለጽ ተጨማሪ ሐሳባቸውን አካፍለዋል።

በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ ሐሳባቸውን የሰጡት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በበኩላቸው መንግሥት ሕጋዊ ሕግ አስከባሪ ነው። ለዚህም ሁለት መሠረታዊ አቅሞች አሉት በማለት እነሱም የሚያስፈጽምበት የሕግ አውድ እና የሚያስፈጽምበት ተቋማት እንደሆኑ አስቀምጠዋል። ከሕግ የበላይነት አኳያ "የትኞቹን ሕጎች ነው ለመግዣነት የተጠቀምንባቸው?" በሚል በመለየት የማሻሻል ሥራ መሥራት ሲቻል፤ መንግሥት ሕጋዊ ሕግ አስከባሪነቱን ማረጋገጥ እንደሚቻል፤ እዚህ ላይም ከዓመት በፊት የሰላም እና የደኅንነት ተቋማቱን የመንግሥት መግዣ ናቸው ብለን ከከሰስን በኋላ በነዚህ ተቋማት ላይ ምንም ማሻሻያ ሳናደርግ ለውጥ መጠበቅ ልክ እንዳልሆነ እና የሚደረጉ ማሻሻያዎች ጊዜ የሚፈልጉ መሆናቸውን አብራርተዋል። በተጨማሪም፤ የተቋማት መለወጥ ማለት ነባሩን ኃይል በአዲስ በመተካት ሳይሆን የሰውን አስተሳሰብ በመቀየር ነው ለውጥ ማምጣት የሚቻለውና መታገስ እና ጊዜ መስጠት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል ።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በተጨማሪም፤ መንግሥት ታጋሽ የሆነው በእጁ ላይ ብዙ ኃይል በመኖሩ ምክንያት እንደሆነና ኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲን የሰማን እንጂ መኖር ያልጀመርን ሕዝቦች እንደመሆናችን ለዚህም የልምምድ ጊዜ ያስፈልጋል በማለት አስረድተዋል። ይህንንም የትዕግስት ልምምድ በብስለት መንግሥት እራሱን ዝቅ አድርጎ ሕዝቡን እና ምሁራንን በማማከር ለጥቂት ዓመታት መምራት የሚቻል ከሆነ ዴሞክራሲን መትከል የሚያስችል ስኬት ሊሆን እንደሚችል፤ ይህንም ለማሳካት መደመር እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል ።

## ማጠቃለያ

በዚህ የአዲስ ወግ መድረክ ላይ ውይይት የተደረገው በሽግግር ወቅት የሕግ የበላይነት ምን መመሰል አለበት በሚሉና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ እንደመሆኑ፤ ሽግግሩ የሕግ የበላይነትን ከማስከበር አኳያ እየሄደ ያለበት መንገድ በሕግ ከመግዛት ወደየሕግ ገዥነት (የሕግ የበላይነት ) እንደሆነ የተለያዩ ማሳያዎች ተነስተዋል። በዚህ ሂደት በጸጥታ ተቋማት ውስጥ ለውጦች እየተደረጉ እንደሆነ እና በፊት ከነበሩ የአሠራር ሂደቶች እና ልምምዶች አንጻር ከተቋማቱም በኩል ከህብረተሰቡም በኩል በለውጡ ሂደት መደናገር እንደተስተዋለ ተገልጿል። ለውጡ ለዴሞክራሲያዊ ልምምድ ሲባል የፈጠራቸውን ነጻነቶች ያለአግባብ በሚጠቀሙ ኃይሎች በአንዳንድ ቦታዎች ላይ የሚፈጠሩ ችግሮችን የሕግ የበላይነትን የሚያስከብሩ ርምጃዎች ያለመወሰዳቸው መንግሥትን እንደደካማ የሚያሳዩ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ እንደሆነም በውይይት ተነስቷል።

በዚህ ወቅት በኢትዮጵያ ውስጥ እየተስተዋለ ካለው የብሔርተኝነት አሳቤ ጋር በተያያዘም እጅግ የበዙ የተበደልኩ ትርክቶች የሚሠራጩ በመሆናቸው፤ በኢትዮጵያዊነት አሳቤ ላይ እና የሕግ የበላይነትን በማስከበር አኳያ አደጋ እየፈጠሩ እንደሆነ፤ ለእነዚህ ከተለያየ አቅጣጫ የተለያየ ዓላማ አንግበው ለሚነሱ ትርክቶች የማስተካከያ እርምት በተገቢው መንገድ እየቀረቡ ባለመሆኑ በሂደት የለውጡን ስኬታማነት የሚገዳደሩ ትርክቶች ሊፈጠሩ ይችላሉና በዚህ በኩል መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ መሥራት እንዳለበት ማሳሰቢያዎች ተሰጥተዋል ፡፡













# 1.2 የአዲስ ወግ አብይ ጉዳይ፤ የሀገረ መንግሥት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት

ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ድሬ ዳዋ

## 1.2.1 ክፍል አንድ

ይህ በሀገረ መንግሥት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት ላይ ያተኮረ የ"አዲስ ወግ" ፕሮግራም ለመጀመሪያ ጊዜ ከአዲስ አበባ ውጭ በድሬ ዳዋ ከተማ ተዘጋጅቷል። በዚህ ፕሮግራም መክፈቻ ላይ አቶ ከድር ጃዋር በምክትል ርዕሰ መስተዳደር ማዕረግ የንግድና ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ኃላፊ (የቀድሞ) የመክፈቻ ንግግር አድርገዋል። በንግግራቸውም የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ይህንን መድረክ በድሬ ዳዋ ከተማ በማዘጋጀቱ ምስጋና አቅርበው የድሬ ዳዋ ከተማ ብዙ ማንነት ያላቸው ሕዝቦች በፍቅር የሚኖሩባት ከተማ መሆንዋን፤ ይህም ፍቅርና የአኗኗር ዘይቤ በሕዝቦች መግባባት ላይ የተመሠረተ እንደሆነ ገልጸዋል። ውይይቱ ለሀገር ግንባታ መሠረት የሚሆኑ ሐሳቦች የሚነሱበት እንዲሆንም መልካም ምኞታቸውን ገልጸዋል።

የፕሮግራሙ ልዩ እንግዳ "የአዲሲቱ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ" የተባለው የሰብዓዊ መብት ንቅናቄ መሥራች አቶ ኦባንግ ሜቶ ድርጅታቸው ኢትዮጵያ ሰዎች ከብሔራቸው፣ ከቋንቋቸው እና ከሃይማኖታው ይልቅ በሰውነታቸው የሚከበሩባት ሀገር እንድትሆን እንደሚሠራና ሁላችንም ነጻ ካልወጣን ነጻ መውጣት አንችልም ብሎ እንደሚያምን ተናግረዋል። ኢትዮጵያውያን በተለይ ደግሞ የፖለቲካ ልሂቃን በመነጋገር ቀድመው የተሠሩ ስህተቶችን ማረም እና የወደፊቷ ኢትዮጵያ ድንጋይ የማይወረወርባት እና የሐሳብ ፍትጊያ ባህል፤ ያደረገ ፖለቲካ ልማድ የዳበረባት እንድትሆን እንዲሠሩ ጥሪ አስተላልፈዋል ።

በዚህ አዲስ ወግ ፕሮግራም ሦስት የውይይት መነሻ ጽሑፎች ቀርበዋል።
እነዚህም፦

- የብሔር ግንባታ ውጣ ውረድ በኢትዮጵያ፣ በዶ/ር ሰሚር የሱፍ
- ጦር የሰበቀ እና ሰላም ያነገበ የፖለቲካ ፍልስፍና፣ በዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ
- ብሔራዊ መግባባትን በማስፈን ሀገረ መንግሥትን ለማሳለጥ የመንግሥት ሚና በዶ/ር ኮንቴ ሙሳ ናቸው። የውይይቱ መሪ ደግሞ ጋዜጠኛ ጌትነት ታደሰ፣ የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ሥራ አስፈጻሚ ናቸው።

የመጀመሪያው ጽሑፍ አቅራቢ ዶ/ር ሰሚር የሱፍ በቅድሚያ የብሔር ግንባታ (Nation Building) እና የንዑስ ብሔር ግንባታ (Ethnic Nation Building) መካከል ያለውን ጉዳይ እና ፍትጊያ አንስተዋል። በዚህም፣ የ"ብሔር ግንባታ" ማለት በሰዎች መካከል ወጥ የሆነ ሁሉንም ማስተሳሰር የሚችል ማንነት እንዲኖር የሚደረግበት የማንነት ግንባታ ሂደት መሆኑን አስረድተዋል። በብሔር ግንባታ የገጠመው ተግዳሮት የመንግሥታዊ ብሔር ግንባታ ለሁሉም ሰው እኩል እንደብሔር ግንባታ ላይታይ መቻሉ ነው። ለአንዱ የብሔር ግንባታ የሆነው ለሌላው እንደብሔር ክስመት የሚቆጠርበት ሁኔታ ሊፈጠር ስለሚችል ይህን መሰል ሀኔታ ውስጥ የገቡ ሰዎች መንግሥታዊውን የብሔር ግንባታ የሚገዳደር የንዑስ ብሔር ግንባታ በሚጀምሩበት ጊዜ መንግሥታዊ ብሔር ግንባታ በተቃራኒው የክስመት አደጋ ስለሚጋፈጥ በሁለቱ ወገኖች ትንቅንቅ በመደረጉ የመንግሥታዊው የብሔር ግንባታ ሂደት የማይሳካበት ሁኔታ ሲፈጠር ተስተውሏል። ከዚህ ሁኔታ በመነሳት አንዳንድ ሀገራት ሁሉንም አካታች የሆነ የፖለቲካ ሥርዓት ለመዘርጋት ተገድደዋል። ሲሉ ዓለም አቀፉን ሁኔታ አሳይተዋል ።

ዶ/ር ሰሚር በኢትዮጵያ በንጉሱ እና በደርግ አስተዳደር ወቅት መንግሥታዊ ብሔር ግንባታ ዋነኛው የመንግሥት ሥራ ሆኖ መቆየቱን አስታውሰው፤ ነገር ግን አልተሳካም ብለዋል። በዚህም፣ በኢትዮጵያ ፖለቲካ፣ ታሪክ፣ ማንነት እና መጻኢ እድል ላይ መግባባት አለመኖሩን እንደማሳያነት አቅርበዋር። መንግሥታዊው የብሔር ግንባታ ያልተሳካውም ተገዳዳሪ የሆኑ የንዑስ ብሔር ግንባታዎች በመፈጠራቸው እንደሆነ አቅርበዋል። "እነዚህ ንዑስ ብሔር ግንባታዎች ለምን ተነሱ?" ለሚለውም አንደኛ፣ የጣልያን የቅኝ ግዛት አስተዳደር ከኢትዮጵያዊነት የተለየ ኤርትራዊ ማንነት እንዲፈጠር ማድረጉ፣ ሁለተኛ፣ ዓለም አቀፋዊ የጸረ ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ የሚደረግበት ዘመን ስለነበር በወቅቱ ልሂቃን ሐሳቡን ከንዑስ ብሔራዊ ማንነታቸው ጋር አስተሰስረው መንቀሳቀሳቸው እና ሦስተኛው፣ በማርክሲዝም ሌኒንዝም እንቅስቃሴ ሳቢያ ከፊውዳሊዝም ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ የታሰበው ኢትዮጵያዊ ማንነት እንደአድሃሪ በመቆጠሩ ምክንያት መሆኑን አብራርተዋል። መንግሥታዊ ብሔር ግንባታ የብሔር ክስመት ስጋት ተደርጎ በመቆጠሩ ልሂቃን ወደሕዝባቸው በመሄድ ቋንቋን እና ታሪክን መሠረት ያደረገ ትምህርት በማስተማር እና እንቅስቃሴ በማድረግ ወደፖለቲካ ትግል በመግባታቸው በተቃራኒው መንግሥታዊው ብሔር ግንባታ የመክሰም አደጋ ስለተጋረጠበት በሁለቱ የአስተዳደር ሥርዓቶች መንግሥታዊ ብሔር ግንባታ ሳይሳካ እንደቀረ አስረድተዋል።

ዶ/ር ሰሚር ቀጥለውም ኢሕአዴግ ወደ ሥልጣን እንደመጣ የኢትዮጵያ ብሔርተኝነት እንቅስቃሴ ከመንግሥታዊ ኃላፊነት ወደ ሕዝብ ኃላፊነት እንደተሸጋገረና አንዳንድ የኅብረተሰብ ክፍሎች እንዲሁም ግለሰቦች ኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት እንቅስቃሴ ማጋጋል ቢጀምሩም መንግሥት ንዑስ ብሔርተኝነት የሚፋፋበትን ተቋማት በማጎልበት የንዑስ ብሔር ግንባታ የሚጠናከርበት መንገድ ማመቻቸት ቀጠለ። ይህም በኢትዮጵያ ብሔርተኝነት እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ ለውጥ የፈጠረ እንደነበር አስረድተው፤ የተፈጠረው ሁኔታም የሁለቱም ዓይነት የብሔርተኝነት እንቅስቃሴዎች በራሳቸው መንገድ እንዲጠናከሩ እና እንዲፋፋሙ ያደረገ ክስተት እንደነበር ተናግረዋል። አክለውም ሁለቱም ወገን ከኢሕአዴግ ጋር ፍልሚያ ውስጥ ነበሩ። ንዑስ ብሔርተኞችም እርስ በርሳቸው በክልል ወሰን፣ በግጦሽ መሬት እና ክልሎችን በመቆጣጠር ጉዳዮች ምክንያት ፍልሚያ ውስጥ እንደነበሩ አስታውሰዋል።

የብሔርተኞችን ፍልሚያ ሲያስረዱም፤ ምንም እንኳን በሦስቱ ወገን የተጠላለፈ ፍልሚያ ሲደረግ ቢቆይም (ሦስተኛው ወገን የኢሕአዴግ መንግሥት ነው) የፖለቲካ ሥርዓቱ ጠንካራ ቁጥጥር የነበረው እንደመሆኑ የብሔርተኝነት ፍልሚያው የመንግሥታዊ ሥርዓቱን ማናጋት ሳይችል የቆየ እንደነበር እና ከ27 (ሃያ ሰባት) ዓመቱ የፖለቲካ ጉዞ በኋላ በዳግማዊ ኢሕአዴግ ጊዜ ግን መንግሥታዊ ቁጥጥሩ ሲላላ የብሔርተኞች ፍልሚያ ገንፍሎ በመውጣት ኢትዮጵያ ያልተገመተ እልቂት እና መፈናቀል እንደገጠማት፤ እንዲሁም የኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ዋነኛ አንቀሳቃሽ የነበሩ አካባቢዎችም በአብዛኛው ወደንዑስ ብሔርተኝነት እንዲሸጋገሩ ያደረገ ሁኔታ መፈጠሩን አስረድተው ይህ ሁሉ ትንታኔ ያሚያሳየን በኢትዮጵያ መንግሥታዊ ብሔር ግንባታ እንዳልተሳካ ነው ሲሉ ሐሳባቸውን አቅርበዋል።

በመጨረሻም፣ እንደመፍትሔ ሊወሰዱ የሚገባቸውን ሐሳቦች ኢትዮጵያን የመሰሉ ብሔር ተኮር ክፍፍል ያለባቸው ሀገሮች ከብሔር አስተሳሰብ ከፍ ብለው ሕዝቦችን ሊያስተሳስሩ የሚችሉ ተቋማት እንደሚያስፈልጓቸው አሳስበዋል። ለዚህም ስኬት ሲባል እርስ በርስ ከሚቃረን የማንነት እሳቤ ወደድርብ ማንነት (Nested Identity) እሳቤ መሸጋገር ያስፈልጋል ነው ሲሉ አሳስበዋል። ይህንንም ለማድረግ አንደኛ፣ የየትኛውም የብሔር አስተሳሰብ አቀንቃኝ ስንሆን/ስንደግፍ እና የብሔር ግንባታ ስናከናውን ለሌላው ብሔር አስተሳሰብ የክስመት ስጋት እንዳንሆን መጠንቀቅ እንደሚገባ፣ ሁለተኛ፤ የእኛን ብሔር ግንባታ ስናከናውን ሌላውን ሊጨምር የሚችል እሴት፣ ተቋም፣ መርሀ እንዲፈጠር በማድረግ በጋራ ለመኖር የሚያስተሳስሩን ነገሮች

እንዲኖሩ መሥራት እንደሚገባ እና ሦስተኛ፣ ሁሉን አቀፍ ፊርጀ ብዙ ውይይት ማድረግ እንደሚገባ በመጠቆም ሐሳባቸውን አጠቃልለዋል።

ሁለተኛው የውይይት መነሻ ጽሑፍ አቅራቢ ዶ/ር ዳኛቸው አሰፋ "ጦር የሰበቀ እና ሰላም ያነገበ የፖለቲካ ፍልስፍና" በሚል ርዕስ ባቀረቡት ሐሳብ፣ በፖለቲካ እና በፖለቲካ ሥርዓት በኩል ትልቅ ልዩነት እንዳለ አስረድተዋል። በዚህም፣ የፖለቲካ ሥርዓት በይዘትም ሆነ በእቅድ ከፖለቲከኛው በላይ እንደሆነ ገልጸው፣ ይህም ማለት ፖለቲካኛው ምንም ያህል ኃያል ቢሆን ከፈጠረው የፖለቲካ ሥርዓት በላይ መሆን እንደማይችል አስረድተዋል። በምሳሌነትም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ከፊውዳሉ ሥርዓት በላይ መሆን እንደማይችሉ አንስተዋል። ሌሎች የፖለቲካ ፍልስፍና ሐሳቦችንም በምሳሌነት ያቀረቡ ሲሆን፤ ሁለት ዓይነት የፖለቲካ አካሄዶች እንዳሉና እነሱንም "ጦር የሰበቀ" እና "ሰላም ያነገበ" ፖለቲካ በሚል ሊታዩ እንደሚችሉ አስረድተዋል።

የመጀመሪያው ጉልበት ምንጊዜም ተቃዋሚን፣ ተገዳዳሪን ማንበርከኪያ እንደሆነ እንደሚያምን፤ ትክክልነትም ከጉልበት ብቻ እንደሚመነጭ እንደሚያምን፤ እንዲሁም ግጭትን ለማስወገድ ከውይይት ይልቅ እስከሞት ድረስ የሚደርሰው የጉልበት ትግል እንደሆነ የሚያምን የፖለቲካ አካሄድ መሆኑን ገልጸዋል። ሁለተኛው ሰላምን ባነገበው የፖለቲካ መንገድ ደግሞ ውይይትና ድርድር የበላይነት ያላቸው የግጭት መፍቻ መንገዶች እንደሆኑ ያምናል። ሥርዓት ያላቸው የግጭት መፍቻ መንገዶችን ጥቅም ላይ ያውላል። በጣም ውስን በሆኑ ሁኔታዎች ምናልባት ጉልበት ሊጠቀም የሚቻልበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል።

ዶ/ር ዳኛቸው "ጦር የሰበቀ" ፖለቲካ ሥርዓት የሚከተሉ ጦርነትን አንድ የፖለቲካ ማስፈጸሚያ መንገድ ነው የሚል እምነት እንዳላቸው እና የፖለቲካ ሂደቱ "ወዳጅ እና ጠላት የሚለይበት ሜዳ" ነው የሚል እሳቤ እንዳላቸውም አስረድተዋል። በተጨማሪም፣ ማክስ ዌቨር የተባለው ሰው ከሞራሊቲ አንጻር የፖለቲካ ሂደቶችን "የኃላፊነት ፖለቲካ" እና "ፍጹማዊ ፖለቲካ" በሚል እንደከፈለው አንስተው ሲያስረዱም፤ የኃላፊነት ፖለቲካ ያለበትን ሁኔታ ያጤነ፤ ሊሆን የሚገባውን እና የማይሆነውን ለይቶ መከውን አለበት። ከግብ ለመድረስ የሚኬድበት መንገድ ምክንያታዊ ሊሆን ይገባል የሚል እሳቤ አለው ብለዋል። ፍጹማዊ ፖለቲካ ደግሞ፣ "ግብህን ለማሳካት የፈለግኸውን መንገድ መጠቀም አለብህ" የሚል እና ጥያቄ የሚከለክል ሥርዓት እንደሆነ አብራርተዋል። ይህንንም ከሀገራችን የፖለቲካ ሁነቶች ጋር በማያያዝ አስረድተዋል ።

ቀጣዩን የውይይት መነሻ ሐሳብ ያቀረበት ዶ/ር ኮንቴ ሙሳ ናቸው። የእርሳቸውም ርዕስ "ብሔራዊ መግባባትን በማስፈን ሀገረ መንግሥትን ለማሳለጥ የመንግሥት ሚና" የሚል ነው። በዚህም፣ የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶቻቸው ከተሟሉላቸው በኋላ አብሮ ለመኖር የሚያስችል የጋራ ሕልም እንዲኖራቸው መሥራት እንደሚገባቸው እና ብሔራዊ መግባባት ሰዕብናን መሠረት ያደረገ መሆን እንደሚገባው ገልጸዋል። ይህም በሁለቱ ታላላቅ ሃይማኖቶች አስተምሮም ያለ ሐሳብ እንደሆነ ጠቁመው፤ የጋራ ፍላጎት ለማስቀጠል እንዲችል ማህበራዊ ውል (Social Contract) ላይ መድረስ የተለመደ እንደሆነ አንስተዋል። በኢትዮጵያ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ የሚስተዋሉ ክፍተቶችን እና መንግሥትም ሊተገብራቸው የሚገቡ ነጥቦችንም አስቀምጠዋል።

በቅድሚያ ያነሱት አሳታፊነት ነው። ቀደም ሲል አሳታፊ የፖለቲካ ሥርዓት እንዳልነበር አስታውሰዋል። በአሁኑ ሰዓት ካለፈው ጊዜ በተወሰነ መልኩ የተሻለ አሳታፊነት ይታያል ብለዋል። በዚህም መሐል እና ዳር (ታዳጊ) በሚል ልዩነት የሚደረግ ፍትጊያ ማስቀረት ተገቢ እንደሆነ ጠቁመዋል። በሁለተኛ ደረጃ ፍትሐዊ የኃብት እና የሥልጣን ክፍፍል በመንግሥት ሥርዓት ውስጥ እንዲኖር ካልተደረገ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ለማሳካት አስቸጋሪ እንደሚሆን አስረድተዋል። በሦስተኛ ደረጃም የሕግ የበላይነትን ማስከበር፣ ምንም እንኳን ሕግን ማስከበር የመንግሥት ብቻ ኃላፊነት ባይሆንም ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ወሳኙ እንደሆነ ገልጸዋል። በአራተኛ ደረጃም መተማመንን መገንባት እንደሆነ አንስተው፤ በምንገነባው መንግሥት ላይ እምነት ከሌለ መንግሥት መገንባት እንደማይቻል አስረድተዋል። በተጨማሪም፣ ጠንካራ ተቋማት መገንባት የሚገባው ማህበራዊ ፍትህን ለማስፈን እንደሆነ፣ ማህበራዊ እርቅን ለማሳለጥ የሲቪክ ማህበራትንና ባህላዊ ተቋማትን ከበፊቱ በበለጠ መጠቀም እንደሚገባ፣ ፍትህን፣ ኃብትን፣ ሥልጣንን ያላከፋፈለ መንግሥት የቀጣይነት ስጋት እንደሚያጋጥመው፤ እንዲሁም የመንግሥት ኃላፊዎችም ከተገልጋይ አመራርነት ወደአገልጋይ አመራርነት እራሳቸውን ካልለወጡ የሀገረ መንግሥቱን ግንባታ ለማሳካት አስቸጋሪ እንደሚሆን አብራርተዋል።

በመጨረሻም የውይይቱ ተሳታፊዎች የተለያዩ ጥያቄዎች ያቀረቡ ሲሆን፤ ሦስቱም ሐሳብ አቅራቢዎች ምላሽ ሰጥተዋል። በዚህም፣ ዶ/ር ዳኛቸው ሁሉም የፖለቲካ ሥርዓቶች ዋነኛ ማስፈጸሚያ መንገዳቸው የሠለጠነ ውይይት መሆን እንደሚገባው ተናግረዋል። በመቀጠልም ዶ/ር ሰሚር በመጀመሪያ ደረጃ ገለልተኛ የሆነ ሀገረ መንግሥት መገንባት ሐሳብ ላይ ገለልተኛ ሀገረ መንግሥት በመገንባት ሌሎች

የብሔርተኝነት አስተሳሰቦች እንዲቀልጡ ማድረግ እንደሚቻል አንስተው፤ ይህንም ለማድረግ አንደኛ የሚገነባው ሀገረ መንግሥት ከባህል፣ ከታሪክ የጸዳ እንዲሆን በማድረግ፤ ሁለተኛ ሁሉንም አካታች የሆነ ሀገረ መንግሥት መገንባት ሲቻል እንደሆነ አስረድተዋል። የመጀመሪያውን አማራጭ ለመተግበር የሚያስችሉ የአስተዳደር ዓይነቶችም አንደኛ ሪፐብሊካኒዝም (Republicanism) ነው። ይህ ሥርዓት ማንነት የግል ጉዳይ እንዲሆንና በአደባባይ አንድን ሕዝብ የሚገልጽ የጋራ አንድ ማንነት ገንኖ እንዲወጣ የሚያደርግ፤ በቱርክ እና በፈረንሳይ የተሞከረ ሥርዓት እንደሆነ አሳይተዋል። ሁለተኛው የሊበራል ብሔርተኝነት (Libral Nation-alism) መሆኑን ጠቁመው ይህም በግለሰቦች መልካም ፈቃድ ላይ የተመሠረተ ሀገራዊ ባህል የሚል እሳቤ ያለው ሲሆን፤ በአሜሪካ ሲተገብር የተሰተዋለው ነው ሲሉ ዶ/ር ሰሚር አስረድተዋል ።

አካታች ባህልን መገንባት በሚሉት ወገን ደግሞ የሚቀርቡት አማራጮች የመጀመሪያ ኮንሴንሴሽናሊስም (Consociationalism) ነው። ይህም ከተለያዩ ብሔሮች የተወጣጡ ልሂቃን የሚያቋቁሙት መንግሥት እንዲኖር የሚያደርግና ሁሉም ክልሎች በራሳቸው ልሂቃን እንዲተዳደሩ የሚያደርግ ሥርዓት ነው። እስካሁንም በሊባኖስ እና በቦስኒያ የተሞከረ እንደሆነ ጠቁመዋል። ሁለተኛው ደግሞ የመጀመሪያው ለንዑስ ብሔር ግንባታዎች ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቷል፤ ሀገራዊ ብሔርተኝነትን ያዳክማል ከሚል ትችት የተነሳ ሲሆን ሴንትርፒታሊስም (Cen-tripetalism) የሚል ስያሜ አለው። እንዲህ ዓይነቱ ሥርዓት ቋንቋን በሚመለከት አካታችነት አለው። ክልሎች ሲመሠረቱም እያንዳንዱን ብሔር በተለያየ ክልሎች ውስጥ እንዲካለል በማድረግ ንዑስ ብሔርተኝነት ለማዳከም እና ሀገራዊ ብሔርተኝነት እንዲዳብር የሚያደርግ የፖሊሲ ሐሳብ በመያዝ መሆኑን አሳይተዋል። በኢትዮጵያም እነዚህ ሁሉ የፖሊሲ አማራጫች ያሉ ሲሆን “የትኛው ይሻለናል?” የሚለውን በውይይት መወሰን እንደሚገባ አሳስበዋል።

## 1.2.2 ክፍል ሁለት

ሐምሌ 15 ቀን 2011 ዓ.ም ድሬ ዳዋ

የሀገረ መንግሥት ግንባታና ብሔራዊ መግባባት በሚለው የአዲስ ወግ ርዕስ ክፍል ሁለት ከበፊቱ የቀጠሉ ርዕሰ ጉዳዮች የተዳሰሱበት ሲሆን በዚህም "በብዙ ጉዳዮች ላይ እንደማንግባባ ይታወቃል። የማንግባባው ለምንድን ነው? እንዴትስ ነው መግባባት የሚቻለው? በምን በምን ጉዳዮች ላይ በምን መልኩ መግባባት ይገባናል?" እንዲሁም፣ "የማንግባባቸውን ጉዳዮች እንዴት ነው ማስተናገድ የሚቻለው?" የሚሉትን ጥያቄዎች የተንተራሱ ሐሳቦች ቀርበዋል። በውይይቱም ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሤ "የሀገረ መንግሥትና የሰላም ግንባታ" በሚል ርዕስ እንዲሁም የድሬ ዳዋ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶ/ር ያሬድ ማሞ "ብሔራዊ ማንነት እና ልዩነት አቃፊ ሥርዓት ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አካሄድ" በሚሉ ርዕሶች የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅርበዋል። የውይይቱ መሪ ጋዜጠኛ ታምርአየሁ ወንድማገኝ ነው።

በመጀመሪያ ወ/ሮ የትነበርሽ ንጉሤ የሀገረ መንግሥት እና የሰላም ግንባታ በሚለው ርዕስ ዙሪያ መነጋገር መቻላችን ትልቅ ስኬት ነው ብለዋል። ይህን እድል ሳያገኙ የፈረሱ ብዙ ሀገሮች እንዳሉ አንስተው ጅምሩ ጥሩ ነው የሚል አስተያየት ሰጥተዋል። ከዚያም በሁለት ጉዳዮች ላይ፣ ማለትም ሀገረ መንግሥትን እና ሰላምን እንዴት ማበልጸግ ይገባናል? በሚሉ ጥያቄዎች ላይ ሐሳባቸውን አካፍለዋል። በዚህም፣ የሀገረ መንግሥት ግንባታ ሂደቱ የመንግሥትም የሕዝብም ኃላፊነት እንደሆነ አንስተው፤ ሀገርን እና መንግሥትን ለይተን መመልከት የሚገባን ጉዳይ ነው ብለዋል። ምክንያቱም፣ ሀገር መንግሥት ከመኖሩ በፊትም የነበረች እና የምትቀጥል ነች። መንግሥታት ግን የሚለዋወጡ መሆናቸውን አውቀን እንደሕዝብ መግባባትን እና ሰላምን ለማስፈን ምን ማድረግ አለብን? የሚለውን ማሰብ ይገባል።

አሁን ባለው ሁኔታ ሁሉም ኢትዮጵያዊ የተበዳይነት ስሜት እንደተጠናወተው በማስታወስ ከዚህ ስሜት ለመውጣት ያስችላሉ ያሏቸውን አራት ነገሮች አስቀምጠዋል፡
-

1. መተማመን፣ በሕዝብ እና በመንግሥት መካከል ከፍተኛ አለመተማመን አለ። በመሆኑም ስለመተማመን ማሰብ አለብን።
2. ተስፋ፣ እንደሀገር እና ሕዝብ "እዚህ እንደርሳለን" የሚል ተስፋ ሊኖረን ይገባል።

3 .የእኔነት ስሜት፣ የሌሎችን ችግር እና ቁስል እንደራሳችን ልንረዳውና ልናስበበት ይገባል።

4 .የጋራ ኃላፊነት፣ "ምን አገባኝ፤ የእነከሌ ጉዳይ ነው" ከሚል ስሜት ይልቅ በችግሮቻችን ላይ የጋራ ኃላፊነት ልንወስድ ይገባል።

ማንነትን በተመለከተም፣ ማንነት አንድ እና አንድ ተብሎ የሚወሰን ጉዳይ አይደለም። ይልቁንም አንጻራዊ ነው። አንድ ኢትዮጵያዊ ኢትዮጵያ ውስጥ አማራ፣ ኦሮሞ ሌላም ሊባል ይችላል። ከኢትዮጵያ ሲወጣ ግን ጥቁር አፍሪካዊ የሚባል ማነነት እንደሚሰጠው አስረድተዋል። በሌላ በኩል፣ የእርቅን ጉዳይ በማነሳት፣ እርቅ የመንግሥት ጉዳይ እና ተግባር ብቻ አይደለም ብለዋል። ምንም እንኳን የመንግሥት ተሳትፎ አስፈላጊ ቢሆንም እርቅ የሕዝብ ጉዳይ መሆን አለበት። እና ሕዝቡ "የኔ" ብሎ በሚቀበላቸው ሥርዓቶች መከናወን እንዳለበት፤ ከእርቅ ጋርም ትብብር እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል። በተጨማሪም፣ አሁን ባለው የኢትዮጵያ ነበራዊ ሁኔታ ፖለቲካ ነክ ነገሮች መብዛታቸው እና ሕዝቡም በፖለቲካ ጉዳዮች ላይ ከልክ ያለፈ ተሳትፎ እያሳየ እንደሚገኝ ተናግረዋል። ፖለቲካውን ለፖለቲከኞች፣ ምሁሩም በሥራው፣ ባለሙያውም በሙያው ላይ እና ሕዝብም በሥራው ላይ ማተኮር ይገባል። በርግጥ መሪዎችን መከተል ማገዝ ያስፈልጋል። የመርህ ሰው መሆንም ግድ ይላል።

መርህ ሲከበር በድርጊት እንዲገለጽ ማድረግ አለብን። በዚህም መንገድ ለመርህ የሚቆም ትውልድ ማፍራት ይቻላል። መንግሥትም ሲያጠፋ ከመርህ እና ከሕግ ተነስተን "አጥፊተሃል ታረም" የምንልበት ደረጃ ላይ መድረስ እንዳለብን አሳስበው ትብብር ለሕዝብ ፋክክር ለፖለቲከኞች አስፈላጊ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

ሁለተኛው የውይይት ጽሑፍ አቅራቢ ዶ/ር ያሬድ ማሞ "ብሔራዊ ማንነት እና ልዩነት አቃፊ ሥርዓት፤ ወቅታዊ ነባራዊ ሁኔታ እና ቀጣይ አካሄድ" በሚል ርዕስ ሐሳባቸውን አቅርበዋል። ዶ/ር ያሬድ በቅድሚያ ልዩነትን በማክበር ጠንካራ ሕዝብ፣ መንግሥት እና ሥርዓት መገንባት ይቻላል ብለዋል። ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑ ባለብዙ ልዩነት ሀገራት መኖራቸውን አንስተው፤ ልዩነት ተከባብሮ መኖርን ሲያሳይ፤ "ተቻችሎ መኖር" የሚለው ሐሳብ ግን አንዱን ቻይ አንዱን ተቻይ የሚያደረግ ሐሳብ በመሆኑ አስፈላጊ እንዳልሆነ አውስተዋል። ማንነት ከግለሰቦች ዘረመል አንስቶ አስከግለሰቦች ክህሎት ባለው ሐሳብ ድረስ የተለያየ ዓይነት መሆኑን ልንገነዘብ ይገባል። እናም የማንነት እይታችን ብዝኃነትን ያማከለ፤ እንዲሁም ብዙ የእይታ ማእዘኖች

ያሉት ነገር መሆኑን ልንረዳ ይገባል ብለዋል። ብሔራዊ ማንነትም በዘመናት የሀገሮች እና የሕዝቦች ጥረት የሚሳካ ጉዳይ መሆኑን መረዳት እንደሚገባ፤ የብሔራዊ ማንነት ግንባታ የአንዴ ወይም የአጭር ጊዜ ተግባር እንዳይደለ አሳይተው በዚሁ መንገድ ታሳቢ እንዲደረግ ሐሳባቸውን አጋርተዋል ።

ቀጥለውም፣ ሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ሆናም በሕዝቦቿ ብዝኃ ማንነት እና ልዩነት ውስጥም እየቀጠለች ዛሬ ላይ የደረሰች መሆኗን አስታውሰዋል። “ቀደምቶቻችን እንዴት ማስቀጠል ቻሉ?” የሚለውን ለማወቅ መጣር እንዳለብንም አስገንዝበዋል። የእነሱን ጥበብም ከእኛው ዘመን ጋር አሰናስለን መጠቀም ይገባልም ብለዋል። አንድ ብቻ እውነት እንደሌለ፤ በተለያየ ማኅበረሰብ፣ እምነት እና በሌሎችም ልዩነቶች ውስጥ የተለያየ እውነት እንደሚኖር ማወቅ እና መቀበል እንደሚያስፈልግ፤ ሁሉንም ልዩነቶች ማስተናገድ እንደሚገባ ገልጸው፤ ልዩነትን አቃፊ ሥርዓት መገንባት የሕዝብም የመንግሥትም ኃላፊነት እንደሆነ አስረድተዋል።

ኢትዮጵያ በዘመናት ሂደት መፈጠሯ እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያውያንን እንዴት መፍጠር እንችላለን የሚለውን ልናስብበት የሚገባ ጉዳይ እንደሆነ ያነሱት ዶ/ር ያሬድ፤ ኢትዮጵያ የሚያደርገውን የሚያውቅ የነቃ ሕዝብ፣ ወጣት እና ምሁር ሊኖራት ግድ ይላል ብለዋል። የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ በዳሰሱበት ንግግራቸውም፤ የተለያዩ የፖሊሲ ችግሮች ሊኖሩ እንደሚችሉ ከሕገ መንግሥት ጀምሮ ያሉት ጉዳዮች ሊታሰብብባቸው እና በውይይት መግባባት ላይ ሊደረስባቸው የሚገቡ መሆናቸውን አንስተው፤ ከሀገሪቱ የፖለቲካ እንቅስቃሴ አንጻር ደግሞ የሚፈጠሩትን ግጭቶች እና የፖለቲካ ክፍተቶች፣ የዜጎችን መፈናቀል፤ እንግልት እና ሞት በቶሎ መፍትሔ አለመስጠት ሌሎች ተመሳሳይ ሁኔታዎች በድጋሚ ቢፈጠሩ ምንም ዓይነት ርምጃ እንዳማይወሰድ መልዕክት እያስተላለፉ እንደሚገኙም አሳስበዋል።

በመጨረሻም፣ በተቋማት ግንባታ ሂደት ጥሩ ጥሩ ሥራዎች እንደመሠራታቸው በተቋማቱ ውስጥ ያለውን ተግባቦት፣ የአፈጻጸም መንገድ እና ሁኔታ መከታተል እና መታረም የሚገባቸውን ማረም እንደሚገባም አሳስበዋል። እንደሕዝብ “ትክክል ናቸው” ብለን የያዝናቸው እና ውጤታቸው የማይጠቅሙንን ጉዳዩች መተው እና አዳዲስ ነገሮችን መማርና መለማመድ ተገቢ ነው በማለት አሳስበዋል።

ከውይይቱ ተሳታፊዎች ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ቀርበዋል። ከእነዚም መካከል በድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደር ላይ የሚታዩ ብልሹ አሠራሮች እና በከተማዋ ላይ

እየተስተዋለ ያለው የሰላም መደፍረስ የሚመለከተው ይገኝበታል፡፡ በሌላ በኩል፣ ኢትዮጵያውያንን የሚያስተሳስሩ አሰባሳቢ እሴቶች ምን ሊሆኑ ይችላሉ? የሚል ጥያቄም ተነስቷል፡፡ ለውጡን በመደገፍ እና ስኬታማ በማድረግ ላይ እና መሪን በመርህ መደገፍ ላይ አስተያቶች እና ጥያቄዎች የተነሱ ሲሆን፤ ዶ/ር ያሬድ በምላሻቸው፣ ፖለቲካን እና ፖለቲከኞችን ተገን አድርገው የግል ጥቅማቸውን የሚፈጥሩ ሰዎች በተለያዩ የአስተዳደር እርከኖች ሊኖሩ እንደሚችሉ ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ምቹ መደላድል እየሆናቸው ያለው የፖለቲከኞች "እኔን አትንካኝ እንጂ እንደፈለግክ ሁን፤ አድርግ" የሚል እሳቤ እንደሆነ አስታውሰው፤ ይህን መሰል ነገሮች በድሬ ዳዋ ከተማ አስተዳደርም ሆነ በሀገር አቀፍ ደረጃ መስተካከል እንደሚገባቸው አሳስበዋል፡፡ ዶ/ር ያሬድ ቀጥለውም "ኢትዮጵያ ትልቅ ሀገር ስለሆነች አትፈርስም ማለት እንዴት ነው? በሚል ለተጠየቁት፤ ትልቅ ሀገር መሆን ብቻ ከመፍረስ እንደማያድን፤ ነገር ግን ትልቅ ሀገር የሚሆነው በትልልቅ ሐሳቦች እና ተቋማት ላይ በመቆም ስለሆነ ኢትዮጵያ እንደሀገር የቆመችባቸው ሐሳቦች እና ተቋማት ግዝፈት እና ጥልቀት በቀላሉ ለመፍረስ ስጋት የሚጥሏት አይደሉም የሚል እሳቤ እንዳለው አስረድተዋል፡፡ ልዩነትን እንዴት እናስተናግድ በሚለው ሐሳብ ላይም ልዩነት ወይም ብዝኃነት የተለያየ አቅም ያላቸውን ሰዎች፤ ተቋማት እና ማህበረሰቦች በማሰባሰብ በጋራ ለአንድ ዓላማ መቆም የሚችል እንደመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃም ትልቅ አቅም እንዲኖረን የሚረዳ ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡ በመጨረሻም፣ በድሬ ዳዋ ከተማ እየተስተዋሉ ያሉትን አንዳንድ የጸጥታ ችግሮች በመፍታት ከተማዋን በቀላሉ ወደቀደመ የፍቅር ከተማነቷ እንድትመለስ ማድረግ እንደሚቻል፤ ለአዲሱ አስተዳደርም በጣም ቀላል እንደሆነ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል፡፡

ወ/ሮ የትነበርሽ በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ ብዙ የተከማቹ ችግሮች ያሉባት ሀገር እንደመሆኗ ችግሮች ሁሉ ባንድ ጊዜ ይፈታሉ ብሎ ማሰብ አይገባም፡፡ ጊዜ መስጠት ግድ ይላል በማለት አሳስበዋል፡፡ ብዙዎቻችን ኢትዮጵያውያን "ሀገሬ ምን አደረገችልኝ?" የምንል መሆናችን ለአንዳንድ የሀገሪን ችግሮች መባባስ ምክንያት እንደሚሆን አመልክተዋል፡፡ ከዚህም የችግር አዙሪት ለመውጣት "ለሀገሬ ምን ላድርግላት?" በሚለውን ሐሳብ ላይ መሥራት እንደሚገባ፤ እንዲሁም መብት ሲሰጥ ከግዴታ ጋር መሆኑን በማሰብ መብታችንን በምንጠይቅበት ጊዜ ግዴታዎቻችንንም መፈጸም ይገባናል በማለት ሰፋ ያለ በምሳሌዎች የተዋዛ ሐሳብ አካፍለዋል፡፡ እርቅን በተመለከተም፤ እርቁን ለማስጀመር በብሔራዊ የእርቅ ኮሚሽን በኩል ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ ጠቁመው፤ በክልሎች እና በማህበረሰቦች መካከል ያሉትን ቅራኔዎች ለማርገብ እና ወደእርቅ ለመሄድ የግድ የተቋማትንና የመንግሥትን

እንቅስቃሴ መጠበቅ እንደሌለበት ገልጸዋል። የጋራ ችግሮችን ለመፍታት በጋራ ቁጭ ተብሎ የመነጋገር ልምድ ማዳበር ይገባል። ይህንም ልምድ በየቤታችን ባህል አድረገን ቀጣዩ ትውልድም በመነጋገር የሚያምን እንዲሆን መሥራት አለብን። ለዚህም፣ የእምነት ተቋማትና አባቶች በሌሎች ተግባራት ላይ ከማተኮር ይልቅ እዚህ ላይ በደንብ መሥራት እንደሚገባቸው አሳስበዋል።

በዚህ ውይይት ማጠቃለያ ላይ የተገኙት የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ፕሬስ ሴክሪታሪያት አቶ ንጉሱ ጥላሁን፤ የአዲስ ወግ ፕሮግራም ዓላማው ከዚህ ቀደም በነበሩ ሁኔታዎች ብዙ ልንነጋገርባቸው እና ተግባብተን ልንፈታቸው ሲገባ ዝም በተባሉ ጉዳዮች መነሻነት የተለያዩ ግጭቶች መፈጠራቸው፤ በዚህም ክቡር የሆነውን የሰው ልጅ ሕይወት እስከማጣት መድረሳችን፤ ብንወያይ፣ “ብንመካከር ግጭቶችን ማስቀረት እንችላለን” በሚል እንደሆነ ገልጸዋል። በዚህም ስለምናምንና ይህንን በሐሳብ የሚደረግ ፋክክር እና ውይይት ባህል ማድረግ ስለምንፈልግ፤ ከብጥብት ወደሐሳብ ክርክር ልንገባ ስለሚገባም “ከጎዳና ወደአዳራሽ፣ ከጥይት ወደማይክ” በአዲስ ወግ ስለሰላምና ፍቅር እንወያይ በሚል እና በጎደለው ላይ እንድንደምርበት በማሰብ የተጀመረ እንደሆነ አሳውቀዋል።

## 1.3 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ የምጣኔ ኃብት ሪፎርም መነሻና አቅጣጫ

ነሐሴ 6 ቀን 2011 ዓ.ም

ይህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም የመጀመሪያ ትኩረቱን በምጣኔ ኃብት ላይ ያደረገ የአዲስ ወግ መድረክ ሲሆን በነሃሴ 6፣ 2011 ዓ.ም ተዘጋጅቷል። ሀገራችን ኢትዮጵያ ባለፉት 15 (ዐሥራ አምስት) ዓመታት የኢኮኖሚ ዕድገት እያስመዘገበች የቆየች ቢሆንም፤ የተለያየ መፍትሔ የሚያስፈልጋቸው የኢኮኖሚ ችግሮችም ኢትዮጵያን እና ኢትዮጵያውያንን እየፈተኑ እንደሚገኙም ይታወቃል። ከእነዚህም የኢኮኖሚ ችግሮች መካከል ሥራ አጥነት፣ የዋጋ ግሽበት (የኑሮ ውድነት)፣ የውጭ ምንዛሬ እጥረት እና ደካማ የፕሮጀክት አፈጻጸም ወ.ዘ.ተ የሚጠቀሱ ናቸው። አዲሱ የለውጥ መንግሥት እነዚህን የኢኮኖሚ ችግሮች ለመቅረፍ የተለያዩ ሥራዎች እየሠራ ሲሆን፤ ከዚህም ዋነኛው የኢኮኖሚ ሪፎርም ማድረግ ነው። በዚህም በተለያዩ የፖለሲ፣ የሕግ እና የአሠራር ሥርዓቶች ላይ ማሻሻያ ለማድረግ እየተሠራ ይገኛል።

በዚህም የአዲስ ወግ መድረክ የምጣኔ ኃብት ሪፎርም ሥራዎች ከሥራ እድል ፈጠራ አኳያ በችግሮች፣ እየተሠሩ ባሉ ሥራዎች እና ተያያዥ ሐሳቦች ላይ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የሥራ ኃላፊዎች፣ ባለኃብቶች፤ እንዲሁም ምሁራን ጋር ውይይት ተደርጓል። በመድረኩ የመወያያ ሐሳብ ያቀረቡት ዶ/ር ብሩክ ታየ፣ ከፋይናንስ ሚኒስቴር (የቀድሞ)፣ አቶ መሳይ ታደሰ ከግል ዘርፍ እና አቶ ብሩክ ፍቅሩ ከግል ዘርፍ ሲሆኑ፤ አቶ ማሞ ምኅረቱ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የምጣኔ ኃብት አማካሪ (የቀድሞ) በምጣኔ ኃብት ሪፎርሙ ዙሪያ አጠር ያለ መረጃ ሰጥተዋል። ፕሮግራሙን በአወያይነት የመራችው በምጣኔ ኃብት ላይ የሚዲያ ሥራ የምታቀርበው ሰላም ተሾመ ናት ።

### ሀገር በቀል የምጣኔ ኃብት ማሻሻያ ሥራዎች

በዚህ ጉዳይ ላይ በመጀመሪያ ሐሳባቸውን ያጋሩት ዶ/ር ብሩክ ታየ ናቸው። እርሳቸውም የምጣኔ ኃብት ማሻሻያ የተደረገባቸውን ሴክተሮች እና የማሻሻያውን ዓላማ እና ትሩፋት አስረድተዋል። ማሻሻያውንም በሦስት ዋና ዋና ነጥቦች ከፍለው አሳይተዋል። እነዚህም፣ አንደኛ በመንግሥት እጅ የነበሩትን የልማት ተቋማት ወደ ግሉ ዘርፍ ማስተላለፍ፤ (Privatization) ሁለተኛ፣ የንግድ አሠራር ማሻሻያ

(Ease of doing business) ሦስተኛ የውጭ ምንዛሬ እጥረትና የውጭ እዳ አከፋፈል ችግሮችን ለመፍታት የተሠሩ ማሻሻያዎች  የሚሉ ናቸው።

በመንግሥት ይዞታ የሚገኙ ተቋማትን ወደግል ማስተላለፍ ያስፈለገበትን ምክንያት ሲያስረዱም፤ ተቋማቱ ሀገራችን ከምትችለው በላይ በእዳ የተዘፈቁ መሆናቸው እና ከእነዚህም መካከል እዳቸውን ከፍለው ውጤታማ የመሆን እድላቸው የጠበበ ተቋማት እንደሚገኙበት የስኳር ፋብሪካዎችን፣ ባቡርን እና የኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ድርጅትን በምሳሌነት በማንሳት አስረድተዋል። እነዚህ ተቋማት ከቻይና ባንክ ከፍተኛ እዳ ያለባቸውና በዚሁ ሥርዓት ውስጥ የሚታዩ እንደሆኑ ገልጸዋል። እነዚህን ተቋማት በተመለከተ በብድር አከፋፈል ሥርዓታቸው ላይ ማሻሻያ የተደረገባቸው እንደሆኑ አሳውቀዋል። በዚህም ረገድ ተቋማት ወደግል ይዞታ ከመተላለፋቸው በፊት "አቋማቸው ምን ላይ ነው?" የሚል ጥናት እና የእዳ ማስተካከል ሥራ እየተሠራ እንደሆነና በፕሮጀክት ደረጃ በእያንዳንዱ የስኳር ፋብሪካ ላይ የፋብሪካ ይዞታ ጥናት፣ የዋጋ ትመና፣ እንዲሁም የአካባቢ ተጽዕኖ ጥናት እየተከናወነ መሆኑን አንስተዋል። በቀጣይም ስድስት የስኳር ፋብሪካዎች ወደግል እንደሚተላለፉ አሳውቀዋል ።

በሌላ በኩል፣ የኢትዮጵያ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት አዋጅ መጽደቁን አንስተው የኮመሙኒሽን ባለሥልጣን ተቋቋሞ ሥራ መጀመሩንና ዓላማውም የኢትዮ ቴሌኮም የተወሰነ ድርሻ ተሸጦ ሁለት ተጨማሪ የቴሌኮም አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲገቡ እና በሦስት አገልግሎት አቅራቢዎች አገልግሎት እንዲሰጥ በማድረግ የአገልግሎት ተደራሽነትን እና የዋጋ አተማመንን መቆጣጠር እና ማመቻቸት እንደሚሆን አሳውቀዋል። ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች አስተዳደር ጋር በተያያዘም፣ በመተዳደሪያ ሕጎች ላይ ማሻሻያ መደረጉን አስታውሰዋል። በዚህም ረገድ ዘረፋ በርከት ያሉ ሥራዎች የተሠሩበት  እንደሆነ ጠቁመው፤ ተቋማት በብድራቸው እና በገቢያቸው መካከል ከፍተኛ ልዩነት በሚፈጠርበት ወቅት በቶሎ የማስተካከያ ርምጃ መውሰድ እንዲቻል ለተቆጣጣሪው ተቋም የሚያሳውቁበትን መንገድ መፍጠር በሕጎቹ ላይ ማስተካከያ የተደረገባቸው ጉዳዮች እንደሆኑ ተናግረዋል።

የንግድ ሥርዓቱን ከማዘመን አኳያም የኢትዮጵያ የንግድ ሥርዓት በቀላሉ የሚገባበት እንዲሆን ለማድረግ የንግድ ሕጉን ከማስተካከል ጀምሮ የፈቃድ አወጣጥ እና የግብር አከፋፈል ሥርዓትን ማዘመን ላይ እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች እንዳሉ ገልጸዋል። የውጭ ምንዛሬ እጥረትን፣ የዋጋ ግሽበትን እና የሥራ አጥነትን በተመለከተ ችግሮቹ ዘላቂ መፍትሔ የሚፈልጉ እንደመሆናቸው መጠን በሕግ ብቻ የሚፈቱ ባለመሆናቸው

እያንዳዱን ዘርፍ ውስጡን በመመልከት በመንግሥት በኩል ከአምስት እስከዐሥር ዓመት ወደፊት ሊያሠሩ የሚችሉ ማስተካከያዎችን ለማድረግ  እየተሠራ እንደሆነ አስታውቀዋል።

ሁለተኛው  የውይይት መነሻ ሐሳብ  አቅራቢ አቶ መሳይ ታደሰ፣ መንግሥት የምጣኔ ኃብት ማሻሻያ ሥራዎች መሥራት ከጀመረ አንስቶ ትልልቅ ፋብሪካዎች ወደግል ይዞታ መሸጋገራቸውን አንስተዋል። በተጨማሪም አየር መንገድን እና ኢትዮ ቴሌኮምን የመሳሰሉት ትላልቅ ተቋሞች ለማስተላለፍ በሚደረገው እንቅስቃሴም ኢትዮጵያውያን ምን ያህል መጠን ያለው ድርሻ መግዛት እንደሚችሉ መረጃው ለሕዝብ ይፋ መደረግ አለበት ብለዋል። የግሉን ዘርፍ ከመንግሥት ጋር በጋራ ለማሳተፍ በወጣው አዋጅ ላይ የግሉ ዘርፍ እንዴት ተሳትፎ ማድረግ እንደሚችልም መንግሥት ዝርዝር መረጃ  እንዲሰጥ አሳስበዋል። ትውልደ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ የግል ባንኮች ውስጥ ሼር መግዛት እንዲችሉ መወሰኑ ለሴክተሩ ጥሩ መሆኑንም ገልጸው፤ ባንኮች ለግል ኢንቨስትመንቶች በተለይ ከፍተኛ የሥራ እድል ለሚፈጥረው የግብርና ዘርፍ የሚያደረጉት የካፒታል አቅርቦት አነስተኛ በመሆኑ ለግብርናው እና ለሎጂስትክሱ ዘርፍ ትኩረት ተሰጥቶ የካፒታል አቅርቦት ችግር ለመፍታት እንዲሠራ አሳስበዋል።

ከካፒታል እጥረት ጋር አያይዘውም፤ በኢትዮጵያ ውስጥ ወደ55 (ኀምሣ አምስት) ሺሕ የሚጠጉ (Social Enterprises) ቢኖሩም ምንም ዓይነት የካፒታል አቅርቦት ማግኘት እንደማይችሉ እና በሕጋዊነት ለመቋቋም የሚያስችላቸው ሥርዓት ያለመኖሩን አንስተዋል። እነዚህ ድርጅቶች ግን ከሥራ እድል ፈጠራ አንጻር በተለይ ለሴቶች ብዙ አስተዋጽዖ ያላቸው መሆናቸውን ገልጸዋል። በመጨረሻም፣ መንግሥት ለሥራ እድል ፈጠራ ትኩረት ሰጥቶ ኮሚሽን አቋቁሞ መሥራት መጀመሩ አበረታች ተግባር መሆኑን ተናግረዋል።

ሌላኛው የመነሻ ሐሳብ  ያቀረቡት አቶ ብሩክ ፍቅሩ፣ በቡና ገበያ ልማት ላይ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች እና አንዳንድ ምጣኔ ኃብታዊ ጉዳዮች ጋር በተያያዘ ትኩረት በማድረግ ሐሳብ አቅርበዋል። በተለይ በቡና ገበያ ላይ የሚታዩትን ችግሮች ለማስተካከል በመንግሥት በኩል የሚሠሩ ሥራዎች ከባድ እንደሆኑ አንስተው፤ በተለይ የዘርፉን ሕግ  ለማሻሻል የሚሠሩ ባለሙያዎች የዓለም አቀፉ የቡና ገበያ እንዴት እንደሚሠራ ግንዛቤ ክፍተት መኖሩ የሌላቸው መሆኑና በዘርፉ የሚደረጉ ማሻሻያዎች ስር ነቀል ለውጥ ከማምጣት ይልቅ ተካታታይ (የሂደት) ለውጥ እንዲያመጡ ታሳቢ ተደርገው የሚሠሩ መሆናቸው ሥራውን ከባድ እንዳደረገው አስረድተዋል። ችግሮቹንም

ሲያሳዩ አንድ ቡና አምራች ገበሬ እንደፈለገ ተንቀሳቅሶ ምርቱን በተሻለ ዋጋ መሸጥ እንዳይችል የሚያደርጉ የኢኮኖሚ ነጻነቱን የሚጋፋ ሕጎች መኖራቸውን ጭምር አንስተው፤ የሚሠሩ ተግባራት የዜጎችን ጥቅም ከግምት ውስጥ ያስገቡ መሆን እንደሚገባቸው፤ ሁሌም የባለኃብቱን ፍላጎት ብቻ መሠረት ያደረጉ ሥራዎች መሠራት እንደሌለባቸው አሳስበዋል።

አቶ ብሩክ በመጨረሻም፣ የዋጋ ግሽበትን፣ በተለይ ደግሞ የምግብን አቅርቦት በተመለከተ የግሽበቱ መንስኤ ምን እንደሆነና በሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ሕዝቡ እንዲያውቅ፤ የመፍትሔውም አካል እንዲሆን መደረግ እንዳለበት አሳስበዋል። ባንኮችም የሕዝብን ገንዘብ በአደራ ተቀብለው እየሠሩ እንደመሆናቸው ሁሉ ከሕዝብ የሰበሰቡትን ገንዘብ ዋጋ የመጠበቅ እና ግሽበቱን የመቆጣጠር ኃላፊነት እንዳለባቸውም ተናግረዋል ።

በውይይቱ ከመነሻ ጽሑፍ አቅራቢዎች ቀጥሎ "የምጣኔ ኃብት ማሻሻያው ቀጣይ አቅጣጫዎች" በሚል መንግሥት ስለወሰደው የምጣኔ ኃብት ማሻሻያ መረጃ የሰጡት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የምጣኔ ኃብት አማካሪ አቶ ማሞ ምኅረቱ ናቸው። አቶ ማሞ ሲያስረዱም የመንግሥት ዋናው ዓላማ ሥልጣን በሕግ የተገራበት፤ የዜጎች ሁለንተዊ መብቶች የተከበሩበት እና ሰላማዊ የሆነ ሥርዓተ መንግሥት መመሥረት እንደሆነ፤ ይህንንም ለማሳካት ኢኮኖሚውን ማሳደግ እና ማዘመን የሚያስችል ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሰነድ መዘጋጀቱን እና በቀጣይ ጊዜያት ከምሁራን ጋር ውይይት እንደሚደረግበት ገልጸዋል። የሰነዱ ዓላማ በለውጡ የተረጋጋ ማክሮ ኢኮኖሚ መፍጠር እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ማሳደግ እንደሆነ አስታውቀዋል።

በተጨማሪም ላለፉት 15 (ዐሥራ አምስት) ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ እድገት ቢያሳይም የሥራ አጥነት መስፋፋት፣ የውጭ ንግድ እጥረት (የውጭ ምንዛሬ እጥረት)፣ ደካማ የፕሮጀክት አፈጻጸም፣ የዋጋ ንረት እና የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ደካማ መሆንን የመሳሰሉ ተግዳሮቶች ገጥመውታል። ለነዚህ ተግዳሮቶችም መፍትሔ የሚሆኑ ሐሳቦች ያሉት ይህ የተዘጋጀው የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሰነድ በማክሮ ኢኮኖሚ ለውጥ፣ የመዋቅራዊ ለውጥና ዘርፍ ተኮር ለውጥ ያካተተ እንደሆነ አንስተዋል። በዚህም በማክሮ ኢኮኖሚው ጥንቃቄ የተሞላበት የፊስካል ፖሊሲ እና የመንግሥት ልማት ተቋማት ሪፎርም እንደሚደረግ፤ በውስጡም የበጀት ጉድለት ማጥበብ፣ የታክስ ሥርዓት ማሻሻል፣ ፕሮጀክቶችን ማስፈጸም እና ወደግሉ ዘርፉ የሚተላለፉ ተቋማትን ሂደት ማፋጠንን እንደሚያካትት፤ የውጭ ምንዛሬን ግኝት ለማስፋት፤ የፋይናንስ ሥርዓቱን ጤናማነት

ለማረጋገጥ እና የዋጋ ንረትን ለመቆጣጠር ሥራዎች እንደሚሠሩ አሳውቀዋል ።

መዋቅራዊ ለውጥ በሚደረግባቸው ሥራዎች ደግሞ፣ የኢንቨስትመንት ከባቢ ሁኔታን ማሻሻል፤ ማለትም ኢንቨስትመንትን የሚያበረታቱ የሕግ፣ የአስተዳደር ሁኔታዎችን ማሻሻል፤ በሎጂስቲክስ ዘርፍ ለውጥ፣ በኃይል አቅርቦት ለውጥ እና በቴሌኮም ለውጥ ላይ የሚደረጉ ሥራዎች እንደሆኑ አሳውቀዋል። ዘርፍ ተኮር ለውጥ የሚደረግባቸው ደግሞ የተለያዩ አምራች ዘርፎችን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግ የሚሠሩ ተግባራትን የያዘ ነው። በዚህም፣ በግብርናው ዘርፍ፣ የአምራች ዘርፉን የሚያበረታታ፤ የማዕድን ዘርፉን በተለየ ትኩረት በማየት የሥራ ፈጠራ እና የውጭ ንግድ አስተዋጽዖውን ለማሳደግ፣ የቱሪዝሙን ዘርፍ ለማበረታታት እና መዳረሻዎችን ለማሳደግ፤ እንዲሁም በአዲስ የእድገት መስኮች የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂው እና የሥነ ጥበብን ዘርፍ ያካተተ የማሻሻያ ዶክመንት መዘጋጀቱን አሳውቀዋል ።

ሁሉም የውይይት መነሻ ጽሑፎች ከቀረቡ በኋላ ተሳታፊዎች አስተያየቶችን ሰጥተዋል። ጥያቄም አቅርበዋል። ከእነዚህም መካከል የአፍሪካ ነጻ ገበያ ስምምነት መፈረማችን ታሳቢ ተደርጎ ስምምነቱ ይዞት የሚመጣውን እድል እና ተግዳሮት ሕዝቡ ምን ያህል እንዲያውቀው ተደርጓል? የመንግሥት ተቋማትስ ምን ዓይነት ዝግጅት እያደረጉ ነው? የሚሉ ጥያቄች ቀርበዋል። የሕግ ማሻሻያዎችን ማድረጉ እንዳለ ሆኖ አንዳንድ ሕጎች እና የአሠራር ሥርዓት አካሄዶች፤ በተለይ ከውጭ ምንዛሬ አስተዳደር ጋር በተያያዘ ትውልደ ኢትዮጵያውያን በሌሎች ተቋማት እና በግለሰቦች በኩል በኢትዮጵያ በከፈቷቸው የባንክ አካውንቶች በሚያስገቡት ገንዘብ ላይ የተጣለው ክልከላ ማስተካከያ ሊደረግበት ይገባል የሚል አስተያየት ተሰጥቷል። በመንግሥት የልማት ድርጅቶች ውስጥ በቦርድ አባልነት የሚሰየሙ ኃላፊዎችን በተመለከተም፣ ኃላፊነቱ ፖለቲካዊ ያለመሆኑ ታሳቢ ተደርጎ በግሉ ዘርፍ በተለይ በሥራው ላይ የሚገኙ እና ለሥራው ቅርበት ያላቸው ግለሰቦችም ሊካተቱበት እንደሚገባ ሐሳብ ቀርቧል።

በተጨማሪም፣ በግብርናው ዘርፍ አዳዲስ የሥራ እድል ለመፍጠር እየተሠራ ቢሆንም፤ ዘርፉ ላለበት ከፍተኛ የካፒታል እጥረት ከባንኮች የሚሰጠውን የብድር መጠን ለማሳደግ ምን ታስቧል? የሚል ጥያቄ ተነስቷል። ቡና አቀናብሮ ወደውጭ መላክ ላይ አለመሠራቱ ብዙ ብክነት እያስከተለ እንደሆነ እና ቡና ተቀናብሮ የሚላክበት መንገድ ቢመቻች ከፍተኛ ለውጥ ማምጣት እደሚያስችል አስተያየት አዘል ጥያቄ ተሰንዝሯል። የሎጂስቲክስ ዘርፍም የሚገባውን ትኩረት እንዳላገኘ እና የግብርናን ምርቶች ለውጭ ገበያ ለማቅረብ የቀዝቃዛ ሰንሰለት አገልግሎት መጀመር እንዳለበት

አስተያየት ቀርቧል ።

በሌላ በኩል፣ በሪፎርሙ የአስፈጻሚው አቅም እንዴት ታስቧል? የሚል ጥያቄ፤ እንዲሁም በአነስተኛ ንግዶች ላይ ከመመስረቻ የንግድ ፈቃድ እና ከታክስ ጉዳዮች ነጻ የሚደረጉበት መንገድ ቢፈጠር የሚሉ አስተያየቶች ቀርበዋል። የመንግሥት ኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶችን በተመለከተ የፕላን ሚኒስቴር ምን ያህል የቁጥጥርና የማስተካከያ ርምጃ የመውሰድ አቅም ተገንብቶለታል? የሚል ጥያቄ፤ እንዲሁም የግል ባንኮች የካፒታል እጥረት ላለባቸው ሴክተሮች የብድር አቅርቦት እንዲያደረጉ የሚያስገድድ ሕግ ቢኖር የሚል አስተያየት ከተሳታፊዎች ተነስተዋል። እነዚህ የልማት ድርጅቶች ለምን እንደሚሸጡ ለሕዝቡ መረጃ ሊሰጠው እና ውይይት ሊደረግበትም እንደሚገባ ተጠቅሷል። በባንክ ዘርፍ ላይ ያተኩሩ በዲጂታል የባንኪንግ ዘርፍ ላይ ምን እየታሰበ እንደሆነም በኢትዮጵያ የልማት ባንክን ጨምሮ በሊዝ ፋይናንሲግ ላይ የሚሠሩ አምስት ተቋማት ቢኖሩም፤ የተቋቋሙለትን ዓላማ ለማስፈጸም እየሠሩ አይገኙም። በሪፎርሙ እዚህ ላይ ምን ታስቧል? የሚል እና አነስተኛ ንግዶች ብድር ለማግኘት በሚጠየቁት የቋሚ ንብረት ማስያዣ ጋር በተያያዘ ምን ሊሠራ ታስቧል የሚል ጥያቄም ተነስቷል። ወደድርሻ ገበያ (stock market) ሥርዓት ልንገባ ይገባል የሚል ሐሳብም ቀርቧል።

ከሥራ አጥነት ጋር በተያያዘ፣ ኢትዮጵያ 48 (ዐርባ ስምንት) በመቶ የሚሆነው ሕዝቧ ከ15 (ዐሥራ አምስት) ዓመት እድሜ በታች የሚገኝ ታዳጊ እንደመሆኑ በሚቀጥሉት ከዐሥር እስከ ዓመታት ውስጥ ኢትዮጵያ የምታድግበት እና ዜጎቿ ወደሥራው ገበያ የሚመጡበት (Demographic transition) በሀገራት ታሪክ አንዴ ብቻ የሚፈጠር የሥነ ሕዝብ ለውጥ እንደሚኖር ታሳቢ አድርገን ከወዲሁ በትንሽ ጊዜ ውስጥ ወጣቶች ጥሩ ክህሎት በሚያዳብሩበት መንገድ ላይ መሠራት አለበት። በሥራ ገበያ ላይ ችግር የሚፈጥረው የመረጃ እጥረት በመሆኑ ለሥራ ፈላጊዎች ሥልጠናዎችን መስጠት እና የተለያዩ የብቃት ፈተናዎችን (Standardized tests) በማዘጋጀት በሥራ ገበያው ላይ መሥራት የሚቻልበት ስልት ቢፈጠር የሚሉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል ።

ለእነዚህ ከላይ ለተነሱት ጥያቄዎች እና አስተያየቶች መልስ የሰጡት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የኢኮኖሚ አማካሪ አቶ አበበ አበባየሁ፣ የንግድ ምዝገባ እና ፈቃድ አዋጅን በማሻሻል ወደንግድ ለሚገቡ ዜጎች ሥርዓቱን ቀላል ለማድረግ መሠራቱን ጠቁመዋል። ከብድር ጋር ለሚነሱ ጥያቄዎችም ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶችን እንደማስያዣ መጠቀም የሚያስችል አዋጅ መውጣቱንም አሳውቀዋል። የግብር አሰባሰብ ሥርዓቱም ዘመናዊ

እና ቀልጣፋ እንዲሆን የሚያስችሉ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸው፤ ይህም የንግዱን ከባቢ ሳቢ በማድረግ አዳዲስ ቢዝነሶች ወደሥራው እንዲገቡ ለማድረግ ታስቦ እንደሆነ አስረድተዋል።

ሌላው በዚህ ፕሮግራም ላይ  ሐሳብ የሰጡት የንግድ ባንክ ፕሬዚዳንት አቶ ባጫ ጊና፤ በግብርናው እና በማንፋክቸሪንግ ዘርፍ ላይ በከፍተኛ ትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ አሳስበዋል። የቀረቡት ችግሮችም በቅንጅት በመሥራት ሊፈቱ እንደሚችሉ ጠቁመው፤ ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ ወጣቶች ከመቀጠር ይልቅ የራሳቸውን ሥራ ፈጥረው የሚሠሩበትን ክህሎት እንዲያዳብሩ ከትምህርት ሥርዓቱ ጋር በጋራ ሊሠራ እንደሚገባ አስረድተዋል። የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ለመቅረፍም የቁም እንስሳት ንግድ ላይ ኮንትሮባንድን የመቆጣጠር ሥራ በትኩረት ሊሠራበት እንደሚገባ አሳስበዋል። ከብድር አቅርቦት ጋር በተደጋጋሚ ለሚነሳው ጥያቄም የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ 22.5 (ሃያ ሁለት ነጥብ አምስት) ቢሊዮን ብር ለግሉ ዘርፍ ብድር መስጠቱን እና ከሁለት ቢሊዮን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለግሉ ዘርፍ መቅረቡን፤ ይህም ካለፉት ዓመታት ጋር ሲተያይ መሻሻሉን አስታውቀዋል ።

በመጨረሻም፣ ዶ/ር ብሩክ በሰጡት ምላሽ፣ ሁሉም የልማት ድርጅቶች ያለባቸው ችግር የተለያየ እንደመሆኑ መጠን እንደችግራቸው መፍትሔ ለመስጠት እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። የብድር ችግር ያለባቸው የባቡር እና የስኳር ፋብሪካዎችም ብድራቸውን መክፈል የሚችሉበት ሁኔታ የሌለ በመሆኑ ወደግል ይዞታ በመተላለፍ መቀጠል የሚችሉበትን መንገድ ለመፍጠር እየተሠራ እንደሆነም ጠቁመዋል። በቴሌኮሙኒኬሽን ዘርፍ ኢትዮ-ቴሌኮም ገበያውን ብቻውን ተቆጣጥሮ ከሚቆይ ሁለት ከፍተኛ የገንዘብ አቅም ያላቸው የውጭ ድርጅቶች እንዲገቡ እና ኢትዮ-ቴሌኮምም ድርሻ በመሸጥ ከሽያጭ በሚያገኘው አቅም እራሱን አዘምኖ በፍክክሩ ውስጥ ገበያውን ውጤታማ እዲያደርግ እየተሠራ እንደሆነ አንስተው፤ ሌሎችም ተጨማሪ ካፒታል የሚስፈልጋቸው ድርጅቶች ድርሻ ሸጠው ካፒታል ቢያገኙ የበለጠ ውጤታማ ይሆናሉ። አዳዲስ የሥራ እድልም ይፈጥራሉ በሚል እየተሠራ እንዳለ አብራርተዋል። በዚሁ ጉዳይ ላይም  ከሕዝብና ከምሁራን ጋር ጠለቅ ያለ ውይይት መደረግ አለበት የተባለውንም እንደግብዓት ወስደው እንደሚሠሩበት አስታውቀዋል ።

በሌላ በኩል፣ የልማት ባንክን በተመለከተ የተሻሉ አማራጮችን በማጥናት ያለበትን ችግር ለማስተካከል እየተሠራ እንደሚገኝ፤ የሎጂስቲክስ ዘርፍም የሪፎርሙ አካል እንደሆነና ሥራዎች እየተሠሩበት እንደሆነ ገልጸዋል። የመንግሥት የልማት ድርጅቶች የቦርድ

አባላትን በተመለከተ በተሻሻለው አዋጅ ላይ ሁኔታዎችን የሚያስተካክሉ መመሪያዎች መካተታቸውን ጠቁመው፤ በአጠቃላይ በመንግሥት ይዞታ ስር የሚገኙትን የልማት ተቋማት ወደግሉ ዘርፍ የማዘዋወር ተግባር ሰፊ የሥራ እድል የሚፈጥር በመሆኑ ሀገራችን ለገጠማት ከፍተኛ የሥራ አጥነት ችግር መፍትሔ እንደሚሆን አስረድተዋል።














# ክፍል ሁለት፤

# የአዲስ ወግ መድረኮች

# 2012 ዓ.ም

# 2.1 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፤ መደመር

ጥቅምት 12 ቀን 2012 ዓ.ም




## ክፍል አንድ

ይህ የአዲስ ወግ ውይይት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "መደመር" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሐፍ ሐሳብ ላይ ያጠነጠነ ነው። መጽሐፉ "የኢትዮጵያን ችግሮች ሀገር በቀል የሆኑ መፍትሔዎች በመጠቀም ተደምረን መፍታት እንችላለን" የሚል ሐሳብ የያዘ ሲሆን መጽሐፉ ተመርቆ ገበያ ላይም ውሏል። ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ይህን የመደመር ሐሳብ ኢትዮጵያን ካሉባት የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማህበራዊ ችግሮች ለማላቀቅ ያቀረቡት ሐሳብ በመሆኑና ሐሳቡን በብስለት መመርመር፣ መተንተን እና መወያየት በማስፈለጉ የዚህ ወር የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ አጀንዳ ሆኗል።

"መደመር" መጽሐፍ አራት ክፍሎች አሉት። ውይይቱም በእያንዳንዱ ክፍል ላይ የተመረኮዘ ነው። የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎችም አራት ናቸው። እነርሱም እያንዳንዱን የመጽሐፉን ክፍል ለውይይት በሚመች መልኩ አቅርበዋል። በዚህም መሠረት፦ የመደመር መነሻ ሐሳቦች በአቶ ዮናስ ዘውዴ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሦስትኛ ዲግሪ ተማሪ፤ የመደመር ፖለቲካዊ ገጽ በአቶ ፍስሃ ይታገሱ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የወቅታዊ ጉዳዮች ሚኒስትር ዴኤታ (የቀድሞ) ፤ የመደመር እሳቤ እና ኢኮኖሚ በአቶ ማሞ ምኅረቱ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የምጣኔ ኃብት አማካሪ (የቀድሞ) እና የመደመር እና የውጭ ግንኙነት ሐሳቦች በአቶ መሐመድ ራፊ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የውጭ ጉዳዮች ተንታኝ (የቀድሞ) ቀርቧል። ፕሮግራሙን በአወያይነት የመሩት የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ጽሕፈት ቤት ሥራ አስኪያጅ ወ/ሪት ሌሊሴ ነሚ ናቸው።

## መደመር እና የሰው ልጅ

በመጀመሪያ ሐሳብ ያቀረቡት አቶ ዮናስ ዘውዴ "መደመር እና የሰው ልጅ" በሚል ርዕስ የመደመር መጽሐፍ በኢትዮጵያ ያለፉት ሥርዓቶች ይከተሏቸው የነበሩትን እሳቤዎች እና ምልከታዎች ተመልክተዋል። በዚህም እሳቤዎቹና ምልከታዎቹ ሀገር የመለወጥ ዓላማ የነበራቸው ቢሆንም፤ ለውጥ ለማምጣት ግን አልቻሉም። በመሆኑም ሀገራችን አሁን ድረስ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ እንደምትገኝ አስረድተዋል። "መደመር"ም "በእነዚህ ጊዜያት ሁሉ ከተለያዩ ዓለማት እየወሰድን ስንከተላቸው የነበሩ እሳቤዎች ለውጥ መፍጠር ካልቻሉ እሳቤያችን ከውስጥ የሚመነጭ ወይንም ሀገር በቀል ሊሆን ይገባል። ለሀገራችን ችግሮች ሀገር በቀል መፍትሔዎች ያስፈልጋሉ።" የሚል ሐሳብ የያዘ መጽሐፍ እንደሆነ ገልጸዋል። መጽሐፉ "ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ የሰው ልጆች ፍላጎት አሉ" ብሎ ያትታል ብለዋል። እነዚህ ሁለቱም የጎልውና ፍላጎቶች እንደሆኑና የሰው ልጅ የሥራ ፍላጎት፣ የመከበር ፍላጎት እና የነጻነት ፍላጎቶቹ ሊሟሉለት እንደሚገባም ሐሳብ የያዘ እንደሆነ አብራረተዋል።

የመደመርን የቃሉን ትርጓሜ ሲያስረዱም፣ "ደመረ" ከሚለው ግሥ የወጣ እንደሆነ እና ቃሉም "መሰብሰብ፣ ማካበት" እና "ማከማቸት" የሚለውን ትርጓሜ እንደሚይዝ፤ መደመር በተናጠል ከመፍጨርጨር ወደአንድ መሰባሰብን የሚያሳይ ሆኖ መጨፍለቅ ማለት ግን እንዳልሆነ መጽሐፉ እንደሚያስረዳና ኢትዮጵያውያን እያንዳንዳችን ያለንን የተለያየ አቅምና እውቀት በማሰባሰብ በጠንካራ አቅም መቆም እንደምንችል ያሳያል ብለዋል። መደመር የበፊቱን አፍርሶ ከምንም ከመነሳት ይልቅ ያለንን በጎ፣ በጎ ነገር (የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የባህል እሳቤዎች፣ የግጭት አፈታት እሴት፣ እንዲሁም ዴሞክራሲያዊ ጽንሰ ሐሳቦች) በማሰባሰብ፤ ደካማውን በማሻሻል፤ ጠንካራውን ደግሞ በመጠበቅ ለቀጣዩ ትውልድ የተሻለች ሀገር ማስረከብ እንዳለብን የሚያትት ጽንሰ ሐሳብ የያዘ እንደሆነ አስረድተዋል። በመቀጠልም መደመር ሦስት ዓላማዎች እንዳሉት ገልጸዋል። አንደኛው መልካም የፖለቲካና የኢኮኖሚ ድሎችን

መጠበቅና ማስፋት፣ ሁለተኛው የተሠሩ ስህተቶችን ማረም እና ሦስተኛው የመጭውን ትውልድ ጥቅም እና ፍላጎት ማሳካት እንደሆነ አስረድተዋል።

የ"መደመር" መጽሐፍ የሰው ልጅ የሕይወት ጉዞ ወደምሉኡነት የሚደረግ እንደሆነ እንደሚያስረዳ እና በዚህ ጉዞ በሰዎች መካከል ፉክክር እና ትብብር የማይቀሩ ግንኙነቶች እንደሆኑ አስረድቶ፤ የበዛ ፉክክርም ሆነ ትብብር ልክ እንዳልሆነ እና መጠን ሊኖር እንደሚገባ እንደሚሳስብ አስረድተዋል። እሳቤው ሁነቶች ሁሉ የተነጣጠሉ እንዳልሆኑ እንድንገነዘብ የሚያደርግ እንደሆነ እና የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካው ፣ የትምህርት ሁሉም ችግሮች የተያያዙ እንደሆኑ፤ ኢትዮጵያ ከችግር እንድትድን ሁሉም ችግር ያለባቸው ጉዳዮች መፍትሔ ማግኘት እንዳለባቸው መጽሐፉ እንደሚያስረዳ አንስተው፤ ለመደመር ተነሳሽነት፣ ሚዛን ማስጠበቅ እና የጋራ ግብ አስፈላጊ ነገሮች እንደሆኑ ገልጸዋል። መደመር እንዳይሳካ የሚያደርጉት የአስተሳሰብ መዛነፎች እንዳሉ ያነሱት አቶ ዮናስ እነዚህም፣ ዋልታ ረገጥነት፣ አቅላይነት፣ ጊዜ ታካኪነት፣ ሙያን መናቅ ፣ የለውጥ እምቢተኝነት፣ አድርባይነት፣ ኀሊና ቢሥነት እና ልግመኝነት መሆናቸውን የመደመር እሳቤ እንደሚያስረዳ አብራረተዋል።

## መደመርና የፖለቲካ እሳቤው

በመደመር መጽሐፍ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ችግሮች እና መፍትሔዎቻቸው ላይ ያተኮረውን ክፍል ተንተርሰው የውይይት መነሻ ሐሳብ ያቀረቡት አቶ ፍስሃ ይታገሱ ናቸው። የመደመር መጽሐፍ "የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ችግሮች" ብሎ የለያቸው ስምንት ነጥቦች "ከመደብ ቅራኔ የሚነሳ መሆኑ፤ ሕዝብን በቡድን የሚከፍል መሆኑ፤ የኢኮኖሚ ቅቡልነት ላይ ብቻ ማተኮሩ፤ የሽግግር ፕሮግራም መሆኑ፤ የመድብለ ፓርቲ ሥርዓትን በአውራ ፓርቲ መቀየሩ፤ የማህበራዊ መሠረት አካታችነት ችግር ያለበት መሆኑ፣ ለዘርፎች ሚዛናዊ ትኩረት የማይሰጥ መሆኑ፤ ፓርቲን እና መንግሥትን የሚደበላልቅ መሆኑ እና የብሔር እና ሀገራዊ ማንነትን የማጣጣም ችግር ያለበት መሆኑ፤" የሚሉት እንደሆኑ ዘርዝረዋል። "መደመር"ም እነዚህን ችግሮች መፍትሔ ለመስጠት የሚጥር እና የኢትዮጵያን ፖለቲካ ከጭቆና ንድፈ ሐሳብ አኳያ እንደሚመለከተው አስረድተዋል። ጭቆናንም የሀገረ መንግሥት ስብራት እንደሆነ በመጠቆም ይህንንም "ሰው ወለድ" ግለሰብን የሚያጠቃ እና "መዋቅራዊ" ቡድኖችን የሚያጠቃ በሚል በሁለት እንደሚከፍለው ገልጸዋል።

መጽሐፉ የኢትዮጵያ ሀገረ መንግሥት በጭቆናና በአመጻ የቆየ ነው የሚል እሳቤ እንዳለው ጠቁመዋል። በተጨማሪም፣ ኢትዮጵያ ታሪኳ በውስጥ እና በውጭ ጦርነቶች የተሞላ እንደመሆኑ፤ መንግሥታት ፋታ አግኝተው የዜጎችን ፍላጎት ለማሟላት እንዳልሠሩ ያሳያል። በዚህም ምክንያት አመጽ እና የነውጥ ንቅናቄዎች የተመለዱ በመሆናቸው መንግሥታት እነዚህን ንቅናቄዎች ለማፈን ጨቋኝ ሥርዓት ሲያስቀጥሉ መቆየታቸውንም ጠቅሷል። ኢትዮጵያም በጭቆና አዙሪት ውስጥ መቆየቷን የገለጠው መጽሐፉ ከዚህም ልንወጣ የምንችለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ስንገነባ እንደሆነ ያስረዳል።

የመደመር መጽሐፍ የ1960ው የተማሪዎች እንቅስቃሴ ሦስት መሠረታዊ የፖለቲካ ጥያቄዎችን አንጥሮ ለይቷል ብሎ እንደሚያምን እና እነዚህም፤ አንደኛ የመሬት ለአራሹ ጥያቄ፣ ሁለተኛ የብሔር እኩልነት ጥያቄ እና ሦስተኛ የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄ እንደሆኑ ያትታል። የመጀመሪያዎቹ ጥያቄዎች ከሞላ ጎደል ቢመለሱም፤ ሦስተኛ ግን ባለመመለሱ ከግጭት እና ከትርምስ መውጣት አልቻልንም ብሎ እንደሚያምን አንስተዋል። ሦስተኛውን ጥያቄም በሪፎርም እንደሚመለስ እንደሚያምን፤ ለዚህም ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት ግድ እንደሆነ እንደሚያስረዳ አቶ ፍሰሃ ይታገሱ ተናግረዋል። በመቀጠል፣ መደመር ምን ዓይነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እንደሚያስፈልግ ያስረዳበትን ሐሳብ በማንሳት የሰዎችን ተደማሪ ፍላጎቶች ማለትም የልማት፣ የእኩልነት እና የነጻነት ፍላጎቶች አስተሳስሮ ዴሞክራሲን እንደ አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከሂደት ጋር ብቻ ሳያይዝ በይዘትም ዴሞክራሲያዊ የሆነ ሥርዓት መሆን እንዳለበት ያምናል። በተጨማሪም፣ ሁሉም የጭቆና ዓይነቶች እንዳይኖሩ የሚያደርግ፣ የብሔርና ሀገራዊ ማንነትን አጣጥሞ የሚኀዝ እና የተሞከረውን የመግባባት ዴሞክራሲን (Concessional Democracy) ያሉበትን ክፍተቶች በመሙላት የሐሳብ ድርድሮችን እና ውይይቶችን በሚያበረታታ መንገድ መጠቀም እንዳለብን አቅጣጫ ያስቀምጣል። የመጨረሻ ግቡም የሲቪክ ባህሎች የዳበሩበት በውይይት ላይ የተመሠረተ የተረጋጋ ዴሞክራሲ መፍጠር እንደሆነ አሳውቀዋል። ይህ እንዳይሳካ ተግዳሮት ይሆናሉ ተብለው በመጽሐፉ የተለዩ ነጥቦች ደግሞ፤ የሀገረ መንግሥት ቅቡልነት ችግር፣ የተቋማት ደካማነት መሆናቸውን በማንሳት ለእነዚህም መፍትሔው የልሂቃንን ስምምነት መፍጠር፣ እርቅ እና ብሔራዊ መግባባት ማስፈን እንዲሁም ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቁ ተቋማትን መፍጠር እንደሆነ አስረድተዋል ።

## የመደመር ኢኮኖሚያዊ እሳቤዎች

ሦስተኛው የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢው አቶ ማሞ ምኅረቱ በመደመር የኢኮኖሚ እሳቤ እና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ዳሰሳ አድርገዋል። በዚህም፣ የመደመር

ኢኮኖሚ ትንተና ዋናው ዓላማ ብልጽግና እንደሆነ፤ መደመር የሚያልመው ብልጽግና ቁሳዊ የሆነ ብቻ ሳይሆን የሰዎችን የነጻነት እና የእኩልነት ፍላጎት እንደሚጨምር፤ መደመር ብልጽግናን እውን ለማድረግ በውድድር ላይ የተመሠረተ ነጻ ገበያ እውን ማድረግ አለብን ብሎ እንደሚያምንም አስረድተዋል። ነገር ግን በሀገራችን የግሉ ዘርፍ ባለማደጉ ገበያ የሚደግፍ መንግሥት እና ኃብት የሚፈጥር የግል ዘርፍ በትብብር መሥራት እንዳለበት እንደሚያምን ገልጸዋል። በተጨማሪም፣ በተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ማዕቀፍ ውስጥ ጥራት ያለው፣ ፈጣን፣ ብቁ እና አስተማማኝ የሥራ እድል የሚፈጥር ኢኮኖሚ መገንባት አለብን ብሎ ያምናል ብለዋል።

"መደመር የኢትዮጵያን ወቅታዊ የኢኮኖሚ ሁኔታዎች እንዴት ይመለከታቸዋል?" በሚለው ላይ ሐሳባቸውን ሲያጋሩም፤ በአለፉት ዓመታት ሀገራችን ያሳካቻቸውን የኢኮኖሚ ድሎች ማስቀጠልና መጠበቅ እንደሚገባ፣ በኢኮኖሚው ዘርፍ ላይ የተሠሩ የአስተዳደር ስህተቶችን ማረም እንደሚገባ ያምናል ብለዋል። የኢኮኖሚ እድገት ጥራት ችግር እንደሆነና የማክሮ ኢኮኖሚ መዛባት፣ የዋጋ ንረት፣ አስተማማኝ የሥራ እድል አለመኖር እና ኢፍትሐዊ የኃብት ክፍፍል የኢኮኖሚው ስብራት ዋነኛ ምልክቶች እና የፍትሐዊነቱ ዋነኛ ችግሮች እንደሆኑም ያምናል። የማክሮ ኢኮኖሚው መዛባት ስንከተለው ከነበረው መንግሥት መር የልማት ፋይናንሲንግ ሥርዓት እና የመንግሥት ስትራቴጂክ የአመራር ስህተቶች ምክንያት እንደሆነና ደካማ የሆነው የፕሮጀክት አፈጻጸም ሥርዓትም በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ የእዳ ጫና መፍጠሩን እንደሚያምን አንስተዋል። ነገር ግን ከላይ የተዘረዘሩት ሁሉም የበሽታው ምልክቶች እንጂ ዋነኛው የኢኮኖሚው ችግር የምርታማነት ችግር እንደሆነ መደመር ያስቀምጣል ብለዋል። በተጨማሪም መንግሥትን ጨምሮ በኢኮኖሚው ሥርዓት ውስጥ ያሉት ተዋንያን የግሉ ዘርፍ፣ የሲቪክ ማህበራት እና የመካነ ትምህርት ተቋማት ኃላፊነታቸውን ባለመወጣታቸው እና ደካማ የእርስ በርስ መስተጋብር መኖሩ ሌላው የኢኮኖሚ ችግሮች መንስኤ እንደሆነ በመጠቆም፤ ለማሳያም መንግሥት በገበያው ላይ ጣልቃ ይገባበት የነበረውን የተዝረከረከ ሥርዓት እንደሚጠቅስ አስረድተዋል።

መደመር የመጻኢውን ትውልድ ጥቅም እና ፍላጎት ለማሳካት እንደሚሠራ የኢኮኖሚው እድገትም ጥራቱን ጠብቆ ብቁ እና አስተማማኝ የሥራ እድል ፈጥሮ ወደብልጽግና መራመድ የሚያስችል ሥራ መሠራት እንዳለበት እንደሚያምን የገለጹት አቶ ማሞ፤ ለዚህም በግብርናው እና በአምራቹ ዘርፍ ብቻ ትኩረት ከማድረግ ብዝኃ ዘርፍ ኢኮኖሚ ወደመገንባትና ያለንን አቅም አሟጥጦ ወደመጠቀም መሸጋገር እንደሚገባ ያትታል ብለዋል። ለዚህም የማዕድኑን፣ የቱሪዝሙን፣የአይ.ሲ.ቲ (ICT)ውን

እና የኢንዱስትሪውን ዘርፍ አሻሽለን መጠቀም እንደሚገባን ያነሳል። ግብርናው እና የገጠር ልማት አሁንም ትልቅ ትኩረት እንደሚሰጠው፤ ነገር ግን ግብርናውን ከዝናብ ጠባቂነት ለማላቀቅ ትልቅ መሠረታዊ ሪፎርም ማድረግ እንደሚገባ እንደሚያሳስብ ጠቅሰዋል። በአጠቃላይም መደመር በቴክኖሎጂ አቅም ላይ የተመሠረተ እውቀት መር ኢኮኖሚ የመገንባት ትልም እንዳለው ገልጸዋል።

በኢኮኖሚው ላይ የመንግሥት ሚና ምን እንደሚሆን ሲያስረዳም፤ የኢትዮጵያ የግሉ ዘርፍ ያላደገ በመሆኑ ኢኮኖሚውን ለግሉ ዘርፍ መተው ትክክል አይደለም። ስለዚህ፤ መንግሥት በኢኮኖሚው ላይ ሚና እንደሚኖረው ያሳያል። መንግሥት ሚናውን የሚወጣውም የግሉን ዘርፍ በማይገድብና ሚናውን እንዲያሳድግ በሚያደርግ መልኩ መሆን እንዳለበትም ያምናል። በመጨረሻም የመደመር የኢኮኖሚ እሳቤ ከተናጠል እይታ ወደሥርዓት እይታ፤ ከመንግሥት ባለፈ የግሉ ዘርፍ ሚና እንዲኖረው ወደሚያበረታታ ሥርዓት፣ በውስን ዘርፍ ላይ ትኩረት ከማድረግ ወደብዝኃ ዘርፍ ትኩረት ያደረገ የኢኮኖሚ እይታ፣ የኢኮኖሚ እድገትን ብቻ ትኩረት ካደረገ ወደጥራት ያለው እድገት ያሻግራል። እንዲሁም፤ መንግሥት መር ከሆነ ኢኮኖሚ በመንግሥት እና በግሉ ዘርፍ ትብብር ወደሚመራ ኢኮኖሚ እንደሚያሻግር፣ ካፒታል ወደመንግሥት ፕሮጀክቶች ብቻ ከመሄድ ወደግሉም ዘርፍ በብድር መልክ እንዲሄድ ያደርጋል። በመንግሥት መሠረተ ልማት ግንባታ ከተመሠረተ እድገት ምርታማ ሴክተሮችን ወደሚደገፍ እድገት፤ እንዲሁም ወደውስጥ ከሚመለከት የኢኮኖሚ ሥርዓት በፉክክር ላይ ወደተመሠረተ እና ወደውጭ ወደሚያማትር የኢኮኖሚ ሥርዓት ለውጥ እንዳለ የመደመር መጽሐፍ ያስረዳል።

## የመደመር የውጭ ግንኙነት እይታ

አራተኛው የውይይት መነሻ ጽሑፍ አቅራቢ አቶ መሐመድ ራፊ ናቸው። እርሳቸውም የመጽሐፉን የውጭ ግንኙነት እይታ እንዲህ ዳስሰዋል። የመጀመሪያው የውጭ ግንኙነት እይታ ሀገራት ግንኙነት እንዲፈጥሩ የሚያደርጋቸው ዋናው ዓላማ የጎልውና ጥያቄ ነው። በተጨማሪም፣ ብሔራዊ ጥቅም እና ዘላቂ የብልጽግና እሳቤ ስላላቸው እንደሆነ ይታወቃል። ይህም ሀገራት ብቻቸውን እንደደሴት መኖር የሚችሉ አካላት ባለመሆናቸው እንደሆነ መደመር ያምናል። ለዚህ ለውጥ መነሻ የሚደርገውም በአሁኑ ወቅት ሀገራዊ ተጨባጭ ሁኔታዎች መቀየራቸው፤ የሕዝብ ፍላጎት መቀየሩ፤ እንዲሁም ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች እየተወሳሰቡ በመምጣታቸው ነው። በዚህ ሁሉ መካከል ኢትዮጵያ ጥቅሟን እና የዜጎቿን ክብር ለማስጠበቅ ከዓለም አቀፍ ሁኔታው ጋር መጓዝ የሚችል ለውጥ ማድረግ እንደሚገባ ያምናል። የመደመር የውጭ ግንኙነት

ዋና ዋና ነጥቦችም፣ ኢትዮጵያ እንደሀገር በውጭ ግንኙነት ዘርፍ ያከማቸችው ወረት፤ ማለትም ረጅም ታሪክ እና ዘመናት የተሻገረ የታላላቅ ተቋማት የዲፕሎማሲ ተሳትፎ፤ እንዲሁም በዲፕሎማሲው ዘርፍ የበቃ የሰው ኃይል መኖሩን ይረዳል። በዚህም ኢትዮጵያ በዓለም አቀፍ የሰላም እና መረጋጋት ሥራዎች ላይ ከፍተኛ ሚና ያላት ሀገር መሆኗን፣ ግንኙነቶቻችን በትብብር እና በመግባባት ላይ የተመሠረቱ መሆን አለባቸው የሚል እሳቤም አለው።

መደመር "ብሔራዊ ጥቅም የሚያስከብር፤ ዘመኑን የዋጀ የውጭ ግንኙነት ይኖረናል" የሚል እምነትም አለው። የጎረቤት ሀገራትን ያስቀደመ የውጭ ግንኙነት እንዲኖር ይመክራል። በዚህም እሳቤው በጎረቤት ሀገራት የሚኖር ችግር የእኛም ችግር ነውና በትብብር ልንሠራ እንደሚገባ እና ከጎረቤት ሀገራት፤ እንዲሁም ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት ከመጠራጠር እና ከመፈራራት በመውጣት በቀጣናው ያለውን የማደግ እድል መጠቀም በሚያስችል መልኩ ሊቃኝ እንደሚገባ ይገነዘባል። እንዲሁም፤ የኢኮኖሚ እይታዎቻችን ቀጣናዊ መሆን እንደሚገባቸው ያስረዳል። በመጨረሻም ብሔራዊ ክብርን የሚያረጋግጥ የውጭ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል የሚል እምነትም አለው።

መደመር በውጭ ግንኙነት እሳቤው ያስቀመጣቸውን ሐሳቦች በሙሉ አንድ ማስፈጸሚያ እንደሚያስፈልጋቸው ይጠቁማል። ለዚህም ሀገራዊ ኃይል እንደሚያስፈልግ እና ይህም ኃይል አንደኛ ጠንካራ የኢኮኖሚ አቅም መሆን እንዳለበት፤ በሁለተኛ ደረጃ ምንም አካል ኢትዮጵያን ከመተንኮሱ በፊት ቀድሞ ሁለት፣ ሦስት ጊዜ እንዲያስብ የሚያስገድደው ጠንካራ የመከላከያ ሠራዊት መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል። መደመር በውጭ ግንኙነት እሳቤው ምሳሌ አድርጎ በሚያስቀምጠው "አለንጋ እና ሰርዶ" እሳቤውም የጠረጴዛ ውይይትን አልፎ የሚመጣን ወገን በጠንካራ የመከላከያ ኃይል መመከት እንደሚገባና ሰርዶን ደግሞ ኃይልን ከመጠቀም ባለፈ ኢትዮጵያ ባላት የዳበረ የባህል ትውፊት በመጠቀም፤ እንዲሁም ጠንካራ ሚዲያ በመገንባት ዓለምን ማንበርከክ የሚችል አቅም መገንባት እንዳሚገባ የሚያስረዱ እሳቤዎች መያዙን አቶ መሐመድ አብራርተው፤ መደመር ዘርፈ ብዙ ዲፕሎማሲ መተግበር አለብን ይላል በማለት አስረድተዋል።

አራቱም አቅራቢዎች ሐሳባቸውን ከገለጹ በኋላ የውይይቱ ተሳታፊዎች አስተያየት እና ጥያቄዎች አንስተዋል። በጥያቄነት ከተነሱት መካከልም፣ "ለውጥ እና ቀጣይነት በመደመር እንዴት እንደተሰናሰሉ ማሳያ ቢቀርብ? ውግንና እና ማህበራዊ መደብ

የሌለው ፓርቲ አለ ወይ?  መደመር ፍኖተ ካርታ ነው ወይስ ርዕዮተ ዓለም? ኢኮኖሚውን በሀገሪቱ ካለው ፖለቲካ እና ከውጭ ግንኙነት ጋር በማስታረቅ ጉዳዮች ላይ መደመር ምን ይላል? ከእርቀ ሰላም (ብሔራዊ መግባባት) እና መደመር የትኛው ይቅደም?" የሚሉት ይገኛሉ።

አቶ ዮናስ ለተነሱት ጥያቄዎች ምላሽ ሲሰጡ፣ መደመር እራሱን እንደእሳቤ ወይም ማዕቀፊ እሳቤ እንጅ እንደአይዲዬሎጂ (ንጥረተ ዓለም) አይመለከትም። ለዚህም አይዲዬሎጂ ቀኖናዊ፣ ማለትም ነገሮችን በአንድ መስመር ብቻ የመመልከት መንገድ ስላለው እንደሆነ መደመር ያስረዳል። ነገር ግን፣ ለውጡን የሚመራበት ማዕቀፍ ነው፡ ፡ የመደመርን ተግዳሮቶችም ማረም የሚቻለው ተግዳሮት የሚሆኑ ነገሮች እዳይደረጉ በመሥራት እና በማስተማር  ይሆናል ሲሉ አስረድተዋል። መደመር "ሲነርጂ" እንዳልሆነ፤ ነገር ግን እንደአንድ ክፍል እንደሚወሰድም ሐሳብ ሰጥተውበታል፡ ፡ አቶ ይታገሱም መደመር የልማታዊ ዴሞክራሲያዊ መንግሥትን እንደሚያስቀጥል አሳውቀዋል። ብልጽግና የሰዎችን የዴሞክራሲያዊ መብቶች እና የኢኮኖሚ ብልጽግና ያስጠብቃል። "እርቀ ሰላም አይቀድምም ወይ"? ለሚለው  ሐሳብ  መደመር እርቀ ሰላም (ብሔራዊ መግባባት) እና የተቋማት ግንባታ ሁለቱንም አብሮ ማስኬድ አለብን ብሎ እንደሚያምን እና የዴሞክራሲ ባህልን በመገንባት ላይም እንደሚያምን ገልጸዋል። ይህ የሚሆነው ግን ቀጣይነት ባለው የረጅም ጊዜ ሥራ መሆኑን አሳውቀዋል። በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ የመደብ ውግንናን ማራመድ ልክ የሚሆንበት ሁኔታ ላይ ስላልሆን መደመር እንደሕዝብ የአርሶ አደሩም፣ የአርብቶ አደሩም፣ የከተማ ድሀውም፣ በተለይ ደግሞ የወጣቱን ውግንና ያራምዳል እንጂ የአንድ ወገን ውግንና የሌለው እሳቤ እንደሆነ መታወቅ አለበት ብለዋል።

የመንግሥትን ሚና በተመለከተ፣ መንግሥት በኢኮኖሚው ላይ ሚና ሊኖረው እንደሚገባ ማወቅ ያስፈልጋል። መንግሥት የሀገርንና የሕዝብን ደኅንነት የማስጠበቅ ሥራ አለበት። በተጨማሪም፣ የግሉ ዘርፍ እንዲሠራ ሥርዓት የማበጀት፤ ፍትሐዊ ተጠቃሚነትን የማረጋገጥ፣ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ሥራ ስላለበት በኢኮኖሚው ላይ ሰፊ ሚና እንደሚኖረው መረዳት ያስፈልጋል በማለት አስረድተዋል። "መንግሥት በኢኮኖሚው ላይ ጣልቃ በሚገባበት ወቅት ጉድለቶችን በምን መልኩ  መሙላት አለበት?" ለሚለው፤ መደመር የሚደርገው አሰላሳይ በሆነና እያንዳንዷን ጥቃቅን ሁነት በጥንቃቄ በሚመለከት አካሄድ እንደሆነ እንደሚያስረዳ፤ በዚህም ወቅት ጠንካራ የቁጥጥር ሥራ እንደሚኖር፤ እንዲሁም የመንግሥት ተግባር የግሉን ዘርፍ የሚደግፍ መሆን እንዳለበት አቶ ማሞ ምላሽ ሰጥተዋል።

“የውጭ ግንኙነት እሳቤው ውጭ ተመልካች ነው” በሚል ለተነሳው ጥያቄ፤ ቀደም ሲል የነበረን ሥርዓት ሲበዛ ውስጥ ተመልካች ነበር። በራሱ ችግር ባይኖረውም ከውጭው ጋር ያለውን ሚዛን ግን መጠበቅ ይገባዋል። ማለትም ነባራዊውን የኢትዮጵያ ሁኔታ ስንመለከት ከዚህ ቀደም ያልነበሩ ጎረቤቶች ተፈጥረዋል። ሶማሊያ መንግሥት መስርታለች። ከኤርትራ ጋር ያለው ግንኙነታችን እንደቀድሞው አይደለም። በቀጣናው ያለውም የኃያላን ፉክክር ወደውጭም ትኩረት በማድረግ ሀገራዊ ጥቅምን ማስጠበቅ እንዳለብን በማሰብ የተደረገ ነው የሚል ምላሽ ተሰጥቷል።









# 2.2 የአዲስ ወግ አብይ ጉዳይ፤ የሚዲያ ሚና ሐሳቦችን ለማቀራረብ

ታኅሣሥ 16 ቀን 2012 ዓ.ም

## 2.2.1 ክፍል አንድ እና ሁለት




ይህን በሚዲያ ሚና ላይ ያተኮረውን የአዲስ ወግ አብይ ጉዳይ የውይይት መድረክ “የሚዲያ ሚና ሐሳቦችን ለማቀራረብ” በሚል ርዕስ የተካሄደ ውይይት ነው። ባለፉት 16 (ዐሥራ ስድስት) ወራት የለውጥ ጊዜያት ሚዲያው የለውጡ አቀጣጣይ በመሆንም እንቅፋት በመሆንም ሲሠራ ታይቷል። በዚህም ውይይትም “የሚዲያው እና የአንቂዎች ጠንካራ ጎኖች ምን ነበሩ?” ብለን የምንማማርበት፤ “ችግሮችስ ምን ነበሩ?” በማለት እነዚህ ችግሮች ከቀጠሉ የህብረሰባችንን አንድነት ስለሚያደናቅፉ፤ ሕዝብ ስለሚያጋጩ፤ ጥላቻ ስለሚዘሩ እዳይቀጥሉ የምንመክርበት እንዲሆን ታስቦ መድረኩ እንደተዘጋጀ አቶ ንጉሡ ጥላሁን የመክፈቻ ንግግር ባደረጉበት ወቅት ጠቁመዋል።

በመጀመሪያው ክፍል ውይይት የመነሻ ሐሳብ ያቀረቡት አቶ ወንድወሰን አንዷለም፣ አቶ አማረ አረጋዊ፣ አቶ ሰለሞን ጎሹ እና ዶ/ር አጋረደች ጀማነህ ናቸው። ውይይቱን የመራው የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ዘጋቢ ጋዜጠኛ መልስካቸው አምኀ ነው። ዶ/ር ሙላቱ አለማየሁ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ "ሚዲያዎች በሽግግር ወቅት ምን መምሰል አለባቸው" የሚል የዳሰሳ ጥናት አቅርበዋል።

ዶ/ር ሙላቱ ጥናታቸው፣ የኢትዮጵያን የዴሞክራሲ ሥርዓት እና የሚዲያ ሚና ለማየት በቅድሚያ "የሀገሪቱ የሚዲያ ሥርዓት ምን ይመስላል? የሚለውን ማየት ይገባል። በሚል "በሀገሪቱ የሚገኙ የመገናኛ ብዙኃን ሽፋን፣ የሚያቀርቧቸው ምንድን ናቸው? እና የጋዜጠኞች ብቃት ምን ይመስላል?" በሚሉ ሐሳቦች ላይ መነሻ እንዳደረገ አንስተዋል። በዚህም፣ 120 (አንድ መቶ ሃያ) ጋዜጠኞችንና ከሚዲያው ጋር ግንኙነት ያላቸውን ግለሰቦች ቃለመጠይቅ በማድረግ፤ የ15 (ዐሥራ አምስት) የመንግሥትና የግል መገናኛ ብዙኃን እና 15 (ዐሥራ አምስት) የፌስቡክ እና የዩቲዩብ ሚዲያዎች የሦስት ወር መረጃ ላይ የተሠራ ትንተና መነሻ እንዳደረገ ገልጸዋል። እ.ኤ.አ ከ1991 ጀምሮ ያለውን የሚዲያን ታሪክ ስንመለከት፤ ከ1992-1996 ያለው ጊዜ በሚዲያ ታሪክ መነቃቃት የተፈጠረበት ወቅት ሲሆን፤ ሚዲዎች ባሳዩት የሙያ ጉድለት ሳቢያ ከ1996-1999 ባለው ወቅት ብዙ ተጽዕኖ ተደርጎባቸው ቁጥራቸውም ስርጭታቸውም በእጅጉ መዳከም ያሳየበት ጊዜ እንደነበር አንስተዋል። ከዚያም ከ1999-2005 ደግሞ ዘርፉ በከፍተኛ ደረጃ የተነቃቃበት፤ አዳዲስ ሐሳቦች የተሠራጩበት፤ ብዙ አዳዲስ ሚዲያዎችም የተፈጠሩበት ወቅት ነበር። በ2005 በተደረገው ምርጫ ላይም ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደነበራቸው ይታመናል። ምርጫውን ተከትሎ እስከ2007 በነበሩት ዓመታት ግን ሚዲያው ከፍተኛ ጫና የተደረገበት፤ በርካታ ሚዲያዎች የተዘጉበት እና ጋዜጠኞች ከፖለቲከኞች ጋር ለእስር የተዳረጉበት ወቅት ነበር። ከ2007-10 የነበሩት ዓመታት ደግሞ የግል ሚዲያዎች የተፈጠሩበት፤ የማህበረሰብ ሬዲዮ ጣቢያዎች የተጀመሩበት እና ብዙ የሚዲያ ሕጎች ተግባራዊ የተደረጉበት ስኬታማ ወቅት እንደነበር አስታውሰዋል። ከ2012 ጀምሮ ያለው ግን ለሚዲያው አስከፊ ወቅት እንደነበር እና በአሁን ወቅት፣ 2018/19 ደግሞ ለሚዲያ አዲስ ተስፋ የተፈጠረበት እንደሆነ አስረድተዋል።

በዚህ ወቅት 20 (ሃያ) የግል የህትመት፣ 23 (ሃያ ) የመንግሥት የህትመት ሚዲያዎች ሲኖሩ፤ 29 (ሃያ ዘጠኝ) የግል እና የመንግሥት የቴሌቪዥን ጣቢያዎች፤ እንዲሁም 72 (ሰባ ሁለት) የሬዲዮ ጣቢያዎች መኖራቸው ተስፋ ሰጭ ቢሆንም፤ ከሕዝብ ቁጥር አንጻር እና አብዛኛው ሚዲያዎች ከተማ ተኮር በመሆናቸው ዝቅተኛ

ደረጃ ላይ እንዳለ የሚያሳይ ነው። ከቋንቋ አንጻር ግን 60 (ስድሳ) ቋንቋዎች በሚዲያዎች ይሠራባቸዋል። በከተማ አካባቢ የሚሠሩ ሚዲያዎች ግን በተወሰኑ ቋንቋዎች (አማርኛ፣ እንግሊዝኛ፣ ኦሮምኛ እና ትግሪኛ) ብቻ ስለሚጠቀሙ በዚህ ረገድም ደካማ ያስብላቸዋል ብለዋል። “መገናኛ ብዙሃኑ ከሚሠሯቸው ይዘቶች አንጻር ምን ይመስላሉ? ምን ዓይነት ፕሮግራሞች ይሠራሉ? የዜና ምንጫቸው ማን ነው? የሴቶች እና የሌሎች ማህበረሰቦች ተሳትፎ ምን ይመስላል?” እና ሌሎች መጠይቆች ስንመለከታቸው ሚዲያዎች የማህበረሰቡን ድምጾች ከማሰማት አንጻር ከፍተኛ ጉድለት አለባቸው። በተለይ ማህበራዊ ሚዲያው የአንቂዎችን ድምጽ ብቻ እንደሚያሰማ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳይ ገልጸዋል። ከዘገባዎች ይዘት አንጻር የፖለቲካ እና የግጭት ጉዳዮች በስፋት ይዘገባሉ።እነዚህ ጉዳዮች በተለይ በማህበራዊው ሚዲያ ላይ ደግሞ ከፍተኛ ትኩረት እንደሚያገኙ ውጤቱ አሳይቷል። የግጭት ዜናዎችን ግጭት በሚያባብስ መንገድ የሚዘግቡ ሚዲያዎች ስለመኖራቸውም በጥናቱ ተረጋግጧል።

“የጋዜጠኞች ብቃት ምን ይመስላል?” ለሚለውም፣ አብዛኛው ጋዜጠኛ በተጽዕኖ ውስጥ እንደሚሠራና ተጽእኖውም ከተደራጁ ቡድኖች እንደሆነ ጥናቱ አሳይቷል። በዚህም የተነሳ ዘገባዎች ሚዛናዊነት እንደሚጎድላቸው፤ የማጋነን፣ ስሜታዊ የማድረግ አዝማሚያም እንደሚታይባቸው፤ የጥላቻ ንግግርንም እንደሚጠቀሙ ተመልክቷል። “መገናኛ ብዙኃን ለኅብረተሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምን ይመስላል?” በሚልም ለተነሳው ጥያቄ  ማህበረሰቡ የሚፈልገው መረጃ በትክክል እንደማያደርሱ፤ አፈጻጸማቸው  ደካማ እንደሆነና አሉታዊ፣ ብሔር ተኮር ዘገባዎች መብዛታቸው አሳሳቢ እንደሆነ ተገልጿል። ዶ/ር ሙላቱ ጥናቱም ተንተርሰው እንደማጠቃለያ ባቀረቡት ምክረ ሐሳብም የኢትዮጵያ ሚዲያዎች አሉታዊ መረጃዎችን በማሠራጨት ላይ የሚያተኩሩ፤ የአንድን ወገን  ሐሳብ  ብቻ የሚያቀነቅኑ የመሆን አዝማሚያ እየታየባቸው ስለሆነ ለመጭው ምርጫ መሳካት ከወዲሁ “የሚዲያው ሚና ምን መሆን አለበት?” የሚለው ሊታሰብበት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በመቀጠልም አቶ ወንድወሰን ሐሳባቸውን አቅርበዋል። እርሳቸውም፣ ከለውጡ በፊት ሜንስትሪም ሚዲያዎች ለመንግሥት ጭፍን ድጋፍ  ያደርጉ እንደነበረ፤ በግል ሚዲያዎች በኩል ደግሞ ጭፍን ተቃውሞ ይደረግ እንደነበረ አንስተዋል። ከመንግሥትም በኩል ከብሮድካስት አዋጆች እና ሕጎች ይልቅ የባለሥልጣናት ፍላጎት በስፋት ይጸባረቅና ይፈጸም እንደነበረም አስታውሰዋል። በዚህም ጋዜጠኛው ይታሰርና ይሳደድ ስለነበር ጋዜጠኝነትን ሙያው የሌላቸው ሰዎች ተቆጣጥረውት መቆየታቸውን

አስረድተዋል። ከለውጡ ወዲህ ግን በርካታ የሚዲያ አማራጮች የተገኙበት፤ ከለውጡ በፊት የነበሩ ጫናዎችን በመቆማቸው በውጭ የነበሩ በተቃውሞው ጎራ የተሰለፉ ሚዲያዎችም ወደሀገር ቤት ገብተው እንዲሠሩ የተደረገበት ሁኔታ ታይቷል። አሳሪ የሚባሉት የሚዲያ ሕጎችም እንዲሻሻሉ ተደርገዋል።

የሚዲያው ነጻነት መረጋገጥ እንዲችል የጋዜጠኛው የራሱ "ሰልፍ ሬጉሌሽን" የሚባለው ሐሳብ ተግባራዊ እንዲደረግም የ"ሚዲያ ካውንስል" እና "ኤዲተርስ ፎረም" የመሳሰሉ የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙ መደረጉ፤ ተቆጣጣሪው ባለሥልጣን ከዚህ ቀደም እንደነበረው መቆጣጠር ብቻ ሳይሆን የሚዲያዎችን አቅም የመገንባት ኃላፊነት የተጣለበት፤ እንዲሁም የሚዲያውን ዘርፍ የሚያበረታቱ ሕጎች ተግባራዊ የተደረጉበት እንደሆነ ገልጸዋል። ባለፉት አንድ ዓመት ተኩል ጊዜያትም ብሮድካስት ባለሥልጣን ሳይንሳዊ የሚዲያ አዝማሚያ ትንተና በመሥራት ለሚዲያዎች ማሳወቁን፤ ለዚህም ሚዲያዎች ግብረ መልስ እንዲሰጡ መድረጉን ጠቁመው፤ በአጠቃላይ በተደረጉ ማሻሻያዎች ኢትዮጵያ በሚዲያ ነጻነት ከነበረችበት 40 (ዐርባ) ደረጃዎች ማሻሻሏን ተናግረዋል። በለውጥ ወቅት በተለያየ አጋጣሚዎች የሰዎች ሰብዓዊ መብቶች ሊጣሱ እና ሊረገጡ የሚችሉበት አጋጣሚ ይኖራል። በዚህ መሰል ወቅት ሚዲያው የትኛውንም የመብት ጥሰት በማጋለጥ ነገሮች እንዲስተካከሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት። ከዚህም ባሻገር ሚዲያው ሕዝቡን ማሳወቅ እንደሚገባው አሳስበዋል።

አቶ አማረ አረጋዊ በበኩላቸው፣ የኢትዮጵያ የመገናኛ ብዙኃን ካውንስልን በተመለከተ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በማብራሪያቸውም የሚዲያው ካውንስል ከተለያየ ውጣውረድ በኋላ የተቋቋመ እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ማሻሻያ ሲደረግ ሕጋዊ እውቅና ያገኘ ማህበር እንደሆነ አስረድተዋል። ማህበሩ የመንግሥትንና የግል ሚዲያዎችን፤ እንዲሁም የተለያዩ የሙያ ማህበራትን በአባልነት ያቀፈ እንደሆነ፤ ዓላማውም የሚዲያውን ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ እና የሕዝቡን መረጃ የማግኘት መብት ማስጠበቅ ሲሆን፤ የሚሰጠው መረጃም ሕዝብን እንዳያሳስትና እንዳይጎዳ የሚቆጣጠር መሆኑን ገልጸዋል። ካውንስሉም ሦስት አካላት እንዳሉት የጠቆሙት አቶ አማረ ይህን መሰል አሠራር በብዙ ሀገሮች የተለመደ እንደሆነ ጠቁመው፤ መንግሥታትም የሚዲያ ነጻነትን ይገድባሉ፤ ጋዜጠኞችን ያስራሉ ከሚለው ወቀሳ እንዲድኑ ያደረጋቸው አሠራር መሆኑን አስረድተዋል።

ሌላኛው የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢ አቶ ሰለሞን ጎሹ የመገናኛ ብዙኃን ሐሳብን የማቀራረብ ሚናቸውን ከሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች እይታ አንጻር በሚል ሓሳብ

አቅርበዋል። እርሳቸውም፣ ዴሞክራሲያዊ ሽግግር በሚያደርጉ ሀገራት የመገናኛ ብዙኃን እና የሲቪል ማህበራት በጋራ በመተባበር ይሠራሉ። ይህንን በተገበሩ ሀገራትም ዴሞክራሲያዊ ሽግግሮችን ሲያፋጥን ተመልክተናል ብለዋል። ይህንም ተሞክሮ ወደሀገራችን ብናመጣውና ሁለቱ አካላት በተደራጀ እና መዋቅራዊ በሆነ መንገድ ሐሳቦችን ለማቀራረብ ቢሠሩ ለውጡን ውጤታማ እና ዴሞክራሲያዊ ለማድረግ ትልቅ ሚና እንደሚጫወቱ አንስተዋል። የፖለቲካ ፓርቲዎችም በዚህ ልዩነት የሚታይባቸው እንደመሆናቸው በጥንቃቄ ሊሠራበት እንደሚገባ አሳስበዋል። የመገናኛ ብዙኃን እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ከለውጡ በፊት በነበሩ ሁኔታዎች በጫና እና በጥብቅ ቁጥጥር ሥራ ሲሠሩ እንደነበር፤ ነገር ግን የለውጡ አስተዳደር የሁለቱንም ተቋማት ሚና በመረዳት የተለያዩ የፖሊሲና የሕግ ማሻሻያዎችን በማድረግ ለውጡን እንዲያግዙ ማድረጉ በመልካም የሚታይ መሆኑን አብራርተዋል።

የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶችም አንደኛ እራሳቸው የጋዜጠኞች የሙያ ማህበራት እና መሰል ተቋማት በመገናኛ ብዙኃን ላይ እንዲሠሩ ማድረጋቸው፣ በሁለተኛ ደረጃ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች በሚዲያ ኅብረተሰብን በማስተማር፣ የሚዲያ ባለሙያዎችን አቅም የሚገነቡ ሥራዎችን በመሥራት፣ ለውሳኔ ሰጭዎች እና ለሚዲያው የሚያገለግሉ የተለያዩ ጥናቶችን እና ትንተናዎችን በማድረግ እንደሚያግዙ ጠቅሰው፤ አሁንም ለውጡ በፈጠረላቸው የፖሊሲና የሕግ ማሻሻያ መልካም አጋጣሚ በመጪው ምርጫ ላይ በጎ አስተዋጽዖ ለማድረግ እየተንቀሳቀሱ እንደሚገኙ ገልጸዋል።

በመጨረሻም ዶ/ር አጋረደች ጀማነህ ነባር የመገናኛ ብዙኃን (Traditional media) በሚባሉት ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥን እና ጋዜጣ ምንነት ላይ ገለጻ አድርገዋል። እነዚህ የሥነ ተግባቦት ዘዴዎች አንድም በብዙ ባለሙያዎች የጋራ ሥራ የሚሠሩ መሆናቸው፤ ለሙያዊ ሥነምግባሮች እንዲከበሩ አንጻራዊ እድል የሚሰጡ እንደሆኑ፤ እንዲሁም ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቁ እንደመሆናቸው በተጽእኖ ውስጥ እንደሚወድቁ፤ በተቃራኒው የማህበራዊ ሚዲያ (ዲጂታሉ) በግለሰቦች የሚዘወር በመሆኑ ለሙያ ሥነምግባር እንደማይገዛ እና የግል ፍላጎት ማራመጃ የመሆን እድሉ ከፍተኛ እንደሆነ አውስተዋል። ለህብረተሰብ የእርስ በርስ ግጭትም ከፍተኛ ሚና እንዳለው አስረድተዋል። የሚዲያ የሥነ ምግባር ችግር ምንጮች ብዝኃነትን አለማካተት፣ የጋዜጠኞች አቅም ውስንነት እና ሕጎችን እና የአሠራር መመሪያዎችን አለማወቅ ወይም አለመተግበር መሆናቸውንም አስረድተዋል።

በቀረበው የውይይት መነሻ ሐሳብ ላይ ከተሳታፊዎች፣ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት

ቤት እዚህ ጉዳይ ላይ መሥራት ይጠበቅበት ነበር ወይ? በሚዲያው ላይ የብዝኃነት እና የውክልና ችግር አለ። በተለይ የሴቶች ውክልና ይህን እንዴት ታዩታላችሁ? ሚዲያውን አሁን ላለንበት ችግር ተጠያቂ የማድረግ አዝማሚያ አለ። ነገር ግን መንግሥት የክልሎች አወቃቀር እና ሕገመንግሥቱ ነው ለዚህ ሁሉ ችግር መንስኤው። ሚዲያው የዚህ ችግር ተጠቂ እንጂ ተጠያቂ አይደለም። ሚዲያው ምንም አልተለወጠም። በዚህ ላይ ለውጥ እንዲመጣ መሠራት አለበት። የማህበራዊ አንቂነት እና ጋዜጠኝነት መለየት ይቻላል ወይ? የሚዲያው አካሄድ አስፈሪ እየሆነ ነው። ይህን ለማስቆምና ችግሩን ለመፍታት መንግሥት በእጁ ያሉ መቆጣጠሪያ ሕጎችን ተጠቅሞ ርምጃ መውሰድ አለበት? የሚሉ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ተነስተዋል።

ዶ/ር ሙላት ዓለማየሁ በሰጡት ምላሽ፤ ሚዲያው በብዙ መንገድ መለወጡን፤ ለዚህም በብዛት ደረጃ ለውጥ እንዳለ፤ በዓይነትም የማህበረሰብ ሬዲዮዎች መበራከታቸው እና በተቃውሞው ጎራ ተሰልፈው በውጭ ሀገር የነበሩ ሚዲያዎችም ሀገር ውስጥ ገብተው እየሠሩ መሆናቸው ትልቅ ለውጥ መሆኑን አስረድተዋል። ነገር ግን ሌሎች አልተለወጠም ሊያስብሉ የሚያስችሉ ባሕሪያት እንደሚኖሩም ገልጸዋል። በጋዜጠኝነት እና በአክቲቪዝም መካከል ስላለው ልዩነትም፤ ጋዜጠኝነት ምህዳሩ ሰፊ እና ለሁሉም ኅብረተሰብ ክፍል የሚሠራ ሲሆን፤ አክቲቪዝም ግን በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ ለምሳሌ በሴቶች መብት፣ ወይም ሰብዓዊ መብት ላይ ብቻ ለሚጽፉ ሰዎች የሚሰጥ መጠሪያ እንደሆነ አስረድተዋል። ከመገናኛ ብዙኃን ጥንካሬ አንጻር መንግሥት ዘርፉን እየደገፈ ባይሆንም ዘርፉ ግን በራሱ መንቀሳቀስ መቻሉ ጥንካሬው እንደሆነ አንስተው ከመንግሥት በኩል መረጃ ለሚዲያዎች የመስጠት ክፍተት ትልቁ የሚዲያው ችግር መሆኑን አንስተዋል።

አቶ ወንድወሰን በበኩላቸው፣ “የሚዲያ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን ለምን ርምጃ አይወስድም?” ለሚለው መንግሥት የሥነ ምግባር ግድፈት ባለባቸው ሚዲያዎች ላይ ርምጃ ከመውሰዱ በፊት እንደስትራቴጂ ይዞ ከዚህ ቀደም አሳሪ ሲባሉ የነበሩ የሚዲያ ሕጎችን ማሻሻል እና የሚዲያ ፖሊሲ ማዘጋጀት፤ እንዲሁም ጋዜጠኞችን በሥነ ምግባር እና በክህሎት ማብቃት፤ በተለያየ መንገድ ሥልጠና በመስጠት የአቅም ክፍተት ለመሙላት እየሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። ባለሥልጣኑ በሚያደርገው ክትትል መነሻነትም ለሁሉም ሚዲያዎች የግምገማ ሪፖርት በማድረስ የማስተካከያ ርምጃ እየወሰደ፤ እንዲሁም ማስጠንቀቂያም እየሰጠ እንደሆነ አስታውቀዋል። በመንግሥት በኩል ያሉ ክፍተቶች ከተስተካከሉ በኋላ ግድፈት ባለባቸው ሚዲያዎች ላይ ርምጃ መውሰድ እንደሚጀምርም አሳውቀው፤ እንደዚያ ከማድረግ የዘገየውም ወደኋላ

መመለስ ነው ተብሎ ስለታመነበት እንደሆነ አስረድተዋል።

አቶ አማረ አረጋዊም ሚዲያው ሀገሪቱ ላይ እተፈጠሩ ላሉ ችግሮች ሁሉ ተጠያቂ ሊደረግ እንደማይገባው መንግሥትም በየሥራ ተዋረዱ በሚፈጠሩት ግጭቶች እና የሰላም እጦቶች ላይ ድርሻ እንዳለው አሳውቀው፤ ካውንስሉ በሚዲያው የሚፈጸሙ የሙያ ግድፈቶችን ለማረም፤ ከሕዝብ ጋር በእርቅ የሚፈቱትን ችግሮች ለመፍታት እና የሙያ ግድፈት የሚያሳዩ ጋዜጠኞችን እና ሚዲያዎችንም ለማረም የተቋቋመ እንጂ የሕግ ሥርዓቱን መተካት ዓላማው እንዳልሆነ በመግለጽ በሕግ ሊጠየቅ የሚገባው ጥፋት ያጠፍ ሚዲያ እና ጋዜጠኛ ተጠያቂ ከመሆን እንደማይቀር አስረድተዋል።

ዶ/ር አጋረደች በጋዜጠኞች የሥነ ምግባር እና የአቅም ችግሮች ላይ ያሉትን የተለያዩ የአዘጋገብ እና የአሠራር ክፍተቶች አንስተው እንዴትስ መስተካከል አለባቸው? ለሚለው መልስ ሰጥተዋል። ውክልናን በተለይም የሴቶችን ውክልና፤ እንዲሁም የብዝኃነት ችግር የሚዲያዎቻችን መገለጫዎች እንደሆኑ አስረድተዋል። በተጨማሪም አቶ ሰለሞን ጎሹ የመገናኛ ብዙኃን ለሁሉም ችግሮች መንስኤ ተደርጎ የመወሰድ አዝማሚያ ልክ እንዳልሆነ ተናግረዋል። ከለውጡ በኋላ ግን በመገናኛ ብዙኃን ላይ ከፍተኛ ለውጥ መኖሩንና በዘርፉ ተዋንያን ላይ ግን የሙያ እና የአቅም ውስንነት እንዳለ፤ ይህም በሚዲያዎች ላይ ለሚታዩ ክፍተቶች ምንጭ እንደሆነም ገልጸዋል።






OF THE PRIME MINISTER


ETHIOPIA:
A NEW HORIZON OF HOPE
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# 2.2.2 ክፍል ሦስት፣ ዲጂታል ሚዲያ

በዚህኛው የውይይት ክፍለ ጊዜ “ዲጂታል ሚዲያ ምንድነው?” እና “በሚዲያው ዘርፍ ያለው ተጽዕኖ ምንድን ነው?” በሚሉ ሐሳቦች ላይ ውይይት ተደርጓል። የውይይቱ መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎችም አቶ ነጻነት ተስፋዬ የኮሙኒኬሽን ባለሙያ፣ ወ/ሮ መስከረም አበራ፤ እንዲሁም አቶ ኤልሻዳይ ነጋሽ የዲጂታል ሚዲያ የኮርፖሬት ጉዳዮችና የኮሙኒኬሽን አማካሪ ናቸው። ውይይቱን በአወያይነት የመራው ጋዜጠኛ ኤልያስ መሠረት ነው።

በመጀመሪያ አቶ ነጻነት ተስፋዬ ማህበራዊ ሚዲያ በኢትዮጵያ ያለው ገጽታ ተጽዕኖው እና ውጤቱ፤ እንዲሁም መፍትሔው ምን ይመስላል? በሚለው ጉዳይ ላይ ሐሳብ አቅርበዋል። አሁን ባለንበት የኢንተርኔት ተደራሽነት መስፋፋት ምክንያት የማህበራዊ ሚዲያው ተጠቃሚ ቁጥር በእጅጉ ጨምሯል። በቀን ውስጥ አንድ ሚሊዮን ያክል የፌስቡክ፣ አራት ሚሊዮን የዩቲዩብ ተመልካቾች ያሉ ሲሆን፤ በአማካኝ አንድ ሰው በቀን 2:23 ሰዓት (ሁለት ሰዓት ከሃያ ሦስት ደቂቃ) በማህበራዊ ሚዲያ ላይ እንደሚያጠፋ ተናግራዋል። በ“ፕላትፎርም” ደረጃ ደግሞ አንድ ሰው በፌስቡክ ላይ 58 (ኀምሣ ስምንት) ደቂቃ እና ዩቲዩብ ላይ 40 (ዐርባ) ደቂቃ በቀን እንደሚያጠፋ እና በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ ተጠቃሚ ያለው ፌስቡክ እንደሆነ አሳውቀዋል። ማህበራዊ ሚዲያ ጠንካራ ማህበራዊ ትስስር መፍጠር አስችሏል። በሥነ ጽሁፍ ተደራሽነት ላይ ብዙ እድል ሰጥቷል። የተለያዩ ሕገወጥ ሥራዎችን ለመከላከል እድል ፈጥሯል። የመረጃን ተደራሽነት አፋጥኗል። የእውቀት ሽግግር ፈጥሯል። የፖለቲካ ፓርቲዎች ተጠቅመውበታል። አንቂዎች መድረኩን ሐሳባቸውን ለማራመድ ተጠቅመውበታል። በአጠቃላይ ሐሳብን ለመግለጽ በሰፊው ጥቅም ላይ ውሏል።

በሌላ በኩል፣ ማህበራዊ ሚዲያውን በመጠቀም ትክክለኛ ያልሆኑ እና በማህበረሰቡ ላይ አሉታዊ ውጤት ሊያሙጡ የሚችሉ ሐሳቦች የሚሠራጩ ወገኖች እንዳሉ እና ታዋቂ ናቸው የሚባሉ ግለሰቦች የሚለጥፏቸውን የትኛውንም መረጃ ያለምንም ማገናዘብ የመቀበል አዝማሚያም በስፋት ይታያል ብለዋል። ግጭት የሚያበረታቱ ሐሳቦችን የሚቃወም ቢኖርም ከፍተኛ ቁጥር ያለው ደጋፊም የሚታይበት መድረክ እየሆነ እንደመጣም አንስተዋል።

ማህበራዊ ሚዲያው በዚህ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉ ጥላቻን ይሰብካል። በተጨማሪም፣ ሐሰተኛን መረጃ እውነተኛ አስመስሎ ለማቅረብ እየተሠራበት ነው። ከ2010 ዓ.ም ወዲህ ለዚህ ዓላማ የሚውሉ በርካታ አካውንቶች ተከፍተውም አስተውለናል።

በዚህም የሀገርን ደኅንነት ስጋት ላይ የሚጥሉ መረጃዎች ይሠራጭበታል። መንግሥትን መቃወም በሚል የተቀነባበሩ ሐሳቦች፤ በከፍተኛ የመንግሥት ኃላፊዎች ላይ ትኩረት ያደረጉ ሐሰተኛ መረጃዎች በስፋት እየተሠራጩ እንደሆነ እና ሚዲያው አሳሳቢ ሀገራዊ የችግር ምንጭ መሆኑን አስረድተዋል። ይህንን ለመከላከልና ጉዳቱን ለመቀነስ መንግሥት ትክክለኛ መረጃ በፍጥነት በማድረስ እንዲሠራና፣ ሕዝቡም ትክክለኛውን መረጃና ምንጭ ለይቶ መጠቀም እንዲለመድ፤ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ምህዳሩን በትክክለኛ መንገድ በመጠቀም ሕዝቡን ትክክለኛ ወደሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዲለማመድ እንዲያደርጉ አሳስበዋል።

ወ/ሮ መስከረም አበራ ትክክለኛ የዴሞክራሲ ግንባታ እና ሽግግር እንዲኖር ትክክለኛ መረጃ ያለው ሕዝብ ያስፈልጋል። ስለዚህ ሕዝብ ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ ደግሞ ሚዲያ ወሳኝ ነው ብለዋል። “ሚዲያ እና መንግሥት፣ ሚዲያ እና ሕዝብ፤” እንዲሁም “ሚዲያ እና የጋዜጠንነት ሥነ-ምግባር” ከሚሉት እሳቤዎች ጋር በተያያዘ የተለያየ ሐሳብ የሚያራምዱ ንድፈ ሐሳቦች አሉ። አንደኛው ፈላጭ ቆራጭ (Authoritarian) የሚባለው ጽንሰ ሐሳብ ነው። በዚህም መንግሥት ሚዲያውን ፈቃድ በመስጠት፣ ቅድመ ምርመራ በማድረግ እና በተለያየ መንገድ ይቆጣጠረዋል። ሁለተኛው የኮሚኒስት ንድፈ ሐሳብ የሚባለው ሲሆን ይኸኛው ደግሞ መንግሥት ሚዲያውን በባለቤትነት ይዞ የፖሮፓጋንዳ ማሽን ያደርገዋል። ሦስተኛው ለዘብተኛ (Libertarian) ጽንሰ ሐሳብ ሲሆን፤ በዚህ ደግሞ ጋዜጠኞች እና የሚዲያ ባለቤቶች የፈለጋቸውን የሚያሠራጭበት ሚዲያ ነው። ነገር ግን ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በዓለም ላይ የተፈጠረውን እልቂት እና የሚዲያውን ተጽዕኖ በማየት ምሁራን አራተኛ ጽንሰ ሐሳብ አፈለቁ። ይህም “ሕዝባዊ ኃላፊነት የሚሰማው” (Social-Responsibility Theory) ይኸ የሚዲያ ጽንሰ ሐሳብ ሚዲያው ነጻነት ቢኖረውም ነጻነቱን በሙያ ሥነምግባር መሠረት እና የማህበረሰብ ደኅንነት መጠበቁን የሚያረጋግጥ አካል ያለበት የሚዲያ ሥርዓት ነው።

ወ/ሮ መስከረም በአራተኛ ደረጃ ባስቀመጡት ጽንሰ ሐሳብ መሠረት ኃላፊነት የሚሰማው ሚዲያ ለሥነ ምግባር የሚገዛ እና ለሕዝብ ደኅንነት ሲባል ትክክለኛ መረጃ የሚያቀርብ፤ በመረጃ ላይ ትንታኔ በማቅረብ በሕዝብ ላይ የሚኖራቸውን ተጽዕኖ የሚያስረዳ መሆን እንዳለበት እና ሕዝብን ማሳተፍ እንደሚኖርበት፤ ነገር ግን፤ ገበያ ተኮር በሆኑ ሥራዎች ላይ መሳተፍ እንደሌለበት የሚከለክል እሳቤ እንዳለው አስረድተዋል። “ይህ ጽንሰ ሐሳብ በዲጂታል ሚዲያው ላይ እንዴት ይተገበራል?”

በሚለው ላይ ግን ብዙዎቹ ኃላፊነት የሚሰማው የሚዲያ ጽንሰ ሐሳብ፣ ማለትም ለሥነ ምግባር ተገዥነት፣ የመረጃ ትንተና መስጠት እና ለሕዝብ ደኅንነት መሥራት የሚሉትን ሐሳቦች ተግባራዊ ማድረጋቸውን መቆጣጠር የማይቻል እንደሆነ፤ ነገር ግን ዲጂታል ሚዲያው ሕዝብን ማሳተፍ የሚያስችል ገጽታ እንዳለው አስረድተዋል። ይህም ማለት የማህበራዊ ሚዲያውን መቆጣጠር አንችልም ወደሚለው ድምዳሜ እንደሚወስደን፤ ነገር ግን ማህበራዊ ሚዲያው የተጠቃሚውን ሕዝብ የሚዲያ ንቃተ ህሊና በማሳደግ ላይ ቢሠራ ሕዝቡ ትክክለኛውን መረጃ ከሐሰተኛው መረጃ መለየት የሚያስችለው አቅም በመፍጠር ችግሩን መቋቋም ወይም መቀነስ እንደሚቻል አስረድተዋል። በአጠቃላይ ይህን የማህበራዊ ሚዲያን ጫና ለመቋቋም ግን መደበኛው የመገናኛ ብዙኃን የሕዝቡን የሚዲያ ንቃተ ህሊና የሚያጎለብቱ ፕሮግራሞችን በስፋት እንዲሠራ ማድረግ ያስፈልጋል። በማህበራዊ ሚዲያው ላይ ያሉ በእድሜ እና በትምህረት የዳበረ ልምድ እና እውቀት ያላቸው ሰዎችም ምህዳሩን ትተው ከመውጣት ይልቅ እዚያው ቆይተው ማስተማር እንደሚገባቸው፣ "ብሎገሮች"ን በማሰባሰብ እንዲደራጁ፤ መረጃ እንዲለዋወጡ የሚያስችል በማህበር የሚታቀፉበትን ሁኔታ በመፍጠር ሊሠራበት እንደሚገባ አሳስበዋል።

በውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች ዝግጅት ላይ መሠረት ያደረጉ፤ በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ለሚጻፉ ነገሮች ተጠያቂነትን ለማስፈን እየተሠራ ያለ ሥራ ነበር የት ደረሰ? የማህበራዊ ሚዲያ ሱሰኝነት እንዴት ይታያል? የሚሉ ጥያቄዎችና የማህበራዊ ሚዲያውን የጥፋት ምንጭ እንዳይሆን የቁጥጥር ሥራ ለመሥራት የሕግ ማእቀፍ ማዘጋጀቱ እንዳለ ሆኖ ጉዳዩ በሕግ ብቻ የሚፈታ ባለመሆኑ ሁሉም የህብረሰተብ ክፍል እና መንግሥት በጋራ የአመለካከት (የግንዛቤ) ሥራ መሥራት ይጠበቅብናል። የሚል አስተያየት ከተሳታፊዎች ተሰንዝረዋል። በተጨማሪም፣ የጥላቻ ንግግር ሕግ ሊወጣ እንደሆነ እየተሰማ ነውና ሕጉ ከመጽደቁ በፊት ሕዝባዊ ውይይት ሊደረግበት ይገባል። በሌላ በኩል፣ የጥላቻን ንግግር የጥላቻ ሕግ በማውጣት ማስቀረት አይቻልም። ይህም በጥናትና በሌሎች ሀገሮች ልምድም የተረጋገጠ ነው የሚሉ ሐሳቦችም ተነስተዋል።
አቶ ንጉሱ ጥላሁን በሰጡት አስተያየት፤ የሚዲያ ሰዎች ይታሰራሉ የተባለው አንዳንድ ስህተቶች እንዳለበት፤ በውጭ የነበሩ ሚዲያዎች ወደሀገር እንዲገቡ በር ክፍት መደረጉን አንስተው፤ በእኛ በኩል ሐሳቦችን ለማቀራረብ ሥራ እንሥራ ብለን ጀምረናል። ነገር ግን ሌሎች ብዙ ችግሮችም አሉ። ሁሉንም በአንዴ መፍታት እንደማይቻል መረዳት ይገባል። በመረጃ ተደራሽነት ላይ ለሚነሱ ጥያቄዎች ግን ከለውጡ በኋላ ከ40 (ዐርባ) እስከ50 (ኀምሣ) የሚደርሱ የሚዲያ ተቋሞች በዘጋቢነት ተመድበው በየቀኑ ከጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት መረጃ እንዲያገኙ

ተደርጓል። ጠቅላይ ሚኒስትሩም በየቀኑ ያላቸውን እንቅስቃሴ እያሳወቁ ስለሆነ ጥሩ ጅምር መኖሩን ማመን ይገባል። ብለዋል።

አቶ ነጻነት በጉዳዩ ላይ ሰፋፊ ጥናቶች መደረግ አለባቸው። ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ሊታሰብበት እና ዩኒቨርሲቲዎች ሊሠሩበት የሚገባ ነው ብለዋል። ከሱሰኝነት ጋር በተያያዘም ጉዳዩ ብዙ የጤና ችግር መሆኑ እየታየ እንደሆነና በዚህም ላይ ማስተማር እና መሥራት እንዳሚገባ አሳስበዋል። የማህበራዊ ሚዲያውን ለጥሩ ነገር ለማዋል በእውቀት እና በርጋታ ልንጠቀምበት ይገባልም ብለዋል። መጪው ጊዜ ምርጫ እንደመሆኑ የማህበራዊ ሚዲያው ላልተፈለገ ተግባር እንዳይውል ቀድመን ልናስብበት እና በወቅቱ ሐሰተኛን  መረጃ የሚከላከል አካል አቋቁሞ ለመሥራት ሊታሰብበት ይገባል ብለዋል። ወ/ሮ መስከረም በበኩላቸው፣ ማህበራዊ ኃላፊነት ያለው የሚዲያ ንድፈ ሐሳብ በዚህኛው የዲጂታል ተለዋዋጭነት አንጻር ክፍተት ሊኖረው እንደሚችል ይታወቃል። ለዚህም መፍትሔ እንደሚያስፈልገው እና በተለያዩ ሁኔታዎች ተቀባይነት ኖሯቸው በሚዲያው ላይ የሚጽፉ ሰዎች እስከ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ድረስ ቀርበው የሚጠየቁበት ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል። እንዲሁም በትላልቅ የመንግሥት ኃላፊነት ላይ የሚገኙ ሰዎች ማህበራዊ ሚዲያው ላይ የሚጽፉበት መንገድ አርዓያ ከመሆን አንጻር ክፍተቶች ይስተዋልበታል እና ማስተካከያ ቢያደርጉ ብለዋል።

አቶ ኤልሻዳይ ማህበራዊ ሚዲያ ሱሰኝነትን የመሳሰሉ ችግሮች እንዳሉት ቢታወቅም "ፕላትፎርሙ"ን እንደአንድ መልካም አጋጣሚ ልናየውና ልንሠራበት እንደሚገባ አስረድተዋል። ለውጥ ከመጣ በኋላ ባለው ጊዜ ውስጥም ሚዲያው በመንግሥት ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራበት መሆኑ ጥሩ እንደሆነ ጠቁመው፤ ነገር ግን አሁን እየተተገበረ ባለው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ላይ ሚዲያው ምንም ቦታ እንዳልተሰጠው ገልጸዋል። ሚዲያው በራሱ የኢኮኖሚ ማሻሻያው አንድ አካል መሆን እንዳለበትም አሳስበው፤ መንግሥት በሚዲያ ላይ  የሚያደርገው ኢንቨስትመንት ከሌሎች ሴክተሮች ባልተናነሰ ከፍተኛ የታክስ ገቢ መሰብሰብ የሚያስችል አቅም እንደሚፈጥር አብራርተዋል።

# 2.3 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ የግብርና ዘርፍ ቁልፍ የሪፎርም ርምጃዎች

ጥር 28 ቀን 2012 ዓ.ም




በዚህ የአዲስ ወግ የውይይት መድረክ “የግብርና ዘርፍ” በሚል ርዕሰ ጉዳይ የለውጡ አስተዳደር ተግባራዊ እያደረገ ባለው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ በግብርና ዘርፍ ላይ የተለየ ትኩረት ሰጥቷል። የግብርናው ዘርፍ ከፍተኛውን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የሚሸፍን ቢሆንም፤ የምርታማነት ችግር ያለበት በመሆኑ በሪፎርሙ የዘርፉ ችግሮች ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ ይገኛል። ይህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም የዚህ የሪፎርም ርምጃዎች ምን እንደሚመስሉ በማየት፤ እንደዚሁም የዘርፉ ባለድርሻ አካላትንም ምልከታ በማካተት ተዘጋጅቷል። በዚህ መድረክ ላይ በግብርና ሚኒስቴር የፖሊሲ አማካሪ ዶ/ር አንተነህ ግርማ በሪፎርሙ ርምጃዎች ላይ አጠር ያለ ገለጻ አቅርበዋል። ሌሎች የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች ደግሞ፤ ወ/ሮ አስከበረች ከኦሮሚያ የኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ፌዴሬሽን ሥራ አስኪያጅ፣ ዶ/ር ወርቅነህ ከግብርና ሚኒስቴር፣ ዶ/ር አለማየሁ ኢኮኖሚስት፣ አቶ ጀማል አሕመድ ደግሞ ከሚድሮክ ኢትዮጵያ ናቸው። የውይይት መድረክ መሪ የግብናና ኢኮኖሚስት እና በዘርፉ አማካሪ የሆኑት ወ/ሮ ላቀች ሚካኤል ናቸው።

## የግብርና ዘርፍ የሪፎርም ሥራዎች

በውይይቱ መጀመሪያ ላይ ዶ/ር አንተነህ ግርማ ባደረጉት ገለጻ የሀገራችን የግብርና ዘርፍ ላለፉት 20 (ሃያ) ዓመታት የተለያዩ የሪፎርም ርምጃዎች ሲያደርግ የቆየ ሲሆን ከ20 (ሃያ) ዓመታት በፊት 100 (አንድ መቶ ) ሚሊዮን ኩንታል ያልሞላ ምርት ይሰበሰብ ከነበረበት በዘንድሮው የምርት ዘመን ወደ 325 (ሦስት መቶ ሃያ አምስት) ሚሊዮን ኩንታል ምርት ማምረት የሚያስችሉ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ ለዚህም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደረጉት የስንዴ ምርት ከ16 (ዐሥራ ስድስት) ወደ29 (ሃያ ዘጠኝ) ኩንታል በሄክታር እና የበቆሎ ከ19 (ዐሥራ ዘጠኝ) ወደ42 (ዐርባ ሁለት) ኩንታል በሄክታር ማምረት በመቻሉ ነው፡፡ በእንስሳት ዘርፍም በጣም ዝቅተኛ የነበረው የወተት ምርት ከ3.7 (ሦስት ነጥብ ሰባት) እስከአራት ቢሊዮን ሊትር መድረስ መቻሉ ትልቅ የምርታማነት ማደግ በመኖሩ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ዘርፍ ለአጠቃላይ ሀገራዊ ምርት ከ19 (ዐሥራ ዘጠኝ) ሚሊዮን ዶላር ወደ27 (ሃያ ሰባት) ሚሊዮን ዶላር እድገት እንዳሳየ፤ ይህም የምርታማነት ዕድገት በገበሬው ሕይወት ላይ ለውጥ እንዳመጣ በ1988 የገጠር የድኅነት ምጣኔ 47.5% (ዐርባ ሰባት ነጥብ አምስት በመቶ) የነበረው በ2008 ዓ.ም ወደ25.6% (ሃያ አምስት ነጥብ ስድስት በመቶ) እንዲቀንስ እንዳደረገም አስረድተዋል ፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ለውጦች እንደተጠበቁ ሆነው የኢትዮጵያ የሕዝብ ቁጥር በከፍተኛ መጠን እየጨመረ በመሆኑ የሕዝቡን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ እያደገ ላለው ኢንዱስትሪ በቂ የጥሬ እቃ ለማቅረብ እና ሀገሪቱ ከወጪ ንግድ የምታገኘውን ገቢ ከፍ ለማድረግ የግብርናው ምርታማት ከዚህ በላይ ማደግ አለበት፡፡ አዳዲስ የግብርና ምርቶችንም ማምረት እንደሚገባ ይታመናል፡፡ በዚህ ሁሉ ሂደት ውስጥ ደግሞ ግብርናውን በማዘመን ለወጣቱ አዳዲስ የሥራ እድሎችን የሚፈጥር ዘርፍ እንዲሆንም እንደሚፈለግ ገልጸዋል፡፡ እንዲሁም የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር የተስማማ እንዲሆን ለማድረግ ግብርናው በአካባቢ ጥበቃ ላይ ብዙ ሥራ እንደሚጠበቅበት አንስተዋል፡፡ የሀገሪቱ ኢኮኖሚ ከዝቅተኛ የምርታማነት ደረጃ ወደከፍተኛ ምርታማነት ወዳለው የኢኮኖሚው ዘርፍ በሚደረገው ሽግግር ግብርና ከታች ሆኖ ማገዝ እንዳለበት እንደሚታመን አስረድተዋል፡፡

ዘርፉ የሚጠበቅበትን ውጤት እንዳይሰጥ ማነቆ የሆኑ ብሎ የግብርና ሚኒስቴር የለያቸው ጉዳዮች አሉ፡፡ እነርሱም የመሬት አስተዳደር እና አጠቃቀም ሥርዓታችን ያልዘመነና

ያልተደራጀ መሆኑ፤ የተበጣጠሰ መሬት አጠቃቀም፣ ለግብርናው በግብዓትነት የሚውሉ የቴክኖሎጂ እና ሌሎች አቅርቦቶች በመንግሥት አቅራቢነት ቀጣይነት በሌለው መልኩ ሲሠሩ መቆየታቸው፣ ለግብርናው ዘርፍ የሚመደበው ፋይናንስ ዝቅተኛ መሆን፤ ለግብርናው ዘርፍ የኢንሹራንስ አቅርቦት ዝቅተኛ መሆኑ፣ የምርት ግብይት ሥርዓቱ አርሶ እና አርብቶ አደሩን የሚያበረታታ አለመሆኑ፤ ግብርናው የዝናብ ጥገኛ መሆኑና የተሠሩ የውሀ ተቋማት በአግባቡ ጥቅም ላይ አለመዋላቸው፣ የግሉ ዘርፍ በግብርናው ዘርፍ በስፋት እንዲሠራ ማበረታቻ አለመኖሩ፤ እንዲሁም የዘርፉን ችግሮች ለመለየት እና ለማረም የሚያስችል ስልት ለመዘርጋት የዘርፉ የማስፈጸም አቅም እጥረት ያለበት መሆኑ ናቸው። በአጠቃለይ፤ የግብርናው ዘርፍ "መዋቅራዊ ሽግግሩ ዘግይቷል" ወይም "ሽግግሩ አልመጣም" በሚል እንደሚወሰድ አስረድተዋል። ስለዚህ እነዚህን ችግሮች ለመፍታት የአስተሳሰብ፣ የሥርዓት እና የአሠራር ለውጥ እንደሚያስፈልግ ሚኒስቴሩ እንደሚያምን ገልጸዋል።

የአስተሳሰብ ለውጥ ሲባል "የኢትዮጵያን ግብርና ወዴት ነው ማሻሻገር ያለብን?" የሚለውን የሚያካትት እንደሆነ እና መሻገር ሲባል ውስጣዊ መዋቅራዊ ሽግግር ማድረግ እና ለሀገሪቱ መዋቅራዊ የኢኮኖሚ ሽግግር መሠረት የሚሆን የግብርና ዘርፍ እንዲኖር ማስቻል እንደሆነ አብራርተዋል። ውስጣዊ መዋቅራዊ ሽግግር ሲባልም ግብርናው ምርትና ምርታማነቱ አድጎ ተወዳዳሪነቱ እንዲጨምር፣ የገበሬው የኑሮ ሁኔታ እንዲሻሻል ማድረግ እና የሀገሪቱን ሥርዓተ ምግብ ፍላጎት ማሟላት የሚችል የግብርና ዘርፍ እንዲኖር ማስቻል እንደሆነ ገልጸዋል። ይህም ሲሆን ለኢንዱስትሪው ዘርፍ በቂ ግብዓት፣ ለወጪ ንግድም የሚሆን ምርት ማቅረብ፣ እሴት የጨመረ የግብርና ውጤት ማቅረብና በገጠር በቂ የሥራ እድል መፍጠር እንደሚችል ስለሚታመን ነው ብለዋል። ሌላው ለውጥ ያስፈለገው የዘርፉ ተዋንያን ድርሻ ለውጥ በማስፈለጉ፤ በግብርናው የግሉን ዘርፍ አስተዋጽኦ ሊኖር እንደሚገባ፤ መንግሥት የግሉ ዘርፍ በማይገባበቸው ሁኔታዎች ላይ መሥራት እንደሚገባው እና የመዋዕለ ንዋይ አቅርቦት ላይ የማመቻቸት ሥራ የመሥራት ኃላፊነት እንደሚኖረው አሳውቀዋል።

ሌላው በግብርናው ሪፎርም እየተሠራ ያለው፤ ቀደም ሲል፣ አቅርቦት ላይ ብቻ ትኩረት በማድረግ ምርታማነትን ለማሳደግ ከሚሠራው ሥራ ከፍ በማለት አቅርቦትን እና ፍላጎትን ባማከለ መልኩ መሥራት አስፈላጊ በመሆኑ፤ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን ለመተካት አስቦ መሥራት ስለሚያስፈልግ፤ ከኢንዱስትሪው መስፋፋት ጋር ፍላጎትን አስቦ መሥራት እንዲሁም ለውጭ ንግድ የሚሆኑ እና የሀገር ውስጡን ፍላጎት መሟላት የሚያስችሉ የግብርና ውጤቶችን ለይቶ መሥራትን ያካተተ ነው። በተጨማሪም፣

የገጠር - ከተማ ትስስሩንም ታሳቢ ያደረጉ ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው፤ የሥርዓት ማሻሻያ ማድረግም አንዱ ጉዳይ እንደሆነ በማሰብ የመሬት አጠቃቀምን ሥርዓት እና ሕጎች ተግባራዊ የሚደረጉበትን መንገድ ለመፍጠር እንደሆነ አስረድተዋል።

የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማበረታታት የግል ዘርፉን በግብርና አገልግሎቶች የማቅረብ ሥራ ከኅብረት ሥራ ማህበራት ጋር በጥብቅ ቁጥጥር እንዲገቡበት ማድረግ፣ ባንኮች ከ30 - 40% (ከሠላሳ እስከሠርባ በመቶ) የብድር አቅርቦት ለግብርናው ዘርፍ እንዲሰጡ የማድረግ፤ እንዲሁም የግብርና ባንክ እንዲኖር መሥራት፣ በግብይት ሥርዓቱ ላይ ደረጃ በማውጣት ምርት በደረጃው መሠረት ክፍያ እንዲያገኝ በማድረግ ገበሬውን የማበረታት ሥራ መሥራት፣ መንግሥት ከግሉ ዘርፍ ጋር በሽርክና መሠረተ ልማቶችን እንዲሠራ ለማድረግ የአሠራር ማሻሻያዎች እንደሚያስፈልጉ አብራርተዋል። ለዚህም የማስፈጸም አቅምን ማሳደግ እንደሚገባና የልማት ፋይናንስ አማራጮችንም በማሳደግ በውጤታማነት በመጠቀም የሪፎርሙን ሥራዎች በአጭር እና በረጂም ጊዜ እቅድ፤ በዘርፉ የዐሥር ዓመት እቅድ፤ እንዲሁም ከሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም ሥራዎች ጋር ተግባራዊ ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል።

## የውይይቱ ሐሳብ አቅራቢዎች ለውይይት ያቀረቧቸው ሐሳቦች

ከዶክተር አንተነህ የመግቢያ ጽሑፍ ቀጥሎ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች በየተራ ሐሳባቸውን አቅርበዋል። የመጀመሪያው ዶ/ር ወርቅነህ ከግብርና ሚኒስቴር ሲሆኑ፤ በእንስሳት ልማት ዘርፍ ለበርካታ ጊዜያት ሠርተዋል፣ እየሠሩም ይገኛሉ። እርሳቸውም፣ በሪፎርም ሥራ ላይ በመሬት አጠቃቀም ጉዳይ ላይ የሚሠራው ሥራ የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን የግድ ነው ሲሉ ገልጸውታል። በግብርና ግብዓትን በማዘመን እና የግል ዘርፉ እንዲገባበት የታሰበው ሰፊ የሥራ እድልም ሊፈጥር የሚችል በመሆኑ ጥሩ ነገር ነው። በእንስሳት ኃብት ረገድ ሲሠራ የነበረው ምርታማነት ላይ ነበር። ነገር ግን ከምርታማነት በተጨማሪ ትርፋማነት ላይ ታሳቢ ተደርጎ ሊሠራ እንደሚገባ ይታመናል። ስለዚህም የእንስሳት ምርቶችና ግብዓቶች ከሌላው በተለየ ከተመረቱ በኋላ የቆይታ ጊዚያቸው ውስን በመሆኑ ይህን ከግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ሥራ መሥራት እንደሚገባ፣ ለእንስሳት ልማት ምቹ የሆኑ ቦታዎችን ለይቶ መጠቀምንም ያካትታል ብለዋል። ልማቱ ረጂም ጊዜ እንደሚወስድም ታሳቢ መደረግ እንዳለባት አሳስበዋል። በሌላ በኩል፣ የግብይት ሥርዓቱ የተዛባ በመሆኑ ከገበሬው ይልቅ ሌሎችን ተጠቃሚ የሚደርግ ነውና እሱንም ማረም ይገባናል። በዚህ ላይ የግሉ ዘርፍ ተሳትፎ ትንሽ ነው።

ምክንያቱም ውጤታማ ባለመሆኑ ነው። በእነዚህ ችግሮች ላይ በመሥራት የዘርፉን ውጤታማት ማሳደግ እንደሚቻል የሪፎርሙም ሥራ ምርትን ብቻ ታሳቢ ያደረገ ሳይሆን ውጤታማ ሥራ ለመሥራት አስፈላጊ በሆነው የበጀት/የፋይናንስ አቅርቦት ላይ ትኩረት ሊያደርግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

በእንስሳት ልማት በወተት፣ በሥጋ፣ በእንቁላልና በዶሮ፣ በመኖ ልማት እንዲሁም በንብ ልማት ላይ መሥራት፤ ተመጋጋቢ ሆነው እንዲያድጉ ማድረግ እንደሚገባ፤ በወተት ልማት ላይ ምርት ከተመረተ በኋላ ምርቱን ለማሰባሰብና ለማቆየት የሚያስችሉ መሠረተ ልማቶችን መሥራት እንደሚገባ፤ ከግብዓት አኳያም የእንስሳት ምርትም እንደሰብል ምርቱ የተለያየ ግብዓቶች እንዲሚያስፈልጉት ታሳቢ ተደርጎ መሠራት እንዳለበት አሳስበዋል።

ሁለተኛው ሐሳብ አቅራቢ ዶ/ር አለማየሁ፣ በግብርና ዘርፍ ትኩረት ሊሰጣቸው በሚገባ ሦስት ጉዳዮች ላይ ሐሳባቸውን ሰጥተዋል። የመጀመሪያው፣ የአነስተኛ መሬት ይዞታ ጉዳይ ነው። በሀገራችን አንድ ሦስተኛው የእህል አምራች ገበሬ የመሬት ይዞታ ከ0.2 (ዜሮ ነጥብ ሁለት) ሄክታር በታች እንደሆነና ይህም የምርት መጠኑን በጣም አነስተኛ ያደርገዋል። ነገር ግን ትንሽ ይዞታ ያላቸው ገበሬዎች የተሻለ የመሬት ምርታማነት እንደላቸው ያሳያል። የመሬት ይዞታ ማነስ ወሳኙ ችግር እንደሆነ የሚያሳይ ነው። ለዚህም ችግር እንደመፍትሔ መሬት ማሰባሰብ (land consolidation) አስፈላጊ እንደሆነ፤ ይህንም ለማምጣት የመሬት ማከራየት ሥርዓት እንዲጀመር ማድረግ ያስፈልጋል ብለዋል። ሁለተኛው ጉዳይ የመሬት መራቆት ነው። በዚህም በመሬት መሸርሸር ችግር ምክንያት ምርታማነት ይቀንሳል። ለድርቅ የመጋለጥ ስጋት ያጋጥማል። የመሬትን ንጥረ ነገሮች ይቀንሳል። ችግሩም በዓመት ከሚመረተው እስከሁለት በመቶ የምርት መቀነስ እንደሚያስከትል ጥናቶችም አሳይተዋል። ለዚህም እንደመፍትሔ የሚሆነው፣ የረዥም ጊዜ እቅድ አቅዶ ሥራዎች ሊሠሩበት እንደሚገባና በከፍተኛ መጠን የተራቆቱ መሬቶች የሚገኙበትን አካባቢ ለይቶ እህል ማምረት ትቶ ወደቋሚ ሰብሎች ማምረት ሥራ እና በከፊል ዘመናዊ ወደሆኑ የወተት ምርት ሥራ እንዲዛወሩ ማበረታታት ያስፈልጋል። ሁለተኛው መፍትሔ ምቹ የሆኑ የቆላማ አካባቢዎች ተለይተው ወደእህል ማምረት ሥራ እንዲገቡ ማበረታታት የሚለው ነው።

ሦስተኛው ጉዳይ የፖሊሲ ቀረጻ እና ትግበራ አቅም ሲሆን፤ በዚህም ሥራ ችግሮችን መለየት እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ፤ አማራጭ ሐሳቦችን መለየት እና ማወዳደር፤

ቅደም ተከተልም ማበጀት፤ ሙከራ ማድረግ እና የሙከራ ውጤቱን መገምገም የሚለው ሂደት ነው። ለዚህም ተግባር እንደመሣሪያ የሚያገለግለውን የማዕከላዊ ስታትስቲክስ መሥሪያ ቤት ነጻነቱን ማስጠበቅ፤ ተጠሪነቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እንዲሆን በማድረግ የተሻለ የበጀት አቅም መፍጠር እንደሚገባ አሳስበዋል። በተመረጡ የግብርና ምርት ዓይነቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት፤ የአገዳ ሰብሎችን ምርታማነት ማሳደግ እና ከፍተኛ ዋጋ ባላቸው የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እንደሚገባም አሳስበዋል ።

ወ/ሮ አስከበረች ከኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ማህበራት የግብርና ፌዴሬሽን በመቀጠል፣ ድርጅታቸው ምን ምን ላይ እንደሚሠራ አሳውቀዋል። በአጠቃላይም የኅብረት ሥራ ማህበራት ለአርሶ አደሩ ግብዓት በማቅረብ እና ለግብርና ሥራ ብድር በማቅረብ በስፋት እየሠሩ እንደሚገኙ አስረድተዋል። መንግሥት በሪፎረሙ የግብዓት አቅርቦት የግሉን ዘርፍ እና ኅብረት ሥራ ማህበራትን በማሳተፍ የመቆጣጠር ኃላፊነት ቢወስድ ጥሩ እንደሚሆን ለኅብረት ሥራ ማህበራት ግብዓት አቅርቦቱን ባጠቃላይ ቢሰጥ ውጤታማ ሥራ መሥራት እንደሚቻልም ገልጸዋል። ለዚህም የኅብረት ሥራ ማህበራት በኤክስፖርት እና ኢምፖርት ላይም ልምድ እያካበቱ ስለሚገኙ ቢታሰብበት ጥሩ እንደሆነ ገልጸዋል። የኅብረት ሥራ ማህበራት ሰፊ የሥራ እድል መፍጠር እንዲችሉ የኅብረት ሥራ የትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ቢዋቀሩ የአርሶ አደሩ ልጆች በቀጥታ ወደግብርናው ሥራ የሚገቡበትንና በቴክኖሎጂ አዘምነው የሚሠሩበትን እድል ስለሚፈጥር ቢታሰብበት የሚል ሐሳብ ሰጥተዋል።

የኅብረት ሥራ ማህበራት የመሬት ችግር አለባቸው። ምንም እንኳን የኅብረት ሥራ አዋጁ ማህበራት መሬት እደሚያገኙ ቢደነግግም፤ መሬት የሚያገኙበት ሥርዓት ግን እንዳልተበጀ ገልጸዋል። በፋይናንስ ረገድም በግብርናው ላይ የሚሠሩ ማህበራት የብድር አገልግሎት እንደማያገኙና ችግር እንዳለባቸው አንስተዋል። የኦሮሚያ ኅብረት ሥራ ባንክ ለኅብረት ሥራ ማህራት በተለይ ለገበሬው አገልግሎት ይሰጣል። ሌሎች የኅብረት ሥራ ባንኮችም ወደገበያው የሚመጡበት ሥራ ሊሠራ ይገባል። የኅብረት ሥራ ማህበራትን የሚመሩ የቦርድ አካላት የማስፈጸም አቅም ትልቅ ችግር አለው። እዚህ ላይም የአቅም ግንባታ ሥራ፤ የኦዲት እና ሌሎች ድጋፎችንም በጥራት የሚያገኙበት ሥርዓት ላይ በትኩረት ቢሠራ የሚሉ ምክረ ሐሳቦች ሰጥተዋል።

የመጨረሻው የውይይቱ ሐሳብ አቅራቢ አቶ ጀማል አሕመድ ከሚድሮክ ግሩፕስ ናቸው። እርሳቸውም፣ በግብርና ሪፎርም ተግባራት ላይ የሚከተለውን ሐሳብ

አንስተዋል። አንደኛው፣ በእቅድ የተመረጡ የግብርና ምርት ዓይነቶችን በተመረጡ ቦታዎች ላይ መርጠን በመሥራት ትልቅ ውጤት ማምጣት እንችላለን። በዚህም የሪፎርሙ ሥራ በትንሽ መሬት ላይ በሚመረቱ አትክልት እና ፍራፍሬ ምርቶች ላይ ያለን ክፍተት ምንድነው? በሚል ለይቶ ቢያተኩር ትልቅ ለውጥ ሊያመጣ ይችላል። የግሉ ዘርፍ የሀገሪቱን ግብርና ለማዘመን ወሳኝ አቅም እንዳለው መረዳት አስፈላጊ ነው። የግሉ ዘርፍ በግብርናው ላይ በስፋት እንዳይሳተፍ ያደረገው ምንድነው? የሚለውን ስንመለከት ዋና ዋናዎቹ የተሰሚነት ችግር፤ የግንዛቤ ችግር እና አላስፈላጊ የሆነ ቁጥጥር መሆናቸውን ከድርጅታቸው ጋር በማያያዝ አስረድተዋል። የግሉ ባለኃብት በግብርናው ዘርፍ ለመሥራት በመንግሥት መዋቅሮች ላይ መስተካከል ያለባቸውን ችግሮች እና የዘርፉን ሁኔታዎች የተረዱ የፖሊሲ እና የሕግ ማእቀፎች እንዲኖሩ በሚያደርገው ጥረት ተሰሚነት እንደሌለው ገልጸዋል። የግብርና ሥራ በገጠር ውስጥ እንደመከወኑ ከታችኛው የመንግሥት መዋቅር ጀምሮ ያለው አስተዳደር በግብርና ሥራ እና ኢንቨስትመንቱ ላይ የግንዛቤ ችግር አለበት። ለምሳሌ በግብርና ሥራ መሬት ላይ የፈሰሰን ካፒታል ተረድቶ የፋይናንስ አቅርቦት ለመስጠት መቸገርን የመሰሉ የግንዛቤ ችግሮች አሉ። በተጨማሪም፣ ከልክ ያለፈ ቁጥጥር በተለያዩ አካላት ይደረጋል። ይህንንም የቡናን ምርት በምሳሌነት አንስተው አስረድተዋል።

## የተሳታፊዎች ጥያቄዎች እና አስተያየቶች

የውይይት መነሻ ሐሳቦች ከቀረቡ በኋላ ተሳታፊዎች አስተያየት ሰጥተዋል። ጥያቄም አቅርበዋል። በዚህም መሠረት፣ የታቀደው የሪፎርም ተግባር ጥሩ ነው። በቶሎ ግን ወደተግባር መግባት አለብን። በምርታማነት ጉዳይ ላይ የመሬትን ምርታማነት ከማሳደግ ጎን ለጎን የሰውንም ምርታማነት ማየት አለብን። ካለው የሥራ አጥ ቁጥር አንጻር የግብርናው ምርታማነት እንዴት ይታያል? ስለመሬት አጠቃቀም ጉዳይ የምንወያይበት ፕሮግራም መዘጋጀት አለበት። የመሬት አጠቃቀም እና ይዞታን ማስተላለፍ የሚያስፈጽም ተቋም እንዲኖር በማድረግ በተጣበበ መሬት ላይ ከሚሠራ ግብርና ወጥተን በአርብቶ አደሩ አካባቢ ያሉ ሰፋፊ መሬቶችን ወደምርት የምናስገባበት መንገድ መፈለግ አለበት። በግብርናው ዘርፍ ኤክስፐርቶች ከገበሬው እና ከግብርናው ጋር ያላቸው ትስስር ዝቅተኛ በመሆኑ ዘርፉን ለመለወጥ ችግር ገጥሞናል። በግብርና ምርምር ሥራ ላይም ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ መሆን ይጠበቅብናል።

በየክልል የተከፋፈሉ የምርምር ተቋማት የሚናበቡ እና ውጤታማ ማድረግ አለብን። በተጨማሪም፣ ግብዓት በማስገባት በተለይ ዘር በማስገባት ሂደት ላይ ያሉ ማነቆዎች

ቢታዩ፤ ከውጭ የማስገባት ፈቃድ ያላቸው ገበያውን በሞኖፖል ይዘውታል። የእንስሳት ህክምና ባለሙያዎች እጥረት አለ። የሚሉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል። በሌላ በኩል፤ ገበሬውን የመሬት ባለቤትነቱ ሳናረጋግጥለት የመሬቱን ምርታማነት ማሳደግ ይችላል ወይ? ሪፎርሙን ከማስፈጸም አኳያ እቅዱ ጥሩ ቢሆንም ያለውን ችግር ግን ጠለቅ ብለን ማየት እና ማሰብ አይጠይቅም ወይ? ለምሳሌ ልጆችን የምንስተምርበት መንገድ ወደከተማ ብቻ እንዲሳቡ እንጂ ግብርናውን እንዲያተኩሩበት የሚያደርግ አይደለም። መንግሥት በቆላ ስንዴ ላይ በምን መልኩ ነው ምርቱን በራሱ እያመረተ የሚሄደው? የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበዋል።

ዶ/ር ወርቅነህ በእንስሳት ምርምር ላይ ለተነሱ ጥያቄዎች መዋቅር መመስረቱ አስፈላጊ ቢሆንም ያሉትን ውጤታማ ማድረግ ስለሚቻል እሱ ላይ መሥራት ያስፈልጋል። በእንስሳት ኃብት ሥራ ላይ በግል የሚሠራ ሥራ የለም። በተለይ የምርምር ሥራ ላይ በግል የሚሠራ የእንስሳት ራንች የለንም። ነገር ግን የእንስሳትን የወጪ ንግድ ለማሳደግ እንፈልጋለን። ይህም ሊሆን የሚችል አይደለም። ስለዚህ በእንስሳት ዘርፍ የምርምሩንም የንግዱንም ሥራ የሚሠራ የግል ባለኃብት እንዲፈጠር ማበረታታት ይኖርብናል። በገጠር ስላለው ከአቅም በታች የመሥራት (under employment) ሁኔታ በጣም ከፍተኛ የሆኑ የጋራ ጥብቅ መሬቶች በየአካባቢው ይገኛሉ። እነሱ ላይ ወጣቶች በንብ እና የሃር ትል ልማት፣ እንዲሁም ሌሎች የግብርና ሥራዎችን እንዲሠሩባቸው ማድረግ ይቻላል። የእንስሳት የግጦሽ ስፍራዎችንም በዚህ መልኩ በጋራ በማስተዳደር ውጤታማ የሥራ እድል መፍጠር የሚስችሉ ሁኔታዎች እንዳሉን ገልጸዋል።

ዶ/ር አለማየሁ በበኩላቸው፣ ገበሬውን የመሬት ባለቤት ሳናደርግ ለውጥ ማምጣት ይቻላል። በሀገሮች ተሞክሮም የቻይናን እና የቬትናምን ልምድ ማየት አለብን። የሚቻልበት መንገድም የመሬት ኪራይ እና አስተዳደር ሥርዓት በመዘርጋት፤ ሌሎች የምርታማነት ማሻሻያዎችን በማድረግ፤ ምርታማነትን ማሻሻል የሚያስችሉ አማራጮችን መዘርጋት ይቻላል። ብለዋል። ወ/ሮ አስከበረችም፣ በግብርና ምርት ላይ በነጻ ገበያ ስም ከፍተኛ የኮንትሮባንድ ሥራዎች እየተሠሩ ነው። የግብርና ግብዓትን የኅብረት ሥራ ማህበራት እናቅርብ ስንል ሁሉንም በሞኖፖሊ እንያዘው እያልን ሳይሆን፤ ከሌሎችም ጋር በቅንጇት የገበያውን ሁኔታ ባማከለ መልኩ ብንሠራ የሚል ሐሳብ ነው እያቀረብን ያለነው የሚል ሐሳብ ሰጥተዋል ።

አቶ ጀማል፣ ምርታመነትን በተመለከት ያሻሻልነው ነገር ቢኖርም በእህል ምርቶች

ላይ በሀገር አቀፍ ደረጃ ምርታማነትን ለማሳደግ እንደየአካባቢው ሁኔታ ምርታማነቱን የሚያሳድጉ ዝርያዎችን እና ቴክኖሎጂዎችን ማቅረብ አለብን። ዘር ከማስገባት ጋር ተያይዞ በግብርና ሚኒስቴር አሠራር ሥርዓት ላይ ያሉ ክፍተቶች አንዳንድ የዘር ዓይነቶች፣ ለምሳሌ፦ ቲማቲም በአንድ ድርጅት እንዲያዝ ብቻ ነው የተደረገው፤ ሌላ ማስገባት የማይቻልበት ሥርዓት ነው ያለው፤ በቡና ምርት ላይ ስላለው ችግር ምርምር መሠራት ያለበት በመንግሥት ነው። ያንን ሳናደርግ የምርት እንቅስቃሴ በመቆጣጠር ብቻ ለውጥ ልናመጣ አንችልም። "የግሉ ባለኃብት በግብርና ላይ እንዲደረግለት የሚፈልገው ምንድን ነው?" ተብሎ ለተጠየቀው፤ በአሁኑ ሁኔታ የሥራ ቦታው እርሻው እና ንብረቶቹ እንዲሁም የሠራተኞቹ ደኅንነት እንዲጠበቅለት ይፈልጋል። ሌላው የፋይናንስ አቅርቦት ያስፈልገዋል። ግብዓት እንዲቀርብለት ይፈልጋል። በተለይ ዘር እና መድሐኒቶችን ሲሉ ገልጸዋል።

በግብርና ምርምር ላይ የግንዛቤ ችግር እንዳለ፤ በተለይ በስንዴ እና በበቆሎ ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገበ ምርምር እንደተደረገ፤ በእንስሳትም እንደዚያው መሆኑ፤ ነገር ግን ውጤቱን ገጠር ያለ ሰው ብቻ እንደሚያወቀው፤ ቡና ላይም የተለያዩ ምርምሮች ቢሠሩም ቡና አዲስ ዝርያ ተተክሎ ቢያንስ እስከአምስት ዓመት ምርት የማይሰጥ በመሆኑ ገበሬው ያለምርት መኖር ስላማይችል አዲሱን ዝርያ እየዘራው አይደለም። ለዚህም አርሶ አደሩ አዲሱ ዝርያ ምርት መስጠት እስከሚጀምር ሕይወቱን የሚደግፍበት የተለያየ መንገድ ልንፈጥርለት ይገባል። ያንን በማድረግ የቡናን ምርታማነት ማሳደግ እንደሚቻል ሐሳብ ተነስቷል።

የግብርና ሚኒስቴርን የመሬት አጠቃቀም በተመለከተ እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል ለእያንዳንዱ ገበሬ የመሬት ካርታ መስጠት እንደሆነ፤ የአርሶ አደሩን የመሬት ተጠቃሚነት የሚያሳድጉ፤ በመሬቱ ብድር እንዲበደርበት እና ሌሎችንም እድሎች በሚፈጥር መልኩ እየተሠራ እንደሆነ፤ የመሬትን አስተዳደር በተመለከተ ግን የገጠሩን መሬት የሚስተዳድረው ማን ይሁን? ሁሉም ዘርፍ በተለያየ መልኩ ለመጠቀም ስለሚፈልግ ይህን የሚያስተባብር እና የሚመራ ኃላፊነት ያለው አካል ያስፈልጋል። መሬት በማሰባበስ ላይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የተለያዩ ልምዶችን በማየት እና ጥናት በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ሐሳብ ተሰጥቷል።

በመጨረሻም፣ በተነሱ ሐሳቦች ላይ ዶ/ር አንተነህ ማጠቃለያ ሲሰጡ፣ የተሰጡ አስተያየቶች እንደሚሠራበቸው ገልጸዋል። የቀድሞው ፖሊሲ እና ፕሮግራሞች አፈጻጸም ምን ይመስላል? የሚሉትን አጥንተን ሳይሆን የተጠኑትን በመከለስ

እንደሆነ፣ ነገር ግን ሪፎርሙ ገና ብዙ ግብዓቶች የሚሰበሰቡበትና ጥናትም የሚሠራበት እንደሆነ፤ ከሌሎች ተቋማት ጋር በቅንጅት የሚሠሩትንም ጅምሮች እንዳሉ፤ ለምሳሌ ከንግድ ሚኒስቴር ጋር ከግብርና ምርት የወጭ ንግድ ጋር በተያያዘ ያለውን ችግሮች በሪፎርሙ በጋራ እንዴት መፍታት እንደሚቻል የፖሊሲ ጉዳዮችንም ለማየት እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። በሌላ በኩል፣ የፕሮግራም ማሻሻያ ብቻ የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች በዐሥር ዓመት አቅድ ተካትተው እየተሠራባቸው እንደሆነ ጠቁመዋል።

"ከምርታማነት ባለፉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ማድረግ አለበት" በሚለው ሐሳብ ላይ በአጠቃላይ በግብርና ላይ፣ በተለይ ደግሞ በእንስሳት ልማት ዘርፍ ላይ ምርታማነትን እንደአንድ ዋና ጉዳይ ይዘነው እየሠራን ነው። ነገር ግን የሕዝብን ቁጥር ያገናዘበ ምርት ማለትም አማካኝ የግለሰብ ፍጆታን (percapita) ያማከለ ምርት፤ እንዲሁም ከምርት ዋጋ እንጻር የሕዝቡን የመግዛት አቅምም ትንተና ውስጥ በማስገባት እየተሠራ እንደሆነ አንስተዋል። የግሉንም ዘርፍ ታሳቢ ያደረገ የዐሥር ዓመት እቅድ እየተዘጋጀ ነው ብለዋል። "የግሉ ዘርፍ ወደ ዘርፉ እንዲገባ የገበያ ትስስር ይፈልጋል። የመሠረት ልማት ሥራዎች እንዲስፋፉለት ይፈልጋል።" የሚሉትን ሁሉ ታሳቢ ያደረገ ሪፎርም እየተሠራ እንዳለ አስረድተዋል።

በመሬት ጉዳይ ላይ አነስተኛ ይዞታ ያላቸውን አርሶ አደሮች በተለይ ግንባር ቀደም አርሶ አደሮች መሬት በማሰባሰብ (land consoldetion) ተጠቃሚ እንዲሆኑና ወደመካከለኛ ደረጃ እንዲያድጉ የማድረግ ሥራ ለመሥራት የሚያስችል በጥናት ላይ የተመሠረተ የሕግ ማዕቀፍ ለማዘጋጀትም መታሰቡን፤ የግሉ ዘርፍ በቴክኖሎጂ ማመንጨት ሥራዎች ላይ እንዲሳተፍ ለማድረግ የፖሊሲ ማሻሻያ ማድረግ መጀመሩን፤ የመንግሥትን የምርምር ሥራ የማሳደግ እና ውጤታማ የማድረግ፤ ተማራማሪውንም የማትጋት ሥራ ሪፎርሙ እንደሚዳስሳቸው አስረድተዋል። የመጀመሪያ ደረጃ እሴት ጭመራ ሥራዎችን በመሥራት አዳዲስ የሥራ እድል ለመፍጠርም የሚሠራበት ነው ብለዋል። በተጨማሪም፣ የዘር እና አግሮ ኬሚካል ምዝገባ ሥራዎች ላይ ከሪፎርሙ በፊት አፋጣኝ ማስተካከያዎችን ለማድረግ በሚኒስቴሩ እየተሠራ እንደሆነ አሳውቀዋል።








የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

## 2.4 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ የሎጅስቲክስ ዘርፍ ሪፎርም

የካቲት 27 ቀን 2012 ዓ.ም




ይህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም በሎጂስቲክስ ዘርፍ እየተደረጉ ባሉት እና በታቀዱ የሪፎርም ሥራዎች ላይ ለመነጋገር የተዘጋጀ የውይይት መድረክ ነው። በፕሮግራሙ ላይ (የቀድሞ) የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር የነበሩት ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ በዘርፉ ስለተሠሩ እና እየተሠሩ ስላሉ ተግባራት አጭር ገለጻ አድርገዋል። ዘርፉ ሁሉንም የሀገሪቱን የማምረት ሂደቶች የሚነካ እንደመሆኑ ሪፎርም እደሚያስፈልገው ታምኖበት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ እንዲጸድቅ መደረጉንም አንስተዋል። የሎጂስቲክስ ስትራቴጂውም በውስጡ ልዩ ልዩ ንዑስ ስትራቴጂዎች እና ወደ 98 (ዘጠና ስምንት) የሚደርሱ ድርጊቶች (in-terventions) ያቀፈ እንደሆነም አሳውቀዋል። ኢትዮጵያ እያካሄደችው ያለው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ሪፎርም እንዲሳካና የግሉ ዘርፍም ውጤታማ ሥራ መሥራት እንዲችል የሎጂስቲክሱ ዘርፍ ከፍተኛ አስተዋጽኦ የሚያበረክት እንደሆነ፤ ለዚህም ሲባል በከፍተኛ ትኩረት እየተሠራ እንዳለ አስረድተዋል።

ባለፉት 15 (ዐሥራ አምስት) ዓመታት የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ አገልግሎት የመሠረተ ልማት ግንባታ እንዲሁም አዳዲስ የአሠራር ሥርዓቶችን የማስጀመር

ተግባራት የተሠሩበት ቢሆንም፤ ዘርፉ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ያለበት የመሆኑን ያህል ያላደገ፤ እንዲሁም ብዙ መጉላላት እና ማነቆዎች ያሉበት ነው። በዚህ የአዲስ ወግ ፕሮግራምም የሎጂስቲክስ ዘርፍ እስከዛሬ የመጣበትን እና የወደፊቱን ሁኔታ ማለትም በዘርፉ ያሉ ችግሮች እና መልካም አጋጣሚዎች፤ በዓለም አቀፍና በሀገር አቀፍ ደረጃ ችግሮችን ለመፍታት ከግሉ ዘርፍ ከመንግሥት እና ከማህበራት ምን ይጠበቃል? ለውጡም ከየት ይጀመር? የሚሉት ሐሳቦች የውይይቱ ዋና ዋና ነጥቦች ሲሆኑ፤ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች አቶ መኮንን አበራ የማሪታይም ጉዳዮች ባለሥልጣን ዋና ዳይሬክተር፣ አቶ ሮባ መገርሳ የባሕር ትራንዚትና ሎጂስቲክስ ዋና ሥራ አስፈጻሚ፣ ዶ/ር ማቲዮስ ኢንሰርሙ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም ወ/ሮ ኤልሳቤጥ ጌታሁን የኢትዮጵያ እቃ አስተላለፊዎች እና መርከብ ወኪሎች ማህበር ፕሬዚዳንት ናቸው። ውይይቱን በአወያይነት የመሩት ደግሞ የዓለም ባንክ የግል ዘርፍ አማካሪዋ ፋንቱ ፋሪስ ናቸው።

### የሎጂስቲክስ ዘርፍ ሪፎርም ዋና ዋና ነጥቦች

በቅድሚያ ንግግር ያደረጉት አቶ መኮንን አበራ፣ "የሎጂስቲክስ ዘርፉ ከየት? ወደየት?" በሚል ባለፈው ጊዜ የኢትዮጵያ የሎጂስቲክጅስ ሥርዓት ብዙ ድክመቶች የነበሩት፤ በሎጂስቲክስ ተወዳዳሪነት መለኪያዎችም በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ እንደነበር ገልጸው፤ ይህን ችግር ለማሻሻል ሲባል የ "መልቲሞዳል" ሥርዓት እንዲተገበር መደረጉን አውስተዋል። በተጨማሪም፣ ደረቅ ወደቦች ተገንብተዋል። የባቡር ትራንስፖርት ተጀምሯል። የተደረጉ ጥሩ ውጤት ያመጡ የመንገድ ጥገና ሥራዎች ተከናውነዋል ብለዋል። ይሁን እንጂ፣ አጠቃላይ ዘርፉ በብዙ ችግሮች ውስጥ ያለ መሆኑ ሀገራችን ለማምጣት በምትሻው ለውጥ ላይ እንቅፋት እንዳይሆን በማሰብ ዘርፉን ሪፎርም የማድረግ ሥራ አስፈላጊነቱ ታምኖበት "የብሔራዊ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ" ጸድቆ ሁሉንም የዘርፉን ተዋንያን የጠራ ራዕይና ግብና የወደፊት አቅጣጫ የሚያሳይ ለሁሉም የዘርፉ ተዋንያን የሚያገለግል ሰነድ መዘጋጀቱን አስታውቀዋል።

የተዘጋጀው የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ የወደፊት አቅጣጫችን መቼ የት መድረስ እንዳለብን የሚሳይ ሲሆን፤ በዘርፉ ያሉ ችግሮችም እንደተለዩና ለችግሮችም በስትራቴጂው 98 (ዘጠና ስምንት) የተለዩ "ኢንተርቬንሽኖች" የተካተቱበት እንደሆነ ገልጸዋል። እነዚህም የተለዩ ለውጥ የሚያስፈልጋቸው ችግሮች ወደፕሮግራም በመቀየር የሚፈቱ እንደሆነ አስረድተዋል። የሎጂስቲክሱ ዘርፍ ዋና መመዘኛዎችም ዋጋ፣ ጊዜ እና ውስብስብነት እንደሆኑ፤ በእነዚህም መለኪያዎች መሠረት የሀገራችን የሎጂስቲክስ ዘርፍ ያለንትን ደረጃ መለየት መቻሉን፤ በስትራቴጂው መሠረት ወደትግበራ

ለመግባት የትግበራ አደረጃጀት መፍጠር ላይ እንደሚሠራ፤ ይህም የሎጂስቲክስ ዘርፉ የተለያዩ ባለድርሻዎችን እና ጉዳዮችን ያካተተ እንደሆነ፤ በቅንጅት ከመሥራት ባለፈ በጋራ አቅዶ በጋራ የመገምገም ሥርዓት አስፈላጊ እንደሆነም እንደታመነበት ጠቅሰው ይህንንም ተግባራዊ የሚያደርግ የሎጂስቲክስ ካውንስል አስፈላጊ እንደሆነ እንደታመነበትም ገልጸዋል ።

በሎጂስቲክስ ዘርፉ አሁን የተጀመሩ የቅንጂት ሥራዎች ውጤት ማስመዝገብ እንደቻሉ፤ በዚህም በሚሊዮኖች የሚቆጠር የውጭ ምንዛሬ ማትረፍ እንደተቻለ አስረድተዋል። በአጠቃላይ የዘርፉ ሪፎርም የተለያዩ የፖሊሲ ማሻሻያዎች የሚፈልግ እንደሆነ፤ በተለይም በ "መልቲሞዳል" ሥርዓት እና በደረቅ ወደብ ሥራ ላይ የግሉ ዘርፍ ተሳታፊ እንዲሆን የሚያደርግ ለውጥ ሊኖር እንደሚገባ እንደታመነበት አንስተዋል። እንዲሁም፣ የዘርፉን የሪፎርም ሥራዎች የሚያስፈጽምና በዘርፉ ከፍተኛ ሀገራዊ አቅም መገንባት የሚያስችል ከኢንዱስትሪው፣ ከትምህርት ባለሙያዎች እና በዘርፉ እውቀት ያላቸውን በማሰባሰብ የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ተቋም በምስረታ ሂደት ላይ እንደሚገኝ አስታውቀዋል። ተቋሙ ዘርፉ ያሉበትን ችግሮች የሚፈታ ብቻ ሳይሆን ወደፊት በጥናት ላይ የተመሠረቱ መፍትሔዎችን በማስፈጸም የሚያገለግል እና ኢትዮጵያን በጥቂት ዓመታት ውስጥ በምሥራቅ አፍሪካ ተቀዳሚና ተመራጭ ማድረግ እንደሚቻል ሐሳባቸውን አካፍለዋል።

አቶ ሮባ መገርሳ የትራንዚት ትራንስፖርት አገልግሎትን የተመለከተ የኢትዮጵያን ገጽታ እና የወደፊት አቅጣጫዎች ተንተርሰው ሐሳባቸውን አጋርተዋል። በዚህም፣ የሎጆስቲክስ ዘርፍ ብዙ ውስብስብ ሁኔታዎች ያሉበት እና የዘርፉ አከናዋኞች በሁኔታው እየተፈተኑ እንዳለ ገልጸው ይህም በመጀመሪያ ከንግዱ ሥርዓት፣ በተለይ ደግሞ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት ችግር ሳቢያ ሊተነበይ የማይችል የውጭ ንግድ ሥርዓት በመኖሩ ምክንያት የዘርፉ አከናዋኞች እና ዘርፉ ብዙ ፈተናዎች ይገጥሙታል ብለዋል። በዚህ ዘርፍ በመጀመሪያ ደረጃ የመሠረተ ልማት ሁኔታዎችን ማየት ጥሩ እንደሆነ አንስተው፣ ይህም "ኢትዮጵያ ምትጠቀመው የትኛውን ወደብ ነው?" የሚለው እና ሌሎችን ወደቦች አጣምሮ በጋራ ለመጠቀም እየተሠራ ያለም ሥራ እንዳለ አንስተዋል። በየብስ ትራንስፖርት ላይ ባቡር እና ተሽከርካሪዎችን እንደምንጠቀም፣ ነገር ግን ምን ዓይነት ተሽከርካሪዎችን እንጠቀማለን? የተለየ ማጓጓዣ ለሚፈልጉ ጭነቶችስ የሚሆኑ ተሽከርካሪዎች አሉን ወይ? የሚለው ብዙ ችግሮች ያሉበት እንደሆነ ገልጸዋል።

የኢትዮጵያ ባሕር ትራንስፖርት እና ሎጂስቲክስ ድርጅት የሀገሪቱን ምርቶች የሚጓጉዝ ሲሆን፤ በተለይ ሁሉንም ገቢ ጭነቶች የሚያስገባ እንደሆነና፤ የ "መልቲሞዳል" አገልግሎት ከሚሰጥበት የገቢ ጭነት መካከል 80 (ሰማንያ) በመቶ ያህሉ በውጭ የመርከብ ድርጅቶች የሚሠራ ሲሆን 20 (ሃያ) በመቶ ብቻ በራሱ መርከቦች አገልግሎት እንደሚሠጥ አስረድተዋል፡፡ ድርጅቱ የኢትዮጵያን ገቢ እና ወጪ ጭነቶች በሚያጓጉዝበት ወቅት እንደፖሊሲ የሚጠቀመው ከዓለም አቀፉ የመርከብ ትራንፖርት አገልግሎት ዋጋ ከ20-24 (ከሃያ እስከሃያ አራት) በመቶ ቅናሽ በማድረግ እንደሆነ አቶ ሮባ አሳውቀዋል፡፡ የ "መልቲሞዳል" ትራንስፖርት አገልግሎት መሰጠት ከጀመረበት ከ2004 ዓ.ም ጀምሮ የ"መልቲሞዳል" ድርሻ እያደገ እንደሆነና ኢትዮጵያ በየዓመቱ በወደብ ላይ ለኮንቴነር ማቆያ ትከፍል የነበረውን እስከ 50 (ኀምሣ) ሚሊዮን ዶላር የሚደርስ ወጭ ማስቀረት እንደተቻለ ገልጸዋል፡፡

የወጪ ንግድን እና ትራንስፖርትን በተመለከተ ወደውጭ የሚላኩ ጭነቶች ላይ "የግሉ ዘርፍ እየሠራ ያለውን መንግሥት በምን መልኩ ነው ማገዝ ያለበት?" የሚለውን፣ ነገሮችን ለይቶ መሠራት እንዳለበት፤ ነገር ግን ደረቀ ወደቦችን ከባቡር ጋር በማገናኘት ጭነት ቀጥታ ወደወደብ የሚሄድበት ሁኔታ፣ የኮንቴነር ማቆያ ቦታ በነጻ የማቅረብ፣ የ "ካስተምስ" የአንድ መስኮት አገልግሎትና ሌሎችም አገልግሎቶች በቴክኖሎጂ ተደግፈው የሚያገኙበት ሁኔታ እንደተመቻቸ አብራርተዋል፡፡ የተወሰኑ ቀሪ መስተካከል ያለባቸው ሁኔታዎች እንዳሉም ገልጸዋል፡፡ በአጠቃላይ በዚህ ዘርፍ የግሉን ተሳትፎ ለማሳደግ መንግሥት በፖሊሲ ደረጃ ያስቀመጠው ነገር አለ፡፡ በዚህም፣ በደረቅ ወደብ፣ በመጋዘን አገልግሎት፣ በቀዝቃዛ ትራንስፖርት አገልግሎት እና በባቡር አግልግሎት ላይ የሚሳተፉበትን መንገድ መፍጠር ይገባል ብለዋል፡፡ ከፋይናንስ ችግሮች ጋር በተያያዘ የሎጂስቲክስ ዘርፍ ዋናው ተግዳሮት የፋይናንስ እንደሆነ ገልጸው፤ ከፋይናንስ አቅራቢ ድርጅቶች ጋር የማሻሻያ ሥራ እንደሚሠራበት፤ የሎጂስቲክስ ፋይናንሲንግ ተቋሞች ወደሥራው የሚገቡበትን ሁኔታ መታሰብ እንዳለበት አሳስበው በዘርፉ ያለውን ችግር ለመፍታት እና ዘርፉን ለማሳደግ በመንግሥት እየተወሰዱ ያሉ ርምጃዎችም አበረታች እንደሆኑ ተናግረዋል ፡፡

ዶ/ር ማቲዎስ ኢንሰርሙ በበኩላቸው፣ በመነሻነት የሎጂስቲክስ አገልግሎትን ፍላጎት ማሟላትን ታሳቢ ያደረገ ምርትን ከመነሻ ወደመድረሻ የማንቀሳቀስ ሥራ ሎጂስቲክስ እንደሆነ እና በውስጥ ብዙ ተዋንያን ያሉት እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ በዓለም አቀፍ የሎጂስቲክስ እይታ ኢትዮጵያ እሴት ያለተጨመረበት ጥሬ እቃ በመላክ እና

ያለቀላቸውን ምርቶች ከውጭ በማስገባት እንደምትታውቅ ጠቁመው፤ በዘርፉም ከፍተኛው ችግር የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እንደሆነ በማንሳት ኢንዱስትሪው ያሉበትን ተግዳሮቶች አጋርተዋል። በዘርፉ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ነገሮች የትኞቹ ናቸው? በሚል ለተነሳው ጥያቄም፣ የኢትዮጵያ ሎጂስቲክስ የዓለም አቀፍ መተላለፊያ ሆኖ ቢገነባ፣ የሀገር ውስጥ የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማት በአራቱንም አቅጣጫ በባቡር ማገናኘት፤ የእሴት ሰንሰለት ደረጃን ማሳደግ፣ የሎጂስቲክስ የሰው ኃብት ልማት፤ ዘርፉን በቴክኖሎጂ ማገዝ፣ የግሉን ዘርፍ ማሳተፍ ቢቻል፤ እንዲሁም በወደብ ልማት ላይ ቢሠራ እና የሎጂስቲክስ አገልግሎት ሰጭዎች ቢዘምኑ መልካም ነው የሚል ሐሳብ አቅርበዋል።

ወ/ሮ አልሳቤጥም፣ በሎጂስቲክሱ ዘርፍ የግል የሎጂስቲክስ አከናዋኞች የችግር ገፈት ቀማሾች እንደነበሩ ጠቁመው፤ ዋና ችግሩም የሎጂስቲክስ ሥርዓት ባለመኖሩ እንደሆነ አንስተዋል። አሁን የጸደቀው የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ ለዘርፉ እና በዘርፉ የተሰማሩትን ባለመዋዕለ ንዋዮች ተስፋ የሰጠ እንደሆነም ገልጸዋል። በተጨማሪም፣ ዘርፉ ትልቅ አቅም ያለው፤ በዓለም አቀፍ ደረጃም ከፍተኛ ካፒታል የሚያመነጭ እንደሆነ፤ መንግሥታትም ከግሉ ዘርፍ ጋር በማጣመር ከፍተኛ ውጤታማ ሥራ እንደሚሠሩበት አንስተው መንግሥት ለዘርፉ ማበረታቻ ማድረግ እንደሚገባው ተናግረዋል።

በመሠረተ ልማት በኩል የተከናወኑ የመንገድ እና የባቡር ሥራዎች እንዳሉ አንስተው፤ እነዚህንም በአግባቡ ለመጠቀም የሎጂስቲክስ ሥራዎች ላይ ዝግመት አለ ብለዋል። ከዚህ ቀደም በአንድ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ የነበርን ቢሆንም ይህን ለማስፋት እና ተጨማሪ ወደቦችን ለመጠቀም እንደታቀደ አዲሱ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂ አሳይቷል። ነገር ግን፣ "መቼ መጠቀም እንጀምራለን?" የሚለው መመለስ እንደሚገባና በመዳረሻ ጣቢያዎች ላይ የመጋዘን አገልግሎቶችን ማዘጋጀት እንደሚገባ አሳስበዋል። የኢትዮጵያ የሎጂስቲክስ እንቅስቃሴ አዲስ አበባን ብቻ ማዕከል ያደረገ መሆኑ ችግር እንደሆነም ተናግረዋል። ኢንዱስትሪው ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የሚያመጣ መሆኑ ላይ የግንዛቤ ችግር እንዳለም አንስተው ይህም ማስተካከያ ተደርጎበት እንደሌሎች ዘርፎች ኢንዱስትሪው ድጋፍ እንዲደረግለት እና ውጤት እንዲያመጣ ዘርፉን በቴክኖሎጂ ማዘመን የግድ እንደሆነ አሳስበዋል።

## ከተሳታፊዎች የተነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች

ተሳታፊዎቹ ከሰጧቸው አስተያየቶች መካከል፤ ዘርፉ ለዘመናት ባለቤት ሳይኖረው

ቆይቷል፤ አሁን አዲስ ነገር እየተፈጠረ ይመስላል። ነገር ግን የሀገሪቱ ኢኮኖሚ እያደገ እንደመሄዱ ዘርፉን የሚያገለግሉ ተሽከርካሪዎች እየተጨመሩ አይደለም። በእቅድ መመራት ያለባቸው ጉዳዮች በእቅድ አለመሠራታቸው በዘርፉ ያሉ አስተላለፊዎች እና የመንግሥት ትልቁ ችግር ነው በማለት ማዳበሪያ ሲገባ የሚፈጠረውን ሁኔታ በምሳሌነት ጠቅሰዋል። ሎጀስቲክሱ ለሰባት ቀናት 24 (ሃያ አራት) ሰዓት መሥራት ይኖርበታል። ስለዚህ በዘርፉ ያሉት ባለድርሻዎች በዚህ መንገድ እንዲሠሩ ግድ ይላል። በጂቡቲ ወደብ ላይ ብቻ ጥገኛ መሆናችን ከፍተኛ ችግር እየፈጠረ ነው። ተጨማሪ ወደብ ያስፈልገናል። ለዚህም በጂቡቲ እና በመንገድ ላይ ያለው ከፍተኛ ችግር ሊታይ ይገባል። የሚሉት ይገኙበታል። በሌላ በኩል፣ "በ98ቱ (ዘጠና ስምንት) "ኢንተርቬሽኖች" ውስጥ ተይዟል ወይ?" በሎጂስቲክሱ ውስብስብ አሠራር ምክንያት በቁም እንስሳት ንግድ የሀገሪቱ ገቢ ቀድሞ ከነበረው በ90 (ዘጠና) በመቶ ያህል ቀንሷል። ይህንን ችግር ለመፍታት ምን ታስቧል? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል።

ኢንጂነር ሐብታሙ ከኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን፣ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂው ለትራንስፖርቱ ዘርፍ አብሮ አቅዶ ለመሥራት የሚያስችል ነው። በሰነዱ በተቀመጠው የብቃት መመዘኛ መስፈርት የቀረበው ዋጋ፣ ፍጥነት እና ውስብስብነት ቢሆንም የአፈጻጸም መለኪያዎችና እና ማሳያ (KPI) በጊዜና በወጭ ተለክቶ ማካተት አለበት ብለዋል። በሌላ በኩል፣ በዐሥሩ ዓመት እቅድ ላይ ከተለያዩ አካባቢዎች የሚመጡ ምርቶች ወደአዲስ አበባ መግባት ስላማይጠበቅባቸው በቀጥታ ወደወደቦች መድረስ የሚችሉበትን የመንገድ አማራጮች ለማሳደግ ታቅዶ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። በአጠቃላይ ግን ስትራቴጂው ወደሀገራዊ እቅድ መቀየር ይኖርበታል የሚል ሐሳብ አካፍለዋል።

አቶ መኮንን አበራ፣ "የሎጂስቲክስ ካውንስሉ ወደትግበራ መግባት አለበት" በሚል ለተነሳው፤ ካውንስሉ የሁሉንም ባለድርሻ አካላት ውክልና ባካተተ መልኩ እንዲመሠረት እንደሚደረግና በክልሎች እና በከተሞችም ቅርንጫፎች እንደሚኖሩት ገልጸዋል። የሚነሱ ጥያቄዎችንም በተደራጀ መልኩ ለውሳኔ ሰጪ አካላት እንዲደርሱ በማድረግ ሥራ ለመሥራት እንቅስቃሴ እየተደረገ እንደሆነ ጠቁመዋል። የፖሊሲና የስትራቴጂው ማስተካከያ እንዳለ ሆኖ፤ "ስትሪንግ" ኮሚቴ እና "ኦፕሬሽናል" ኮሚቴ በማቋቋም ከስትራቴጂ ሥራዎች ጎን ለጎን አስቸኳይ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነም አንስተዋል። ከጭነት ማንሳት አቅም እና የማዳበሪያ ማጓጓዝ ሥራ ጋር የተያያዙ ችግሮች እንዳሉ እንደሚታወቅ እና የባቡር ማጓጓዣንም ጨምሮ የማንሳት አቅምን ለማሳደግ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነ በመጥቀስ፤ የፋይናንስ እጥረት፣ ማለትም የዶላር አቅርቦት እና ወረፋ በዘርፉ እንቅስቃሴ እና በአከናዋኞች ላይ የሚያስከትለውን ጫና አስረድተዋል።

በመሆኑም፣ በአፈጻጸሙ ያሉ ችግሮች እንዳሉ ታሳቢ ተደርገው፤ የ"FOB"ን ጉዳይ መረዳት ያለብን እንደሀገር ጭነት ከመነሻ ወደብ ተነስቶ መድረሻ ወደብ ድረስ ያለው ጉዞ ላይ ያሉ ወጭዎችን እኛ ብንሸፍን ለሀገር ማስቀረት የምንችለውን ተጨማሪ ወጪ ከመቀነስ አኳያ ሊታይ ይገባል የሚል ምላሽ ሰጥተዋል። የሎጂስቲክሱ ሀገራዊ ማስተር ፕላን ከስትራቴጂው ከወጡት አንዱ ኢንተርቬንሽን እንደሆነና በዚህ ማስተር ፕላን ከወደብ የሚመጡ ጭነቶች አዲስ አበባ መምጣት ሳይጠበቅባቸው ወደመዳረሻቸው የሚሄዱበትን ሥርዓት እና መሠረተ ልማት የመዘርጋት እንዲሁም ወደወደብ የሚሄዱ ጭነቶችንም የሚቀርባቸውን ወደብ የሚጠቀሙበትን የተጨማሪ ወደብ አገልግሎት የሚያካትት እንደሚሆን አሳውቀዋል።

አቶ ሮባ መገርሳ በእቅድ ከመመራት እና 24 (ሃያ አራት) ሰዓት ከመሥራት ጋር ተያይዞ ለተነሳው አስተያየት፤ አስተያየቱ ልክ እንደሆነና በጂቡቲ ወደብ እንደዚያ እየተሠራ እንደሚገኝ የሞጆ ደረቅ ወደብንም 24 (ሃያ አራት) ሰዓት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ ሙከራ እና እቅድ እንዳለ ጠቁመዋል። ጭነት ከማንሳት አቅም ጋር የሚያያዙ ችግሮች እንዳሉብን እና ከጂቡቲ ወደብ አንስቶ እስከመዳረሻዎች ድረስ ከፍተኛ የመንገድ ብልሽት እንዳለ እና በጂቡቲ በሾፌሮች ላይ ይደርሳል የተባለውን መጉላላት እና ተጽዕኖም ለማስተካከል እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል። የፋይናንስ ችግር በሚል የተነሳው ጉዳይ የውጭ ምንዛሬ አቅርቦት እጥረት የሚያመጣው ችግር እንደሆነ፤ ነገር ግን የጅቡቲ ወደብ አገልግሎት፣ የመርከቦች አገልግሎት የኢትባትሎድ መርከቦች ከ327 (ሦስት መቶ ሃያ ሰባት) ወደቦች ጭነት ሲያነሱ ክፍያው በውጭ ምንዛሬ የሚከፈል በመሆኑ ዘርፉ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ፍላጎት እንዳለው አመልክተዋል። የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ከማዋል አንጻር የተነሳው ትክክለኛ ሐሰብ እንደሆነና የሀገር አቀፍ የአንድ መስኮት አገልግሎት ጅማሬ እንደሆነና ሌሎችም በመሠራት ላይ ያሉ ሥራዎች እንዳሉ አሳውቀዋል። የመጋዘን ግንባታ እና አገልግሎት በግሉ ዘርፍም ትኩረት ተሰጥቶ ቢሠራበት ለሎጂስቲክስ ዘርፉ ትልቅ እመርታ የሚያመጣ እንደሆነ ገልጸዋል። በተመሳሳይ፣ ዶ/ር ማቲዎስ እና ወ/ሮ ኤልሳቤጥ በሰው ኃይል ማብቃት ላይ፣ በኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ማዘመን እና በፋይናንስ እጥረት ላይ ተመሳሳይ አስተያየቶችን አቅርበዋል።

አቶ ማሞ ምኅረቱም ዘርፉ ከመቼውም በበለጠ ከፍተኛ ትኩረት እንደተሰጠው አንስተው፤ ይህም በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው መቀመጡንና የሎጂስቲክስ ዘርፍ ሌሎችን ዘርፎች የሚያበቃ እና ውጤታማነታቸውን የሚወስን፤ የራሱንም ገቢ የሚያመነጭ የእድገት ዘርፍ በመሆኑ እንደሆነ አሳይተዋል። የሎጂስቲክስ ስትራቴጂው

አዲስ ይዞት የመጣው ሐሳብ ሥርዓት ተኮር (systemic approach) የችግሮች አተያይ እንደሆነ፤ ይህም የችግሮች ምንጭ ከብዙ ቦታ እንደሚመጣ የሚረዳ፤ ችግሩ በአንዴ እንደማይፈታ የሚረዳ እና በሂደት እየተማማርን ችግሮችን እየፈታን የምንሄድበትን መንገድ የሚከተል እደሆነም አሳይተዋል። ስለሆነም፣ ይህን ለማድረግ ሁሉም ባለድርሻ ኃላፊነቱን እንዲወጣ የሚያስችል መሆኑና ለምዘናም ሦስቱ መለኪያዎች በቀላሉ የሚከወኑ መሆናቸው እንደሆነ አስረድተዋል፡ ፡ ወደትግበራ ይገባ በሚል የሚነሳው ጉዳይ ላይ ትላልቅ የትግበራ ሥራዎች ውስጥ እንደተገባ፤ ሞጁን ለማዘመን እየተሠራ ያለው ሥራ፣ በጉምሩክ በኩል የአንድ መስኮት አገልግሎት መሰጠት መጀመሩ፣ በሎጂስቲክስ ስትራቴጂው የግሉን ዘርፉ ወደኢንዱስትሪው ለመጋበዝ የተወሰነው ውሳኔ፤ እንዲሁም በጉምሩክ የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ የተሠራው ሥራ ሁሉ ወደትግበራ ውስጥ መግባቱን የሚያሳይ እንደሆነ አንስተዋል። ለወደፊትም በሎጂስቲክስ ኢንዱስትሪው በመንግሥት የሚሠሩ ያሏቸውን ሦስት ጉዳዮች ሲያስቀምጡ፣ አንደኛ፣ የሎጂስቲክስ መሠረተ ልማቶችን መገንባት፤ ሁለተኛ፣ የግሉን ዘርፍ በሎጂስቲክሱ እንዲሳተፍ ማድረግ፤ እና ሦስተኛው የዘርፉን የሕግ እና አስተዳደር ጉዳዮች ማዘመን እንደሆኑ አስታውቀዋል። በተለይ የኢባትሎድን ድርሻ ወደግል ለማስተላለፍ የታቀደው እቅድ የውጭ ምንዛሬ ከማግኘት ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው እና ዋናው ዓላማ ዘርፉ ለሌሎች ዘርፎች አስቻይ አቅም ያለው እንደመሆኑ ዘርፉን ማዘመን ብቻ እንደሆነ አስረድተዋል።

የትራንስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ዳግማዊት ሞገስ በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ በሰጡት ሐሳብ በሎጂስቲክስ ዘርፉ የሚነሱ ጥያቄዎች ለረጅም ጊዜ እንደቆዩ ጠቅሰው፤ በዚህ አንድ ዓመት ውስጥ በዘርፉ ያለውን ችግር ለመፍታት የሠራናቸው ሥራዎች ገና በጅምር ላይ መሆናቸውን ተረድተው ተሳትፏቸውን እንዲያጠናክሩ ጠይቀዋል። በተያዘው የሪፎርም ሥራ የዘርፉን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ እየተሠራ እንዳለ እና የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ ለማሳደግ አብራችሁን እንደትሠሩ የሚል ማሳሰቢያ አቅርበዋል። የጭነት ማንሻ ተሽከርካሪዎች እጥረት እንዳለ፤ ይህንንም ለማስተካከል እየሠራናቸው ያሉ ሥራዎች መኖራቸውን፤ እንዲሁም በመጋዘን አገልግሎት ላይ ያለውን ችግር እንድትረዱና የግሉ ዘርፍም በሁሉም ችግሮች ላይ የድርሻውን ወስዶ በመሥራት ችግሮችን በጋራ እንድንፈታ ሲሉ ጥያቄ አቅርበዋል።

በተጨማሪም፤ የሎጂስቲክስ ስትራቴጂውን መጽደቅ ተከትሎ የሎጂስቲክስ ትራንስፎርሜሽን ቢሮ ተቋቁሞ ወደሥራ እየገባ ነው። ካውንስሉ እንደሚቋቋም፤ ነገር ግን ካውንስሉ በከፍተኛ ኃላፊዎች ደረጃ የሚቋቋም እንደመሆኑ የእለት ተእለት

ሥራን የማስፈጸም/የመምራት እድል እንደማይኖረው ጠቁመዋል። ያም ሆኖ ግን በተዘዋዋሪ እየታቀደ ባለው የዐሥር ዓመት እቅድ በዘርፉ ባለድርሻ የሆኑ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቶች ዘርፉን ለማገዝ በጋራ ተቀናጅተው እቅድ እያቀዱ እንደሆነ አስታውቀዋል። የግሉ ዘርፍም በዚሁ ልክ የራሱን ድርሻ ወስዶ ለመሥራት ዝግጁ እንዲሆን አሳስበዋል። በመጨረሻም እንደሀገር በዐሥሩ ዓመት እቅድ ላይ የኢትዮጵያን የሎጂስቲክስ አገልግሎት በዓለም አቀፍ ደረጃ አሁን ላይ ካለበት የስልሳኛ ደረጃ ወደዐርባኛ ደረጃ ለማማጣት በጋራ መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።







# 2.5 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ “ዌቢናር” አንድ፣ ፈጠራ በቀውስ ጊዜ

ሚያዝያ 21 ቀን 2012 ዓ.ም




ይህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት እንደሌላው ጊዜ በአዳራሽ ውስጥ የተደረገ አይደለም። ይልቁንም፣ በቴክኖሎጂ በመጠቀም የተደረገ ውይይት ሲሆን፤ የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኢትዮጵያ ስጋት በመሆኑ፤ የተነሳ የሰዎችን የእርስ በርስ ግንኙነት እና እንቅስቃሴ በመገደቡ በአካል በመራራቅ የተደረገ ውይይት ነው። የመወያያ ርእሱም “ፈጠራ በቀውስ ጊዜ” የሚል ነው። በየዘመኑ ያለፉት ትውልዶች በፈተና ወቅት ፈጠራን ተጠቅመው ችግሮችን ማለፍ መቻላቸውን ታሳቢ አድርገን እኛም በዚህ ወቅት ምን ዓይነት ፈጠራ ተጠቅመን ይህን ፈተና እንለፈው? በዚህ ጊዜ ምን ተምረን ማለፍ አለብን? የሚለውን ዓላማው አድርጎ የተካሄደ ውይይት ነው። የፈጠራን ሚና ከታሪክ፣ ከሳይንስ፣ እና ከሥነልቦና አኳያ በማንሳት ያለፈው እና ያሁኑ ሁኔታ የተቃኘበት ውይይት ነው። ውይይቱን የመሩት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ምኒስትር ዶ/ር አብርሃም በላይ (የቀድሞ) ናቸው።

በዚህ የአዲስ ወግ “ዌቢናር” ውይይት ላይ በውይይት ሐሳብ አቅራቢነት የተሳተፉት

(የቀድሞ) የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ ሙፈሪያት ካሚል፣ ወ/ሮ ሰብለ ኃይሉ የሥነ ልቦና ባለሙያና የ"እንዴ የማማከር አገልግሎት" መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ፣ ዶ/ር ታምራት ኃይሌ የታሪክ ምሁር፣ አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ የ"ኤክስ ሃብ አዲስ" መሥራች፣ አቶ የሱፍ ራጃ የ"ኢትዮጆብስ" መሥራችና ዋና ሥራ አስኪያጅ፤ እንዲሁም ዶ/ር ፍጹም አሰፋ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ናቸው።

የመጀመሪያ ንግግር ያደረጉት የሰላም ሚኒስቴር ሚኒስትር ወ/ሮ መፈሪያት ካሚል ሲሆኑ፤ በንግግራቸው የኮቪድ -19 ወረርሽን በዓለም አቀፍ ደረጃ በሰው ልጆች እና ሰብዓዊነት ላይ እያስከተለ ያለው ችግር ዓለም አቀፋዊ እና ሀገራዊ አንድምታው፣ ችግሮችን ለመፍታት እየተደረጉ ያሉ የመከላከያ መንገዶች እንዴት በጋራ ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ፤ ችግሩን በትብብር ብቻ ለማጋፈጥ መሞከሩ ውጤት ሊያመጣ እንደሚችል አንስተዋል። በዚህ መሰል የቀውስ ወቅት ፈጠራዎች ምን መምሰል አለባቸው በሚለው ሐሳብ ላይም ሦስት መሠረታዊ የፈጠራ መርሆዎች እንዳሉ ጠቁመዋል። የመጀመሪያው በፈጠራ ሥራዎች ውስጥ የሞራል እሴቶችን ማሳደግ እንደሆነ፤ የተፈጠረው ችግር ሁሉንም የሰው ልጆች እያጠቃ እንደመሆኑ የፈጠራዎች ቀዳሚ ዓላማ የሰውን ልጆች ማዳን፤ ከሞት መታደግ ሊሆን እንደሚገባው፣ ሁለተኛው፣ ፈጠራዎች ከወትሮው የተለየ የአስተሳሰብ ወይም የአመለካከት ቅኝት በማስፋት አዳዲስ አቅጣጫዎችን መጠቆም በሚያስችል የፈጠራ ሥራ ላይ ማተኮር፤ ይህም የፖሊሲ እና መሰል ጉዳዮችንም የሚያካትት ሲሆን ሥራ የሚያቀልሉ፤ አድካሚ የቢሮክራሲ አሠራሮችን ማቀላጠፍ የሚችሉ ፈጠራዎች ላይ ማተኮር እንደሚኖርበት እና ሦስተኛው መርሆ ደግሞ፣ ሁሉም የፈጠራ ሥራዎች ሰብዓዊነትን ያከበሩ መሆን ይገባቸዋል የሚሉት እንደሆኑ አስረድተዋል ።

ዶ/ር ታምራት ኃይሌ  በበኩላቸው፣ በዓለማችን ታሪክ በቀውስ ወቅት ስለተካሄዱ የፈጠራ ሥራዎች ተናግረዋል። በዚህም፣ ዓለማችን በጦርነት፣ በተስቦ በሽታ፣ በጉንፋን፣ በኮሌራ እና በፈንጣጣ ወረርሽኞች በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎችን ሕይወት ያጣችባቸውን ክስተቶች፤ ኢትዮጵያም "ክፉ ቀን" በሚባለው እና በ"ኅዳር በሽታ" ምን ዓይነት ጉዳት እንደደረሰባት አሳይተዋል። በእነዚህ ጊዜያት የተለያዩ ዓይነት ፈጠራ የታከለባቸው በሽታን እና ተያያዥ ችግሮችን የሚከላከሉ ሥራዎች ይሠሩ እንደነበር፤ አሁን ድረስም ጥቅም ላይ የሚውለው የለይቶ ማቆያ  ሐሳብ (quarantine) በዚህ መሰል ችግር ወቅት በጣሊያን የተጀመረ መሆኑን በኢትዮጵያም የ"ኅዳር በሽታ" ተብሎ በሚታወቀው ወረርሽን ጊዜ "ወሸባ" በሚል

ጥቅም ላይ እንደዋለና በዚሁ ወቅት አዲስ አበባ ክፉኛ በወረርሽኙ ተጠቅታ ስለነበር እስከ20 (ሃያ) በመቶ የሚሆነው ነዋሪዋም ሕይወቱን በማጣቱ የነዋሪውን ሕይወት ለማታደግ በጎ ፈቃደኞች ቤት ለቤት በመሄድ ምግብ ያከፋፍሉ እንደነበር፤ የመቃብር ስፍራዎች ላይም ንክኪ እንዳይኖር እና የክቡሩ ሰው ልጅ አስከሬንም እንዳይገላታ በሚል በኖራ ምልክት በማድረግ እንዳይነካ የማድረግ ሥራ ይሠሩ እንደነበር ዶ/ር ታምራት አንስተዋል።

አቶ የሱፍ ራጂ የኮቪድ-19ን ወረርሽኝ ከሥራ ሁኔታዎችና ከሥራ ፈጠራ ጋር በተያያዘ ንግግር አድርገዋል። በዚህ ወረርሽኝ ወቅት የበሽታውን መዛመት ለመግታት ተብሎ በሚወሰደው ማህበራዊ ርቀትን መገደብ ምክንያት የሰዎች የእርስ በርስ ግንኙነት በመገደቡ ለሕዝብ አገልግሎት በሚሰጡ ሆቴሎች፣ መዝናኛ ስፍራዎች ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች አንዳንዶች ሙሉ በሙሉ ሥራ አቁመዋል። አንዳንዶች ደግሞ በውስን አቅማቸው ሥራ እየሠሩ እንደሚገኙና በቢሮ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ ሥራዎችም በዚህ ወረርሽኝ ምክንያት መስተጓጎል እንደገጠማቸው አንስተዋል። በእነዚህ ምክንያቶች ብዙ ሰው ሥራ ያቆመበት እና መደበኛ ሕይወቱን ይመራበት የነበረው ገቢው የተስተጓጎለበት ሁኔታ መፈጠሩንም አስታውሰዋል። ችግሮችን ለመፍታት እየተወሰዱ ያሉ መፍትሔዎች አዳዲስ የአሠራር ሥርዓት እና ፈጠራንም እያበረታቱ እንዳሉም ጠቅሰዋል። እንደማሳያም ሆቴሎች እና መሰል አገልግሎት ሰጭዎች የ“ደሊቨሪ” አገልግሎት በስፋት መጀመራቸው፣ ቢሮ ውስጥ ይሠሩ የነበሩ የዴስክ ሠራቶኞች ቴክኖሎጂዎችን በመጠቀም በቤታቸው ሆነው እንዲሠሩ መደረጉን እና ሌሎችም አዳዲስ አሠራሮች ተግባራዊ እየተደረጉ እንደሆነ አስረድተዋል። ቀውሱ የዲጂታል ግብይቱን በከፍተኛ ሁኔታ እንዳሳደገውም ይህም ለብዙ ሰዎች የሥራ እድል እንደፈጠረ አብራርተው።

አቶ ቴዎድሮስ ታደሰ በንግግራቸው፣ በታሪክ ውስጥ ብዙ ፈታኝ ወቅቶች ለፈጠራ ምክንያት እንደነበሩና በምዕራብ አውሮፓ “ጥቁር ሞት” ተብሎ በሚታወቀው ወረርሽኝ ወቅት ያጋጠማቸው ፈተና አሁን ለደረሱበት የሥልጣኔ ደረጃ መሠረት የሆኗቸውን የፈጠራ ሥራዎች እንዲሠሩ ያስገደዳቸው አጋጣሚ እንደነበር ገልጸዋል። አሁን ዓለምን የገጠማት ዓይነት ፈተና ለፈጠራ ሥራዎች ምቹ ሁኔታ እንደሆነም ሲያስረዱ፤ አንድም እንደልብ መንቀሳቀስ ባለመቻሉ ምክንያት ብዙ ያልተሟሉ ፍላጎቶች መኖራቸው እና አብዛኛው ሰው ተረጋግቶ የሚያስብበት ሰፊ ጊዜ በቤቱ ማግኘቱ ለፈጠራ ማደግ ምክንያት እንደሚሆኑ አስረድተዋል። አሁን በሀገራችን የኮቪድ 19 ወረርሽኝ የፈጠረው ቀውስም ለዚሁ የፈጠራ ሥራ ማደግ ምክንያት

እንደሆነ የኦንላይን የግብይት መተግበሪያዎች፣ የክፍያ መፈጸሚያ መተግበሪያዎች እና የሰውን ንክኪ የሚቀንሱ መሣሪያዎች በስፋት እየተሠሩ እንደሆነ አስታውቀዋል።
ዶ/ር ፍጹም አሰፋ ሐሳባቸውን ያቀረቡት በዚህ መሰል የቀውስ ጊዜ ምላሽ በሚሰጡ የመንግሥት አደረጃጀቶች እና ሌሎች ጊዜያዊ መዋቅሮች አደራጃጀት እና ሥራ ላይ ነው። በቋሚነት ለዚህ መሰል ክስተቶች ምላሽ የሚሰጥ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን በቋሚነት ለቀውስ ጊዜዎች ምላሽ ለመስጠት የሚሠራ እንደሆነና ለኮቪድ-19 ምላሽ መስጠት በሚያስችል ሁኔታም እራሱን እያደራጀ እንደሚገኝ አስረድተዋል። በሌላም በኩል፣ በጊዜያዊነት በዚህ ችግር ላይ የሚሠሩ አደረጃቶችም ተፈጥረዋል። ዋነኛው በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚመራው ብሔራዊ ኮሚቴ ሲሆን፤ በስሩ የጤና፣ የኃብት አሰባሰብ፣ የቴክኖሎጂ፣ የኢኮኖሚ፣ እና የሕዝብ ግንኙነት ንዑሳን ኮሚቴዎች አንዳሉ እና በሥራቸውም ጥናቶችን በማድረግ አዳዲስ አሠራሮችን የሚያቀርቡ የቴክኒክ ኮሚቴዎች ተቋቁመው እስከታችኛው የመንግሥት መዋቅር ድረስ መሥራት መጀመራቸውን ገልጸዋል። በዚህ ቀውስ ከፍተኛ ተጋላጭ የሆነውን ድኃውን ሕዝብ በቀላሉ ለማገዝ የሚያስችሉ ሌሎች ሥራዎችም እየተከወኑ እንደሆነ ጠቅሰው፤ በዚህ ረገድ በአዲስ አበባ የተቋቋሙት 1200 (አንድ ሺሕ ሁለት መቶ) የሚጠጉ የምግብ ባንኮች ድሃውን በማገዝ ላይ እንደሚገኙ እና የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ጨምሮ በሥርዓት ደረጃም የተለያዩ ሕጎች እና ደንቦች እየወጡ መሆኑን አስረድተዋል።

በተጨማሪም፣ በቀውሱ ምክንያት ብዙ ዓይነት ፈጠራዎች እንደታዩ፤ ትናንሽ ቢዝነሶች እራሳቸውን ለማዳን በሚል ምግብ ቤቶች ምግብ እስከቤት የማድረስ፣ ወፍጮ ቤቶች ቤት ድረስ የማድረስ፣ የሬዲዮ፣ የቴሎቪዥን እና የመስመር ላይ የትምህርት ሂደቶች ስብሰባዎች እና ሥራዎችን በቴክኖሎጂ መከወን እንደሚቻል እንደታየ አብራረተዋል። በተቋማት ደረጃ ደግሞ ያሉን ተቋማት ይህን መሰል የቀውስ ጊዜያት መቋቋም እንደማይችሉ እና ደካማ እንደሆኑ፤ እንዲሁም አብዛኛው የኢኮኖሚው እንቅስቃሴ እና የመንግሥት አገልግሎት በአካል መገኘትን የሚጠይቅ ደካማና ያልዘመነ መሆኑን መገንዘብ እንዳስቻለ፣ ከፍተኛውን የኦኮኖሚ ድርሻ የሚይዘው ኢመደበኛው የኢኮኖሚው ክፍል በከፍተኛ ሁኔታ በመጎዳቱ ምክንያት ኢኮኖሚያችን በጣም መጎዳቱን፣ የመረጃ እና የግንኙነት ሥራዎች ባህላዊ የሆነና ወደዘመናዊ "አውቶሜትድ" ወደሆነ መንገድ መግባት እንዳለብን ያሳየ እንደነበር ገልጸዋል። በተለያዩ ተቋማት መካከል የቅንጅት ጉድለት እንዳለ መታየቱና እነዚህን መሰል ችግሮች መፍታት እንደሚገባም የተረዳንበት ቀውስ እንደነበር አስረድተዋል።
በመጨረሻም የመነሻ ሐሳባቸውን ያጋሩት ወ/ሮ ሰብለ ሲሆኑ፤ በቀውስ ወቅት በሚኖር የሥነ ልቦና ሁኔታ እና ፈጠራ ላይ ያተኮረ ነበር። አሁን ያለንበትን የመሰለ ቀውስ ሰዎችን

በሥነልቦና ቀውስ ውስጥ የሚያስገባ እንደሆነና ሁኔታውንም የሚያባብሱ እንደሆኑ፤ በሰዎች አስተሳሰብ ላይ ደግሞ ሕይወታችን በእኛ ቁጥጥር ላይ እንዳልሆነች የሚያሳይ አስተሳሰብ የሚፈጥር ሲሆን፣ በሌላ መንገድ ቀውስ ፍርሃትን፣ የሃዘን ስሜትን እንደሚፈጠር አንስተዋል። የአሁኑ ቀውስ ብዙ የሥነልቦና ችግሮችን የሚያስከትል፣ ማህበራዊ ሕይወታችንም በብዙ መንገድ የሚቀይር እንደመሆኑ እነዚህን ሁሉ ሁኔታዎች ለማስተካከል የምንወስዳቸው ርምጃዎችም ፈጠራ በታከለበት መንገድ ችግሮች የሚፈቱበት እና ጤናማ የሥነልቦና ሁኔታ መፍጠር በሚያስችል መንገድ መጠቀም እንደሚኖርብን አስረድተዋል። ለምሳሌ በቤት ውስጥ የሚደርሱ ጥቃቶች የሚጨምሩበት ሁኔታ ካለ እነዚህን የግጭት ሁኔታዎች ከወትሮው በተለየ በመነጋገር ለመፍታት መሞከር እንደሚገባ አሳስበዋል።

## ለቀረቡ ጥያቄዎች የተሰጡ ምላሾች

“ወረርሽኙን በመቆጣጠር ላይ የተገኙ ስኬቶች እና ሁሉም አስተዳደር አካላት ቅንጂት እንዴት ነው?” የሚል ጥያቄ ለሰላም ሚኒስትሯ ቀርቦላቸው ምላሽ ሲሰጡ፣ በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ መንግሥትም፣ ሕዝቡም ቅድሚያ ሰጥቶ እየሠራ ያለው ሕይወትን ለማዳን እንደሆና በዚህ ሕይወትን በማዳን ሥራ እንደመንግሥት የሚቀድመው ነገር በሽታው ከመመርመር አቅም ጋር እንደሚያያዝ፤ የመጀመሪያ ታማሚ በሀገራችን ከተገኘ አንድ ወር ከዐሥራ አምስት ቀን ቢሆንም በዚህ ጊዜ ውስጥ ናሙና ወደውጭ ልኮ ከማስመርመር አሁን ላይ ወደ24 (ሃያ አራት) የምርመራ ላብራቶሪዎች መቋቋማቸውን፤ የመመርመር አቅማችንም አሁን 4500 (አራት ሺሕ አምስት መቶ) ገዳማ መድረሱን፤ በቀጣይ ሳምንት ከአምስት ሺሕ እስከ ሰባት ሺሕ ለማድረስ እየተሠራ እንደሆነም መረጃ ሰጥተዋል። በማቆያ ተቋማት ላይም እስከ250 (ሁለት መቶ ኀምሣ) ሺሕ ሕዝብ ማስተናገድ የሚችሉ ማቆያዎች ማዘጋጀት ተችሏል ብለዋል። የተከሰተው ወረርሽኝ በአካል አብሮ መሆንን የሚገድብ ከመሆኑ አንጻር በህብረተሰቡ እና በመንግሥት የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሆነም አስረድተዋል።

በተጨማሪም፣ በመንግሥት ዲፕሎማሲ ሥራ ኢትዮጵያ የወረርሽኙን ሁኔታ ለመከላከል በሚደረገው ጥረት የአካባቢውን ሀገራት እና የአፍሪካን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚከናወኑ ለኢትዮጵያም ለአፍሪካ ሀገራትም በእርዳታ የሚገኙ የመከላከያ ቁሳቁሶችን በማሰባሰብ በትብበር እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል። በኃብት ማሰባሰብ ላይም በሀገር አቀፍ ደረጃ እየተሠራ እንደሆነ፤ ከገንዘቡም በላይ አብሮነትን ለመፍጠር በዚህ ወቅት ሁላችንም አብረን ተባብረን

የምናልፍበትን ሥራ እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል። የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥም ግብዓት ከማቅረብ ጀምሮ በትናንሽ ቦታዎች በመጠቀም ምግብ ለማምረት የሚያስችል የከተማ ግብርና ሥራም እየተሠራ እንዳለ፤ "የከፋ ችግር ቢመጣ" በሚል አዲስ አበባ ላይ የተጀመረውን የምግብ ባንክ ልምድ ወደክልሎች ለማስፋት እንቅስቃሴዎች መጀመራቸውን፤ በየአካባቢውም ንጽህናን ከመጠበቅ አንጻር ወጣቶች በበጎ ፍቃድ በየሰፈሩ እየሠሯቸው ያሉ ሥራዎች እና በእምነት ተቋማት በኩል የሚደረገው የአምልኮ ሥነሥርዓት የሕዝቡን አንድነት እና እይታ ያሳዩ ሥራዎች እንደሆኑ አስረድተው፤ ህብረተሰቡ መዘናጋት እንደማይገባው እና የጥንቃቄ ተግባራትን በአግባቡ መፈጸም እንዳለበት አሳስበዋለል።

ዶ/ር ታምራት ኃይሌ በበኩላቸው፣ "መሰል ቀውሶች በተፈጠሩባቸው የታሪክ ክስተቶች የምግብ ዋስትና እና ከምግብ አቅርቦት እንዲሁም ከለይቶ ማቆያ ጋር የተወሰዱ የመፍትሔ ርምጃዎች ምን ነበሩ?" በሚል ለተነሳው ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ፤ በኢትዮጵያ ታሪክ አስከፊ ገጽታ የነበረው "ክፉ ቀን" በሚል በሚታወቀው ወረርሽኝ ወቅት ከፍተኛ ቁጥራ ያላቸው እንስሳት በመሞታቸው እና ገበሬው የእርሻ ሥራ መከወን ባለመቻሉ ምክንያት ከፍተኛ የምግብ እጥረት ተከስቶ እንደነበር አንስተዋል። በኅዳር በሽታ ወረርሽኝ ወቅትም የአዲስ አበባ ከተማ ነዋሪዎች በከፍተኛ ሁኔታ በወረርሽኙ ተጠቅተው ስለነበር በበጎ ፈቃደኝነት ነዋሪውን ከረሃብ ለመካላከል ቤት ለቤት ምግብ የማከፋፈል ሥራ የሚሠሩ ሰዎች እንደነበሩ አስታውሰዋል። እንዲሁም፣ በቤተ መንግሥት ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሕዝብ ግብር ይበላ ስለነበር እንደወትሮው ሁሉንም ሰው የወትሮውን ዓይነት ምግብ ማዳረስ ባለመቻሉ ምክንያት በቤተ መንግሥት ፍትፍት (ፍርፍር) እና ንፍሮ ለሕዝቡ ይሰጥ እንደነበር ገልጸዋል። በአውሮፓ "ጥቁር ሞት" (Black Death) በሚባለው ወቅት ደግሞ ሀገራት ከፍተኛ ቁጥር ያለውን የጉልበት ሠራተኛ በበሽታው በማጣታቸው ምክንያት የምግብ እና የምርት እጥረት እንዳይፈጠር የተመረጡ ምርታማ ሰብሎችን ለም በሆኑ በተመረጡ መሬቶች ላይ በማልማት ቀሪውን መሬት ለእንስሳት ርባታ በማዋል የምግብ እጥረትን እና ምርታማነታቸውን ማስቀጠል የቻሉበት የታሪክ አጋጣሚ እንደነበር አስረድተዋል።

አቶ ቴዎድሮስ ታደሰም፣ "እንዲህ ባለ የቀውስ ጊዜ ለምን ስለፈጠራ እናወራለን? የሚል ጥያቄ ቀርቦላቸው፤ ስለኮቪድ19 ዓለም አውቆ ወይንም ሠርቶ የጨረሰው ጉዳይ አለመሆኑ፤ በሽታውን ልናውቅ፣ ልንማር፣ እንዲሁም በመከላከያው ላይ ልንሠራ ስለሚገባ፤ ብዙው ወጣት፣ መሥራት የሚችል የሰው ኃይል በዚህ ቀውስ ምክንያት በቤት ውስጥ ተቀምጦ መገኘቱ፤ ከዚህ ቀደም ጊዜ ሰጥተን ባላሰብናቸውን ጉዳዮች

ላይ በሰፊው ማሰብ የሚያስችለን ጊዜ በመኖሩ እና ሀገራችን በቀውሱም ጊዜ በፊት ልንፈታቸው የሚገቡ ብዙ ችግሮች ያሉብን ስለሆነ እነዚህ ሁሉ ችግሮች ልንፈታቸው የምንችለው ፈጠራን ስናበረታታ እና አዳዲስ የአሠራር መንገዶችን፣ መሣሪያዎችን መፍጠር ስንችል በመሆኑ ስለፈጠራ መነጋገር አለብን ሲሉ አስረድተዋል። ወረርሽኙ ከተከሰተ ጀምሮ በዓለም ላይ እስከ 60 (ስድሳ) ሺሕ ፈጠራዎች መሠራታቸውን እና በእኛም ሀገር በትምህርት ላይ የሚሠሩና በ"ኦንላይን" ግብይት ላይ የተሠሩ ብዙ ፈጠራዎች እንዳሉ አሳውቀዋል።

"ድርጅቶች ለዚህ ቀውስ እንዴት ምላሽ ሰጡ? ሠራተኞችስ እንዴት ተጠቃሚ ሆነው መቀጠል ይችላሉ? በሚል ለተነሱ ጥያቄዎችም፣ በምርት ሥራ ላይ የተሰማሩ ድርጅቶች "ማህበራዊ ርቀትን ማስጠበቅ" የሚለውን ሕግ ተግባራዊ በማድረግ በምርት ሂደት የሠራተኞችን ቁጥር በመቀነስ፤ በፈረቃ የማሠራት አካሄድ እየታዘብን ሲሆን፤ በቢሮ ሥራ ላይ የነበሩ ሠራተኞች ደግሞ ቴክኖሎጂ በመጠቀም በቤታቸው ሆነው የሚሠሩበትን መንገድ እየተገበሩ እንደሆነ አስረድተዋል። ከሥነ ልቦና አንጻርም "በዚህ ወቅት ሰዎች የፍርሃትን ስሜት ለመጋፈጥ ምን ማድረግ አለባቸው?" ለሚለው ጥያቄ፣ በፍርሃት ስሜት ውስጥ ስንገባ መጀመሪያ "ምንድን ነው ያስፈራኝ?" በማለት ተግባራዊ ምላሽ ያስፈልገዋል። ወይም በሐሳባችን ብቻ የፈጠርነው ነገር መሆኑን አስበን ምለሽ በመስጠት እና ያን የፍርሀት ኃይል ወደበጎ ስሜት በመቀየር ምላሽ መስጠት እንደሚቻል አሳውቀዋል።

ከኢኮኖሚ አኳያ፣ "ይህ ወረርሽኝ ኢኮኖሚያችንን በከፍተኛ ሁኔታ ይጎዳል ተብሎ ይታሰባልና ትናናሽ ቢዝነሶችን ከዚህ ለመታደግ ምን ታስቧል?" በሚል ለተነሳው ሐሳብ ዶ/ር ፍጹም አስተያየት ሲሰጡ፤ ወረርሽኙ ዓለም አቀፉን ኢኮኖሚ ያሚያናጋ እንደሆነ እና ለአነስተኛ ቢዝነሶች ጉዳቱ የከፋ እንደሚሆን በማሰብም የኢትዮጵያ መንግሥት የተለዩ ርምጃዎች እየወሰደ እንደሚገኝ አሳስበው፤ አንዱም 15 (ዐሥራ አምስት) ቢሊዮን ብር በብሔራዊ ባንክ በኩል ወደግል ባንኮች እንዲደርስ የተደረገ ሲሆን፤ ይህም አነስተኛ ቢዝነሶች የብድር ጊዜያቸው እንዲራዘም እና ተጨማሪ ብድርም እንዲያገኙ ለማስቻል ያለመ እንደሆነ ተናግረዋል። በዚህ ወረርሽኝ ምክንያት የምግብ እጥረት የሚገጥማቸውን፤ በአጠቃላይ የእለት ጉርሳቸው የሚያጥራቸውን 15 (ዐሥራ አምስት) ሚሊዮን ዜጎች ከወትሮው በሴፍቲ ኔት ድጋፍ ከሚደረግላቸው 15 (ዐሥራ አምስት) ሚሊዮን ያክል ዜጎች ጋር በአጠቃላይ 30 (ሠላሳ) ሚሊዮን ዜጎችን ለመመገብ የሚያስችል ሥራ እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል። ለወትሮው ሀገራችን ወደ17 (ዐሥራ ሰባት) ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ከውጭ የምታስገባ ሲሆን፤

አሁን በዓለም አቀፋዊው ሁኔታ ምክንያት የሚሸጥ ሀገር ላይገኝ ስለሚችል ይህን ችግር ለመከላከል ሁሉም የሀገራችን መሬቶች ጦም እንዳያድሩ በሚል በእርሻ ሥራ ላይ ከፍተኛ ሥራ እየደጀመረ አስረድተዋል።

በፋብሪካዎች በኩል ሥራዎች እየተሠሩ እንዲቆይ እና ሠራተኞችን እንዳይቀንሱ፤ ወረርሽኙን ለመከላከል የሚያገለግሉ የአፍ እና የአፍንጫ መሸፈኛዎች፣ እንዲሁም "ሳኒታይዘሮችን" ወደማምረት የሚሸጋገሩበትን መንገድ በማመቻቸት ላይ እየተሠራ እንደሆነና የውጭ ንግድንም ለማስፋፋት የቁም ከብቶችን ወደመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ለመላክ ጥረት እየተደረገ እንደሆነ፤ የሀገር ውስጥ ምርቶችን የመጠቀም ልምድ ለማዳበር እና ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ወስጥ ለመተካት እያበረታቱት እንደሆነ አስረድተዋል።

በመጨረሻም፣ በዚህ "ዌቢናር" ላይ ተሳትፈው ንግግር ያደረጉ እንግዶች "በዚህ የኮቪድ ወረርሽን ወቅት ያስደመማችሁ ፈጠራ ምንድን ነው?" በሚል ለቀረበላቸው ጥያቄ ከዘረዘሯቸው የፈጠራ ሥራዎች መካከል  የቤት ውስጥ ሰላምን መፍጠርና አዲስ የቤተሰብ ባህል መፍጠር የቻሉ ሰዎች፤ የአምልኮ ሥርዓቶች በቀጥታ የቴሌቪዥን ሥርጭት  መተላለፉ ትኩረታቸውን የሳባቸው እንደሆነ፤ መካኒካል ቬንትሌተሮች፣ በእንግሊዝ ሀገር እጅን ወደአፍ እንዳንሰድድ የሚያደርገው ፈጠራ፣ የበር መክፈቻዎች፣ ትምህርትን በኦንላይን መስጠትና እና ማስክ ማምረት የጀመሩ ወጣቶች፤ በሱቆች ላይ በረጅም እንጨት ገንዘብ መቀባበልን የመሰሉ ፈጠራ የታከለባቸው የእለት ተእለት እንቅስቃሴዎች ትኩረታቸውን እንደሳቧቸው ተናግረዋል።

ለሕዝቡም በአስተላለፉት መልዕክት፤ በቀላል ፈጠራዎችና ሕይወታችንን በሚለውጡ ሥራዎች ላይ እንዲያተኮር፤ በድንገት የመጣው አጋጣሚ በድንገት እንዳያመልጠን የራሳችንን ምግብ፣ የመድሐኒት፣ እንዲሁም መሠረታዊ ነገሮች ወደማምረት የሚወስደን አጋጣሚ አድርገን በመጠቀም ነጻ ሕዝቦች መሆናችንን የምናረጋግጥበት እንዲሆን፤ ቀውሱ የሰዎች ልጆች የጋራ ፈተና እንደመሆኑ በጋራ በመቆም መንግሥት የሚያስተላልፋቸውን የጥንቃቄ ተግባራት በመስማት እና ተግባራዊ በማድረግ ለጋራ ደኅንነት መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል። በተጨማሪም፣ ሐሳብ በማዋጣት የሀገራችንን እጣ ፈንታ እንድንሠራ፤ ከታማኝ ምንጮች የተረጋገጡ መረጃዎችን በመስማት ከአላስፈላጊ መደናገጥ እራሳችንንና አካባቢያችን መጠበቅ እንደሚገባ መልዕክት አስተላልፈዋል።

# 2.6 አዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ “ዌቢናር” ሁለት ፣ ፈጠራ በቀውስ ወቅት፤ ከታሪክ ምን እንማር? በሥነ ልቦና እንዴት እንጠንክር?

ሚያዝያ 21 ቀን 2012 ዓ.ም




ይህ የአዲስ ወግ “‘ዌቢናር’ ፈጠራ በቀውስ ወቅት፣ ከታሪክ ምን እንማር? በሥነልቦና እንዴት እንጠንክር?” በሚል ርዕስ ከባለፈው ወር የቀጠለ፤ በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በዙም (Zoom) የግንኙነት መላ የተደረገ ሁለተኛው ውይይት ሲሆን በግንቦት 24፣ 2012 ዓ.ም ተካሂዷል። ካለፈው ወር በቀጠለው “ፈጠራ በቀውስ ወቅት ምን መምሰል አለበት? ከአለፈ ታሪክስ ምን እንማር? እና በሥነልቦናስ እንዴት መጠንከር አለብን” ውይይት የተደረገበት ፕሮግራም ሲሆን በውይይቱ ዶ/ር ታምራት ኃይሌ፣ ረዳት ፕሮፌሰር አበባው አያሌው የታሪክ መምህርና የቅርስ ጥበቃ ባለሥልጣን ምክትል ዳይሬክተር፣ ዶ/ር ቢንያም ወርቁ እና ዶ/ር ባርኮት ሚልኪያስ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የጤና ሳይንስ ኮሌጅ የአዕምሮ ሕክምና ረዳት ፕሮፌሰሮች የተሳተፉ ሲሆን፤ ዶ/ር ታምራት ኃይሌ ሐሳብ ከማቅረብ በተጨማሪ ውይይቱን በማመቻቸት መርተውታል።

## ቀውስ የፈጠሩ ዓለም አቀፍ ወረርሽኞች ታሪክ

ዓለማችን በርካታ አስከፊ እልቂቶችን ያስተናገደችባቸው ታሪካዊ የቀውስ ክስተቶች አሉ። በበሽታ ወረርሽኝ ምክንያት ብዙ የሰው ሕይወት ከመቅሰፍ እና ሁለንተናዊ

ቀውስ ከመፍጠር አንጻር ዋና ዋና ተብለው በታሪክ ከተመዘገቡት ወረርሽኞች መካከል የመጀመሪያው ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ1500 ዓ.ዓ በፊት ተከስቶ ለሁለት ክፍለ ዘመን የአሁኑን አውሮፓ በከፍተኛ ሁኔታ በማጥቃት እስከ100 (አንድ መቶ) ሚሊዮን ሕዝብ ሕይወት ያሳጣ ወረርሽኝ ሲሆን፤ ቀጣዩ "ጥቁር ሞት" (Black Death) በመባል የሚታወቀው በ14ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ተከስቶ የነበረው እስያን እና አውሮፓን ያጠቃው፤ በተለይ ደግሞ በምዕራብ አውሮፓ ከፍተኛው ጉዳት ያደረሰው ነው። በዚህም እስከ200 (ሁለት መቶ) ሚሊዮን ሕዝብ ሕይወት  ያሳጣ፤ በ18ኛው ክፍለ ዘመን በሰሜን አሜሪካ የሰሜን አሜሪካን ነባር ሕዝቦች 30 (ሠላሳ) በመቶውን ቁጥር ለኅልፈት የዳረገው የፈንጣጣ ወረርሽኝ፣ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በእስያ፣ በተለይ በህንድ ተከስቶ የነበረው የኮሌራ ወረርሽኝ እስከሁለት ሚሊዮን ሰዎች ሕይወት  የነጠቀው ወረርሽኝ እና በ20ኛው ክፍለ ዘመን መባቻ በዓለም ላይ ተከስቶ የነበረውና ኢትዮጵያንም ያጠቃው "ስፓኒሽ ፍሉ" በመባል የሚታወቀው በዓለም ላይ እስከ50 (ኀምሣ) ሚሊዮን ሰዎችን ሕይወት ያሳጣ ወረርሽኝ፤ እንዲሁም "ኤድስ"ን እና "ሳርስ"ን የመሰሉ ወረርሽኞችም የብዙ ሰዎችን ሕይወት ያሳጡ፤ ዓለማችን ካሳለፈቻቸው ቀውስ ፈጣሪ ወረርሽኖች የሚመደቡ እንደሆኑ ዶ/ር ታምራት አስረድተዋል ።

ከላይ የተዘረዘሩትን ወረርሽኞች ቀውስ ሊያስብላቸው የቻለውን ምክንያት ሲያስረዱም፤ ወረርሽኞቹ የሸፈኑት የዓለማችን የቆዳ ስፋት ከፍተኛነት፤ በፍጥነት ተዛማጅነታቸው፤ አጣዳፊነታቸው፣ አዲስነታቸው፣ ተቋማትን የሚያወድሙ እና የማህበራዊ ግንኙነትን የሚያዛቡ መሆናቸው ዓለም አቀፍ ቀውስ አስብሏቸዋል ብለዋል። አቶ አበባው አያሌው በኢትዮጵያ ታሪክ የተመዘገቡትን ወረርሽኞች ሲዘረዝሩ፤ የመጀመሪያው ከክርስቶስ ልደት በፊት በ420 ዓ.ዓ "የአቴንስ ወረርሽኝ" ተብሎ በግሪካውያን ተጽፎ የምናገኘው መነሻው በሰሜን ኢትዮጵያ እንደነበርና በሰሜን አፍሪካ አድርጎ እስከግሪክ እንደደረሰ፤ ነገር ግን ምን ያክል ሕዝብ እንደገደለ የማይታወቀው ሲሆን፤ ከዚያ በኋላ በ739 ዓ.ም አካባቢ (ከክርስቴስ ልደት በኋላ) የተከሰተው ወረርሽኝ፤ በ1258 ዓ.ም ምሥራቅ ኢትዮጵያን ያጠቃው ወረርሽኝ፤ ከ1350-1360 ዓ.ም የተለያዩ የኢትዮጵያ ቦታዎች ያጠቃ ወረርሽኝ ነበር። ይህም ወቅት የአውሮፓው የ"ጥቁር ሞት" ወረርሽኝ ዘመን ነበር። በ15ኛው ክ/ዘ ደብረ ብረሃንን ያጠቃው ወረርሽኝ፤ በ17ኛው ክ/ዘ በጎንደር ተከስቶ የነበረው ወረርሽኝ ሁሉንም ያጠቃ ስለነበር "ምንን ትታ" የሚል ስያሜ ተሰጥቶት ነበር። በ1849 በጎንደር ተከስቶ የተስፋፋ ወረርሽኝ እንደነበርና በ20ኛው ክ/ዘ የ"ኅዳር በሽታ" እና "ኤድስ"ም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ሕይወት  አሳጥቷል። ወባም እንዲሁ

ከኢትዮጵያውያን ጋር ለረጅም ዘመን አብሮ የቆየ ወረርሽን እንደሆነ አስረድተዋል ።
በነዚህ ሁሉ ወረርሽኞች መካከል ማህበረሰቡ የተለያየ የሥነልቦና ጫና ሲያጋጥመውና ማህበራዊ መስተጋብሮች ሲቋረጡ እንደነበር፤ በሕዝብ ላይ ጭንቀት፣ ፍርሃት ይፈጥር እንደነበር፤ "እግዚአብሔር ተጣላን" የሚል እሳቤ ውስጥም ያስገባ እንደነበር አብራርተዋል። በተጨማሪም፣ በየጊዜው ወረርሽኞችን ውህዳን የማህበረሰብ ክፍሎች እንዳመጧቸው በማሰብ ይገለሉ እንደነበር ታሪክ አጣቅሰው አስረድተዋል ።

## የወረርሽኞች አካላዊና ሥነልቦናዊ ጉዳቶች

የሰው ልጅ ሁለት ዓይነት የበሽታ መካላከያ መንገዶች አሉት። አንደኛው አካላዊ የሰውነታቸው በሽታን የመካላከል ዘዴ፤ ማለትም በሽታ አምጪ ተኀዋሲያን ወደሰዎች ሰውነት ከገቡ በኋላ እነርሱን ጉዳት ከማድረሳቸው በፊት ለመከላከል ሰውነታችን የሚያደርገው ነገር ሲሆን፤ ሌላኛው ደግሞ ባሕሪይያዊ የሰው ልጆች የበሽታ መከላከያ ዘዴ ነው። ይህ ደግሞ በሽታ የታየባቸውን ሰዎች መለየት፤ መራቅ፤ ወይም ማግለል እና ነውር የሆኑ ነገሮችን መፍጠር ነው። ነውር ደግሞ በሽታ የሚያመጡ ነገሮችን፤ ምግቦችን እና አኗኗሮችን የሚከለክል የባህል ክፍል እንደሆነና አሁን ከተከሰተው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ አኳያ ሰዎችን ማግለሉ ከፍተኛ ጉዳት እንዳያስከትል ማስተማር እንደሚገባ፤ ነገር ግን የበሽታውን ሥርጭት ለመከላከል ሲባል አዳዲስ ነውሮችን ማለትም ወረርሽኙን ሚያዛምቱ ተግባራትን የሚከለክል የአኗኗር ሥርዓት መፍጠርም እንደሚገባ አስረድተዋል።

የኮቪድ-19ን መሰል ወረርሽኞች በሚከሰቱበት ወቅት ሰዎች በከፍተኛ ድንጋጤ እና ፍርሃት ውስጥ ስለሚገቡ በተለያየ መንገድ ምላሽ እንደሚሰጡ ሐሳባቸውን ያጋሩት ዶ/ር ባርኮት አስረድተዋል። በዚህም፣ ሰዎች በበሽታዎች ሳቢያ የሚደርስባቸውን ሞት ከመፍራት የተነሳ በሦስት መንገድ ለወረርሽኞች ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ ብለዋል። አንድም የተጋነነ ወይም ከልክ ያለፈ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ። ሁለትም አግባብነት ያለው ምላሽ ሊሰጡ እንደሚችሉና በሦስተኛ ደረጃ ደግሞ የተገታ ወይም ቸልተኛ ምላሽ ሊሰጡ ይችላሉ። ይህም ከመረጃ አለመኖር ወይንም ከከፍተኛ ፍርሃት ሊመነጭ እንደሚችል አስረድተዋል።

## በጥቅም ላይ የዋሉ የወረርሽኙ መከላከያ መንገዶች

በዓለም አቀፍ ደረጃ በተከሰቱ ወረርሽኞች ምክንያት በአሁን ወቅት የማህበረሰብ ጤና አጠባበቅ (Public Health) ዘዴ ሆነው ግልጋሎት ላይ እየዋሉ ያሉ ዘዴዎች በታሪክ ተመዝግበው እንደሚገኙና አብዛኛው ወረርሽኞች በሰዎች ንክኪ የሚተላለፉ

መሆናቸውን በመረዳት ታማሚዎችን ለይቶ የማቆየት (Quarantine) ዘዴን በጣልያን ሀገር ተከስቶ ለነበር ወረርሽኝ መከላከያ ተደርጎ የተወሰደው ልምድ አሁን በዓለም አቀፍ ደረጃ ቀዳሚው ወረርሽኝ መከላከያ መንገድ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል። በኢትዮጵያም ወረርሽኞችን ለመከላከል የተለያዩ ዘዴዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ እንደነበር፤ ከነዚህም መካከል እምነትን ማጠናከር፤ ወረርሽኞች ከፈጣሪ ቁጣ ጋር ስለሚያያይዙ ማህበራዊ መስተጋብሮችን እና ግንኙነቶችን መቀነስ፤ ማቋረጥ፤ ይህም ገበያን፣ የመነኮሳትን እንቅስቃሴ፣ እንዲሁም የሌሎችን ግንኙነቶች ማቋረጥን የሚያካትት እንደነበር ይነገራል። ሌላው ዘዴ ደግሞ ወታደሮችን መበትን እና የ"ነጠላ ተሰሪ ሥርዓት"ን ማበጀት፤ በዚህም አንዳንድ ወታደሮች በየገበሬው ቤት ተመድበው ሌላ እንቅስቃሴ ሳያደርጉ በዚያ የሚኖሩበት ሥርዓት ሲሆን፤ ሌሎች አካባቢን ጥሎ መሄድን የመሰሉና እንደኅዳር በሽታ ባለው ወቅት ደግሞ የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ እንደመከላከያ ተደርገው በኢትዮጵያ ሲተገበሩ እንደነበር ሐሳብ ተሰጥቶበታል።

በወረርሽኝ ምክንያትም ይሁን በሌሎች ምክንያቶች የሚፈጠሩ ቀውሶች የሰው ልጆችን ጫና ውስጥ በመከተታቸው እና ብዙ የሚጓደሉ ፍላጎቶች የሚፈጠሩበት ሁኔታ ሰፊ እንደመሆኑ ሰዎች በጫና ውስጥ በሚሆኑበት ሰዓት ለችግራቸው መፍትሔ በመፈለግ ተፈጥሯዊ ሂደቶች የፈጠራ ሁኔታዎች የሚጨምሩበት እድል እንደሚኖር ዶ/ር ባርኮት አስረድተዋል። አክለውም፣ በዚህ መሰል የቀውስ ወቅቶች ለትልልቅ እና ከፍተኛ አቅም ለሚፈልጉ ችግሮች መፍትሔ ከመፈለግ ይልቅ ትንንሽ በግል ሕይወታችን ላይ የገጠሙንን ችግሮች ለመፍታት በሚያግዙ ፈጠራዎች ላይ ማተኮር እንደሚገባም አሳስበዋል። ዶ/ር ቢንያም በበኩላቸው፣ በዚህ መሰል የቀውስ ወቅት ሁለት ዓይነት ፈጠራዎች ሊኖሩ እንደሚችሉ አንስተዋል። እነዚህም አንደኛው ህመሙን ለማቋቋም የሚደረጉ ፈጠራዎች እና የህመሙን ተጽዕኖ ለመቋቋም የሚደረጉ ፈጠራዎች ናቸው። ኮቪድ 19ን መሰል ወረርሽኞች ክፉኛ የሚያጠቋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች እንደሚኖሩ፤ በእድሚያቸው የገፉ የማህበረሰባችን አባላት ወይንም አረጋውያንን ክፉኛ እንደሚያጠቃ፤ ይህንንም ለመከላከል የሚያግዝ የማህበራዊ ከለላ (community shield) በማዘጋጀት አረጋውያን በያሉበት የሚያስፈልጋቸውን የምግብም ይሁን የህክምና መድሐኒት እና ሌሎች ግብዓቶች የሚሞሉበትን መንገድ መፈለግ እንደሚገባና በቤት ውስጥም የበሽታውን መከላከያ መንገዶች ተግባራዊ ማድረግ እንደሚያስፈል አንስተዋል። በበጎ ፈቃደኝነት የተደራጁ አካላት ይህንን መከወን የሚችሉበት ሁኔታ ሊመቻች እንደሚገባም አንስተዋል። በሌላ በኩል ወረርሽኙን በመከላከል ከፍተኛ ተጠቂ የሚሆኑትን የሕክምና ባለሙያዎች በተለያየ መንገድ ከገንዘብ ድጋፍ ውጭም ቢሆን ድጋፍ ሊደረግላቸው እንደሚገባ ሐሳባቸውን

አካፍለዋል።

በውይይቱ መገባደጃ ላይ ለታሪክ መምህሩ አበባው አያሌው “ከትናንት ምን እንማራለን?” ለዶክተር ቢንያም “መዘናጋት እና ቸልተኝነት እንዴት መጣ? እንዴትስ እንከላከለው?” የሚልና ለዶ/ር ባርኮት “የተከሰተው ወረርሽኝ በአዕምሮአችን ላይ ክፉ ጠባሳ ጥሎ እንዳያልፍ ምን ይደረግ?” የሚሉ ጥያቄዎች ቀርበውላቸው ምላሽ ሰጥተዋል። በምላሻቸውም፣ ካለፈው የወርርሽኝ ታሪካችን ተሞክሮ በመውሰድ የጤና ሥርዓታችን እና ተቋሞቻችን ለኮቪድ መሰል ድንገተኛ ወረርሽኞች የመከላከል እና የመቆጣጠር አቅም መገንባት ይገባቸዋል። በስፋት አብረውን የሚኖሩትን ወባን መሰል ወረርሽኞችንም የመከላከልና የመቆጣጠር ሥራ መሥራት ይገባል። ሰውን ከሚያጠቁ ወረርሽኞች ባለፈም እንስሳትን እና እጽዋትን የሚያጠቁ ወረርሽኞችንም በትኩረት መከላከል እና መቆጣጠር ያስፈልጋል። እንዲሁም፣ ለብዙ ወረርሽኞች መንስኤ በመሆን የሚያገለግለውን የግልና የአካባቢን ንጽህና አጠባበቅ ማሳደግ እንዳለብን፤ መማር እንደሚገባን አቶ አበባው አይሌው አስረድተዋል።

የመዘናጋትን ምክንያቶች በተመለከተ ለተነሳው ጥያቄም፤  ወረርሽኙ በሀገራችን ጉዳት ለማድረስ የወሰደበት የጊዜው መርዘም፣ የሚጠበቁት የባሕሪይ ለውጦች ከፍተኛ መሆን፤ የሰዎችን ቁርኝት በከፍተኛ ሁኔታ መስበር ከባድ መሆኑ፣ የእውቀት ወይም የመረጃ ክፍተት በተለይ በገጠር አካባቢ በሚኖረው ማህበረሰብ  እና ህመሙ ያሚያመጣውን ጉዳት በእራሳችን ላይ አለማየታችን እንደሆኑና መፍትሔውም በበሽታው ምክንያት እየደረሰ ያለውን ጉዳት ለሕዝቡ በማሳየት እና በማስተማር ለውጥ ለማምጣት መሥራት እንደሚገባ ዶ/ር ቢንያም አስረድተዋል። በወረርሽኞች አስፈሪ ጊዚያት እና ውጤቶቻቸው መካከል ያለው የጊዜ ልዩነት ለመዘናጋት መንስኤ እንደሆነ፤ ለዚህም ጭንቀትን መመጠን እና መቋቋም ስንችል ተገቢ ርምጃ መውሰድ፤ መነሳሳት ሲጨምር መዘናጋትን የሚያጠፉ ይሆናል ብለዋል። ጭንቀት ሲመጣ አለመደንገጥ እና አለመፍራት፤ አካላዊ ጤንነት በሚሰጡ ነገሮች ላይ መሥራት፤ ጤናማ አመጋገብ፣ የአካል ብቃት እና በቂ እንቅልፍ ማግኘት፤ አካላዊ ርቀት እንደተጠበቀ ሆኖ ማህበራዊ ግንኙነታችንን ማጠናከር፤ ከዚህ በፊት የጠቀሙንን ልምዶች ማሳደግ፤ ጠቃሚ ያልሆኑትን ማስወገድ ይገባል። በተጨማሪም፣ የታመኑ የመረጃ ምንጮችን መጠቀም ክፉ የአዕምሮ ጉዳት እንዳያደርሱብን የሚያስችሉ መንገዶች እንደሆኑ አስረድተዋል፡ ፡ በአጠቃላይ የግላችንን እና የቤተሰባችንን ጤና ለመጠበቅ የምናደርገው በጎ ተግባር ለአዕምሮ ጤናችንም ጥሩ ስለሚሆን እራሳችንን እና ቤተሰባችንን በሚጠብቁ ነገሮች ላይ በትኩረት መሥራት እንደሚገባ ዶ/ር ባርኮት አስረድተዋል።

# 2.7 አዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ ከሸገር ወደ ሀገር

ነሐሴ 21 ቀን 2012 ዓ.ም




ይህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም "ከሸገር ወደሀገር" በሚል ርዕስ በክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ "የኢትዮጵያ ከፍታ" በሚል የተዋወቁት ሦስቱ አዲስ አበባን የማስዋብ ፕሮጀክቶች፤ ማለትም፣ የአንድነት ፓርክ፣ የእንጦጦ ፓርክ እና የሸገር ፓርክ መልዕክታቸው ምንድን እንደሆነ፤ ለሀገር ያላቸው ፋይዳስ ምንድነው? ሦስቱም ፕሮጀክቶች ላይ ሲጀመሩ እና ሲጠናቀቁ ምን ዓይነት ገጽታ እንዳላቸው፤ በሥራው ሂደት ምን ምን ችግሮች አጋጠሙ? ምንስ ተማርን? በሚሉ ሐሳቦች ላይ ውይይት ማድረግ ነው። በውይይቱም ስለፕሮጀክቶቹ ሐሳባቸውን በማካፈል የተሳተፉት በሦስቱም ፕሮጀክቶች ላይ በተለያየ መንገድ ከፍተኛ ተሳትፎ ሲያደርጉ የነበሩት ዶ/ር አብርሃም በላይ (የቀድሞ) የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር እና የሦስቱም ፕሮጀክቶች አስተባባሪ፤ ኢንጂነር ኃብታሙ ተገኝ የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣን ዋና ሥራ አሥፈጻሚ (የቀድሞ)፣

ወ/ሮ መስከረም አሰግድ የዞማ ቤተ - መዘክር መሥራችና በፓርኮቹ ግንባታ የሥነጥበብ ባለሙያ ሆነው የሠሩ እና ዶ/ር እዮብ ተካልኝ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ

ሲሆኑ ውይይቱን የመሩት የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ፕሬስ ሰክሪታሪያት ቢልለኔ ስዩም ናቸው።

## የፕሮጀክቶቹ ተምሳሌታዊነት እና አስተማሪ የነበሩ ሂደቶች

በውይይቱ የመጀመሪያው ሐሳብ አቅራቢ ዶ/ር አብርሃም በላይ፤ የሦስቱም ፕሮጀክቶች አጀማመር እና አሠራር ምን ይመስል እንደነበር፤ እንዲሁም ተምሳሌትነታቸውን ባስረዱበት ንግግራቸው ሦስቱም ፕሮጀክቶች (የአንድነት ፓርክ፣ የእንጦጦ ፓርክ እና የሸገር ፓርክ) የተሠሩባቸው ቦታዎች፤ አንድነት ፓርክ በቤተ መንግሥት ውስጥ ሆኖ ብዙ ሕዝብ የማያውቀው ቦታ ቢሆንም ቆሻሻ ይጣልበት የነበር እና ለማየት እንኳን የማይመች የነበረ፤ ሸገር ፓርክም እንደዚያው በከተማዋ እንብርት ያለ ግን ቆሻሻ የበዛበት፤ እንጦጦም አስፈሪ ገጽታ የነበረው እና አሁን ወዳለበት ሁኔታ ለማምጣትም መሬት ከማስተካከል ጀምሮ ከፍተኛ ሥራ የተሠራበት እንደነበረ አንስተዋል። በአሁኑ ሰዓት ሦስቱም  አስገራሚ ለውጥ ማሳየት የተቻለባቸው ፕሮጀክቶች ናቸው ብለዋል። የሦስቱም ፕሮጀክቶች  ሐሳብ  ባለቤት ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ እንደሆኑና ጠቅላይ ሚኒስትሩ በባሕሪያቸው የሥራ ከባቢን ምቹና ሳቢ ማድረግ ለአገልግሎት ሰጪውም ለአገልግሎት ተቀባዩም ምቹት የሚሰጥና ውጤታማነትን የሚያሳድግ ነው ብለው ቀድመው የተረዱ በመሆናቸው ከዚህ ቀደም የሠሩባቸው እና በኃላፊነት  የመሯቸው ተቋማት ማሳያ እንደሆኑ አስረድተዋል። በዚህም እሳቤያቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በቅድሚያ ጽሕፈት ቤታቸውን የማስዋብ ሥራ እንደሠሩ፤ ከዚያም በቤተ - መንግሥቱ ውስጥ የአንድነትን ፓርክ፣ ከቤተ መንግሥት በመውጣትም የእንጦጦን እና የሸገርን ፓርክ በማሠራት የለውጡ ሀሳብ የሚመራበትንም መንገድ ያሳዩባቸው ፕሮጀክቶች እንደሆኑ ገልጸዋል።

የሦስቱን ፕሮጀክቶች ተምሳሌትነት ሲያስረዱም፤ የሦስቱ ፕሮጀክቶች  ሐሳብ ዓይናችንን ከፍተን ምን እንዳለን እንድናውቅ እና "ሀገራችን ምን አላት?" የሚለውን እንድናስብ ያደረጉን እንደሆኑ፤ ሁሌም ወደውጭ ከማየት ወደውስጥ በማየት ምን እንዳለን፤ ምን መሥራት እንደምንችል ያስተማሩን እንደሆኑ ጠቁመው፤ ኃብት በማሰባሰቡ ሂደት የግሉን ዘርፍ ያሰተባበሩበት ሥርዓት መንገድ ከፋች እንደሆነ አሳይተዋል። በፕሮጀክትም ላይ ይሁን በሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ከትንሽ በመነሳት ሀገራችንን እንዴት መለወጥ እንደምንችል ያሳዩን፤ ደካማ ለሆነው ሀገራዊ የፕሮጀክት አፈጻጸም ልምዳችን  ፕሮጀክቶችን በታቀደላቸው ጊዜና ጥራት እንዴት ማሳካት እንደምንችል ያሳየን፤ እንዲሁም፣ በመንግሥት እና በግሉ ዘርፍ ሊኖር የሚገባው ጥምረት ምን መምሰል እንዳለበት ያሳዩን ፕሮጀክቶች እንደሆኑ አስረድተዋል።

የእነዚህ ፕሮጀክቶች ስኬት በቀጣይ የለውጥ ጉዟችን፤ በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎቻችን በዐሥሩ ዓመት እቅዳችን ለማሳካት የያዝናቸውን እቅዶች በመደመር እሳቤ የብዙዎችን አሻራ በማሳረፍ ስኬት ማምጣት እንደምንችል ያረገገጥናባቸው ናቸው ሲሉም አስረድተዋል።

ኢንጂነር ኃብታሙ ተገኝ ስለፕሮጀክቶቹ አሠራር እና በሂደቱ ስለነበሩ ፈተናዎች እንዲሁም ስለተገኙ ልምዶች ሲያስረዱ፤ በመጀመሪያ የፕሮጀክቶቹ ሐሳብ የኢትዮጵያን ከፍታ እና ልክ ታሳቢ አድርገው በሰፊው እና በጥራት ለመሥራት የታሰቡ እንደሆኑና ሐሳብ አፍላቂው ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ኢትዮጵያ ለታላቅነቷ እና ለክብሯ የሚመጥን ታለቅ ሥራ ለመሥራት ማሰባቸውን ያሳዩባቸው ናቸው። በሂደታቸውም ብዙ ሰዎች ኃብት በማዋጣት፤ ዲዛይን በመሥራት እና በሌሎች መንገዶች በበጎ ፈቃድ እንዲሳተፉባቸው የተደረጉባቸው እንደነበሩ፤ በፕሮጀክት አፈጻጸም ሥርዓታችንም ላይ ትልቅ ጥያቄ በማንሳት "እንዲህም መሥራት እንችላል ወይ?" ብለን እንድናስብ እና እንድናምን ያደረጉ ነበሩ ሲሉ ገልጸዋል። በጅማሬያቸው ላይ ብዙዎች "በዚህ ጊዜ መፈጸም እንችላለንን?" የሚል ጥርጣሬ እንደነበራቸው፤ ነገር ግን የጠቅላይ ሚኒስትሩ አመራር ፣ ክትትል፣ ትኩረት እና በሂደቱም ለነበሩ ስኬቶች ይሰጡት የነበረው እውቅና በፕሮጀክቱ ላይ የተሳተፉትን ሁሉንም አካላት ያነሳሳ እንደነበር፤ ይህም ለስኬቱ ትልቅ ሚና እንደነበረው አስረድተዋል።

በፕሮጀክቶቹ ሥራ ላይ ያጋጠሙ ተግራሮቶች በምን መልኩ መማሪያ እንደነበሩ ሲያሳዩም፤ ፕሮጀክቶቹን በሰባት ወር፣ ለዚያውም በክረምት መሥራት ከፍተኛ ተግዳሮት ነበር። የፕሮጀክት አፈጻጸም ዋናው ነገር የሆኑትን ኃብት፣ ጊዜ እና ጥራት በአግባቡ መጠቀም የተቻለበትም ነበር። ኮቪድ-19ም ሌላው ተግዳሮት እንደነበር አስታውሰው በፕሮጀክት አመራር ልምዳችን ላይ ትልቅ ተሞክሮ፤ በተለይ ለከፍተኛው አመራር ቁርጠኝነት ካለ ማሳካት የማይቻል ነገር እንደሌለ እና አዲስ የፕሮጀክት አፈጻጸም ባህል መገንባት ያሚያስችሉ ልምዶች የተገኙባቸው፤ ቢሮክራሲውንም የፈተኑ እና መስተካከል ያለባቸውን ሥርዓቶች ያሳዩ እንደነበሩ አንስተዋል። ይህን መሰል እቅድ በጊዜው ፈጽሞ የማሳየት ልምድ በመንግሥት እና በሕዝብ መካከል መተማመንን የመፍጠር አቅም ያለው እንደሆነም አስረድተዋል። በቀጣይ እነዚህን መሰል ፕሮጀክቶች በክልሎች ሊሠሩ መሆናቸው ክልሎችን እና የክልል መሪዎችን በዚህ ልክ እንዲማሩባቸው የሚያደርግ እንደሆነም ገልጸዋል።

በሦስቱ ፓርኮች ውስጥ ከፍተኛ የሥነ ጥበብ ሥራዎች ተግባራዊ ተደርገዋል። በዚህም ሥራ ላይ የተሳተፉት የዞማ ሙዚየም ባለቤት ወ/ሮ መስከረም አሰግድ የፓርኮችን የሥነ ጥበብ ሥራ ዲዛይን ከማድረግ ጀምሮ በርካታ ተግባራት አከናውነዋል። በሌላ በኩል፣ በእንጦጦ ፓርክ በግላቸው ያለሙት ሬስቶራንት አላቸው። እርሳቸውም በፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ላይ ያስተዋሉትን የእደ ጥበብ ሚና እና ለጥበብ የተሰጠውን ድርሻ ሲያስረዱ፤ በአንድነት ፓርክ ግንባታ ሂደት ላይ አካባቢው ቀድሞ የቆሻሻ፣ የአፈር እና የድንጋይ ማከማቻ ይመስል እንደነበር አውስተዋል። በቅድሚያም ይህን ቦታ እንዴት መቀየር እንችላለን? በሚል ሰፊ ጥናት ማድረጋቸውን ጠቁመዋል። ምክንያቱም ቦታው ብዙ ታሪካዊ ግንባታዎች ያሉበት እንደመሆኑ ከፍተኛ ጥንቃቄ ይፈልግ ስለነበር ነው። ግንባታዎች ለምን እንደዚያ እንደተሠሩ በማስተዋል እና አካባቢው ውህማ ከመሆኑ ጋር ሰፋ ያለ ጥናት በማድረግ ለሁሉም፣ ለወጣቱም፣ ለአቅመ ደካሞችም ምቹ የሆነ ስፍራ ለማዘጋጀት እዚያው በነበረ ድንጋይ እና አፈር (ሲሚንቶ በብዛት ሳንጠቀም) እንዲሁም የሀገራችንን የደረቅ ግንባታ ጥበብ ገንቢዎች ከራያ በማስመጣት መሥራት እንደተቻለ ገልጸው፤ በሂደቱም ጠቅላይ ሚኒስትሩ እያንዳንዷን ጥቃቅን ነገር ሁሉ በትኩረት ይከታተሉ እንደነበር አስረድተዋል።

በእንጦጦ ፓርክም፣ መሬቱ የነበረውን መልክዐ ምድር ሳይቀየር፤ ዛፍም ሳይቆረጥ በምሰሶ የቆመ ሬስቶራንት መሥራት እንደተቻለ አስረድተዋል። በሁለቱም ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ ሀገር በቀል የግንባታ እና የዲዛይን ጥበብ ጥቅም ላይ በማዋል ውብ ሆነው ለህገራችን እና ለሕዝቧ በሚመጥን መልኩ የተሠሩ ፓርኮች እንደሆኑ ተናግረዋል። ከፕሮጀክቶቹ የፋይናንስ አጠቃቀም ጋር በተያያዘ፤ ፕሮጀክቶቹን የገጽታ ግንባታ ሥራ ብቻ የማድረግ እሳቤ ትክክል እንዳልነበረና የፕሮጀክቶቹ እውነተኛ ሀገራዊ ፋይዳ ምን እንደሆነ ያስረዱት ደግሞ የፋይናንስ ሚኒስትር ዴኤታው ዶ/ር እዮብ ተካልኝ ናቸው። በንግግራቸውም እነዚህ ሦስት ፕሮጀክቶች የማስዋብ ሥራ ብቻ እንዳልሆኑ እንደሀገር የተውናቸውን ኃብቶቻችንን በምን መልክ መጠቀም እንዳለብን የሚያስተምሩ ፕሮጀክቶች እንደሆኑና፤ ፕሮጀክቶቹ እንደሀገር በቀጣይ በሀገር በቀል የኢኮኖሚውም ከፍተኛ ትኩረት የተሰጠው የቱሪዝሙ ዘርፍ ላይ ምን መሥራት እንደሚገባን፤ እንዴት መሥራት እንዳለብን ማሳያ ተደርገው መወሰድ ያለባቸው ፕሮጀክቶች እንደሆኑ አስረድተዋል። ፕሮጀክቶቹ የሚያመጡትን ጥቅም ሲያስረዱም አንደኛ በቀጥታ የሥራ እድል ይፈጥራሉ። በተለይ ደግሞ እንደሀገር 42 (ዐርባ ሁለት) ቢሊዮን ብር እንድናባክን ያደረገንን የፕሮጀክት አፈጻጸም ችግራችን ላይ ከፍተኛ አስተማሪ እና ማሳያ ሆነው እንደሚያገለግሉ አንስተዋል። እነዚህን ፕሮጀክቶች ከማስጀመራችን በፊት በፕሮጀክት አፈጻጸም ምክንያት ተጓትተው የቆዩትን አጠናቅቀን እና ቃል ተገብተው ያልተሠሩ ፕሮጀክቶችን አስጀምረን በአዲስ

የፕሮጀክት አፈጻጸም “ስታንዳርድ” ለመፍጠርም የምንጠቀምባቸው እንደሆኑ ገልጸዋል። በአጠቃለይ በፕሮጀክቶች ላይ የእይታ ለውጥ በማድረግ በጊዜ እና በእቅድ መጨረስን የምናስተምርባቸው ናቸው ሲሉ አስረድተዋል።

በሌላ በኩልም፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች የኅብረተሰብን ተጠቃሚነት እና አሳታፊነት የምናረጋግጥባቸው እንደሆኑ በመግለጽ እንደምሳሌ ኮይሻ እና አካባቢውን በከፍተኛ መልኩ ተጠቃሚ የሚያደርግ ፕሮጀክት እየተሠራ እንደሆነ አስረድተው፤ የፕሮጀክቶቹ ጥቅም ግን በራሳቸው ብቻ የሚታይ እንዳልሆነ የኢትዮጵያ ልክ ምን እና በምን መልክ መሠራት እንዳለበት የሚያሳዩ እንደሆነ ተናገረዋል። በሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ትኩረት የተሰጠው የቱሪዝሙ ዘርፍም መዳረሻዎችን ከባለሃብቱ ጋር በትስስር እንዴት ማልማት እንዳለብን እና የቱሪስቶችን የቆይታ ጊዜ ማርዘም እንደሚገባ፤ በዚህም ገቢ ማሳደግ እንዳለብን ታሳቢ እንዳደረገ አስረድተዋል።

ዶ/ር አብርሃም በላይ በበኩላቸው፣ በፕሮጀክቶች ምን ዓይነት የኃብት ማሰባሰቢያ መንገድ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ሲያስረዱ፤ ፕሮጀክቱ ከመጀመሩ በፊት በገበታ ለሀገር የኃብት ማሰባሰቢያ መርሀ ግብር ተከናውኗል። ፕሮጀክቶቹ ከተጀመሩ በኋላ ደግሞ ባለሀብቱ በራሱ እንዲገነባ እና ኪራይ ታስቦለት በዘላቂነት የተገነቡት እና የተሠሩት መሠረተ ልማቶች የሕዝብ ኃብት የሚሆኑበትን አዲስ ሥርዓት በመፍጠር የግሉን ባለሀብት ማሳተፍ እንደተቻለ ገልጸዋል።

## ከተሳታፊዎች የተነሱ አስተያየት እና ጥያቄዎች

በቅድሚያ አስተያየታቸውን የሰጡት በውይይቱ ላይ በክብር የተገኙት የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለ ማርያም ደሳለኝ ሲሆኑ፤ የሦስቱ ፕሮጀክቶች ጉዳይ በቀላሉ የገጽታ ግንባታ ሥራ እንዳልሆነና ከፍተኛ ሀገራዊ አስተዋጽዖ ያለው፤ በተለይ በቱሪዝሙ ዘርፍ ከፍተኛ ችግር የነበረውን ለቱሪስት የቆይታ ጊዜ የሚጨምሩ የቱሪዝም ውጤቶች ላይ ለውጥ መፍጠር የሚችሉ እና የቱሪስቱን የቆይታ ጊዜ የሚጨምሩ እንደሆኑ ገልጸዋል። ከፍተኛ ቁጥር ያለው ኢትዮጵያዊ ተላላፊ ባልሆኑ በሽታዎች እየተጠቃ በመሆኑ፤ ምንም እንኳን መንስኤው እንደአደጉት ሀገራት የአኗኗር ዘይቤ ለውጥ ብቻ  ባይሆንም ዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ያለው ኢትዮጵያዊም በዚህ እየተጠቃ በመሆኑ ሰዎች ተንቀሳቅሰው ጤናቸውን የሚጠብቁበትን እድል የሚሰጥ እንደሆነ አንስተዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የፕሮጀክት አፈጻጸም ችግር መኖሩን አንስተው ዋነኛው የፕሮጀክቶቹ ተምሳሌትነትም ለዚህ ሀገራዊ ችግር መፍትሔ የሚሆን የአሠራር ሥርዓት እና የአመራር ቁርጠኝነት ያሳየ እንደሆነ ጠቅሰዋል።

ይህንንም ከጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ባለፈ በሁሉም ደረጃ ላይ የሚገኙ የሀገሪቱ አመራሮች ቁርጠኛ እንዲሆኑ በማድረግ ከፍተኛ ለውጥ ለማምጣት የሚያስችል ነው ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

ከሌሎች ተሳታፊዎችም ሰፊ ሐሳቦች የተነሱ ሲሆን አብዛኛው ሐሳቦች ፕሮጀክቶቹ ለከተማዋ ብሎም በሀገር አቀፍ ደረጃ ለቱሪዝም ዘርፍ ከፍተኛ ፋይዳ እንዳላቸው የሚያረጋግጡ ናቸው። እንዲሁም፣ የእነዚህ ፕሮጀክቶች አፈጻጸም በቀጣይ ሀገራችን ለምትሠራቸው ሜጋ ፕሮጀክቶች አርአያና ማስተማሪያ የሚሆን መሆኑን የሚያነሱ ናቸው። በተጨማሪም፣ የኩሪፍቱ ሪዞርት ባለቤት አቶ ታዲዮስ ስለፕሮጀክቶቹ እና ስለአጠቃላይ የቱሪዝሙ ዘርፍ በሰጡት አስተያየት፣ ከዚህ ቀደም የውጭ ቱሪስቶችን ለመሳብ መንግሥትም ባለሃብቱ በግልም ከፍተኛ ገንዘብ ኢንቨስት አድርገው የማስተዋወቅ ሥራ የተሠራ ቢሆንም እነዚህም መሰል የቱሪዝም መዳረሻዎች በስፋት ባለመኖራቸው ውጤት ሳይመጣ እንደቆየ አንስተዋል። አሁን የተሠሩት ፕሮጀክቶች በዘርፉ ብዙ ለውጥ የሚያመጡ እንደሆኑና መንግሥት ከግል ባለሃብቱ ጋር አብሮ ለመሥራት የሄደበት መንገድ የሚበረታታ እንደሆነ አረጋግጠዋል። እርሳቸው እና ሌሎች በዘርፉ ላይ ያሉ ባለሃብቶችም በዚህ መንገድ ያለምንም ማቅማማት ተሳትፎ እያደረጉ እንደሚገኙ ምሥጋና አዘል አስተያየት ሰጥተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም፣ የቱሪዝሙ ዘርፍ ገቢ እያስገኘ ያለ ቢሆንም የፖሊሲ ችግር አለበት፤ ይህን ለመፍታት መታሰብ አለበት። ሴክተሩን የሚመሩ ሰዎች ባለሙያዎች ሊሆኑ ይገባል። እንዲሁም ከአዲስ አበባ ውጭ የታሰቡትና በገበታ ለሀገር የታቀፉት ፕሮጀክቶች ቁጥር በጣም አንሷል። የሚሉ አስተያየቶች ከተሳታፊዎች ተሰንዝረዋል። የቱሪዝም ኢትዮጵያ ዋና ዳይሬክተር አቶ ስለሺ ግርማ፣በእነዚህ ሦስት የቱሪዝም መዳረሻ ፕሮጀክቶች ግንባታ ላይ የታየው የፕሮጀክት አፈጻጸም ሥርዓት እና ሰርቶ የማሳየት ብቃት ለመንግሥት በሕዝብ ዘንድ አመኔታን ያስገኘ እንደነበር አንስተዋል። ከዚህ ቀደም ኢኮኖሚያችንን ከግብርና ወደአምራች ዘርፍ ለማሸጋገር ጥረት በሚደረግበት ወቅት ቱሪዝሙንም ጨምሮ ለአገልግሎቱ ዘርፍ እዚህ ግባ የማይበል ትኩረት ተሰጥቶት እንደነበር፤ ነገር ግን በአሁኑ ሰዓት የአገልግሎቱ ዘርፍ ጥሩ ትኩረት እንዳገኘ፤ እነዚህን መሰል ፕሮጀክቶች ማሳያ እንደሆኑ ገልጸዋል። ይህም ሀገራችን ኢትዮጵያ ካላት የቱሪዝም ኃብታ አንጻር ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ ሊያደርጋት የሚችል እንደሆነ፤ ጥሩ የውጭ ምንዛሬ የሚያስገኝ ዘርፍ እንደሆነ አስረድተዋል። ሌሎች ተሳታፊዎችም፣ የተገነቡትን ሦስት ፓርኮች እንዴት እናስተዳድራቸው? በባለሙያ የሚተዳደርበትን መንገድ መፍጠር ላይ ምን ታስቧል? በፕሮጀክቶቹ የአፈጻጸም

ሥርዓት ላይ ያጋጠሙ ከፍተኛ ችግሮች ምን ነበሩ? ምንስ ልንማርባቸው እና በቀጣይ በሀገር አቀፍ ደረጃ የፕሮጀክት አፈጻጸም ሥርዓታችን ላይ ምን ልናርም ይገባል? የሚሉ ጥያቄዎችም ቀርበዋል።

ለተነሱት ጥያቄዎች በቅድሚያ ምላሽ የሰጡት ዶ/ር አብርሃም በላይ ናቸው። በምላሻቸውም በፕሮጀክቶቹ አፈጻጸም ወቅት ትልቁ ፈታኝ የነበረው ነገር ለፕሮጀክቶቹ የተያዘው ጊዜ አጭር መሆን፣ ሥራዎች መሥራት የነበረባቸው በከፍተኛ የጥራት ደረጃም ስለነበር ሁለቱን አስታርቆ ያለምንም የጥራት ጉድለት በተያዘለት ጊዜ መጨረስ ፈታኝም እጅግም አስተማሪ፣ እንደገናም ውጤታማ የጊዜ አጠቃቀም ሥርዓት የሚጠይቅ ነበር ብለዋል። "ከቋሚው የሥራ ኃላፊነታችሁ ጋር እንዴት አስታረቃችሁት?" በሚል ለተነሳላቸውም፣ ፕሮጀክቶቹ ቀንም ማታም ይሠሩ እንደነበር፤ ከዚያም ባለፈ ከፍተኛ የታቀደ የጊዜ አጠቃቀም ልምድ በማዳበር እንደተወጡት አሳውቀዋል። የፓርኩን አስተዳደር በተመለከተ ለተነሳው ጥያቄም የፓርክ አስተዳደር ሥራው ከፕሮጀክቱ ሥራ ጋር አብሮ በሀገር ወስጥና በውጭ ባለሙያዎች፣ በመንግሥት እና በባለሃብቶች አጋርነት (PPP) አሠራር መሠረት የታሰበበት ዝግጅት እየተደረገበት እንደሆነ፤ የፓርኮቹም መሠረተ ልማት አስተዳደር፣ የጎብኝዎች አስተዳደር፣ የጥበቃ እና የብራንዲንግ ሥራዎች ሁሉ በዘርፉ ከፍተኛ ባለሙያዎች የሚመሩ እና የሚተዳደሩ መሆናቸውን አሳውቀዋል። በሀገር አቀፍ ደረጃ ሊሠሩ የታሰቡት ፕሮጀክቶች ቁጥር አነስተኛ ነው ለሚለው ጥያቄም ዶ/ር አብርሃም በመልሳቸው በሀገራችን የምናውቃቸውን የቱሪዝም መዳረሻዎች እናልማ ቢባል እንኳን ከፍተኛ አቅም የሚጠይቅ እንደሆነ፤ እንዲሁም በአዲስ አበባ የተሠሩት ፕሮጀክቶች እንዳሳዩት ሥራዎችን ከትንሹ በመነሳት በቅደም ተከተል መሥራትን መሠረት ተደርጎ መፈጸም አንዱ እንደሆነና በየአካባቢው ያሉ መልማት የሚገባቸው የቱሪዝም መዳረሻዎች ተለይተው እንደተቀመጡና በሂደት በቅደም ተከተል የሚለሙበት አካሔድ እንደሚኖር አስረድተዋል። ሦስቱ የታቀዱት ፕሮጀክቶች ሦስት ብቻ በሚል መወሰድ እንደሌለባቸው በውስጣቸው ብዙ ለብቻቸው አንድ ፕሮጀክት ሆነው መውጣት የሚችሉ ሥራዎች እንዳሏቸውም ገልጸዋል።

ኢንጂነር ኃብታሙ በሰጡት አስተያየት፣ የተሠሩት ፕሮጀክቶች በፕሮጀክት አፈጻጸም እና በአጠቃላይ ሥራዎች ላይ አዲስ "ስታንዳርድ" የሚስቀምጡ፤ በአስተሳሰብ ደረጃም የወትሮውን የአሠራር ሂደት በተለይ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሚታየውን የሚቀይሩ እንዲሆኑ ታስበው የተሠሩ ነበሩ ማለት ይቻላል ብለዋል። በግንባታ ዘርፍ የተለያዩ ተግዳሮቶችን እያነሱ ፕሮጀክቶች የሚጓተቱበት ልምድ ብዙ ነው። በእነዚህም

ፕሮጀክቶች ግን ተግዳሮት የነበረው በአጭር ጊዜ ውስጥ በተቀመጠው ዓለም አቀፋዊ ጥራት ሠርቶ መጨረስ ነበር። ነገር ግን የጠቅላይ ሚኒስትሩ ለፕሮጀክቶቹ የነበራቸው ቁርጠኝነትና ሁለንተናዊ ድጋፍ፣ እንዲሁም በፕሮጀክቶቹ የተሳተፉት ሁሉም ሠራተኞች ባሳዩት ልዩ የሥራ አፈጻጸም እና ቁርተኝነት ፕሮጀክቶቹ በታቀደላቸው ጊዜና ጥራት ተሳክተዋል። ይህም ሲታቀዱ ጀምሮ በአጭር ጊዜ መሥራትን እንድንማርባቸው የታሰቡ በመሆናቸው ብዙ የተማርንባቸው እና ከዚህ በፊት "ተግዳሮት" እያልን ስናስቀምጣቸው የነበሩ ጉዳዮች "እውን ችግሮች ነበሩ ወይ?" በሚል እንድንጠይቅ ያደረጉ ናቸው ብለዋል። "የቅንጦት ፕሮጀክቶች ናቸው" በሚል ለሚነሳው ሐሳብም፣ እነዚህ ፕሮጀክቶች ሲሠሩ ለብዙ ሠራተኞች ሥራ እድል የፈጠሩ፤ በዘላቂነትም በቱሪዝም ዘርፉ ብዙ የሥራ እድል የሚፈጥሩ፤ እንዲሁም ለሀገራችን ክብር በሚገባት ደረጃ የተሠሩ ገቢ ያሚያመጩ ሆነው እያለ እንዴት የቅንጦት ናቸው ሊባል ይችላል ብለዋል።

ኢንጂነር ኃብታሙ ከእነዚህ ፕሮጀክቶች ውጭ በሚመሩት የመንገዶች ባለሥልጣን 80 (ሰማንያ) የሚሆኑ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍልች የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻዎችን በመንገድ የሚያገናኙ ፕሮጀክቶች እየተሠሩ እንዳሉ ጠቁመው፤ በሂደት በአዲስ አበባ ላይ የተሠሩትን ዓይነት መዳረሻዎች የማልማት ሥራ እንደባህል ተወስዶ በስፋት የሚሠራበት እንደሚሆን አስረድተዋል። አሁን የተሠሩትንም ሆነ ወደፊት የሚሠሩትን ፕሮጀክቶች በዘላቂነት ዓለም አቀፍ ደረጃቸውን አስጠብቆ ማቆየት እና የታለማላቸውን ዓላማ ማሳካት እንዲችሉ መሥራት የሁሉም ኃላፊነት ነው ሲሉ አሳስበዋል። ሌላኛዋ የውይይቱ ሐሳብ አቅራቢ ወ/ሮ መስከረም አሰግድ፣ የትኛውም ሥራ የራሱ ሆነ ተግዳሮቶች እንዳሉትና በነዚህም ፕሮጀክቶች ላይ ጥራትን የጠበቀ ሥራ መሥራት ዋነኛው ሥራቸው እንደነበር፤ ይህን በማድረግ ሂደት ውስጥ ጊዜ ፈተና እንደነበር አውስተዋል። ነገር ግን ዘመን ተሻጋሪ የጥበብ ሥራ ለመሥራት ሲባል ከዲዛይን ጀምሮ ጥራት ታሳቢ ተደርጎ ይሠራ ስለነበር ፕሮጀክቶችን በጥራት ማጠናቀቅ እንደተቻለ አስረድተዋል።

ዶ/ር እዮብ፣ በሀገር አቀፍ ደረጃ ቱሪዝም ያለውን የኢኮኖሚ አስተዋጽኦ አስመልክቶ ለተነሳው ጥይቄ በኢኮኖሚ ሪፎርሙ ኢኮኖሚያችን የውጭ ምንዛሬ እጥረት መለያው እንዳይሆን በሚል ለወትሮው ትኩረት ተነፍጓቸው በነበሩ ዘርፎች ላይ ትኩረት አድርጎ መሥራት እና የኢኮኖሚ ዘርፎችን በማሰባጠር እሳቤያችን መሠረት ቱሪዝሙም ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ያለውን አቅም እና አስተዋጽኦ ባማከለ መልኩ ትኩረት እንደተሰጠው እና ዘርፉ ለኢኮኖሚው የሚስገኘው የውጭ ምንዛሬ ወሳኝ እንደሆነም

አሳውቀዋል። ከፖሊሲ ጋር ለተነሳው ጥያቄም የዘርፉን የማደግ አቅም ባማከለ መልኩ የፖሊሲ ማሻሻያ ሊደረግለት እንደሚያስፈልግ፤ ይህም ተቀባይነት ያለው ሐሳብ እንደሆነ ተናግረዋል።

በተጨማሪም፣ ፕሮጀክቶቹ አስፈላጊ እንደሆኑ የሚያሳዩ ሦስት ነጥቦችን አስቀምጠዋል እነዚህም፣ አንደኛ የአሠራር ባህልን እና ልምድን የሚቀይሩ በመሆናቸው፤ ሁለተኛ የተሠሩት ፕሮጀክቶች እንደሌሎች ከፍተኛ ደረጃ ላይ ያለውን የሕዝብ ክፍል ብቻ የሚያስተናግዱ ሳይሆኑ ሁሉም ኢትዮጵያዊ በእኩል ሊጠቀምባቸው የሚችል የሕዝብ ኃብት መሆናቸው፤ እና ሦስተኛው ሌሎች መሠራት ያለባቸው ፕሮጀክቶች በመተው የተሠሩ አለመሆናቸው እንደሆነ ለዚህም ስንዴ ላይ "አንድም መሬት ጾም አይደር" በሚል እየተሠራ ያለው እና በአጠቃላይ የግብርናውን ዘርፍ ለማዘመን እየተሠሩ ያሉ ሥራዎች ማሳያ እንደሆኑ አንስተዋል። ሲያጠቃልሉም፣ ሌሎች አካላትም ቢሠሩ ብለው የሚያስቧቸው የዚህን መሰል ፕሮጀክቶች በተለያየ መንገድ መሥራት እንደሚገባ አሳስበው፤ መንግሥት ሁሉንም ቦታዎች ማልማት የሚችል አቅም እንደሌለው አስረድተዋል። በመጨረሻም፣ በነዚህ ፕሮጀክቶች ውጤት ማሳየት እንደተቻለ እና በሌሎች አላስፈላጊ ጉዳዮች ጊዜ እና ጉልበት ከማባከን በተጀመረው ሀገር የመገንባት ሥራ ላይ ሁሉም በሚችለው ልክ ቢሳተፍ መልካም ነው የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።








FRIENDSHIP SQUARE
ENTOTO PARK

# ክፍል ሦስት፣

## የአዲስ ወግ መድረኮች

## 2013 ዓ.ም

# 3.1 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ የቆላ አካባቢዎች እና የአርብቶ አደር ዜጎች የልማት ጉዞ

ጥር 6 ቀን 2013 ዓ.ም




በወርሃ ጥር የተደረገው የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ ፕሮግራም ርዕሱን “የቆላ አካባቢዎች እና የአርብቶ አደር ዜጎች የልማት ጉዞ” በሚል ነው። በኢትዮጵያ አርብቶ አደሮች በስፋት የሚገኙባቸው ስድስት ክልሎች ያሉ ሲሆን፤ ስልሳ በመቶ የሚሆነውን የሀገሪቱን የቆዳ ስፋት ይሸፍናሉ። በሕዝብ ብዛትም ከ12 (ዐሥራ ሁለት) እስከ14 (ዐሥራ አራት) በመቶ ያህሉን የሕዝብ ቁጥር ይይዛሉ። ከለውጡ በኋላ ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ፕሮግራም በቆላማ አካባቢዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት በማድረግ ስንዴን ጨምሮ የተለያዩ የሰብል ምርቶች ለማልማት እየተሠራ እንደሆነ ይታወቃል። የዚህ ፕሮግራምም ዋነኛ ዓላማ በእነዚህ አስቸጋሪ የአየር ንብረት ባላቸው አካባቢዎች ላይ የሚኖረውን ሕዝቡ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚያስችሉ የፖሊሲ ለውጦች ምን መምሰል አለባቸው? የኢኮኖሚውን ሽግግር ለማሳካትና የሕዝቦችን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ምን መሥራት ያስፈልጋል? በሚሉ ጉዳዮችና ባለፉት 15 (ዐሥራ አምስት) ዓመታት ከተሠሩ ሥራዎች እና ከተገኙ ውጤቶች ምን እንማራለን? በሚሉ ሐሳቦች ላይ ውይይት ማድረግ ነው።

በውይይቱ ዶ/ር ማንደፍሮ ንጉሤ በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ዘርፍ የልማት ሚኒስትር ዴኤታ (የቀድሞ)፣ ወ/ሮ ሃኒ ሀሰን የግብርና ምጣኔ ኃብት ባለሙያና የአርብቶ አደሩ አካባቢ ተወላጅ፣ እንዲሁም አቶ አብዱራህማን በሶማሌ ክልል የመስኖና የተፋሰስ

ልማት ቢሮ ኃላፊ በውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢነት ተሳትፈዋል። ውይይቱን የመሩት በጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት የፖሊሲ አማካሪ ብሌን ንጉሤ (የቀድሞ) ናቸው።

## የአርብቶ አደሩ አካባቢ የአኗኗር ዘይቤና ችግሮች

በመጀመሪያ ንግግር ያደረጉት ወ/ሮ ሃኒ ሃሰን፣ የአርብቶ አደሩ ኑሮ ሁኔታ ምን ይመስላል? የሚሉና ተያያዠ ጉዳዮችን አንስተዋል። በንግግራቸውም "አርብቶ አደር" ማለት የሕይወት ዘይቤ እንደሆነና ሦስት ዋና ዋና ነገሮች እንዳሉትም ገልጸዋል። የመጀመሪያው የተለያየ ጎሳ እና ባህላዊ አስተዳደር ያላቸው ሕዝቦች፤ የተለያዩ ዓይነት እንስሳትን እና የተፈጥሮ ኃብትን መሠረት ያደረገ የሕይወት ዘይቤ ያላቸው፤ አርብቶ አደሮች የሚኖሩበት አካባቢ ሞቃታማና ለሌሎች የእርሻ ሥራዎች ተመራጭ ያልሆነ በተፈጥሮ በጣም አነስተኛ የዝናብ መጠንና ሥርጭት ያለው አካባቢ የሚሉትን እንደሚያጠቃልል አስረድተዋል። አርብቶ አደሩ ለእንስሳቱ ውሀና ግጦሽ ፍላጎት ሲል የዝናብ ሁኔታውን መሠረት  ያደረገ አሠራር ያለውና እንቅስቃሴ የሚያደርግ እንደሆነም ገልጸዋል። ነገር ግን በተለምዶ እንደሚባለው "የእንስሳትን ጭራ የሚከተል" እንዳልሆነ የተደራጀ እና የተጠና የእንስሳት እንቅስቃሴ የሚያደርግ የኅብረተሰብ ክፍል እንደሆነ፤ በጎሳ መሪዎቹ ወይም በሌሎች የአስተዳደር ሥርዓቶቹ የተደራጀና የታቀደ ጥብቅ እንቅስቃሴ የሚያደርግ ማህበረሰብ መሆኑን አብራረተዋል። በተጨማሪም፣ በሀገራችንም ሆነ በተለያየ የዓለም ክፍል የሚኖር አርብቶ አደር ሁሉም ተመሳሳይ ዓይነት የኑሮ ዘይቤ የሌለው እንደሆነ፤ ይልቁንም፣ እንደየአካባቢው እና የተፈጥሮ ኃብት የአኗኗር ሥርዓቱ የሚለያያይ እንደሆነ አስረድተዋል።

ባለፉት 15 (ዐሥራ አምስት) ዓመታት  "የአርብቶ አደሩን ሕይወት ይቀይራሉ" በሚል በመንግሥት በኩል የተለያዩ ሥራዎች  ሲሞከሩ እንደነበር ገልጸው፤ የተሳኩ ሥራዎች እንደመኖራቸው ሁሉ የአርብቶ አደሩን ነባራዊ ሁኔታ ካለመረዳት የተነሳ የከሸፉም  ሥራዎች እና ፖሊሰዎች እንደነበሩ አንስተዋል። ለምሳሌ፦ አርብቶ አደሩን ባጠቃላይ ተንቀሳቃሽ አድርጎ የሚታሰበው ነገር ልክ አለመሆኑን ተናግረዋል። በርግጥ አርብቶ አደር ተንቀሳቃሽ መተዳደሪያ (livelihood mobility) እንደሚከተል ይታወቃል። ነገር ግን የማህበረሰብ እንቅስቃሴ (community mobility ) እንደሌለ መረዳት ያስፈልጋል። የአርብቶ አደር አካባቢዎች ብዙ መሠረተ ልማት ችግር ያለባቸው እንደሆኑና የሚሠሩ መሠረተ ልማቶችም የኅብረተሰቡን ዘላቂ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ መሆን እንደሚገባቸው አስረድተዋል። አብዛኛው የኢትዮጵያ አርብቶ አደር በድንበር አካባቢ የሚገኝ እንደመሆኑ ምርቶቹን ማለትም የቁም ከብቶችን ለሀገር ውስጥ እና ለውጭ ለገበያ

የሚያቀርብበት ሥርዓት ባለመኖሩ በድንበር አካባቢ የቁም ከብቶች በሕገወጥ መልኩ ወደጎረቤት ሀገራት የሚሸጡበት ልማድ አለ። ይኸ የአርብቶ አደሩንም የኢትዮጵያንም ተጠቃሚነት እንደሚጎዳ አንስተዋል። በተጨማሪም፣ የአርብቶ አደሩን አካባቢዎችና ታዳጊ ክልሎች ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍል ጋር በእኩል ዓይን የማይታዩበት ሥርዓት አንዱ ችግር እንደነበር አስታውቀዋል።

ባለፉት ዐሥራ አምስት ዓመታት በአርብቶ አደሩ ላይ ትኩረት አድርገው የወጡ ፖሊሲዎች እና የነበራቸው ውጤት ምን ይመስል ነበር በሚለው ነጥብ ላይ አቶ አብዱራህማን ሐሳባቸውን ሲያጋሩ፤ አርብቶ አደሩን እና የአርብቶ አደሩን አካባቢ መሠረት ያደረጉ ፖሊሲዎች ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን ጀምሮ ተግባራዊ ሲደረጉ እንደነበር አንስተው፣ ዋነኛ ትኩረታቸውም ለአስተዳደር ያመች ዘንድ አርብቶ አደሩን በአንድ ቋሚ አካባቢ ለማስፈር መሥራት እንደነበር ጠቁመዋል። ባለፉት ዓመታትም በፌዴራል ጉዳዮች ሚኒስቴር በኩል የአርብቶ አደሩን ሕይወት ማሻሻልን ያለሙ ፖሊሲዎች ወጥተው ተግባራዊ ሲደረጉ መቆየታቸውን፤ በፖሊሲዎቹ እንደዋነኛ ተግባር የተቀመጠውም የእንስሳት ኃብታቸውን በተለያየ ምክንያት ያጡ አርብቶ አደሮችን በቋሚነት በወንዝ ተፋሰሶች ዙሪያ ማስፈር፤ ትምህርትንና የጤና አገልግሎትን ማስፋፈት እንደነበር አንስተው፤ ነገር ግን ሁሉንም አርብቶ አደር ለማስፈር ሙከራ ይደረግ እንደነበር አስታውሰዋል። የፖሊሲዎች ዋነኛ ድክመትም የአርብቶ አደሩን ትክክለኛ የአኗኗር ሁኔታ ከግንዛቤ ሳያስገቡ የተቀረጹና ያልተተገበሩ መሆናቸው እንደሆነ አስረድተዋል። ፖሊሰዎቹ መደበኛ ያልሆነ ትምህርት ማስፋፋት፤ እንዲሁም የተጠናከረ የእንስሳት ጤና ሥርዓት መዘርጋት መቻላቸው ደግሞ በጎ ውጤታቸው እንደነበር ገልጸዋል።

በአሁኑ ሰዓት ኢትዮጵያ ተግባራዊ ለማድረግ እየሠራችበት ያለው የፖሊሲ ማሻሻያ ባለፉት ዓመታት በፖሊሲ ችግር ምክንያት በአርብቶ አደሩ ላይ ሲደርሱ የነበሩ ችግሮችን እንዴት ለመፍታት ታስቧል? በሚለው ላይ አስተያየት የሰጡት ዶ/ር ማንደፍሮ፤ ከለውጡ በኋላ ለግብርናው ዘርፍ በተሰጠው ከፍተኛ ትኩረት ላለፉት ዓመታት ስንጠቀምበት የነበረው የገጠር እና የግብርና ፖሊሲ እየተከለሰ ይገኛል። በዐሥሩ ዓመት እቅድም በፖሊሲው የሚሻሻሉትን ነገሮች ታሳቢ በማድረግ እንደታቀደ እና በፖሊሲው ላይ ዐሥር የተለያዩ አጀንዳዎች ለውጥ እንደሚያስፈልጋቸው ታምኖበት እየተሠራ እንዳለ አስታውቀዋል። ከእነዚህ መካከል አንዱና ዋነኛው ቆላማ አካባቢዎችንና አርብቶ አደሩን የሚመለከት እንደሆነ ገልጸዋል። የሚፈለገው የገጠር ፖሊሲ ሁሉንም ዓይነት የግብርና ሥራዎች በእኩል እና ቀጣይነት ባለው መልኩ

ለማከናወን የሚያስችል እንዲሆን፤ የአርብቶ አደሩ አካባቢም ትኩረት እንዲያገኝ የሚስችለው እንደሆነ ጠቁመዋል። ከዚህ ቀደም የነበረው ፖሊሲ በአርብቶ አደሩ አካባቢ ትልልቅ የተቀናጁ የእርሻ ሥራዎች ለመሥራት ይደረግ በነበረው እንቅስቃሴ አርብቶ አደሩ ከአካባቢው ሲፈናቀል እንደነበር እርሻዎችም ውጤታማ ሳይሆኑ ቀርተዋል ብለዋል። የአሁኑ ፖሊሲ ግን የአርብቶ አደሩን ተጠቃሚነት የሚያረጋግጥ ልማት ለማከናወን የሚያስችል እንደሚሆን ተናግረዋል።

በተጨማሪም፣ አርብቶ አደር የሚኖርባቸው ቆላማና ዝቅተኛ የኢትዮጵያ ስፍራዎች አነስተኛ የውሀ መጠን ያላቸው እንዳልሆኑ፤ የዝናብ ሥርጭት እጥረት ቢኖርባቸውም ከፍተኛ የከርሰ ምድር ውሀ እና ታላላቅ ወንዞች የሚገኙባቸው አካባቢዎች እንደሆኑ አንስተው፤ ትልቁ ችግራችን በእነዚህ አካባቢዎች ያለውን የውሀ ኃብት የመጠቀም አቅም አለመኖሩ እንደሆነ አብራርተዋል። ከዚህ ቀደም በአርብቶ አደሩ አካባቢ ጥጥ ያመርቱ የነበሩ ገበሬዎች አሁን ስንዴ በተጨማሪነት እንዲያመርቱ እየተደረገ እንደሆነ፤ ይህ ግን ሁሉም አርብቶ አደር ወደእርሻ ይገባል ማለት እንዳልሆነ አውስተዋል። በአካባቢው የእህል እና የእንስሳት መኖ በተመጣጣኝነት እንዲመረት በማድረግ የሀገር ውስጡን የመኖ ፍላጎት አሟልቶ ወደውጭ መላክም እንደሚቻል ታስቦ እየተሠራበት ያለ ጉዳይ ነው። በዚህ አካባቢ ያለው የዝናብ መጠን አነስተኛ እና ወጥ አይደለም። በመሆኑም፣ አርብቶ አደሩ ዝናብ በሚያገኝበት ወቅት መኖ አምርቶ በማቆየት ዝናብ በማይኖርበት ወቅት መጠቀም የሚችልበት አሠራርም እየተተገበረ እንደሆነ፤ በዚህም፣ አርብቶ አደሩ መኖ፣ ውሀ እና ሕክምና ፍለጋ የሚያደርገውን እንቅስቃሴ በመቀነስ እንስሳቱ የሚያባክኑትን ኃይል በመቀነስ ውጤታማነታቸው እንዲጨምር ማድረግ እንደሚቻል አስረድተዋል። በዚህም፣ የአርብቶ አደሩ የግብርና ሥራ እንዲሻሻል፣ ሕይወቱ እንዲለወጥ እና ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ የሚያበረክተው አስተዋጽዖ እንዲያድግ በጥናት ላይ የተመሠረተ ሥራ መሥራት ግድ እንደሚል አሳስበዋል።

## የተሳታፊዎች አስተያየት፣ ጥያቄ እና መልስ

በውይይቱ ወቅት ከተሳታፊዎች የተለያዩ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች ተነስተዋል። በአስተየየቶችም በሀገራችን ካሉ ትላልቅ ተፋሰሶች መካከል አምስቱ (ባሮ አኮቦ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ ሸበሌ እና አዋሽ ተፋሰሶች) በቆላማ እና አርብቶ አደር አካባቢ የሚገኙ መሆናቸውን፤ በነዚህም አካባቢዎች እስከአራት ሚሊዮን ሄክታር መሬት በመስኖ ማልማት የሚያስችል አቅም መኖሩን፤ በሀገራችን ካሉ ዐሥራ አምስት የመስኖ ኮሪደሮች ዐሥሩ በአርብቶ አደሩ አካባቢ እንደሚገኙ፤ በተያዘው ዓመት

65 (ስድሳ አምስት) ሺሕ ሄክታር መሬት የሚያለማ የመስኖ ፕሮጀክት በጥናት ላይ እንደሚገኝ፤ 17 (ዐሥራ ሰባት) ሺሕ ሄክታር መሬት የሚያለማ የመስኖ ሥራ በግንባታ ላይ እንደሚገኝ መረጃ ሰጥተው ይህ ሁሉ ግን ካለው ኃብት ጋር ሲተያይ በጣም አነስተኛ እና ብዙ ሥራ የሚጠይቅ መሆኑን ተገልጿል። በአንዳንድ የአርብቶ አደሩ አካባቢዎች ያሉ የመስኖ ፕሮጀክቶች የውሀ ማፋሰሻ ችግር አሉባቸው በሚል የተነሳው ሐሳብ በዲዛይን እና ፕሮጀክት ግንባታ ችግር ምክንያት እንደዚህ ዓይነት ችግሮች ሊከሰቱ እንደሚችሉ አንስተው፤ በሂደት ችግሮቹ የሚፈቱበት መንገድ እንደሚፈለግ አስተያየት ሰጥተዋል። ከፋርም አፍሪካ የተወከሉ የውይይቱ ተሳታፊ አዲስ እየተሻሻለ ያለው የገጠር እና የግብርና ፖሊሲ ላይ የተለያዩ ባለድርሻ አካላትን በማስተሳሰር እንዲፈጸም ተደርጎ መዘጋጀቱን አንስተው በጎ ተግባር እንደሆነ ተናግረዋል።
በሌላ በኩል፣ የአርብቶ አደሩን ምርታማነት ለማሻሻል ምን ዓይነት አሠራር መጠቀም አለብን? የአርብቶ አደር ጉዳዮች ከላይ ወደታች ብቻ ከሚመጡ አርብቶ አደሩ የሚፈልገውን እና የሚያስፈልገውን ማሳወቅ የሚቻልበትን መንገድ ቢፈለግ፤ አርብቶ አደሩም በኢንቨስትመንት እንዲሳተፍ ምን ዓይነት የፋይናንስ አገልግሎት ለማቅረብ ታስቧል? የአርብቶ አደሩ ዘመናዊ ቄራዎችን ተጠቅሞ የከብት ሥጋ ለውጭ ገበያ የሚልክበት ሥርዓት ነበረው። አሁን ግን ይህ አሠራር ተከልክሏል። ለምን? የሚሉ ጥያቄዎች ተነስተዋል።

ለጥያቄዎች በቅድሚያ ምላሽ የሰጡት ዶ/ር ማንደፍሮ፣ በአሁን ሰዓት እየተሠራ ያለው የፖሊሲ ማሻሻያ ስለሆነ የነበሩትን ችግሮች በማጥናት ማስተካከያ እንደሚደረግ፤ ነገር ግን አዲስ ፖሊሲ የሚቀረጽ ቢሆንም ከታችኛው የአርብቶ አደር ማህበረሰብ ጀምሮ ወደላይኛው የመንግሥት ሕግ አውጪ አካል የሚመጣበት ሥርዓት ሊሆን እንደሚችል አስታውቀዋል። አሁን እየተደረገ ያለው የፖሊሲ ማስተካከያ ሀገራችን ያለባትን ችግር፤ ፖሊሲው ያለበትን ችግር ለመቅረፍ፤ እንዲሁም ከሀገራዊ ሪፎርሙ ጋር አብሮ የሚጓዝ የገጠር እና የግብርና ፖሊሲ እንዲኖረን ለማድረግ እንደሆነ፤ በዚህ ሂደትም ሁሉንም አርብቶ አደር፣ አርሶ አደር እና ከፊል አርብቶ አደር ያማከለ፤ እንዲሁም ሁሉንም የአየር ጠባይ ከግምት ውስጥ ያስገባ የግብርና ፖሊሲ እንዲሆን ተደርጎ እየተሠራ እንደሆነ አስረድተዋል። ከፋይናንስ አቅርቦት ጋር ለተነሳው ጥያቄም፣ የግብርና የፋይናንስ አቅርቦት አንዱ የማሻሻያው አካል እንደሆነና ይህም የግብርና ባንክ እስከማቋቋም ድረስ የሚያድግ እንደሚሆን ጠቁመዋል። ከእንስሳት ተዋጽዖ (ሥጋ) ምርት እና ንግድ ጋር ለተነሳው ጥያቄም በሰጡት ምላሽ፣ አንድን ምርት በየቀኑ ለገበያ እንዲቀርብ ከተፈለገ ምርቱን ያለመቆራረጥ ማምረት ያስፈልጋል። የእኛ ሀገር የእንስሳት ምርት በዚያ ደረጃ ነው ወይ የሚመረተው? የሚለው ትልቅ

ጥያቄ እንደሆነ አንስተው የእንስሳትን ምርት ቀጣይነት ባለው መንገድ ለማቅረብ ግን የተቀናጀ እና ሰፊ ሥራ መሥራት እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

በመጨረሻም አቶ አብድራህማን፣ በመሠረተ ልማት እና የፋይናንስ ችግር ላይ የተነሳው ጉዳይ የአርብቶ አደሩን አካባቢና የአርብቶ አደሩን ሕይወት እንዳይሻሻል ከሚያደርጉት ዋና ዋና ችግሮች መሀል እንደሆኑ አንስተዋል። በተለይ በአርብቶ አደሩ አካባቢ የመሠረተ ልማት ችግር በስፋት እንደሚታይ እና የልማት ሥራዎችንም ለመሥራት እንቅፋት እንደሆነ ገልጸዋል። አርብቶ አደሩ የግብርናውን ሥራ ለማሳደግ ከፍተኛ የፋይናንስ ችግር እንዳለበትም ጠቁመዋል። እየተሸሻለ ባለው የገጠር እና የግብርና ፖሊሲ ቀደም ሲል የነበረውን በተቀናጀ መልኩ የማስፈጸም ክፍተት አይቶ ባለድርሻ አካላትን አጣምሮ መሠራቱ ጥሩ ውጥን መሆኑን አንስተዋል። ከለውጡ በኋላ ቋሚ ያልሆኑ ንብረቶችን በማስያዣነት መጠቀም እንዲቻል የወጣው ሕግ እና የሸሪዐን ሕግ የሚተገብሩ የ"እስላሚክ" ባንኮች መመስረታቸው በተለይ በብዛት የእስልምና እምነት የሚከተለውን አርብቶ አደር በከፍተኛ ሁኔታ የሚጠቅሙ እንደሆኑም አቶ አብዱራህምን አስታውቀዋል።

በሌላ በኩል፣ ከእንስሳት እርድ እና ገበያ ጋር በተነሳው ጉዳይ ከዚህ ቀደም በሥራ ኃላፊነታቸው ካጠኑት ታሪክ ጋር አስተሳስረው በመሃል ሀገር ያሉ የቄራ የእንስሳት ግዥዎች የእንስሳውን ክብደት መሠረት አድርገው ዋጋ በኪሎ የሚወስኑ መሆናቸውን አንስተው በሶማሌ ክልል ግን ይህ አሠራር የማይታወቅ እና እንስሳት "ባይተሽ" የሚሸጡበት ባህል የተለመደ በመሆኑ በሶማሌ ክልል ተጀምሮ የነበረው የእንስሳት ቄራ ችግር እንደገጠመው አስረድተዋል። በድንበር አካባቢም እንስሳት በሕገወጥ መንገድ ወደውጭ ገበያ የሚሸጡበት ሥርዓት የተለመደ መሆኑን፤ በዚህም ሳቢያ በሕጋዊ መንገድ ከገበሬው ገዝተው ወደውጭ የሚልኩ አካላት ከውጭ ምንዛሬ ጋር ባለ ልዩነት ምክንያት፣ ማለትም ገበሬው በተለመደው መንገድ ሸጦ ገንዘቡን በጥቁር ገበያ የምንዛሬ ዋጋ የሚረከብ ስለሆነ፤ በሕጋዊው አሠራር በባንክ የምንዛሬ ዋጋ ሲሸጡ በሚኖረው የዋጋ ልዩነት የተነሳ የእንስሳት ንግዱን አስቸጋሪ እንደሚያደርገው አንስተዋል።

በተጨማሪም፤ የሶማሌ ክልል በጣም ሰፊ መልክዐ ምድር ያለው መሆኑና በክልል የድንበር ንግድ እንዲካሄድ የተፈቀደበት አንድ የድንበር ቦታ (ውጫሌ) በመሆኑ ምክንያት ከ1000 (አንድ ሺሕ) ኪሎ ሜትር ርቀት ድረስ ያሉ አርብቶ አደሮች ባሉበት የድንበር አካባቢ እንስሳቱን ከሕጋዊው ሥርዓት ውጭ እንዲሸጡ

እንደሚያስገድዳቸው ጠቁመዋል። ለዚህም በየአካባቢው የጉምሩክ ጣቢያዎች እንዲከፈቱና የግብይት ሥርዓቱም እንዲስተካከል ቢደረግ ኢትዮጵያም፣ አርብቶ አደሯቿም የሚጠቀሙበትን ሥርዓት መፍጠር ይቻላል ብለዋል።









# 3.2 የአዲስ ወግ አብይ ጉዳይ፣ ሰላም እና ደኅንነት በምርጫ ወቅት (የሰላማዊ ምርጫ መገለጫዎች እና መስፈርቶች)

መጋቢት 21 ቀን 2013 ዓ.ም




ይህ በመጋቢት 21 እና 22፣ 2013 ዓ.ም የተደረገው የአዲስ ወግ አብይ ጉዳይ የውይይት ፕሮግራም “ሰላም እና ደኅንነት በምርጫ ወቅት” በሚል ርዕሰ ጉዳይ የተዘጋጀ ሲሆን “የሰላማዊ ምርጫ መገለጫዎች እና መስፈርቶች”፣ “በምርጫ ወቅት ሰላምን ለማስፈን ሰላምን የሚያንጹ ሀገር በቀልና ዘመናዊ ተቋማት ሚና” ፤ እንዲሁም “ሐሰተኛ መረጃ በሰላማዊ ምርጫ ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መግታት” በሚሉ ንዑስ ርዕሶች ላይ የተለያዩ ምሁራን እና ባለሙያዎች፣ እንዲሁም የሕዝቡ አካላት ለሁለት ተከታታይ ቀናት ያደረጉትን ውይይት የያዘ ነው። ውይይቱ ስድስተኛው ብሔራዊ ምርጫ ፍትሐዊ እና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ለማስቻል፤ እንዲሁም ለዜጎች ሰላማዊነቱ እና ደኅንነቱ ስለተጠበቀ ምርጫ ግንዛቤ ለመፍጠር የተዘጋጀ ነው።

## 3.2.1 ክፍል አንድ

የመክፈቻ ንግግር ያደረጉት የሴቶች ማረፊያና ልማት ማህበር ዳይሬክተር ወ/ሮ ማሪያ ሙኒር ናቸው። በንግግራቸው ምርጫ የሕይወታችን አንድ አካል እንደሆነና የፖለቲካ ምርጫ ሕዝብን የሚመራና ሀገርን የሚያስተዳደር መሪ የሚመረጥበት ሥርዓት እንደመሆኑ ሰላማዊ እና ታማኝ መሆን ይጠበቅበታል ብለዋል። በ1992 ዓ.ም ምርጫ የኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያ ሴቶችን ማህበር ወክለው ሴቶች በምርጫ እንዲሳተፉ በሠሩበት ወቅት የነበሩትን ሁኔታዎች በማስታወስ ለምርጫው መሳካት እና ሰላማዊነት ሁሉም ኃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት አሳስበዋል። ሚዲያዎች እና ጋዜጠኞችም ያለምንም ወገንተኝነት መሥራት እንደሚገባቸው ተናግረዋል። እንዲሁም፣ ከምርጫ በኋላ ውጤቱን በጸጋ መቀበል እንደሚገባ አሳስበዋል። በውይይት መድረኩ ሐሳብ ያቀረቡት በእርቀ ሰላም ኮሚሽን በተለያየ ኃላፊነት ያገለገሉት እና የአንድምታ ማህበራዊ ውይይት ማህበር መሥራች ወ/ሮ ሕይወት አለማየሁ እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሕግ ክፍል ከአስተማሪነት እስከዲን ደረጃ ያገለገሉት፤ በተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች በተመራማሪነት የሠሩት ዶ/ር መሰንበት አሰፋ ናቸው። ውይይቱን የመራው ጋዜጠኛ ጥበቡ በለጠ ነው።

### የሰላማዊ ምርጫ መገለጫዎች

በመጀመሪያ ዶ/ር መሰንበት አሰፋ "ሰላም እና ደኅንነት በምርጫ ዙሪያ እንዴት ይረጋገጣል?" በሚል የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅርበዋል። በዚህም፣ ምርጫ የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገለጫ እንደሆነና የመንግሥት ሥልጣን በሕዝብ ፍላጎት እና ልዕልና የሚወሰንበት ሥርዓት ስለሆነ ሰላማዊ መንገድ መከተል ግድ ይላል ብለዋል። ከሰላማዊ መንገድ ውጭ በአመጽ እና በጦርነት ሥልጣን መያዝ በዓለም አቀፋዊ ሕግ መሠረት የተከለከለ እንደሆነም አስረድተዋል። የመምረጥ መብት ዓለም አቀፋዊ እውቅና የተሰጠው የሰብዓዊ መብት እንደሆነና የመሠረታዊ ዴሞክራሲ ሥርዓት አካል መሆኑንና ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ ተነጥሎ የሚታይ ሐሳብ እንዳልሆነ አንስተዋል።

የምርጫ ታሪካችንን በተመለከተም፣ ያለፉት አምስት ምርጫዎች ብዙ በጎ ያልሆኑ ልምዶች የታዘብንባቸው እና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደታችንም ላይ እንቅፋት የነበሩ እንደሆኑ አስታውሰዋል። በተለይ የ1997 ዓ.ም ምርጫ በሀገራችን ፖለቲካ ላይ ትልቅ ጫና ያሳረፈ እንደነበር አንስተው፤ ዓለም አቀፋዊ ጥናቶችን በመጥቀስ በአፍሪካ ውስጥ ከሚደረጉ ምርጫዎች 20 (ሃያ) በመቶ

ያህሉ ግጭት እንደሚያስከትሉ የሚያሳዩ መረጃዎች በመኖራቸው ኢትዮጵያም ለመጭው ምርጫዋ ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ መሆን ከወዲሁ መዘጋጀት አለባት ሲሉ አሳስበዋል። "ምርጫችን ሰላማዊ እና ደኅንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ምን ማድረግ ይጠበቅብናል?" በሚለው ጉዳይ ላይ አምስት መሠረታዊ ነጥቦች አንስተዋል።

የመጀመሪያው የሰብዓዊ መብቶች መከበር፤ የሰብዓዊ መብቶች በየትኛውም ጊዜ መከበር ቢኖርባቸውም በምርጫ ወቅት ግን የመንግሥትን ሥልጣን የሚወስን እንደመሆኑ መጠን የሕዝቦችን ተሳትፎ ለማረጋገጥ እና ለምርጫው ሰላማዊነት ሲባል መከበር አለባቸው። ሁለተኛው የሕግ የበላይነት፤ ዜጎች እንዲሁም ከመንግሥት ውጭ ያሉት የፖለቲካ ኃይሎች ሁሉ ከመብታቸው ባለፈ ግዴታቸውን ማወቅና መተግበር ይገባቸዋል። በተለይ ሐሳብን በነጻነት ከመግለጽ ጋር በተያያዘ የምርጫውን ሰላማዊነት የሚያውኩ መረጃዎችን ከማሠራጨት መቆጠብ አለባቸው። ዴሞክራሲ በሂደት የሚገነባ ሥርዓት እንደመሆኑ ዴሞክራሲ የሚፈልጋቸውን ሥነ-ሥርዓቶች እና ሥርዓቶች ተግባራዊ ማድረግ ካልጀመርን ዴሞክራሲን ማሳካት እንደማይቻል ማወቅ ይገባናል። ሦስተኛ የሐሰተኛ መረጃን ሥርጭት መግታት፤ በሕግ ማስከበር ጊዜ እንደተደረገው የአስቸኳይ ጊዜ መረጃ ማጣሪያ ሥርዓት በምርጫ ወቅትም የሐሰተኛ መረጃዎችን ሥርጭት በተመሳሳይ መንገድ መግታት ይገባል። አራተኛ የፖለቲካ ኃይሎች በምርጫ ማሳካት የሚፈልጉትን (political expectations) መቆጣጠር ይገባቸዋል። ፓርቲዎች በምርጫው ማሸነፍ እና ሙሉ በሙሉ መሸነፍን ከማሰብ ይልቅ አነስተኛ ድምጽም ቢገኝ ውጤቱን ተቀብሎ ተሳትፎን በማሳደግ የዴሞክራሲ ልምምዳችን ለማሳደግና በሐሳብ ለመሞገት ራስን ማዘጋጀት ይገባል። አምስተኛ የጸጥታ አካላት ለምርጫው ሰላማዊነት ያለባቸውን ኃላፊነት መወጣት አለባቸው፤ እንዲሁም የምርጫ ሥርዓት ሂደት እንደመሆኑ በምርጫው ቀን ብቻ ሳይሆን በቅስቀሳ ወቅት፣ በምርጫ ቀን እና ውጤት በሚታወቅባቸው ጊዜያት ሁሉ ሰላማዊነታቸው ሊረጋገጥ እንደሚገባ አሳስበዋል። የምርጫ ቦርድን አስመልክቶም፤ የምርጫውን ሰላማዊነት ለማረጋገጥ ከክልል እና ከፌዴራል የጸጥታ ተቋማት ጋር በመቀናጀት የጸጥታውን ሁኔታ ለመቆጣጠር መሥራት አለበት። ከእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ጋር የሚኖረውን የመረጃ ልውውጥም ማቀላጠፍ ይጠበቅበታል። የሲቪክ ማህበራት በታዛቢነት እና ለመራጮች ትምህርት በመስጠት ተሳትፏቸውን እንዲጠናከሩ በቅንጅት መሥራት እንደሚጠበቅበት አሳስበዋል። ይህንም ተግባር በአግባቡ ለመፈጸም ቦርዱ የአመራር አቅም እና የሕዝብ ቅቡልነት እንዳለው አስረድተዋል።

ሁለተኛዋ ሐሳብ አቅራቢ ወ/ሮ ሕይወት በምርጫ ወቅት ሰላምን ለማስጠበቅ

የባለድርሻ አካላት ሚና ምን መሆን እንደሚገባው እና ሰላማዊ ምርጫ ለማካሄድ ልንከተላቸው የሚገቡንን መንገዶች ጠቁመዋል። ካነሷቸው ሐሳቦች መካከልም፣ ምርጫ ሕዝብ የሥልጣን ምንጭ መሆኑን የሚያረጋግጥበት ሥርዓት በመሆኑ በሂደቱ ሕዝብ መከበር እና ደኅንነቱ መጠበቅ አለበት። ግዴታውን እንዲወጣም የሕግ የበላይነት በሁሉም አካላት መከበር ይኖርበታል። የምርጫ ተሳታፊዎች ማለትም ሚዲያዎች፣ ታዛቢዎች፣ የሲቪክ ማህበራት፣ የጸጥታ እና የሕግ አካላት ገለልተኛ ሆነው ተሳትፎ ማድረግ ይገባቸዋል። ሥልጡን ውይይት ማካሄድ እንደሚገባና በዚህም መንገድ የሁሉም ወገን ሐሳብ መደመጥ እንዳለበት፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ሕግን እንዲያከብሩና አባላቶቻቸውንም ከሕገወጥ ተግባር እንዲቆጠቡ መከታተል አለባቸው ብለዋል። የጸጥታ አካላት በምርጫ ወቅት በምን መልኩ ሰላምን ማስከበር እንዳለባቸው ሥልጠና እንዲያገኙ ማድረግ፣ የሚዲያ አካላት ወገንተኛ ከሆኑ ሥራዎች እንዲታቀቡ ማድረግ፤ እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት እና የእምነት ተቋማት ሕዝቡን ስለሰላማዊ ምርጫ እንዲያስተምሩ ማድረግ ተገቢ ነው ብለዋል። የነጋዴው ማህበረሰብም በምርጫ ወቅት የሚፈጠሩ የዋጋ መናር እና መሰል ክስተቶችን እንዲከላከል ማድረግ እንደሚያስፈልግ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያን የምርጫ ባህል እና ታሪክ መሠረት አድርገው ባቀረቡት ሐሳብም የምርጫ ልምድ እና ባህል በሂደት የሚገነባ እንደሆነ፤ ኢትዮጵያም ከዚህ ቀደም ያደረገቻቸው ምርጫዎች ውጤታማ ነበሩ የሚባሉ እንዳልሆኑና ለምርጫ ልምምድ እድገትም እንቅፋት እንደነበሩ አውስተው፤ የአሁኑ ምርጫ ያለፉት ምርጫዎች ባለእዳ እንደሆነ አሳስበዋል። ለምሳሌነትም በ1997 ዓ.ም የተደረገው ምርጫ በፈጠረው የሕዝብ አመኔታ ማጣት ምክንያት ከዚያ በኋላ የተደረጉ ሁለት ምርጫዎች የሕዝብ ተሳትፎ በከፍተኛ ሁኔታ የቀነሱ፤ የአንድን የፖለቲካ ፓርቲ የበላይነት ብቻ ለማረጋገጥ የተደረጉ እንደነበር አስታውሰዋል።

## ከተሳታፊዎች በተነሱ አስተያየት እና ጥያቄዎች ላይ የተሰጡ ምላሾች

የውይይቱ ተሳታፊዎች የወጣቶች የምርጫ ተሳትፎ ችግር ያለበት ነው። ቀደም ተብሎ ወጣቱ የመምረጥ እና መመረጥ መብቱን እንዲጠቀም፤ ከዚያም አልፎ በምርጫ ወቅት በሚፈጠሩ የጸጥታ መደፍረሶች መጠቀሚያ እንዳይሆን የማድረግ ሥራ ለምን ይዘነጋል? ተፎካካሪ ፓርቲዎች ቢያሸንፉ ጥምር መንግሥት መሥርተው ሀገር ማስተዳደር ይችላሉ ወይ? የሚሉ ጥያቄዎች አንስተዋል። በሌላ በኩል፣ ከሰላማዊ ምርጫ መገለጫዎች መካከል የዴሞክራሲ ተቋማት ተቀባይነት እና ታማኝነት እንደአንድ መወሰድ አለበት። የሰብዐዊ መብት ተቋማት፣ ፓርላም፣ እንዲሁም

ሌሎች ተቀባይነት እና ታማኝነት እንዲኖራቸው መሥራት አስፈላጊ ነው። በአሁኑ ሰዓት እንደ ከዚህ ቀደሙ መንግሥት የተፎካካሪ ፓርቲዎችን በማፈን ከሚታወቅበት ልምድ አልፎ አንዳንድ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሌላውን ተፎካካሪ ፓርቲ "እዚህ አካባቢ አትንቀሳቀስም" የሚሉ ክልከላዎች ይስተዋላሉ። የሚሉት ጉዳዮች ለምርጫ ሰላማዊነት አስፈላጊ ስለሆኑ ሊታሰብባቸው ይገባል የሚሉ አስተያየቶች ሰንዝረዋል። ዶ/ር መሰንበት ለጥያቄዎቹ እና ለአስተያየቶች በሰጡት ምላሽ፤ ወጣቱን ማሳወቅ፤ እንዲሁም ተሳትፎ እንዲያደርግ ማበረታታት ግዴታ እንደሆነና የሁሉም የምርጫው ባለድርሻ አካላት ኃላፊነት እንደሆነ አሳስበዋል። የፓርቲዎችን የጎንዮሽ ፍትጊያ የሚመለከቱ እና የጸጥታ ተቋማት ቅደመ ማስጠንቀቂያዎችን ተጠቅመው የሕዝብን ደኅንነት የማረጋገጥ ክፍተት አለባቸው በሚል ለተነሱ ሐሳቦችም ተፎካካሪ ፓርቲዎች በቅስቀሳ ወቅት የሚፈጥሩትን ፍትጊያ መሠረታዊ ከሆነው የዴሞክራሲ እና የምርጫ እሳቤ ያፈነገጠ ተግባር መሆኑና አንስተው፤ ተግባሩን ማስቆም የሁሉም ግዴታ እንደሆነና የጸጥታ አካላትንም በምርጫ ሰዓት ተገቢውን የሕዝብ ደኅንነት ማስጠበቅ እንዲችሉ የታስክ ፎርስ ተቋቁሞ ቢሠራ፤ እንዲሁም ግጭት ሊፈጠር የሚችልባቸውን ቦታዎች ለይቶ መሥራትም እንደሚገባ አስገንዝበዋል። መረጃ የማጣራትን እና የማረጋገጥን ሥራ (fact checking) ማን ይሥራው? በሚል ለቀረበው ጥያቄ፣ ምርጫ ቦርድ ገለልተኝነቱ የተረጋገጠ ስለሆነ ከሁሉም አካላት በተሻለ ምርጫ ቦርድ ሊሠራው ይገባል ብለዋል። ወ/ሮ ሕይወት በበኩላቸው፣ የወጣቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ ሁሉም በከፍተኛ ሁኔታ መሥራት እንደሚጠበቅበት አሳስበው፤ የምርጫውን ሰላማዊነት ለማስጠበቅ በሚደረገው እንቅስቃሴ ውስጥ የጸጥታ ተቋማት በሕዝቡ ያላቸው ታማኝነት እና ቅቡልነት ቅድሚያ ሊታሰብበት እና ሊሠራበት እንደሚገባ፤ ይህንንም በማድረግ መራጩ ሕዝብ ያለምንም ፍርሃት እና ስጋት በምርጫው እንዲሳተፍ ማድረግ ለምርጫው ሰላማዊነት ወሳኝ መሆኑን አስረድተዋል።

በዚህ የውይይት ፕሮግራም መጨረሻ ላይ ክቡር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ተገኝተው ሐሳብ ሰጥተዋል። በዚህም፣ በምርጫው ላይ የተለያየ ፍላጎት ያላቸው አካላት ከቅርብም ከሩቅም እንደሚገኙ፤ ነገር ግን ኢትዮጵያውያን በመተባበር እና ሰላምን በየአካባቢያችን በማስጠበቅ የምርጫ ባህላችንን አንድ እርምጃ ማራመድ እንደሚጠበቅብን አሳስበው፤ ለዚህም መንግሥት እና ፓርቲያቸው ቁርጠኛ እንደሆኑ፤ ከፍተኛ በጀት ተመድቦም ሁሉንም የሚያሳትፍ እና የሁሉም ድምጽ የሚሰማበት ምርጫ ለማድረግ እየተሠራ እንዳለ ተናግረዋል። ምርጫ ልምምድ እና ሂደት እንደመሆኑ በዚህ ምርጫ ሀገራችንን አንድ እርምጃ በማራመድ ላይ ሁላችንም መሥራት እንዳለብን፤ በዚህ መሠረት ፓርቲያቸውም በምርጫው ቢሸነፍ በማግስቱ

ሥልጣን ለማስረከብ ዝግጁ መሆኑን አሳውቀዋል።

በመጨረሻም፣ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎቹ የማጠቃለያ አስተያየት ሰጥተዋል። በዚህም ዶ/ር መሰንበት፣ ምርጫውን ሰላማዊ ለማድረግ ብዙ መሥራት እንደሚገባን እና ሰላማዊነቱን ከማረጋገጥ በላይም የፖለቲካ ኃይሎች ከምርጫው የሚጠብቁትን (political expectations) ከማሸነፍ እና መሸነፍ ባለፈ ሀገራችን ብዙ የፖለቲካ ችግሮች ያሉባት እንደመሆኗ እነዚያን ችግሮች በዴሞክራሲያዊ መንገድ ለመፍታት አንዱ የምርጫ ባህልን ልምምድ ማሳደግ መሆኑን በመረዳት በዚህ ምርጫ ኢትዮጵያ አንድ እርምጃ ተራምዳ የፖለቲካ ባህላችንን የምናድስበትን መንገድ ታሳቢ እንዲያደርጉ አሳስበዋል። ወ/ሮ ሕይወትም ምርጫው ሰላማዊ እንዲሆን ብዙ ሥራ እንደሚጠብቀን አሳስበዋል። “ምርጫው ሰላማዊ ይሁን” ሲባል “የሐሳብ ትግል አይኑር” ማለት እንዳልሆነ እና የሀገራችንን ምርጫ በሰላማዊነቱ የሚጠቀስ ማድረግ እንደሚቻል ገልጸዋል።






ሰላም


FAKE NEWS
FAKE NEWS
ሰላም እና

## 3.2.2 ክፍል ሁለት፣ በምርጫ ወቅት ሰላምን ለማስፈን ሰላም የሚያጎጹ ሀገር በቀል እና ዘመናዊ ተቋማት ሚና

መጋቢት 21 ቀን 2013 ዓ.ም

ሁለተኛው ክፍል የውይይት ፕሮግራም "በምርጫ ወቅት ሰላምን ለማስፈን ሰላም የሚያጎጹ ሀገር በቀል እና ዘመናዊ ተቋማት ሚና" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው። በዚህኛው የውይይት ክፍለ ጊዜ በሀገራችን ሰላምን ለማስጠበቅ የሚሠሩ ዘመናዊ እና ሀገር በቀል ተቋማት ወይም ሥርዓቶች በምርጫ ጊዜ ምን ሚና ይኖራቸዋል? ተቋማቱ እና ሥርዓቶቹስ የትኞቹ ናቸው? የሚል ሐሳብ ዋና አጀንዳ አድርጎ የተደረገ ውይይት ሲሆን፤ ዶ/ር የራስወርቅ አድማሴ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር የ"ፎረም ፎር ሶሻል ስተዲስ" ዋና ዳይሬክተር እና ዶ/ር ሳሙኤል ተፈራ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአፍሪካና የእስያ ጥናትና ምርምር ማዕከል ረዳት ፕሮፌሰርና በሰላም ሚኒስቴር የሚኒስትር አማካሪ ናቸው። ውይይቱን የመራችው አርቲስት እና ጋዜጠኛ አዜብ ወርቁ ናት።

በምርጫ ወቅት የዘመናዊ እና ሀገር በቀል የሰላም ማስጠበቅ ተቋሞች/ሥርዓቶች ሚና፤

በመጀመሪያ በ"ሀገር በቀል የሰላም እሴቶች" ላይ ንግግር ያደረጉት ዶ/ር ሳሙኤል ተፈሪ ናቸው። በዚህም፣ "ሰላም ለኢትዮጵያውያን ምን ማለት ነው?" የሚለውን በመመለስ ነበር። ሰላም ለኢትዮጵያ ገበሬ በሰላም አርሶ፤ ዘርቶ፤ አጭዶ ልጆቹን አሳድጎ እና ድሮ መኖር ሲሆን፤ ለአርብቶ አደሩ ደግሞ ዝናብ ዘንቦ፤ እንስሳቱን መግቦ እና ነግዶ ያለምንም ግጭት መኖር መቻሉ ነው። ሌላውም በሰላም ወጥቶ ሠርቶ መግባቱን ሰላም በሚል እንደሚረዳው፤ ኢትዮጵያውያን ለሰላም ያላቸውን ጽኑ ፍላጎት ለማንጸባረቅም ከስም አወጣጥ ጀምሮ ሰላም፣ ፍቅር እና መሰል ስሞችን በተለያዩ ቋንቋዎች ውስጥ መስማታችን ማሳያ እንደሆነ አስረድተዋል። በኢትዮጵያ ውስጥ ከሰሜን እስከደቡብ፣ ከምሥራቅ እስከምዕራብ በሁሉም አቅጣጫ የሚኖሩ ማህበረሰቦች የራሳቸው የግጭት መፍቻ ወይንም ሰላምን መጠበቂያ ባህላዊ ተቋሞች/ሥርዓቶች አሏቸው ሲሉ ገልጸዋል። የተለያዩ ማህበረሰቦች የሚጠቀሙባቸውን የግጭት መፍቻ ሥርዓቶችም የተወሰኑትን ዘርዝረው አስረድተዋል። በኦሮሚያ "ስንቄ"፣ በሲዳማ "ሲቆ" ፣ ወደሰሜን ደግሞ ያጠፋ ሰው ቤተክርስቲያን ውስጥ

ደወል የሚደውልበት ሥርዓት፣ በራያ የ"ደባርተ" ሥርዓት እንዲሁም፤ በሐመር ፈጣሪን የሚለምኑበት "ባርጆ አለን" የመሰሉና በሌሎችም ማህበረሰቦች ውስጥ ብዙ ሥርዓቶች መኖራቸውን አንስተዋል። እነዚህን የሰላም መስጠበቂያ ሥርዓቶች ምን ያህሉን እናውቃቸዋለን? ምን ያህሉንስ ከዘመናዊው ሥርዓት ጋር አብረን እንጠቀምባቸዋለን? የሚል ጥያቄ አዘል ሐሳብ አንስተዋል።

በሁሉም ማህበረሰቦች ውስጥ ሰላምን የሚያስጠብቁና ግጭትን የሚያስቀሩ የእርቅ ሥርዓቶች፤ የሽምግልና ባህሎች እንዳሉ እና እነዚህን ባህሎች ለተተኪው ትውልድ በማስረከብ ወጣቱ ከዘመናዊ ሥርዓት ጋር አስተሳስሮ እንዲጠቀምባቸው የሚያስችል እንደሆነ አንስተዋል። ለዚህም፣ በቡራዩ ተነስቶ ለነበረው ግጭት የጋሞ አባቶች ግጭቱን እንዴት ማስቀረትና ሰላምን ማስጠበቅ እንደቻሉ ማሳያ እንደሆነ አመልክተዋል። እነዚህን መሰል ባህላዊ ሥርዓቶች በምርጫ ወቅት እንዴት ልንጠቀምባቸው እና ሰላምን ልናስጠብቅ እንችላለን? ለሚለው የሰላም ሚኒስቴር የሀገር ሽማግሌዎችን፣ የተፎካካሪ ፓርቲ መሪዎችን፣ ምሁራንን፣ የታሪክ ባለሙያዎችን በተለየ መንገድ የማወያየት ሥራ እየተሠራ እንደነበር ገልጸው፤ ዓላማውም የግጭት መንስኤ የሆኑ የታሪክ፣ የፖለቲካና ሌሎች እሳቤዎች ላይ መግባባት ለመፍጠር ያለመ እንደነበር አስረድተዋል። ከላይ የዘረዘርናቸውን ዓይነት የግጭት መፍቻ ሥርዓቶች በአሁኑ ምርጫ ከዘመናዊው ጋር አጣምረን መጠቀም ባንችልም ለቀጣዮቹ ምርጫዎች ተግባራዊ ማድረግ ስለሚገባ እንዴት መጠቀም እንዳለብን ማሰብ እንደሚገባ አሳስበዋል።

ዘመናዊ የሰላም እና የደኅንነት ማስጠበቂያ ዘዴዎችን በተመለከተ ሐሳብ ያቀረቡት ዶ/ር የራስ ወርቅ አድማሴ ደግሞ፤ ሀገር በቀል የግጭት መፍቻ ዘዴዎች ውጤታማ የሚሆኑት ተመሳሳይ ማንነት ያለው የህብረሰተብ ክፍል በሚኖርባቸው አካባቢዎች መሆኑን አንስተው፤ አዲስ አበባን ጨምሮ በትልልቅ ከተሞች እና የግንኙነት መስመሮች ላይ የሚነሱ ግጭቶች በባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገድ መፍታት እንደማይቻል ገልጸዋል። ይህም ብዝኃ ማንነት ያላቸው ሰዎች የሚገኙበት ስፋራ በመሆኑ እንደሆነ አሳስበው፤ በዚህ መሰል ስፍራዎች ብቸኛው የግጭት መፍቻ እና የሰላም ማስጠበቂያ ዘዴ የሚሆነው በሕግ እና በመንግሥታዊ የጸጥታ እና የደኅንነት ተቋማት እንደሆነ አስረድተዋል። በቅድመ ምርጫ ወቅት፣ በምርጫ እና በድህረ ምርጫ ወቅት የሀገር ሽማግሌዎችን በታዛቢነት ማሳተፍ ግጭት የሚፈጥሩ አካላትን ከሕግ ሥርዓት ውጭ በሆነ መንገድ በመገሰጽ፤ በማሳፈር፤ ወ.ዘ.ተ ግጭቱን ሊያስቆሙ ወይም ሊፈቱ ስለሚችሉ ቢሠራበት ተገቢ እንደሆነ አንስተዋል። ከምርጫ በፊት የነበሩ የግጭት ቁርሾዎችን መፍታት ሰላማዊ ምርጫን ለመከወን እንደሚረዳም ጠቁመዋል።

ሌላው የተፎካካሪ ፓርቲዎች ተወካዮች በየአካባቢው ኮሚቴ ፈጥረው የምርጫውን እንቅስቃሴ ከታዛቢዎች ጋር ጭምር ቢሠሩ ሰላም ለማስጠበቅ እንደሚቻል አሳስበዋል። በመጨረሻም፣ በዚህ ዘመናዊ ጊዜ እና ከ100 (አንድ መቶ) ሚሊዮን በላይ ሕዝብ ባለው ሀገር ውስጥ የምርጫንም ሆነ የዜጎችን ሰላምና ደኅንነት የማስጠበቅ ኃላፊነት ያለበት መንግሥት እንደሆነ ገልጸዋል። እንዲሁም፤ ከላይ የተጠቀሱት ባህላዊ የግጭት መፍቻ መንገዶች እድል መስጠት እንዳለበት አሳስበዋል። ለምሳሌም የሸሪዓን ፍርድ ቤት አሠራር አንስተው በመጠቆም በምርጫ ወቅት በሚፈጠር ግጭት መጠቀም ይቻላል የሚል መልዕክት አስተላልፈዋል።

## ከተሳታፊዎች የተነሱ ሐሳቦች

የውይይቱ ተሳታፊዎች የተለያየ ይዘት ያላቸው አስተያየቶች እና ጥያቄዎች አንስተዋል። በዚህም፤ ባህላዊ የግጭት አፈታት ዘዴዎችን በተመለከተ ከምርጫ ግጭቶች በላይ የሆኑ የማህበረሰብ አካላት በግጭት በሚገዳደሉበት ወቅትም እንኳን የበዳይን እና የተበዳይን ቤተሰብ በአንድ አቁመው እንዲስማሙ፤ "ጉልበት አለኝ" የሚልም ከሽማግሌዎች በላይ አለመሆኑን አውቆ የሚዳኝበት ሥርዓት በብዙው የሀገራችን ማህበረሰብ ውስጥ እንደሚታይ አንስተዋል። እነዚህን ባህላዊ ሥርዓቶች በከተማም መጠቀም የማይቻልበት ሁኔታ እንደሌለ፤ በአንዳንድ ከተሞችም ጥቅም ላይ ሲውል እንደሚታይ፤ ይህም ከዘመናዊ ሥርዓት ጋር አጣምሮ ማስኬድ እንደሚቻል ማሳያ እንደሆነ ሐሳብ ተሰጥቷል። ሁለቱን ሥርዓቶች በምናጣምርበት ወይም ባንድ ላይ በምንጠቀምበት ወቅት ግን "በምን ያክል ደረጃ ነው ማጣመር ያለብን?" የሚለው ሊታሰብበት ይገባል። ለዚህም የሀገር ሽምግሌዎች ከመንግሥታዊ አስተዳደር ጋር በተጣመሩ ቁጥር ተቀባይነት እንዳያጡ መታሰብ እንዳለበት ያሳሰቡት አስተያየት ሰጪው፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የመንግሥት ሽማግሌና የሀገር ሽማግሌ በሚል ከመንግሥት ጋር የሚሠሩትን ተቀባይት የማሳጣት ሂደት እየተፈጠረ እንዳለም አስረድተዋል።

በሌላ በኩል ምርጫው ቀኑ እየተቃረበ ቢመጣም ከፌዴራል መንግሥቱ በታች ያሉት የአስተዳደር አካላት እና የጸጥታው ዘርፍ ዝግጅት በታቀደው መሠረት እንዳልሆነ እየታዘብን ነው ብለዋል። ባህላዊ የግጭት መፍቻ ዘዴዎችን ጥቅም ላይ ለማዋል ስናስብ በሕዝቡ ዘንድ ያላቸውን ቅቡልነት ታሳቢ ማድረግ እንደሚገባም ተመልክቷል። የምርጫውን ሰላማዊነት ለማስጠበቅ ሲባል ሕዝቡን ማሳተፍ እንደሚገባም ተሳታፊዎች አሳስበዋል። በዚህም፣ ሕዝቡን የሚወክሉ የሀገር ሽምግሌዎችን፤ እንዲሁም ሌሎች አደረጃጀቶችን በተለያየ መንገድ ተሳታፊ ማድረግ እንደሚገባ፤

ቤተሰብ ልጆቹ ከግጭት እራሳቸውን ኢንዲጠብቁ ማድረግ እንደሚገባው አስተያየት ሰጭዎች አሳስበዋል።

በመጨረሻም ሐሳብ አቅራቢዎቹ የማጠቃለያ ሐሳብ ሰጥተዋል። በዚህም፣ ዶ/ር ሳሙኤል የሃይማኖት አባቶች እና የሀገር ሽማግሌዎች ሰላምን ለማስጠበቅ ከመንግሥትና ከሌሎች ባለድርሻዎችም ጋር መሥራት እንዳለባቸው፤ እንደማህበረሰብ ግን ሁሉም የጉዳዩ ባለቤት እንደሆነ አሳስበዋል። የሰላም ሚኒስቴር ሲሠራቸው የነበሩ ሥራዎችም ሀገራዊ ቁርሾዎችን በዘላቂነት በመፍታት ሰላምን ለማረጋገጥ ያለሙ እንደሆነ አንስተው፤ ለዚህኛው ምርጫ ግን በቶሎ ሊከወኑ የሚገባቸውን ሥራዎች ለይቶ መሥራት እንዳለበት ጠቁመዋል። ዶ/ር የራስ ወርቅ አድማሴም በበኩላቸው፣ የባህላዊ ተቋማትን በታዛቢነት እንዲሳተፉ በማድረግ ችግሮችን ቀድሞ መፍታት እንዲቻል፤ ከፓርቲዎች ተወካይ ኮሚቴዎች፣ በፓርቲ አባላት እና በመሪዎች የሚሠሩትን ሕገ ወጥ ሥራዎች ለመቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት በመፍጠር ከሕጋዊ የሰላም ማስከበርና የደኅንነት ተቋማት ጋር ተጣምሮ መሥራት እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።




ሰላም


ወቅት


አዲስ ወግ
FAKE NEWS
FAKE NEWS
ሰላም እና ደኅንነት በምርጫ ወቅት
MINISTER

## 3.2.3 ክፍል ሦስት፣ ሐሰተኛ መረጃ በሰላማዊ ምርጫ ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መግታት

መጋቢት 22 ቀን 2013 ዓ.ም

የዚህ የሦስተኛው እና የመጨረሻው ክፍል መወያያ አጀንዳ በሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት እና በምርጫ ላይ ስለሚኖረው ተጽዕኖ ሲሆን፤ "ሐሰተኛ መረጃ በሰላማዊ ምርጫ ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ መግታት" የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል። በውይይቱም ሐሰተኛ መረጃዎች ምንድን ናቸው? ከሕግ አኳያ የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት እንዴት ይታያል? የሐሰተኛ መረጃን ሥርጭት ለመከላከል ዓለም አቀፋዊው ተሞክሮ ምን ይመስላል? እና የሃቅ ማጥራት (fact checking) ምንድን ነው? የሚሉና ተያያዥ ሐሳቦች ተነስተውበታል። በዚህ ውይይት የውይይት መነሻ ሐሳብ ያቀረቡት ጋዜጠኛ፣ መምህርና የሚዲያ ሕግ ባለሙያ ሰለሞን ጎሹ እና በጋዜጠኝነት እና ከ"ኮድ ፎር አፍሪካ" ጋር በሚሠራው የመረጃ ማጣሪያ የ"ፔሳ ቼክ" ኮፒ አዲተር ኤደን ብርሃኔ ናቸው። ውይይቱን የመራው ደግሞ የአሜሪካ ድምጽ ሬዲዮ ጋዜጠኛ እስክንድር ፍሬው ነው።

### የሐሰተኛ መረጃ ምንነት እና ጉዳቱ

የመጀመሪያው ሐሳብ አቅራቢ አቶ ሰለሞን ጎሹ በኢትዮጵያ የኢንተርኔት ተደራሽነት ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋ በመምጣቱ እና የፖለቲካ ሽግግሩ በፈጠረው ሐሳብን በነጻነት የመግለጽ መብት መዳበር የሐሰተኛ መረጃዎች ሥርጭት እየጨመረ እና በጉዳት ደረጃም በግለሰቦች እና በሀገር ህልውና ላይ ከፍተኛ አደጋ እየፈጠረ ይገኛል፤ ብለዋል። በቅርብ በወጣው የሐሰተኛ መረጃ ክልከላ አዋጅ መሠረት፤ "ሐሰተኛ መረጃ" ማለት "የመረጃውን ሐሰትነት እያወቀ ያሠራጨ ወይም በሥራ ባሕሪይው አንጻር የመረጃውን ትክክለኛነት ሊያጣራ እና ሊያውቅ ሊገባው የነበረና መረጃው በመሠራጨቱ ጉዳት ካደረሰ" በሚል እንደሚተረጉመው አስታውቀዋል። የሀሰተኛ መረጃ ዓይነቶችንም 1ኛ አሳሳች ይዘትና የውሸት ግንኙነት (Minsinformation) 2ኛ መረጃ ማዛባት (Disinformation) እና 3ኛ መረጃን መበከል (Malinformation) ናቸው፤ ሲሉ አስረድተዋል።

ሐሰተኛ መረጃዎች ከሚያደርሱት ሀገራዊ ጉዳት አንጻር የሀገራችን ሁኔታ ሲታይ፤ የዚህን መሰል መረጃ ሥርጭት የሚያበረታታ ነገር ባይኖርም፤ በሕዝብ ደረጃ መረጃ

አጣርቶ ከመጠቀም አንጻር የሚዲያ ንቃተ ኅሊና (media literacy) ክፍተት እንዳለ እንደሚታወቅ አስረድተዋል። ለዚህም እንደምክንያት የሚቀርበው፤ አንድም የመገናኛ ብዙሃኑ (መደበኛውም ሆነ የማህበራዊ ሚዲያ) በሚያቀርበው መረጃ ላይ ሕዝብ አመኔታ ስለሌለው እና የሕዝቡ ዝቅተኛ የሚዲያ አጠቃቀም ትምህርት መሆናቸውን አንስተዋል። በተጨማሪም፣ የሀገራችን ፖለቲካ ሽግግሩ ባልጸናበት ሁኔታ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ፖለተካ ነክ ሐሰተኛ መረጃዎች ሥርጭት መስፋፋት ከማህበራዊ ሚዲያው ቴክኖሎጂ ውስብስብነት አኳያ ችግሩ እየተባባሰ እንደሚሄድም ማሳያ አድርገው አስረድተዋል። የኢንተርኔት ተደራሽነቱና የማህበራዊ ሚዲያ ተጠቃሚው መብዛት ለሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት ትልቅ ሚና እንዳለውም ጠቅሰዋል። የመደበኛው ሚዲያ ተኣማኒነት መሸርሸር፤ የፖለቲካ ኃይሎች የሐሰተኛ መረጃውን ሥርጭት ለሌላ ዓላማ ማስፈጸሚያነት መጠቀማቸው በሀገራችን ለግለሰቦች ሞት እና ለንብረት መውደም ምክንያት እንደሆነ ገልጸዋል። ይህ የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት በቀጣይ "የኢትዮጵያን የፖለቲካ ሁኔታ ይቀይራል" ተብሎ በሚጠበቀው ስድስተኛውን ምርጫና በመራጩ ሕዝብ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ በማሳደር የምርጫውን ውጤት ችግር ውስጥ ሊጥለውና አጠቃላይ የዴሞክራሲ ልምምዱንና ሽግግሩንም ሊጎዳ እንደሚችል አስረድተዋል።

አቶ ሰለሞን የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት ለመጪው ምርጫ ከፍተኛ ስጋት የሚያደርጉትን ነገሮች ሲያስረዱም፤ የማህበራዊ ሚዲያው የሚጠቀመዉ ሞዴል፣ በሚወጡ ይዘቶች ምንም ዓይነት ቁጥጥር የሌለ መሆኑ፣ ማንነታቸው ያልታወቁ ሰዎችን ማሳተፉ እና ሐሰተኛ መረጃዎችን ለማሠራጨት የሚውሉ "ሶፍትዌሮች" እና "አልጎሪዝሞች" ጥቅም ላይ የመዋል ምልክቶች መታየታቸው እንደሆኑም አብራርተዋል። ይህን ችግር ታሳቢ ያደረገ የመገናኛ ብዙኃንን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚመሩ የሕግ ማዕቀፎች ወጥተዋል። ከማህበራዊ ሚዲያ አቅራቢ ድርጅቶችም ጋር ቁጥጥር ለማድረግ የሚያስችል ሕግ ወጥቷል። ወደፊት የማስፈጸሚያ ደንቦች እና መመሪያዎች እንደሚወጡም አንስተዋል። ሕጉም ሰብዓዊ መብት ተኮር የሆነና ያለብንን ችግር ለመፍታት ያለመ መሆኑንና መቅጣትን የመጨረሻ አማራጭ በማድረግ በማስተማር መከላከልን እና ሃቅ ማረጋገጥን አማራጭ አድርጎ ያስቀመጠ እንደሆነም አስረድተዋል። መፍትሔን በተመለከተም ቅድሚያ ማስተማር፣ ፓርቲዎች ሥነምግባርን አክብረው የመረጃ ፍሰት እንዲያደርጉ፣ ጋዜጠኞችን እና ሚዲያዎችን ማብቃት፤ እንዲሁም የእርስ በርስ ቁጥጥርን የሚያሣድጉ እንደሚዲያ ካውንስል ያሉትን ማህበራት ማጠናከር እና የሃቅ ማጣራትን ሥራ በተቀናጀ መንገድ መሥራት ተገቢ እንደሆኑ አስረድተው፤ ምርጫው ወሳኝ የሽግግር ሂደት መሆኑን ከግንዛቤ

ውስጥ በማስገባት ባለድርሻዎች ሐሰተኛ መረጃን በመከላከል ላይ በንቃት መሳተፍ እንዳለባቸው አሳስበዋል። በተጨማሪም፣ አሁን ካለው ጊዜ አንጻር የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች ቀደም ብለው መሠራት እንዳለባቸው፤ ነገር ግን ከሃቅ ማጣራት ሥራ አንጻር ከአንድ ዓመት ቀደም ብሎ የተጀምሩ ብዙ ፕሮጀክቶች መኖራቸው መልካም ተሞክሮ ነው ብለዋል።

ጋዜጠኛ ኤደን መረጃን ወይም ሃቅን ማጣራት ምንነት በተመለከተ ትንታኔ ሰጥተዋል። በዚህም፣ ሦስት ዓይነቶቹ የሐሰተኛ መረጃዎች እንዳሉ ሆነው፤ ሐሰተኛ የሆነ፣ ከአውድ ውጭ ግንኙነት ያለው፣ የተጭበረበረ፣ የተቀየረ ምስል እና ቪዲዮ፣ የተቀናበረ፣ የፈጠራ ውጤት የተጨመረበት፣ ትንኮሳ፣ የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ ዜና ሁሉ በሐሰተኛ መረጃነት ተፈርጀው መጣራት እንደሚገባቸው አስረድተዋል። እነዚህ ሁሉ "ሐሰተኝነታቸው በማን ይበየን?" በሚለው ጉዳይ ላይ ብዙ መስማማት የሌለ እና አወዛጋቢ እንደሆነ ገልጸዋል። ሐሰተኛ መረጃዎችን የማጣራት ሥራውም ማስረጃን መሠረት አድርጎ በአጣሪዎች እንደሚሠራ፣ "ማን ያሠራጫቸዋል?" ለሚለውም ሁሉም በመረጃ ልውውጥ ላይ ያለ አካል በማወቅም ሆነ ባለማወቅ መረጃዎችን እንደሚያሠራጭ አስረድተዋል።

"ሐሰተኛ መረጃ መቼ ነው በብዛት የሚሠራጨው?" የሚለውንም ሥርጭቱ ሁልጊዜም እንደሚኖርና አብዛኛው የሐሰተኛ መረጃዎች ሥርጭት የሚታየው ግን በውጥረት፣ በግጭት፣ በምርጫና መሰል ጊዜያት እንደሆነ ገልጸዋል። እንደማሳያም በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ወቅት በሀገራችንም "ነጭ ሽንኩርት እና ዝንጂብል የመሰሉ ነገሮች መድሐኒት ናቸው" የሚል መረጃ በስፋት ሲሠራጭ እንደነበር፤ ይህንንም የኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት "ይህ መረጃ ሰዎች እራሳቸውን ከበሽታው እንዳይከላከሉ ያደርጋል" በሚል ሐሰተኛ መሆኑን ጠቅሶ ማስተካከያ መረጃ ሲሰጥ እንደነበር አስታውሰዋል። በምርጫ ወቅት ብዛት ያላቸው አካላት ተሳትፎ እንደማድረጋቸው መጠን ብዛት ያለው የመረጃ ልውውጥ ስለሚኖር በዚህ ወቅት የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት በምርጫ ውጤት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድርበት እድል ሰፊ ነው። በዚህና መሰል ወቅቶች የመረጃ እጥረት ለሐሰተኛ መረጃዎች ሥርጭት ሚና ይኖረዋል ተብሏል። የተለመዱ የኢንተርኔት መሠረተ ልማቶችን መዝጋትም ተገቢ እንዳልሆነና በሌሎች የግንኙነት ዘዴዎች የሚደረገውን የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት እንደሚያባብስ፣ እንዲሁም የመደበኛ ሚዲያው እና የመንግሥትን ተአማኒነት የሚያሳጣ ተግባር እንደሆነ ተገልጿል። በመረጃ ማጣራት ወቅት ከይዘት በተጨማሪም የቃላት አጠቃቀም እራሱ ሐሰተኛ መረጃን ሊያስፋፋ ስለሚችል ጥንቃቄ መደረግ

እንዳለበት፣ ኅብረተሰቡም የሚደርሰውን መረጃ “ለምን ለእኔ ደረሰኝ?” ማለት እና ከሁለት፣ ሦስት ምንጮች ማረጋገጥ እንዳለበት አሳስበዋል።
“ሐሰተኛ መረጃን እንዴት እንከላከለው?” ለሚለውም ጥያቄ ጋዜጠኛ ኤደን ሐሰት ከሰው ልጅ ጋር አብሮ ያለ ነገር እንደመሆኑ ሐሰተኛ መረጃም እንዲያ እንደሚሆን በማንሳት መረጃ በማጥራት ሥራ ላይ ሁሉንም ሐሰተኛ መረጃ ማጣራት እንደማይቻል፤ ነገር ግን የጉዳት መጠናቸው ከፍተኛ በሆኑት ላይ እንደሚሠራ፤ በአጠቃላይ ግን ዋነኛው መከላከያ የኅብረተሰብን የሚዲያ አጠቃቀም ንቃተ ኅሊና ማሳደግ፣ የተቋማትን ዲጂታል ተገኝነት ማሳደግ (digital presence) እና የመደበኛ ሚዲያው ደግሞ ይህን በማስተማር ቀዳሚው መሆን እንደሚገባው አስረድተዋል።

## ከተሳታፊዎች የተነሱ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች

መደበኛ ሚዲያዎች ከመሠረታዊ ዓላማቸው ወይም ከባለቤትነት ጋር በተያያዘ ሐሰተኛ መረጃዎችን ሊያስተላልፉ እንደሚችሉ ታሳቢ ማድረግ ያስፈልጋል። በሌላ በኩልም፣ በአሁኑ የሀገራችን ፖለቲካ ብሔርተኝነቱ በጋዜጠኛውም ላይ የራሱ ጫና ሊኖረው ስለሚችል ጋዜጠኛውን ማመጣጠን ይገባል። ከመንግሥት በኩልም ትክክለኛው መረጃ በተገቢው ሰዓት ሊቀርብ ይገባል የሚሉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል። በተጨማሪም፣ ሐሰተኛ መረጃን ለመከላከል ሃቅን በማጥራት ሥራ ላይ እንደሀገር የተጀመሩ ነገሮች ቢኖሩም ውስን መሆናቸውን በማንሳት ሥራው ምርጫ በመጣ ወይም ችግር በተፈጠረ ቁጥር የሚሠራ ሳይሆን በመደበኛነት እንዲሠራ ለማድረግ ማን በምን አቅም ይሥራው የሚለውን ረጂሙ መንገድ ሊታሰብ ይገባል ተብሏል። “ጋዜጠኛው ሃቅን እያጣራ መረጃ ለሕዝብ ያድርስ” ካልንም ተያይዘው ለሚነሱ የአቅም እና የበጀት ጥያቄዎች ማሰብ እንደሚገባ ተጠቁሟል። “የሐሰተኛ መረጃ ሥርጭትን ሃቅን በማጥራት እንከላከለዋለን የሚለው አተያይ ሁሌም ልክ ነው” በሚለው እሳቤ ላይ ላይሆን የሚችልበት እድል ሰፊ መሆኑን በመገንዘብ ጥንቃቄ እንዲደረግ፤ የመረጃ ትንተና በመሥራት ሊከሰቱ የሚችሉ የመረጃ መዛባቶችን ቀድሞ አውቆ ሕዝቡንም እንዲጠነቀቅ ማድረግንም እንደአንድ መፍትሔ ሊታሰብበት እንደሚገባ እና ሐሰተኛ መረጃዎችን ለማረጋገጥ ምንጭ መኖሩ ብቻ በቂ መሆን እንደሌለበት፤ ምንጮችንም መመርመር እንደሚገባ የሚያሳስቡና በምሳሌ የተደገፉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

ከተሳታፊዎች ለተሰነዘሩ አስተያየቶችና ሐሳቦች ምላሽ ሲሰጥም፤ በጸደቀው ሕግ ላይ ሃቅን የማጥራት እና ሐሰተኛ መረጃን በፍጥነት የማስወገድ ሥራ

የሚዲያ “ፕላትፎርሞች” እንደሚሠሩ ይደነገጋል። መንግሥት ይህን ለማስፈጸም እንደሚሠራም ያትታል። ለሚዲያው እና ለጋዜጠኛው የአቅም ግንባታ መስጠትም የጥቅም ግጭት ውስጥ እንዳይገቡ ሊታሰብ ይገባል። የሙያ እና የኑሮ ደረጃቸውን ማስተካከልም ሊታሰብበት እንደሚገባ፤ እንዲሁም በሕጉ ላይ የምርጫን ወቅት ታሳቢ በማድረግ አንዳንድ ትእዛዞች የሚፈጸሙበት የጊዜ ገደብ አጭር ሆኖ እንደተዘጋጀ አቶ ሰለሞን አስታውቀዋል። መደበኛ ሚዲያዎችም በአንጻራዊነት ነው እንጂ ፍጹም ከሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት የጸዱ ናቸው ማለት አይቻልም። ሃቅን ማጥራት አንድ አካል ብቻ ይሥራው ተብሎ የሚሰጥ ጉዳይ ባይሆንም ምርጫን በተመለከተ ግን ተገቢው ሥልጣን ያለው ምርጫ ቦርድ ቢሠራው የሚል ሐሳብ ሰጥተዋል። ጋዜጠኛ ኤደንም የብሮድካስት ባለሥልጣን ለሚዲያዎች ፈቃድ በሚሰጥበት ጊዜ የሃቅ ማጣሪያ ቡድን ማቋቋምን እንደሌሎች መስፈርቶች ቢያየውም ጥሩ እንደሆነ አሳስበዋል።

በመጨረሻም፣ በምርጫ ወቅት ፓርቲዎችና መሪዎቻቸው በሐሰተኛ መረጃ ሥርጭት እንዳይሳተፉ ወይንም በስማቸው የሐሰተኛ መረጃ እንዳይሠራጭ፤ የማህበራዊ ሚዲያ አካውንቶቻቸውን የተረጋገጡ እንዲያደርጉ መሠራት እንዳለበት እና ኅበረተሰቡም የሚደርሱትን መረጃዎች ምንጮች የማረጋገጥ ልምድ በማዳበር እራሱን እንዲከላከል ማሳሰቢያ ተላልፏል።








FAKE NEWS
ሰላም እና ደኅንነት በምርጫ ወቅት
FAKE NEWS
Ethiopia

# 3.3 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ በዴሞክራሲ አንድ እርምጃ፣ የ6ኛው ብሔራዊ ምርጫ ምልከታዎች

ሐምሌ 14 ቀን 2013 ዓ.ም




ይህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም ሰኔ 14 ቀን 2013 ዓ.ም ከተደረገው ስድስተኛው ብሔራዊ ምርጫ በኋላ የተደረገ "የአዲስ ወግ" ፕሮግራም ሲሆን፤ "በዴሞክራሲ አንድ እርምጃ፣ የ6ኛው ብሔራዊ ምርጫ ምልከታዎች" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው። በዚህ መድረክ ከምርጫው በፊት በ"አዲስ ወግ አንድ ጉዳይ" እና በ"አብይ ጉዳይ" በምርጫ ወቅት ሰላም እና ደኅንነት ዙሪያ፣ እንዲሁም "ፈተናዎች እና መልካም እድሎች" ላይ የተደረጉ ውይይቶች ለምርጫው በስኬት መጠናቀቅ የነበራቸው አበርክቶ ተዳስሷል። ከዚህ በተጨማሪም በምርጫው ከፍተኛ ሚና የተጫወቱ አካላት አስተዋጽዖም ታይቷል። በምርጫው የታዩ መልካም ጎኖችና የተገኙ ልምዶች፤ እንዲሁም ጉድለቶች ተነቅሰው ወጥተው ለሚቀጥሉት ጊዜያትና ምርጫዎች ትምህርት በሚሆኑበት መንገድ ላይ ውይይት ተደርጓል።

በውይይቱ ላይ የመነሻ ሐሳብ ያቀረቡት አቶ ሲሳይ ቶላ የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ ፕሮፌሰር ካሳሁን ብርሃኑ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካ ሳይንስ መምህርና የአስተዳደር ወሰንና ማንነት ኮሚሽን አባል እና ዶ/ር ንጉሱ አክሊሉ የ"ዴስትኒ ኢትዮጵያ" መሥራች ሲሆኑ፤ ውይይቱን የመሩት አቶ ሰይፈ ደርቤ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር ናቸው።

በቅድሚያ ፕሮፌሰር ካሳሁን ብርሃኑ፣ "የምርጫ ቦርድ እና ሌሎች አጋር አካላት ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ ያስቻላቸው ምንድን ነው?" በሚለው ጥያቄ ላይ ትኩረት አድርገው ሐሳብ አቅርበዋል። በዚህም በለውጡ ማግስት እንደአዲስ የተመሠረተው የብሔራዊ ምርጨ ቦርድ ውጤታማ እንዲሆን ያስቻሉት ነገሮች ናቸው በሚል ሦስት ነጥቦች አስቀምጠዋል። የመጀመሪያው የቦርዱ አባላት በሕዝብ ጥቆማ ተመርጠው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በተወካዮች ምክር ቤት እንዲጸድቁ የሚያስችል ሥርዓት መዘርጋቱ፤ ሁለተኛው መልማይ ኮሚቴ በገለልተኝነት እንዲመሠረት መደረጉ እና ሦስተኛው በቀረቡት እጩዎች ላይ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከተፎካካሪ ፓርቲዎች ጋር ምክክር ማድረጋቸው እንደሆኑ አንስተዋል። ይህም የምርጫ ቦርድን እንደአዲስ ለመመስረት ጥቅምት 2012 ዓ.ም የወጣውን አዲስ አዋጅ ጨምሮ የቦርዱን አባላት ለመምረጥ የተሄደበት አዲስ አሠራርና አካሄድ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው እና ተአማኒ እንዲሆን እንዳስቻለው አስረድተዋል። በይበልጥ ደግሞ ቦርዱ ከተመሠረተ በኋላ በሕግ እና በአፈጻጸሙ ላይ የታየው መጣጣም ለምርጫው ውጤታማነት እና ለቦርዱም ተቀባይነት ከፍተኛ ድርሻ ነበራቸው ብለዋል።

የፖለቲካ ሥርዓቱ ወይንም አዲሱ አመራር ከፍተኛ የለውጥ ፍላጎት እና ፈቃደኝነት ያለው መሆኑ፣ የሕግ ማሻሻያ ማድረጉ፤ እንዲሁም በምርጫ አስፈጻሚ አካላት አመላመል እና አሰያየም ላይ ሰፊ ተቀባይነት ያላቸውን ግለሰቦች በሙያ፣ በልምድ እና በተቀባይነት መስፈርት መሠረት ማካተቱ፤ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት መቋቋሙ የምርጫው መልካም ልምምዶች እንደሆኑ ተጠቅሰዋል። በመጨረሻም፣ መንግሥት የሲዳማን የክልልነት ጥያቄ ተከትሎ መሰል ጥያቄዎችን በአፋጣኝ መፍታት ለሀገራዊ ሰላም የሚኖረውን ሚና ማወቅ በመቻሉ በሲዳማ የሕዝበ ውሳኔ መደረጉ ምርጫ ቦርድ ልምድ የገነባበት መሆኑ ለምርጫው ስኬታማነት ድርሻ የነበራቸው ጉዳዮች ናቸው በሚል ፕሮፌሰር ካሳሁን ዘርዝረዋል።

ፕሮፌሰር ካሳሁን በምርጫው ሂደት ላይ ታይተዋል ያሏቸውን ችግሮች ሲተነትኑም፤ የቁሳቁስ አቅርቦት ችግር በመጠኑ እንደነበር፤ አንዳንድ ያልተገቡ ጣልቃ ገብነቶች መታየታቸው፣ ውጤትን ከምርጫ ቦርድ ውጭ የመተንበይ ሙከራዎች መታየታቸው፣ የምርጫ ጣቢያዎችን ከምርጫ ሰዓት በፊት የመክፈት አዝማሚያ መታየቱ፤ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት በሚመደብላቸው የሥራ ማስኬጃ በጀት ላይ ፍትሐዊ የሀብት ክፍፍል እንዲኖር የሚያስችል ሥርዓት አለመኖሩ በችግርነት የሚታዩ ነገሮች እንደነበሩ አስረድተዋል። የምርጫ ቦርድ በቅድመ ምርጫ መዋቅር የመዘርጋት ሥራ መሥራቱን፤ ፓርቲዎችን መመዝገቡን፤ የምርጫ አስፈጻሚዎችን መመልመሉን፤ ለመራጩ ስለምርጫ ትምህርት መስጠቱን፤ የመራጮች ምዝገባ፤ በፓርቲዎች መካከል የነበሩ ውዝግቦችን በሕግ መሠረት አይቶ ውሳኔ መስጠቱ፤ የሀብት ክፍፍል ማደረጉን፤ እንዲሁም በትግራይ ክልል ከፌዴራል መንግሥት ውጭ የተደረገውን ምርጫ ማገዱን አንስተዋል። ቦርዱ በምርጫው እለት፣ የተጓደሉ የምርጫ ካርዶች በአፋጣኝ እንዲሟሉ ማድረጉ፤ በምርጫ ሰዓት እጥረት ምክንያት ይታዩ ለነበሩት ከፍተኛ ሰልፎች የምርጫ ሰዓት እንዲራዘም ማድረጉን ገልጸዋል። በድህረ ምርጫ ወቅትም ቦርዱ፣ ቅሬታዎችን በመስማት የተለያዩ ማስተካከያዎች ማድረጉን፣ ከሲቪክ ማህበራት እና ሌሎች ገለልተኛ ተቋማት የተገኙ የሕግ ባለሙያዎች ለቦርዱ ውሳኔ የሚያግዝ ሐሳብ እንዲያቀርቡ ያደረገበት ሥርዓት መኖሩ፤ የሲቪክ ማህበራት በምርጫው ትምህረት በመስጠት እና በታዛቢነት እንዲሳተፉ ማድረጉን አስረድተዋል።

በምርጫው ወቅት ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የነበሩ ግንኙነቶችን አስመልክተውም፤ ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለምርጫ ማስፈጸሚያ የሚውል ድጋፍ እንዲገኝ መደረጉን፣ የአፍሪካ ህብረት 60 (ስድሳ) ታዛቢዎችን ልኮ የምርጫውን ሁኔታ እንዲታዘብ እና አስተያየት እንዲሰጥ ማድረጉን በበጎ አንስተው፤ የአውሮፓ ኅብረት በሰሜኑ የሀገራችን ክፍል ያለውን ሁኔታ በቅድመ ሁኔታነት በማንሳት በምርጫው ለመታዘብ ፍቃደኛ አለመሆኑንም አንስተዋል። በአጠቃላይ ለወደፊት በሚደረጉ ምርጫዎች ላይ ትኩረት በሀገር በቀል እና አህጉራዊ ድርጅቶች ላይ መሆን እንደሚገባው አሳስበዋል። ይህን ማለት ግን ከተቀረው ዓለም ጋር የሚኖረን ግንኙነትም ችላ ሊባል እንደማይገባው ጠቁመዋል።

“በምርጫው ሰላማዊነት እና ደኅንነት ዙሪያ ምን ምን ስኬት ተገኝቷል? ለወደፊቱስ ምን እንማርበታለን?” በሚለው ሐሳብ ላይ የመወያያ ሐሳብ ያቀረቡት የብሔራዊ መረጃና ደኅንነት አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሲሳይ ቶላ፣ በስድስተኛው

ሀገራዊ ምርጫ የጸጥታው ዘርፍ ትልቁ ትኩረት የነበረው ይህ 37.4 (ሠላሳ ሰባት ነጥብ አራት) ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን የሚሳተፉበት እና ከ49 (ዐርባ ዘጠኝ) ሺሕ በላይ የምርጫ ጣቢያዎች ላይ የሚደረገውን ምርጫ ሕዝቡ ያለምንም ችግር በሰላማዊ መንገድ እንዲያካሂድ ማስቻል እንደነበር አንስተዋል። በተጨማሪም፣ የጸጥታ እና የደኅንነት መዋቅሩ በሦስቱም የምርጫው ምዕራፎች ያከናወናቸውን ሥራዎች አሳይተዋል።

በተጨማሪም፣ በቅደመ ምርጫ ወቅት ምርጫው ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ ለማስቻል ሥራ የመለየት እና የማቀድ፣ የስምሪት ሥራ መሥራታቸውን፣ ሀገራዊ እቅድ በማቀድ ከባለድርሻ አካላት ጋር መግባባት ላይ መደረሱ፣ የደኅንነት እና የጸጥታ ኮሚቴ ማቋቋም፣ በተጨማሪም ልዩ የምርመራ ኮሚቴ፣ በፍርድ ቤት በኩል ልዩ ችሎቶች ማቋቋም እና የዳኞች ምልመላ መካሄዱ፣ በምርጫው ለሚሳተፉ ጸጥታ አካላት በምርጫ ሕጎች እና በጸጥታው ዘርፍ ገለልተኝነት ዙሪያ ሥልጠና መስጠቱ፣ የምርጫ ቁሳቁሶችን ማቅረብ፣ ማድረስና ደኅንነት ማስጠበቅን፣ እንዲሁም የብሔራዊ ደኅንነት ስጋትን መሠረት ያደረገ የጸጥታ አካላት ስምሪት ማድረግ እንደተቻለ፤ ስጋት በነበራቸው ስፍራዎች መከላከያ እንዲመደብ፤ መለስተኛ ስጋት ያለባቸው ስፍራዎች  ደግሞ በፌዴራል ፖሊስ ሰላማቸው እንዲጠበቅ በማድረግ ቀሪው በአካባቢ ባሉ የጸጥታ ኃይሎች እንዲሠራ እንደተደረገ አስረድተዋል። በቴክኖሎጂ ዝግጅትም የመረጃ ቅብብሎሽ የሚያሳልጡ እና ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ዝርጋታዎች በቅድመ ምርጫ ወቅት መደረጋቸውን አቶ ሲሳይ አስረድተዋል።

በምርጫው ጊዜም በሁሉም ምርጫ በሚደረግባቸው የሀገሪቱ ክልሎች የምርጫው ሂደት እንዳይታወክ፤ የምርጫው ተሳታፊዎች ደኅንነታቸው እንዲጠበቅ፤ የምርጫ ጣቢያዎች እና ቁሳቁሶች እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳያጋጥም፤ ቅሬታዎች እንዲፈቱ በማድረግ ምርጫውን ስኬታማ ማድረግ እንደተቻለ አስረድተዋል። አቶ ሲሳይ ምርጫው ዴሞክረሲያዊና ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ያስቻሉ ነገሮችን ሲይስረዱ ሦስት መሠረታዊ ነጥቦች አንስተዋል። የመጀመሪያ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሕጋዊ መንገድ  መሳተፋቸው እና መንቀሳቀሳቸው፤ ሁለተኛው የሕዝቡ ነጻ፣ ዴሞክራሲያዊ እና ሰላማዊ  ምርጫ እንዲካሄድ የነበረው ፍላጎት፤ ሦስተኛው መንግሥት የሥልጣን ሽግግር ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ቁርጠኝነቱ ስለነበረው እንደሆነ ገልጸዋል።

በሦስተኛነት ንግግር ያደረጉት ዶ/ር ንጉሱ አክሊሉ የወክሉት Multi stock-holder initiative for national dialogue Ethiopia (MIND) ስምንት የኢትዮጵያ ድርጅቶች ጥምረት መሆኑን አስረድተዋል። እርሳቸውም፣ ባለፉት ሦስት ዓመታት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ለውጥ አንቅስቃሴዎች ላይ የተስተዋሉ፤ ለወደፊት የኢትዮጵያ ሰላማዊነት እና ዴሞክራሲን ባህል ለማሳደግ የተደረጉ የሚመስገኑ ያሏቸውን ተግባራት አንስተዋል። እነዚህም፣ የሲቪል ማህበረሰብ ሕግ መለወጡ፤ በሚዲያው ላይ የሚታይ ለውጥ መደረጉና ምህዳሩ መስፋቱ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ መሰባሰብ መቻላቸው፤ የምርጫ ቦርድ እና የኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ከፍተኛ ለውጥ ማድረጋቸው እንደሆኑ አንስተዋል። በምርጫው ሂደት የተስተዋሉ ጠቃሚ ተሞክሮዎች ናቸው በሚልም የሕዝቡን ለምርጫና ለዴሞክራሲ ግንባታ የነበረውን ቁርጠኝነት አንስተዋል። የምርጫ ቦርድ፣ የጸጥታ አካላት እና ሚዲያው ያሳዩት ገለልተኝነት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ኃላፊነት ተሰምቷቸው እራሳቸውን ለውይይት ማዘጋጀታቸው፤ ሁሉም ሚዲያዎች እና የሲቪክ ማህበራት የምርጫ ክርክሮችን ተደራሽ በማድረግ መራጩ ሕዝብ መረጃ እንዲያገኝ ማስቻላቸው፤ እንዲሁም የሲቪክ ማህበራት መራጩን ማስተማራቸው እና በታዛቢነት መሳተፋቸው፤ እንደነበሩ አሳይተዋል። በመጨረሻም፣ “ከዚህ ምርጫ ለቀጣይ ሁሉም ችግር በምርጫ እንደማይፈታ በማወቅ ከክርክር ወደትብብር መሄድ እንደሚገባ አሳስበዋል።

## የተሳታፊዎች አስተያየት እና ጥያቄዎች

ተሳታፊዎች በሰጧቸው አስተያየቶች በቅድመ ምርጫ ወቅት በሕዝብ ውስጥ ብጥብጥ ወይም የፖለቲካ ቀውስ ሊፈጠር ይችላል የሚል ስጋት እንደነበርና ምርጫው በሰላም መጠናቀቁ ከምርጫ በኋላ ያለው ሁኔታም አስተማማኝ መሆኑ በጣም እንዳስደሰታቸው ገልጸዋል። በዚህም ኢትዮጵያዊ ጭዋነት የታየበት ምርጫ እንደነበር፤ ሕዝቡ ምን ያህል ሰላም ፈላጊ እንደነበር የታየበት፤ የፖለቲካ ፓርቲዎችም በሐሳብ እና በውይይት የሚያምኑ መሆናቸውን ያሳዩበት እንደነበርም ገልጸዋል። በቀጣይም የተመረጡ ሰዎች ፓርላማ ገብተው የሕዝብን ድምጽ በአግባቡ እንዲያሰሙ ለማድረግ መከታተል እንደሚጠበቅ አስታውቀዋል። በተጨማሪም፣ ኢትዮጵያ የዴሞክራሲ ግንባታዋን በራሷ ማሳደግ እንደምትችል ያሳየነብት ምርጫ እንደነበር እና አንድ እርምጃ መራመድ የታቻለበት እንደሆነ፤ ይህም ሲባል ገለልተኛ እና ነጻ ተቋማት ገንብተን ያሳየንበት፤ ሕዝቡም ከምርጫ ውጭ ሌላ መንገድ ወደሥልጣን እንደማያመጣ በቁርጠኝነት ያሳየበት እና ቀጥሎ የምናደርጋቸው ምርጫዎች ከዚህ በላይ የምንራመድባቸው እንደሚሆኑ ተስፋ የታየበት መሆኑን ገልጸዋል።

ከዓለም አቀፍ አጋሮች እና የምርጫ ታዛቢዎች ጋር የሚኖረን ግንኙነት ምን መምሰል እንደሚገባው ለቀረበው ጥያቄ ፕሮፌሰር ካሳሁን ምላሽ ሲሰጡ፤ ምርጫው ከጉድለት ነጻ ነው የሚል እምነት እንደሌላቸውና ጉድለት ቢኖርበትም ግን መሻሻል የሚችሉ ጉዳዮች እንዳሉ አውስተዋል። የአውሮፓ ኅብረት በሰሜን ኢትዮጵያ የነበረውን ሁኔታ ያማከለ ቅድመ ሁኔታ በማቅረብ ታዛቢ እንዳልላከ አንስተው፤ ይህም ከሀገር ሉአላዊነት ጋር ተያይዞ መታየት እንዳለበት ገልጸዋል። ነገር ግን፣ ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚኖረው ግንኙነት መቋረጥ እንደሌለበት፤ የምርጫ ተአማኒነት ደግሞ ለመራጩ ሕዝብ ለኢትዮጵያውያን ብቻ መሆኑን ታሳቢ ማድረግ እንደሚገባ እና ለኢትዮጵያውያን ተአማኒ በሆነ ምርጫ ላይ ትኩረት ማድረግ እንደሚገባ አሳስበዋል።

አቶ ሲሳይም  በተነሱ ሐሳቦች ላይ ምልከታቸውን ሲሰጡ፤ ከምርጫ በፊት ሕዝቡ ስጋት ላይ እንደነበር አንዳንድ የውስጥ እና የውጭ አካላትም ምርጫ አስፈላጊ እንዳልሆነ፤ በድርድር ሥልጣን እንዲሰጣቸው ሲሞክሩ የነበሩ አካላት እንደነበሩ፤ ነገር ግን ሕዝቡ “ሥልጣን በምርጫ ብቻ መገኘት አለበት” የሚል እምነቱ ምርጫው ሰላማዊ ሆኖ እንዲጠናቀቅ እንዳደረገ፤ የምርጫ ቦርድ ገለልተኝነት እንደሀገር፣ ሕዝብ እና መንግሥት ለዴሞክራሲ እና ለተቋም ግንባታ ቁርጠኝቱን ያሳየበት እንደነበር፤ ለምርጫው ስኬትም ቦርዱ ትልቅ ድርሻ እንደነበረው አንስተዋል። በምርጫው ላይ የታዩ በቀጣይ ልንማርባቸው የሚገቡ ጉዳዮችን መረጃ ተቋማቸው አደራጅቶ ለምርጫ ቦርድ እንደሚያቀርብም አሳውቀዋል።








የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# ክፍል አራት፣

# የአዲስ ወግ መድረኮች

# 2014 ዓ.ም

# 4.1 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ በአዲስ መንፈስ አዲስ ውል

መስከረም 19 ቀን 2014 ዓ.ም




ይህ "የአዲስ ወግ" ፕሮግራም በኢትዮጵያ አዲስ ጅማሮ ከሆነው ሰላማዊ ሽግግር ከተስተናገደበት የስድስተኛው የብሔራዊ ምርጫ በኋላ የተደረገ የመጀመሪያው የአዲስ ወግ የውይይት ፕሮግራም ሲሆን "በአዲስ መንፈስ አዲስ ውል" በሚል ርዕስ ላይ ትኩረቱን አድርጎ ተካሂዷል። የውይይቱ ዓላማም "ከውስጥ እና ከውጭ የተጋረጡብንን ፈተናዎች ተቋቁመን ብቁ የጸጥታ እና የደህንነት ተቋማት እንዴት እንገንባ? ፣ "ከእርዳታ የተላቀቀ ኢኮኖሚ እንዴት እንገንባ?" ፣ "የመንግሥት አገልግሎት ሙያ ባላቸው እና የአገልጋይነት መንፈስ በተላበሱ ብቁ ባለሙያዎች እንዴት ይሰጥ?" እንዲሁም፣ "ብሔራዊ መግባባትን በማምጣትና በመተባበር የችግር መፍቻ ዘዴዎችን እንዴት ልንፈጥር እንችላለን?" በሚሉ አራት ጥያቄ አዘል ነጥቦች ላይ ውይይት ለማድረግ ነው።

በውይይቱ በመነሻ ሐሳብ አቅራቢነት (የቀድሞ) የጠቅላይ ሚኒስቴር ጽሕፈት ቤት ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ፍስሐ ይታገሱ፣ የመከላከያ ግንባታ የጥናት እና ምርምር

ማዕከል ዳይሬክተር ኮሎኔል ፍቅረ ኢየሱስ ከበደ፣ የፕላንና ልማት ኮሚሽን ሚኒስትር ዶ/ር ፍጹም አሰፋ እና የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ኮሚሽነር አቶ በዛብህ ገብረየስ (የቀድሞ) የተገኙ ሲሆን፤ ውይይቱን የመሩት የኢትዮ ኢንጂነሪንግ ዋና ሥራ አስፈጻሚ ኢንጂነር ሕይወት ሞሲሳ (የቀድሞ) ናቸው።

## ብሔራዊ መግባባት ላይ እንዴት እንድረስ?

በመድረኩ የመጀመሪያውን እና በብሔራዊ መግባባት ላያ ያተኮረውን የውይይት መነሻ ሐሳብ ያቀረቡት አቶ ፍስሐ ይታገሱ ናቸው። እርሳቸውም፣ የሀገር ግንባታ የሚቆምባቸው ሦስት መሠረታዊ መዋቅሮች እንዳሉ አንስተዋል። የመጀመሪያው ነጻ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው ተቋማት መኖር፤ ሁለተኛ በሕዝብ እንዲሁም በልሂቃን መካከል በሀገራዊ ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ መግባባት መኖር፤ ሦስተኛ የዴሞክራሲ ግንባታ ሂደት ደረጃ ናቸው። የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታ ሲያሳዩም ተቋማት ነጻ እና ገልልተኝ ሆነው ባለመገንባታቸው ብዙ ዓይነት ብልሹ አሠራሮች ይታያሉ። በዋና ዋና ሀገራዊ ጉዳዮች፣ በሕገ መንግሥት ፣ በሰንደቅ ዓላማ እና በሌሎች ጉዳዮችም መግባባት የለም። ይህም ላለፉት ሦስት ዓመታት ለብዙ ችግሮች ሲዳርገን ነበር ብለዋል።
እነዚህን ችግሮች ለመፍታት ብሔራዊ መግባባት እንደሚያስፈልግ፤ ብሔራዊ መግባባት ላይ ለመድረስ ደግሞ መደመር፣ ይቅርታ እና የወንድማማችነት እሳቤ አስፈላጊ እንደሆነ ታምኖበት እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል። ይህም ብዝኃ ማንነት ያለባት ሀገር ባለቤት እስከሆንን ድረስ ችግሮቻችንን በዴሞክራሲያዊ መንገድ ብቻ ሊፈቱ ስለማይችሉ የአንዳችን ችግር የሁላችንም በመሆኑ በወንድማማችነት መርህ መተያየትና መነጋገር አስፈላጊ እንደሆነ አሳስበዋል። “ብሔራዊ መግባባት” ሲባል ልዩነትን መጨፍለቅ ሳይሆን ልዩነቶችን ያከበረ አንድ የፖለቲካ ማህበረሰብ መገንባት እንደሆነ፤ የብሔር ማንነቶች ከኢትዮጵያዊ ማንነት ጋር በጋራ ታርቀው መቆም እንዲችሉ ማድረግ እንደሚገባ፤ ብዙ ጽንፍ የያዙ ሐሳቦች ሀገርን ለብተና አደጋ ስለሚዳርጉ እንደሆነም አስታውቀዋል።

አካታች ብሔራዊ ውይይት ብሔራዊ መግባባት ለማምጣት የመፍትሔ መንገድ መሆን እንደሚገባም ጠቁመዋል። በዚህ ውይይት አጀንዳዎች ከፖለቲካ ልሂቁ ሳይሆን ከሕዝብ የሚመጡበት፤ እንዲሁም ውይይቱ በኢትዮጵያውያን የሚመራ መሆን እንዳለበትና የሐሳብ እርቅ ተደርጎ በቀጣይ ትውልድ ላይ ከፍተኛ ሥራ መሠራት እንዳለበት አሳስበዋል። በዚህ በአዲስ የመንግሥት ምስረታ ሂደት ላይ ለሁሉም፣ በሁሉም እና ከሁሉም የሆነች ሀገር መገንባት ላይ በማተኮር ተቃዋሚውንም ያካተተ መንግሥት መመሥረቱ ለብሔራዊ መግባባቱ አንድ እርምጃ ወደፊት መሆኑንም

አመልክተዋል።

## የመከላከያ ሪፎርም እና የሀገረ መንግሥት ግንባታ

ሁለተኛው የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢ ኮሎኔል ፍቅረ ኢየሱስ ከበደ ከሀገረ መንግሥት እሳቤ ጋር የሚያያዙ ነጥቦችን በማንሳት ጀምረዋል። የአንድ ሀገር የሀገረ መንግሥት ግንባታ እንዲሳካ ብሔራዊ ጥቅሞች ማለትም የዲፕሎማሲው፣ የመረጃ እና ደኅንነቱ፣ የኢኮኖሚው እና የመካላከያ ኃይሉ የሀገሪቱን ኅልውና፣ ሉአላዊነት እና ብሔራዊ ጥቅም ሊያስከብሩ እንዲችሉ ተደርገው በትክክለኛ መንገድ መመስረት እና መገንባት አለባቸው። የአንድ ሀገር የመከላከል አቅም በሁለት ተከፍሎ ይታያል። አንደኛው ለስላሳ አቅም የሚባለው፤ የሞራል ልእልና (ሥነልቦናን ያካትታል) ሁለተኛው ጠንካራ አቅም የሚባለው፤ ይህ ደግሞ ወታደራዊ አቅም (የምድር ኃይል፣ የባሕር ኃይል፣ የአየር ኃይል፣ የሳይበር አቅምን እና የህዋ ላይ አቅምንም ይጨምራል) የሀገራት መከላከያ ኃይል ሁለቱንም አቅሞች አካትቶ ይገነባል። መከላከያ የተገዳዳሪ ኃይሎችን እና የአደጋ ስጋት ትንተና በመሥራት፤ ያለንበትን የጸጥታ ምህዳር (security environment) ባገናዘበ መልኩ ይገነባል። ኢትዮጵያ የምትገኝበት ከባቢም በጣም ተለዋዋጭ እና ኢተገማች ነው። በመሆኑም፣ የምንጠቀመው ጠንካራ አቅም ወይም የመሣሪያ ኃይል እና ለስላሳ ኃይል በሚል የገለጽናቸውን የሥነ ልቦና ኃይሎች አጣምረን እንደሆነ አስረድተዋል። ከለውጡ በኋላ እየተገነባ ያለው ሠራዊት ገለልተኛ አቅምና ብቃት ያለው ሠራዊት ነው። ይህም ገለልተኛነቱ ፕሮፌሽናል ሠራዊት እንዲሆን እንዳስቻለው አሳውቀው፤ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 87 መሠረት መከላከያው የሁሉም የኢትዮጵያ ብሔሮች እና ብሔረሰቦች ውክልና እንዲኖረው ተደርጎ የተገነባ እንደሆነና ትንሿን ኢትዮጵያን እንደሚመስል አስረድተዋል።

የመከላከያ ሠራዊቱ እንደተቋም ከሲቪሉ አስተዳደር ጋር ያለው ግንኙነትም በአዲስ መልኩ እንደተቃኘ፤ በፊት ይታይ የነበረውን የፖለቲካ ኃይሉን ጣልቃ ገብነት በማስቆም ወጥ የሆነ የቁጥጥር ሥርዓት እንዲኖር ተደርጓል። የሠራዊቱን ቀጣይነትም ለማረጋገጥ እንዲቻል በየጊዜው ከወቅታዊ ሁኔታዎች እና ዓለም አቀፍ ክስተቶች ጋር አብሮ ሊያድግ የሚያስችለው ሥርዓትም ታሳቢ ተደርጎ እየተገነባ እንዳለና ግንባታው ሲጠቃለልም ጠላት ኢትዮጵያን ለማጥቃት ከመሞከሩ በፊት ደጋግሞ እንዲያስብ የሚያደርግ የ (Deterrence) አቅም እና ጦርነትን በአነስተኛ መስዋዕትነት እና ጊዜ መፈጸም የሚችል፤ የኢትዮጵያን ዳር ድንበር በጽኑ የሚያስከብር፤ ዓለም አቀፋዊ ተወዳዳሪ የሆነና በሀገራዊ አደጋ ጊዜ ዜጎችን ለመታደግ ቀድሞ የሚደርስ

መከላከያ እንደሚሆን አስረድተዋል።

## የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ከመንግሥት ምስረታ አንጻር

በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ሐሳብ ያቀረቡት ዶ/ር ፍጹም አሰፋ ባለፉት ዓመታት የተደረጉ የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች ፍሬ፤ እንዲሁም ያጋጠሙ ተግዳሮቶችን አስታውሰው ምንም እንኳን በፈታኝ ሁኔታ ውስጥ የተደረገ ምርጫ ቢሆንም በኢኮኖሚው ዘርፍ የተጀመሩ የማሻሻያ ሥራዎችን ታሰቢ በማድረግ ሕዝቡ ድምጹን እንደሰጠ አንስተዋል። አዲስ የሚመሠረተው መንግሥትም ማህበራዊ ፍትህ የማረጋገጥ፤ ልማትን ፍትሐዊ በሆነ መልኩ የማዳረስ ሥራ እንደሚሠራና የሕዝብን ተሳትፎ እና ተጠቃሚነትም እንደሚያሳድግ፤ ፍትሐዊ የኃብት ክፍፍል ለማረጋገጥ፤ ትምህርትን ለሁሉም ለማዳረስ እና ለወጣቱ የሥራ እድል ለመፍጠር እንደሚሠራ አስረድተዋል። ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ለማስመዝገብ በግብርናው እና በሌሎችም ሴክተሮች የተጀመሩ ሥራዎች ተጠናክረው ይቀጥላሉ። እንዲሁም፣ በኢኮኖሚ እድገት ውስጥ የማክሮ ኢኮኖሚ መዛነፍ እንዳይፈጠር የኑሮ ውድነትን ለማስተካከል፤ ፍላጎትን እና ምርትን ለማጣጣም እንደሚሠራና ጥብቅ የገንዘብ ፖለሲ ቁጥጥርም እንደሚተገብር ገልጸዋል።

ከላይ የተቀመጡት ግቦች እዲሳኩም መንግሥት የፖሊሲ እና የሕግ ማዕቀፎችን ያወጣል። ኢኮኖሚውን ይመራል፤ በኢኮኖሚው ውስጥ ጤናማ ውድድር እንዲኖር ያደርጋል። በግሉ ዘርፍ የማይሸፈኑትን የመሠረተ ልማት ሥራዎች ይሠራል። የከባቢ አየር ብክለትን በመቆጣጠር ላይም ይሠራል። የተረጋጋ የኢኮኖሚ ሁኔታ እንዲፈጠር የማድረግ ኃላፊነቱን ይወጣል። እንዲሁም፣ የምዕራቡ ዓለም ሀገራት በሀገራችን ላይ እያደረጉት ያለውን ሁለንተናዊ ጫና ተቋቁሞ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት እንዲመጣ ይሠራል፤ ብለዋል። ለዚህም፣ የብዙ ዘርፍ ስትራቴጂ እንደሚከተል ጠቅሰዋል። ከዚህም በተጨማሪ፣ ፍትህዊ ተጠቃሚነተን የማረጋግጥ፤ የግሉን ዘርፍ ተሳትፎ የማሳድግ፤ በምግብ እራስን የሚያስችሉ ተግባራት በመሥራት ብልጽግናን ማረጋገጥ እንደሚጠበቅበትም ተናግረው፤ አዲስ የሚመሠረተው መንግሥት ከሕዝብ ጋር ተባብሮ የሚሠራ እንደሆነና ለግቦቹ መሳካት የሕዝቡ ቀና ተሳትፎም አስፈላጊ እንደሆነ አመልክተዋል።

## የሰው ኃይል እና የተቋማት ግንባታ

በዚህ ርዕስ ንግግር ያደረጉት አቶ በዛብህ ገብረየስ ሲሆኑ፤ እሳቸውም ኢትዮጵያውያን የሥራ ስንፍና እና የተቋማት ደካማነት ችግር እንዳለብን አንስተዋል። መንግሥት የሚንቀሳቀሰው በተቋማት በኩል ለሕዝብ በሚሰጠው አገልግሎት ሆኖ እያለ ስንፍናው

ጎልቶ የሚታየው በመንግሥት ተቋማት ላይ ነው ብለዋል። ተቋማት የሰዎች፣ የሕጎች፣ የአደረጃጀቶች፣ እና የአሠራር ሥርዓት ጥምር ውጤቶች ናቸው። ተቋማት ብቁ የሚባሉት የሠለጠነ ብቁ የሰው ኃይል እና ቴክኖሎጂ ሲጠቀሙ እንደሆነና የሚመሠረቱትም የሚንቀሳቀሱትም በሕግ እንደሆነ ገልጸዋል።

የተቋሞቻችን መገለጫ የሆነው የመልካም አስተዳደር ችግር በመዋቅሮች መካከል ጥምረቱ ሲላላ፣ ውል ባልተገባበት ሙያ እና ፍላጎት ሲደበላቅ፤ ማለትም ፖለቲካው እና የመንግሥት ሥራ ሲቀላቀል፤ በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሲቪክ ማህበራት የግል ባለሃብቶች እና መንግሥት በጋራ የሚሠሩባቸው ሁኔታዎች ሲጠፉ፤ እንዲሁም የሀገር እና የሕዝብ ጥቅም ተገቢውን ትኩረት ሲያጣ ሊከሰት እንደሚችል አስረድተዋል። በመሆኑም፣ የኢትዮጵያ መንግሥት ተቋማት ነጻ፣ ገለልተኛ እና ብቃት ያላቸው፤ ተገቢውን ሥራ መሥራት የሚያስችሉ ሕጎች ያሏቸው፤ በሕግ የሚመሩ መሆን አለባቸው። ለዚህም፣ የሠራተኞችን የኑሮ ሁኔታ እና የሥራ አካባቢ ምቹ ማድረግ፤ እንዲሁም የመንግሥትን እና የፖለቲካን ሥራ መለያየት፤ ለሕዝብ የሚገባውን አገልግሎት መስጠት እንደሚገባ አስረድተዋል።

## የተሳታፊዎች አስተያየት፣ ጥያቄዎች እና የተሰጡ ምላሾች

አራቱ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች ጽሑፋቸውን ካቀረቡ በኋላ ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት፤ መንግሥት ለግል ሴክተሩ በተለይ ለአምራች ኢንዱስትሪዎች ድጋፍ ማድረግ አለበት። ከውጭ የሚገቡ አምራች አንዱስትሪዎችም በምርት ሂደታቸው ከፊል ምርቶችን በራሳቸው ከሚያመርቱ ይልቅ ለሌሎች የሀገር ውስጥ ድርጅቶች እንዲሰጡና የሥራ እድል እንዲፈጥሩ በመንግሥት በኩል ድጋፍ እንዲደረግ ይጠበቃል። በአዲሱ መንግሥት በተቋማት ላይ ተጠያቂነትን ማስፈን እንደሚጠበቅ እና ዜጎችን በማሠልጠን የበቃ የሰው ኃይል የማምረት ሥራ ላይ ትኩረት መደረግ እንዳለበትም ተነስቷል። የመከላከያው ግንባታ እንዳለ ሆኖ በውስጥ ለሚፈጠሩ ልዩነቶች ምን ዓይነት ዘዴ ተጠቅመን መፍታት እንዳለብን ማሰብ እና መሥራት ይገባናል። ሪፎርሙን በክልሎች ላይ ቅድሚያ ተሰጥቶት መሠራት አለበት የሚሉትን ነጥቦች አንስተዋል።

በሌላ በኩል፣ ሜቴክን የመሰሉ ኢኮኖሚውን የሚጎዱ ተቋማት እንደነበሩን እና ብዙ ሀገራዊ ጥፋት እንዳስከተሉ ይታወቃል። አሁንስ እነዚህን መሰል ተቋማት ስለአለመኖራቸው ምን ያህል እርግጠኛ ናችሁ? የዐሥሩ ዓመት እቅድ በጦርነቱ ምክንያት እርምት ይደረግበታል ወይ? የብዝኃ ኢኮኖሚ ሲባል ምን ማለት ነው?

የፖለቲካውን እና የመንግሥትን አስተዳደር ለመለየት የተሠራ ሥራ አለ ወይ? የመንግሥት ሠራተኛው አገልጋይ እንዲሆን እና ከምንም ዓይነት ወገንተኛነት እንዲጸዳ ምን ተደርጓል? በመከላከያ ላይ በብሔር ተዋጽኦ መሠራቱ ልክ አይደለም፤ እዚህ ላይ ምን ታስባላችሁ? የኢኮኖሚ እድገቱ ሥራ ካልፈጠረ ምን ፋይዳ አለው? የሚሉ ጥያቄዎችም ቀርበዋል።

አቶ ፍስሃ ይታገሱ ከተሳታፊዎች ለተነሱት አስተያየቶችና ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ፤ በቀጣዩ አምስት ዓመት አዲሱ አስተዳደር በትውልድ ላይ እንደሚሠራ፤ ብዙ ተቋማትን ለማስተካከል እየተሠራ ቢሆንም ውጤት እየተገኘ እንዳልሆነ፤ በተለይ የሲቪል ሰርቪሱ ከፍተኛ ችግር እንዳለበት፤ ለማስተካከልም ፈታኝ እንደሆነና ዘርፉን መለወጥ ቀጣይ የትኩረት አቅጣጫ እንደሆነ አንስተዋል። በአሁኑ ወቅት በአስከፊ ሁኔታ ወደጦርነት እንደተገባ ገልጸው ጦርነቱን በጥበብ በመምራት ሀገርን ከመፍረስ ማዳን መቻሉን ገልጸዋል። በአጠቃላይ በዚህ ምርጫ ወደፊት አንድ እርምጃ መራመድ እንደተቻለ አንስተው፤ ሁሉም ችግሮቻችን በምርጫ የሚፈቱ ባይሆኑም በዚህ መልኩ ዴሞክራሲያዊ መንገድን መከተል ሌሎች ችግሮቻችንም ለመፍታት እንደሚጠቅም አሳስበዋል።

ኮሎኔል ፍቅረ ኢየሱስ በበኩላቸው፣ "ትውልድ በምን እና በማን መታነጽ አለበት?" የሚለውን ስናስብ ልጆች ኢትዮጵያዊ እሴቶችን አውቀው እንዲያድጉ ለማድረግ ከቤተሰብ ጀምሮ እንደማህበረሰብ የትምህርት ሴክተሩንም ጨምረን ልንሠራ ይገባል ብለዋል። ይህም በእድሜ ያደገው የማህበረሰብ አባል ለልጆች ምሳሌ ሆኖ መገኘትን የሚጠይቅ እንደሆነ አሳስበዋል። ከብሔር ተዋጽዖ ጋር ለተነሳው ጥያቄም የሠራዊቱ አደረጃጀትና ሪፎርም የብሔር ውክልናውን ብቻ ታሳቢ ተደርጎ ሳይሆን የብቃት ደረጃቸውም ታይቶ ሁለቱን በማመጣጠን እንደሚሠራ፤ ይህም በሕዝብ ዘንድ የእኔነቱ መንፈስ እንዲሰርጽ፤ እንዲሁም በግዳጅ አፈጻጸም ብቃት ላይ መከላከያው ከሕዝብ መረጃ የማግኘት እና አብሮ የመሥራት ቁመናውን በማሳደግ ውጤታማ እንደሚያደርገው ገልጸዋል።

ዶ/ር ፍጹም ኢኮኖሚውን አስመልክቶ ለተነሱ ጥያቄዎች መልስ ሲሰጡ፤ የ10ሥር ዓመት እቅድ ክለሳ ላይ ለተነሳው ጥያቄ ከእቅዱ በኋላ የተከሰተው ጦርነት ውስብስብ ኢኮኖሚያዊ ሁኔታዎችን የፈጠረ ቢሆንም፤ እቅድ ሲታቀድ የሚይዘው የአደጋ ጊዜ መቋቋሚያ ስትራቴጂዎች መኖራቸውን ገልጸው እነሱንም ጥቅም ላይ ለማዋል እየተሞከረ እንዳለ አስረድተዋል። የኢኮኖሚው ከፍተኛ ፈተና በሆነው የውጭ

ምንዛሬ ግኝት ላይም የተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ እንደዋሉ አሳይተዋል። “ብዝኃ ኢኮኖሚ” በሚል ለተነሳው ጉዳይም ኢትዮጵያ ትልቅ አቅም ያላት ሀገር እንደመሆኗ፤ ኢኮኖሚያችንን በአንድ ዘርፍ ላይ ብቻ እንደማንገነባ፤ የብዝኃ ተሳትፎ ሲባልም መንግሥት ብቻ ከሚዘውረው ኢኮኖሚ ሥርዓት ወደግሉ ዘርፍ የሚመራ ኢኮኖሚ እንዲሆን መንግሥት የቁጥጥር ድርሻውን እንዲወጣ ለማድረግ እንደሚሠራ፤ ለዚህም የግሉን ዘርፍ በማብቃት እንደሚያግዝ፤ የግሉ ዘርፍም በአጭር ጊዜ ትርፍ ከሚያስገኙ ዘርፎች ባለፈ የረጅም ጊዜ ሥራ የሚጠይቁ እና ቀጣይነት ባላቸው ጠንካራ የምርት ወይም የንግድ ሴክተሮች ላይ መሳተፍ እንደሚገባው አሳስበዋል።

በመጨረሻ አቶ በዛብህ በሀገረ መንግሥት ግንባታ ላይ የሲቪል ሰርቪሱ ሚና ከፍተኛ እንደሆነ ጠቁመው ከአዲሱ መንግሥት ምስረታ በኋላ ተቋማት ተገቢ ሥራቸውን ለመሥራት በሚያስችል አቋም እንደገና እንደሚዋቀሩ፣ መንግሥትም በራሱ የሚሠራውን እና የማይሠራውን ለይቶ እንደሚያስቀምጥ፤ ይህም ከብዝኃ ኢኮኖሚ ግንባታ ጋር በቀጥታ እንደሚያያዝ፤ ሲቪል ሰርቪሱን የመቆጣጠር ሥራ (check andbalance) የሚሠሩ ተቋማት በነጻነት እና በሙሉ አቅማቸው እንዲንቀሳቀሱ እንደሚደረግ፤ በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ በሕዝቡ የሚነሱትን ቅሬታዎች ለመመለስ የአገልግሎት አሰጣጡ ከሰዎች ንክኪ ርቆ በይነ መረብን መሠረት ያደረገ እንዲሆን እንደሚደረግ፤ የመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ፖሊሲ እንደሚወጣ፤ እንዲሁም ሲቪል ሰርቪሱ ብቃትን (merit) መሠረት ያደረገ የሰው ኃይል ምደባ እንደሚከተል አስታውቀዋል።






Federal Democratic Republic of Ethiopia
OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# 4.2 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፤ የኅልውና ጥሪ እና ሀገርን የማዳን ርብርብ

ኅዳር 2 ቀን 2014 ዓ.ም




የዚህ አዲስ ወግ መድረክ ትኩረት የህወሓት የሽብር ቡድን በኢትዮጵያ መከላከያ ሠራዊት ላይ የክህደት ጥቃት ከሰነዘረበት ከጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ጀምሮ ኢትዮጵያ የገጠማትን የውስጥ እና ውጭ ጫና ተቋቁሞ ለማሸነፍ በሚደረገው ሀገራዊ የኅልውና ጥሪ ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን በህዳር 2፣ 2014 ዓ.ም ተካሂዷል። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ ከውስጥ ከሃዲዎች እና ከውጭ አጋሮቻቸው ከፍተኛ የኅልውና አደጋ ተደቅኖባታል። በዚህም፣ ከውስጥ በመደበኛ ጦርነት በሽብርተኛው የህወሓት ኃይል ተከፍቶባታል። ከውጭ ኢ-መደበኛ የሆነ የተቀናጀ የጦርነት ዘመቻ በታሪካዊ ጠላቶቿ፣ እንዲሁም በምዕራባውያን ሀገሮችና ድርጅቶች ተከፍቶባታል። በዓለም አቀፍ ሚዲያዎችም ከፍተኛ የሐሰት መረጃ የማሠራጨት ዘመቻ ተከፍቶባታል። እንዲሁም፣ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ጦርነቱን ሰበብ በማድረግ ከፍተኛ የምጣኔ ኃብት ጫና ውስጥ እንድትገባ እየሠሩ ይገኛሉ።

የዚህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም ዋና ዓላማም ኢትዮጵያ ከላይ በተዘረዘሩት እና ሌሎች ጫናዎች ውስጥ ሆና ኅልውናዋን ለማረጋገጥ እያደረገችው ባለው ትግል ዜጎች እንዲሁም ትውልደ ኢትዮጵያውያን እና የኢትዮጵያ ወዳጆች ምን ይጠበቅባቸዋል?

በሚለው ሐሳብ ላይ ለመመከር እና መፍትሔ ለመጠቆም ነው።
በዚህ መድረክ የመወያያ ሐሳብ አቅራቢዎች ዶ/ር ቢቂላ ሁሪሳ፣ በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት የዴሞክራሲ ሥርዓት ግንባታ ማዕከል አስተባባሪ ሚኒስትር (የቀድሞ) እንዲሁም ኮሚሽነር እንደሻው ጣሰው፣ የብሔራዊ መረጃ እና ደኅንነት አገልግሎት ምክትል ዳይሬክተር ጄነራል ናቸው። የውይይቱ መሪ ጋዜጠኛ መታሰቢያ ቀጸላ ናት።

የመጀመሪያው የውይይቱ ሐሳብ አቅራቢ ዶ/ር ቢቂላ ሁሪሳ ኢትዮጵያ በታሪክ አጣብቂኝ ውስጥ ገብታ የኅልውና አደጋ ገጥሟት የነበረበትን ዘመን አስታውሰው፤ ባላፉት ታሪኳ በልጆቿ ብርቱ ክንድ እና መስዋዕትነት አደጋዎችን ሁሉ አልፋ ክብሯን አስጠብቃ እንደኖረች አስረድተዋል። የታሪክ አጋጣሚ ሆኖ የዚህ ትውልድ ኢትዮጵያውያንም ህወሓት የተባለው የውስጥ ጠላት በሀገራችን ላይ የደቀነውን የኅልውና አደጋ ለመጋፈጥ ተገድደናል። ህወሓት ኢሕአዴግ ሥልጣን ይዞ ኢትዮጵያን ይመራ በነበረበት ወቅት መንግሥታዊውን ሥልጣን ተጠቅሞ የኢትዮጵያውያንን አንድነት በእምነት እና በተለያዩ ትርክቶች ሲያፈራርስ እንደኖረና የኢትዮጵያውያንን አንድነት መጥፋት ዓላማ አድርጎ በስፋት ይሠራ እንደነበር አብራርተዋል።

አሁን የገጠማት አደጋም ኢትዮጵያን እንደሀገር መቀጠል እና ያለመቀጠል የሚወስን እንደሆነ አሳስበው፤ ህወሐት ኢትዮጵያን ለማጥፋት ሁለት ስልቶች እየተጠቀመ እንደነበር አንስተዋል። አንደኛው በሥልጣን በነበረበት ወቅት ኢትዮጵያን እነርሱ እንደፈለጓት ረግጦና በዝብዞ መግዛት ሲሆን፤ በ2010 ዓ.ም በከፍተኛ የሕዝብ ቁጣ ከሥልጣን ሲወገዱ ይህ ህልማቸው ባለመሳካቱ በሁለተኛው እቅዳቸው፤ ማለትም መቀሌ መሽገው “እኛ ያልመራናት ኢትዮጵያ መፍረስ አለባት” በሚል በኃይል ኢትዮጵያን ለማፍረስ ከሁለት ዓመታት በላይ የሠራዊት፣ የመሣሪያ እና የዲፕሎማሲ ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተው ጥቅምት 24 ቀን 2013. ዓ.ም በመከላከያ ሠራዊት የሰሜን እዝ ላይ ታሪክ ይቅር የማይለው ክህደት ፈጽመዋል። ኢትዮጵያን የማፍረስ ጦርነትም በግልጽ ጀምረዋል። የኢትዮጵያ የውጭ ታሪካዊ ጠላቶች፤ እንዲሁም በቀጣናው ላይ የራሳቸው ፍላጎት ያላቸው ምዕራባውያን ሀገራትም ኢትዮጵያ ጠንካራ ኢኮኖሚ እንዳይኖራትና በውጭ እርዳታ ጥገኛ እንድትሆን ካላቸው ፍላጎት የተነሳ በራሷ አቅም እየገነባች ያለውን የሕዳሴ ግድብ፤ የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራ ለማደናቀፍ ሲሉ እና እነሱ የሚዘውሩት የአሻንጉሊት መንግሥት ለማስቀመጥ፤ ከህወሓት ጋር አብረው እየሠሩ እንደሆነ አብራረተዋል።
የህወሓት የሽብር ቡድን መቀሌ መሽጎ የትግራይን ሕዝብ ከሌላው ኢትዮጵያዊ ወንድሙ ለመለየት ሐሰተኛ ትርክቶችን ሲፈጥር እንደነበርና በተለያየ የሀገሪቱ

ክፍሎችም በተከፋይ ቡድኖች አማካይነት ግጭት ሲያስፋፋ፤ ሕዝብን ከሕዝብ ሲያጋጭ እንደነበር አስታውሰዋል። አሁንም መንግሥት የጀመረውን ሕግ የማስከበር ርምጃ አቁሞ ለትግራይ ሕዝብ የጥሞና ጊዜ ለመስጠት እና ገበሬው ፋታ እንዲያገኝ በሚል ያደረገውን የተናጠል የተኩስ አቁም በመግፋት በአማራና በአፋር ክልል ያደረሰው የሰብአዊ፣ ቁሳዊ እና ሥነ ልቦናዊ ውድመት የዘር ማጥፋት እንደሆነና የዓለም አቀፉ ማህበረሰብም ይህን ተግባር ለማለባበስ ሲሞክር፤ አንዳንዶች ለዚህ ቡድን ድጋፋቸውን ሲያሳዩ፤ ሌሎች ደግሞ ይህን ወንጀል ባለማውገዝ ቡድኑን መተባበራቸውን አንስተዋል።

በዚህ ሁሉ ጫና መካከል ለሀገሩ ቀናኢ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በሀገሩ ላይ የተጋረጠውን አደጋ በመመከት የአርበኝነት ተግባር እንደፈጸመ ገልጸዋል። የመንግሥት ሀገርን የማዳን ጥሪም ሦስት ሐሳቦች እንዳሉት ጠቁመው፤ የመጀመሪያው ዝመት እንደሆነ፤ ይህም አቅሙና ጤንነቱ ያለው ሀገሩን ለማዳን እንዲዘመት፤ ደጀን ሆኖም ሠራዊቱን እንዲያግዝ እንደሆነ፤ ሁለተኛው ጠብቅ፤ አካባቢህን ከጸጥታ እና ከደኅንነት አካላት ጋር ተባብረህ ከሽብርተኛ፣ ከመሣሪያ አዘዋዋሪ እንዲጠብቅ እንደሆነና ሦስተኛው ደግሞ ደግፍ እንደሆነ፤ ይህም ሠራዊቱን በገንዘብ፣ በቁሳቁስ፣ በስንቅ፣ ደም በመለገስ እንዲሁም መረጃ በመስጠት እንዲደግፍ ጥሪ እንደተደረገ አስረድተዋል። በጥሪው መሠረት ኢትዮጵያውያን ያለምንም ልዩነት ከሁሉም የሀገሪቱ አቅጣጫዎች ወጣቱ ወደዘመቻ እየተመመ እንደሆነና ከየአካባቢውም ድጋፍ እየተደረገ እንደሆነ ገልጸዋል። በዚህ መሰል የኢትዮጵያውያን አርበኝነት ተግባር የኢትዮጵያ ሉአላዊነት ሳይደፈር እንደሚቀጥል ሐሳባቸውን አጋርተዋል።

የውይይቱ ሁለተኛ ሐሳብ አቅራቢ ኮሚሽነር እንደሻው ጣሰውም የተከፈተብን ጦርነት ዘርፈ ብዙ እንደሆነና እንዴት ከመከላከል ወደአጥቂነት መሻገር እንዳለብን ሐሳባቸውን አጋርተዋል። ህወሓት ከምዕራባውያን ኃይሎች ጋር በጋራ ተቀናጅቶ ኢትዮጵያን በማጥቃት ላይ እንደሚገኝ ገልጸው፤ በሥልጣን ላይ በነበረት ወቅት በተለያየ የዓለም አቀፍ ተቋማት ውስጥ የራሱን ቅጥረኞች ሲያስገባ እንደነበር፤ አሁን ላይም እነዚህ ቅጥረኞች ያሉባቸውን ዓለም አቀፍ ተቋማት ተጠቅሞ የኢትዮጵያን ስም የማጠልሸት ሥራ በተቀናጀ መንገድ እየሠራ እንደሚገኝ፤ በማሳያም ትላልቅ መገናኛ ብዙኃን እንደአልጀዚራ እና ሲኤንኤም ያሉ ሚዲያዎችም የዚህ ቡድን ድብቅ አጀንዳ ማስፈጸሚያ ሆነው እያገለገሉ እንደሚገኙ፤ እንዲሁም በሀገር ውስጥም ለዚህ ተግባር የሚያግዟቸው እንዳሉ አስረድተዋል።

ይህ የተደራጀ ኃይል በዋናነት ከአካላዊ ጦርነቱ ይልቅ በሐሰተኛ መረጃ ሕዝብን

በማሸበር ተግባር ላይ እየሠራ እንደሚገኝ አንስተዋል። የዓለም አቀፉን ማህበረሰብም ነጭ ውሸቱን እንዲያምን እየሠራ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ለአብነትም ለዓለም አቀፉ ማህበረሰብ ምንም እርዳታ እንዳልደረሰ እየተናገረ፤ በጎን ግን እርዳታ ለማድረስ ወደትግራይ የተላኩ ከመቶ በላይ ተሽከርካሪዎችን አግቶ ለጦርነት አገልግሎት እያዋለ እንደሚገኝ፤ የገባውንም የሰብዓዊ ርዳታ ቁሳቁስ ለሠራዊቱ እየተጠቀመ እንደሆነ፤ የትግራይን ሕዝብ ለቡድናዊ ዓላማው መጠቀሚያ እያደረገው እንደሚገኝም አብራርተዋል። ይህ ጦርነት እተደረገ ያለው ኢትዮጵያን አፈርሳለሁ ብሎ አቅዶ ከተነሳ ሽብርተኛ ጋር ሀገርን ለማዳንና የኢትዮጵያን ህልውና ለማስቀጠል እንደሆነ አንስተው፤ እነርሱ እንደሚሉት አንድ ቡድን ለማጥፋት እንዳልሆነ ተናግረዋል፡ ፡ በመጨረሻም፣ ይህን የተቀናጀ ዘመቻ ለመመከት እና አጥቂ ለመሆን የሚስችሉ ሦስት ነጥቦችን አጋርተዋል። የመጀመሪያው ሕዝቡ ከመንግሥት የሚያገኘውን መረጃ በአግባቡ በመቀበል ለሌሎችም እንዲደርስ ማድረግ እና ከመንግሥት የሚሰጡ እቅጣጫዎችን ተግባራዊ ማድረግ እንደሚገባው፤ አካባቢውንም ነቅቶ መጠበቅ እንዳለበት፤ የሽብርተኛው ቡድን ወኪሎች በማህበራዊ ሚዲያ ከሚያሠራጩት መረጃ እራሱን እንዲጠብቅ እና የእነርሱን መረጃም ከማዛመት እንዲቆጠብ፤ በሁለተኛ ደረጃ የኢትዮጵያ ወዳጅ ሀገራት በዓለም ላይ እየተሠራጨ ስላለው ሐሰተኛ መረጃ እንዲረዱ እውነተኛ እና የተደራጀ መረጃ በየወቅቱና በአግባቡ እንዲደርሳቸው ማድረግ፤ በሦስተኛ ደረጃም አውቀው መሳሳት የሚፈልጉ፤ አውቆ አጥፊዎች ያሏቸው ቡድኖች የሐሰተኛ መረጃዎችን የሚጠነስሱም የሚያዛምቱም በመሆናቸው በተለያየ የዘመናዊ ሚዲያ አውታሮች (የራሳቸውን ሚዲያ ጨምሮ) ለሚያሠራጩት ሐሰተኛ መረጃ ኢትዮጵያውያን በሙሉ ምላሽ እንዲሰጡና በማህበራዊ ሚዲያ ላይም እንዲሞግቱ አሳስበዋል።

## የጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ መልዕክት

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ በዚህ አዲስ ወግ ውይይት ላይ ተገኝተው ስለ አጠቃላይ የጦርነቱ ሁኔታ መረጃ ሰጥተዋል። ለኢትዮጵያውያንም መልዕክት አስተላልፈዋል። በዚህም፣ ግጭቱ የተጀመረው በጥቅምት 24ቱ የመከላከያ ጥቃት እንዳልሆነ፤ በዚህ ጊዜ ነው የተጀመረው ብለን ካሰብንም የግጭቱን ምሉእ እይታ እንደማናገኝ እና ለሰላማዊ መፍትሔዎችም ጠቃሚ እንደማይሆን አሳስበዋል። ግጭቱ መዋቅራዊ ቅራኔዎች የፈጠሩት እና የጥቅምት 24ቱ ጥቃት የመጨረሻ ወደሆነው ጦርነት ያስገባው ሁኔታ እንደሆነ፤ ዋናው መንስኤ ግን ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት፤ የኢትዮጵያውያንን አንድነት ለመበታተን፤ በጋራ መኖር እንዳይችሉ ለማድረግ ቀደም ብሎ ሲሠራ የነበረ ሥራ እንደሆነና በአሁን ላይ ኢትዮጵያን የማፍረስ ፍላጎት ላይ

ደርሶ በግልጽ አቅደው መሥራታቸው እንደሆነ ገልጸዋል።

ይህ ኢትዮጵያን የማፍረስ ሐሳብ ሲጀመር የጥቂት ቡድኖች እንደነበር በሂደት ግን ብዙዎች ሀገር ለመዝረፍ ሲሉ እየተሳተፉበት እንዳሉ፤ ሀገር የመዝረፉን የተቃወሙትን የማሳደድ፤ የማሰር፤ እንዲሁም የተለያዩ ከሰብዓዊነት የወጣ ግፍ ሲያደርስ የነበረ ቡድን እንደነበር፤ ለዝርፊያ ዓላማው ሲልም ሕዝብን ከሕዝብ በማጣላት ሥራ ተጠምዶ እንደነበር ገልጸዋል። በዚህም፣ በአማራ እና በቅማንት፣ በኦሮሞ እና በሶማሌ፣ በወላይታ እና በሲዳማ፣ በመተከል፣ እንዲሁም በቡራዩ ኢትዮጵያውያንን እርስ በእርስ ለማፋጀትና ሀገር ለማፍረስ፤ የሕዝቦችን በራስ የመተዳደር መብት በኃይል ሲከለክል እና የታሪክ ሽሚያ ውስጥ ገብቶ ብዙ ሲሠራ እንደነበር አብራርተዋል። ይህ ሁሉ ተግባሩ እና ሀገር የማፍረስ ውጥኑ አልሳካ ሲለው ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም ያሠለጠናችን፤ አስታጥቆም ሥልጣን የሰጣቸውን ኃይሎች አሰማርቶ ሀገሩን በሚጠብቀው መከላከያ ላይ የክህደት ጥቃት አደረሰ። ይህን የክህደት ተግባር ኢትዮጵያ በታሪኳ አይታው የማታውቅ እንደሆነ አስረድተዋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በጦርነቱ ገጽታ ላይ ማብራሪያ ሲሰጡም፤ ጦርነቱ የሥነልቦና ጦርነት በከፍተኛ ሁኔታ ያካተተ ነው። ጦርነቱ የማጭበርበር ጦርነት ነው። ለዚህም የተለያዩ ሐሰተኛ መረጃዎች በማሠራጨት ሕዝብን ለማደናገር እየተጠቀሙበት እንዳለ፤ በዚህም ምክንያት የጦርነቱ ከፍተኛ ተግዳሮት ውጊያው ከመሆን ይልቅ የሐሰተኛ መረጃው ሥርጭት እንደሆነና ህወሓት በ1983 ዓ.ም በአዲስ አበባ ዙሪያ ምንም ጦርነት ሳያደርግና በማጭበርበር የደርግ መሪዎች እንዲከፋፈሉ በማድረግ ያለምንም ችግር አዲስ አበባ እንደገባው ሁሉ፤ ዛሬም እንደዚያ ለማድረግ እየሞከረ እንዳለ አስረድተዋል። አሁን ያለው አካል ካለፈው የተማረ እንደሆነና ሕዝብም በዚህ መሰል መረጃ መደናገር እንደሌለበት መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል። ለዚህ ሕልም ስኬት ሲሉ በተለያዩ የዚህ ቡድን ደጋፊዎች ሕዝቡን "ውጡ፤ ሽሹ" የሚል ምክር እያሰሙ እንደሆነ አንስተው፤ ኢትዮጵያ የኢትዮጵያውያን እንደሆነች፤ "ሁለት ሀገር የለንም፤ ስንኖር ኢትዮጵያዊ ስንሞት ኢትዮጵያ እንሆናለን እንጂ የምንሸሸበት ሀገር የለንም" ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

የኢትዮጵያን ስም ለማጥፋት በዓለም አቀፍ ደረጃ የተከፈተውን ዘመቻ አስመልክተውም፤ በሳምንታት ውስጥ በዓለም አቀፉ ሚዲያ ኢትዮጵያ የተሳለችበት መንገድ እና በጥቂት ወራት ውስጥ በተ.መ.ደ የጸጥታው ምክር ቤት ስብሰባዎች ላይ ኢትዮጵያ የተሳለችበት መንገድ የማያሸብረው ፖለቲካኛ እንደማይኖር አንስተው፤ ኢትዮጵያዊነት ግን ከዚህ በላይ እንደሆነና ጥቂት ሀገራት ብቻ እንዲህ ተደርጎባቸው

ሀገራቸውን ማዳን እንደቻሉ አስታውሰዋል። በኢትዮጵያ ላይ ይህን መሰል ተግባር ቀድሞ ተደርጎ እንዳለፍነው አሁንም እንደምንደግመው አስረግጠው ተናግረዋል። በዚህ ወቅት ፈተናዎች ብለው ካስቀምጧቸው ነጥቦች መካከል አንደኛው፣ የወገን ኃይል መረጃ ማቀብ አለመቻሉ እንደሆነ፤ በዚህም ረገድ በማህበራዊ ሚዲያው ላይ ሁሉም ተንታኝ የሆነበት እና የተገኙ መረጃዎችንም ጠላትን በሚጠቅም መልኩ በማሠራጨት ብዙ ጉዳት በወገን ኃይል ላይ እንዲደርስ መደረጉ፤ በሁለተኛ ደረጃ የጠላት የሐሰት ፕሮፓጋንዳ ሲሆን፤ ጠላት ሐሰተኛ መረጃ ሥራው አድርጎ እየሠራ እንደሚገኝ፤ ለዚህም የአካልም የሞራል ተጠያቂነት የሌለው ቡድን መሆኑን አንስተው፤ በወገን በኩል ይህን ብዙዎች የጠላት መረጃ መስማታቸው ሳያንስ በማባዛትና በማሠራጨት እንደሚሳተፉ አንስተው መታረም የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ አሳስበዋል። አያይዘውም፣ የእኛን ስትራቴጂ በሚዲያ እንዲነገረው የሚፈልግ ኃይል መኖሩን አንስተው ይህም ተገቢ ጥያቄ እንዳልሆነ መታወቅ ያለበት ብቻ ማወቅ እንደሚጠቅምም መልዕክታቸውን አስተላልፈዋል።

በመጨረሻም፣ በዚህ ጦርነት መንግሥት ዋና ዋና ግቦች አድርጎ የያዛቸውን ሐሳቦች ሲያስረዱ፤ ኢትዮጵያ እንደማትፈርስ ለሁሉም ጠላት በተግባር ማሳየት እንደሆነ፤ ኢትዮጵያ የማትሸነፍ ሀገር እንደሆነች ሊለያዩን ለሞከሩት ሁሉ አንድ ሆነን እንደምናሸንፍ ማሳየት እና ለኢትዮጵያውያን ሰላም እና እፎይታ ማምጣት ዋና ዋና ግቦች እንደሆኑ ገልጸዋል። ኢትዮጵያውያን ባለፉት 30 (ሠላሳ) ዓመታት ኢትዮጵያዊነትን የሚያዳክም፤ ትስስሩንም የሚያላላ ብዙ ሥራ በህወሓት ሲሠራ እንደነበር አስታውሰው፤ አሁን ያለንበት ሁኔታ የኢትዮጵያን አንድነት በጽኑ መሠረት ላይ ለማቆም እነጀርመን፣ ጃፓን እና ኮሪያ ተፈትነው ኃያል እንደሆኑት ሁሉ ኢትዮጵያም በሁሉም መንገድ የተደረገባትን ጫና እና ጦርነት አሸንፋ በጽኑ መሠረት ላይ ቆማ ሰንደቃችንን ከፍ አድርገን የምናውለበልብ እንደሆነና ችግሮቻችን ሕዝባችንን እያስተሳሠሩ ያሉ ችግሮች ውስጥ መሆናችንንም በማወቅ በጋራ በመቆምና ሀገራችንን በመጠበቅ ፈተናውን እንደምናሸንፍ መገንዘብ ይገባል ብለዋል።

## በተሳታፊዎች የተነሱ አስተያየቶች እና የተሰጠ ምላሽ

የመወያያ ሐሳቦች ከቀረቡ በኋላ የውይይቱ ተካፋዮች አስተያየት ሰጥተዋል። በዚህም፣ ኢትዮጵያ አሁን እየደረሰባት ያለው ጫና ሕዝቦቿን እያሰባሰበ ነው። የተከፈተባትም ዘመቻ የዘመናችን "አድዋ" በመሆኑ መላው አፍሪካዊ ከጎናችን እንዲቆም የሚያደርግ ሥራ መሥራት ይገባል። ሚዲያዎቻችን የሚያስተላልፉት መልዕክት ወጥነት እና ታማኝነት ያለው መሆን አለበት። ሕዝቡ በያለበት ይህን ጠላት

“አልፈልግህም” ብሎ እየተፋለመ ስለሆነ፤ በአንድ አስተባብሮ መዋጋት ላይ ትኩረት መደረግ አለበት። “ይህ የሽብር ቡድን የዛሬውን ተግባሩን ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ላይ አድርጎት አያውቅም ወይ?” የሚለውን ማሰብ ይገባል። የምዕራብ ሀገሮችስ ከዚህ ቡድን ጋር አብረው እየሠሩ ያሉት ለምንድን ነው? እነርሱም የተዳከመች ኢትዮጵያ እንድትኖር ጽኑ ፍላጎት ስላላቸው እንጂ፤ ህወሓት አታልሏቸው እንዳልሆነ ማወቅ ይገባናል። ለዚህም ምላሽ በሚዲያው ላይ አፍሪካውያንን የሚያስተባብር ሥራ መሥራት ይገባል የሚሉ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል። በተጨማሪም፣ በህወሓት አስተዳደር ዘመን በዜጎች ላይ ከፍተኛ የሰብአዊ መብት ጥሰት ይደርስ እንደነበር መታወስ አለበት። እና የዚህ ቡድን አባላት እነዚያ ተግባሮቻቸው በኢትዮጵያውያን ለሰላም ሲባል ይቅር ቢባሉም እነርሱ ግን ወደጦርነት መግባታቸው ጦርነቱን ለኢትዮጵያውያን ፍትሐዊ ያደርገዋል። የምዕራባውያን ሚዲያዎች እያደረጉት ያለው ጫና የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን የጥናት ውጤት እንኳን ትኩረት እንዳያገኝ እያደረገ ያለ አድሏዊ አሠራር መሆኑን መረዳት ይገባል። የህወሓትን ጥቃት ለማክሸፍ እና የምዕራቡን ዓለም ድጋፍ ለማግኘት ተፎካካሪ ፓርቲዎች የዲፕሎማሲ ዘመቻ መጀመር ይገባቸዋል። ዳያስፖራው በዓለም አቀፍ ተቋማት እና መድረኮች ላይ የኢትዮጵያን ድምጽ እንዲያሰማ የሚያደርግ ሥራ ቢሠራ፤ እየተሠራ ከሆነም ምን ደረጃ ላይ ነው የሚሉ ጥያቄ አዘል ሐሳቦችም ተነስተዋል።

በመጨረሻም፣ ዶ/ር ቢቂላ፣ ይህ የሽብር ቡድን ከውጭ ጠላቶች ጋር በመሆን የፈጠረውን የጎላውና አደጋ ለመቀልበስ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ልዩነቱን ወደጎን በመተው አንድ ላይ በመሰለፍ ታሪካዊ ሀገር የማዳን ኃላፊነቱን የሚወጣበት እንደሆነ አንስተው፤ የሽብር ቡድኑ በአፋር እና በአማራ ክልል ሕዝቦች ላይ ፈርጀ ብዙ ጉዳት እያደረሰ እንደሚገኝ፤ የእነዚህ ሁለት ክልል ሕዝቦች እና የጸጥታ መዋቅሩ የዚህን ቡድን ጥቃት ለመመከት እና ለመቀልበስ የሚያደርጉት ተጋድሎም የሚመሰገን እና የሁሉንም ኢትዮጵያዊ ድጋፍ የሚሻ ጉዳይ መሆኑን ገልጸዋል። ሁሉም ኢትዮጵያዊ በያለበት ሀገር የማዳን ታሪካዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣም አጽንኦት ሰጥተው አሳስበዋል። ኮሚሽነር እንደሻው በበኩላቸው፣ የህውሓትን የቆየ ታሪክ መረዳትና የዚህ ቡድን ፍላጎትም የሥልጣን እና የኃብት እንደሆነ ሊታሰብ ይገባል። ጦርነቱን በበላይነት ለማጠናቀቅ በውጭ እና በሀገር ውስጥ ያለው ኢትዮጵያዊ የመከላከያ ኃይልን በኢኮኖሚ እና በቴክኖሎጂ ማጠናከር እንደሚገባው አሳስበዋል። የመከላከያ ኃይልን ለማጠናከርም ኢትዮጵያውያን ወጣቶች መዝመት ይገባቸዋል። በየአካባቢው ያለው ኃይልም በአንድ በመከላከያ እዝ ስር በመደራጀት በአንድነት መሪውን በመከተል ጦርነቱን ማሸነፍ ይገባል ብለዋል።








OFFICE OF THE PRIME MINISTER

# 4.3 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ ኅልውናን መጠበቅ፤ ዕድገትን ማዝለቅ

*ታኅሣሥ 14 ቀን 2014 ዓ.ም*




ይህ የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ ውይይት የተደረገው በታህሳስ 14፣ 2014 ዓ.ም ሲሆን ኢትዮጵያ ሀገራችን ዓለምን ደጋግሞ ከመታው የኮሮና ወርርሽኝ ጉዳት ሳታገግም ከውስጥ አጥፊ ልጆቿ ጋር የተባበሩ የውጭ ጠላቶቿ ከፍተኛ እሳት ለኩሰውባት ወላፈኑ እየለበለባት ባለበት ወቅት ነው። ወቅቱ ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን ሉአላዊነት ለማስከበር የአስቸኳያ ጊዜ አዋጅ ታውጆ በኅብረ ብሔራዊ አንድነት ዘመቻ በጋራ የዘመቱበትና ጠላትን እየተከላከሉ ያሉበት ጊዜ ነው። ሀገራችን ኢትዮጵያ በዲፕሎማሲው መድረክ ከፍተኛ ጫና እየደረሰባት ያለበት ወቅትም ሲሆን ይህን ጫና ለመመከት ትውልደ ኢትዮጵያውያን የ"#በቃ!" እንቅስቃሴ በማድረግ ለአፍሪካውያን ምሳሌ መሆን የቻሉበት ሥራም የተሠራበት ነው። የዚህ የአዲስ ወግ መድረክ የውይይት ርዕስ "ህልወናን መጠበቅ፤ እድገትን ማዝለቅ" በሚል የተዘጋጀ ሲሆን ዓላማውም ሰላሟ የተጠበቀ፤ ሉአላዊነቷ የተከበረ፤ የበለጸገች ሀገር ለመጪው ትውልድ ለማስረከብ በየፈርጁ ምን ምን እየተሠራ ነው? ወደፊትስ ምን ይሥራል? ከእያዳንዱ ኢትዮጵያዊስ ምን ይጠበቃል? በሚለው ሐሳብ ላይ ውይይት ለማድረግ

ነው።

በዚህ ውይይት በመነሻ ሐሳብ አቅራቢነት የተገኙት ዶ/ር ለገሰ ቱሉ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር፣ አቶ አሕመድ ሽዴ የገንዘብ ሚኒስቴር ሚኒስትር እና አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን (የቀድሞ) የውጭ ጉዳይ ምኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ ሲሆኑ ውይይቱን የመሩት የጠቅላይ ሚኒስትሩ የማህበራዊ ጉዳዮች አማካሪ ሙአዘ ጥበባት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት ናቸው።

## ሀገራዊ ደኅንነት እና የመንግሥት ኮሙኒኬሽን

በመጀመሪያ የውይይት መነሻ ሐሳብ ያቀረቡት ዶ/ር ለገሰ ቱሉ የኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ናቸው። ዶ/ር ለገሰ በአጠቃላይ በሀገራዊ የደኅንነት ሁኔታ ላይ አተኩረው የተሠሩ ሥራዎችን፤ ውጤታቸውን እና ችግሮችን ለማሳየት ሞክረዋል። የህወሐት ኃይል ጥቅምት 24 ቀን 2013 ዓ.ም በመከላከያ ሠራዊት ላይ ጥቃት ካደረሰ በኋላ መንግሥት ተገድዶ ሕግ ለማስከበር ወደጦርነት ውስጥ እንደገባና የተዘረፉ መሣሪያዎችን በማስመለስ፤ በሕግ የሚፈለጉትን የሽብር ቡድኑ መሪዎች በቁጥጥር ስር በማዋል ጦርነቱንም በአጭር ጊዜ እንዳጠናቀቀ ገልጸዋል። በወቅቱም ዓለም አቀፉ ሚዲያ በተቀናጀ ዘመቻ "መንግሥት በትግራይ የዘር ተኮር ጥቃት እያደረሰ ነው። በሰብዓዊ አቅርቦትም እንዳይደርስ አድርጓል፤" የሚል መረጃ በማሠራጨት የስም ማጥፋት ሥራ ሲሠራ እንደነበር አንስተዋል። መንግሥት የሕግ ማስከበሩን ዘመቻ ካጠናቀቀ በኋላ በትግራይ ሊከሰት የሚችለውን የድርቅ እና የርሃብ አደጋ ለመከላከል ሲል ለሕዝቡ የጥሞና ጊዜ በመስጠትና ገበሬው የእርሻ ሥራ እንዲሠራ በማሰብ የተናጠል የተኩስ አቁም በማድረግ ከትግራይ ወጥቷል። ሆኖም፣ የሽብር ቡድኑ የመንግሥትን ውሳኔ ወደጎን በማለት ዳግም ጦርነት በማወጅ የአማራን እና የአፋርን ክልሎች በመውረር ከፍተኛ ሰብዓዊ እና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ እንዳደረሰ አስረድተዋል።

በእነዚህም ጊዜያት የሽብር ቡድኑ ደጋፊዎች ጭምር በተለያዩ ሚዲያዎች ሕዝብን የሚያወናብዱ እና በፍርሃት ውስጥ የሚከትቱ የሐሰት መረጃዎች በማሠራጨት የተቀናጀ የሚዲያ ዘመቻ ሲያካሂዱ እንደነበር፤ በዚህም አዲስ አበባ እንደተከበበች አድርጎ በማቅረብ የማሸበር ሥራ መሥራታቸውን አስታውሰዋል። በሌላ በኩል፣ በከተሞች የነበረው የጦር መሣሪያ ዝውውር ከመብዛቱ የተነሳ መንግሥት ችግሩን ለመፍታት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዳወጀ ገልጸዋል። ከአስቸኳይ ጊዜ አዋጁም በኋላ መንግሥት የተቀናጀ እቅድ እንዳዘጋጀ፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ የሠራዊት ዝግጅት አድርጎ በሕዝባዊ ማዕበል ስልት ጥቃት የከፈተውን የጁንታ ኃይል ለመመከት የሚያስችል የጦር ስልት

በመንደፍ ሕዝቡን፣ መከላከያውን እና የጸጥታውን ኃይል እንዲቀላቀል በማድረግ ጥቃቱን መክቷል። የብልጽግና ማዕከላዊ ኮሚቴም ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ ዘምተው ጦሩን እንዲመሩ ባስተላለፈው ውሳኔ መሠረት በእርሳቸው መሪነት ጦሩ በከፍተኛ ወኔ የጠላትን ኃይል እንዳጠቃ እና ጠላት ይዟቸው ከነበሩ የአማራ እና የአፋር አካባቢዎች እንደወጣ አስረድተው፤ የጠቅላይ ሚኒስትሩ መዝመት በሕዝቡ እና በሠራዊቱ ውስጥ ከፍተኛ ወኔ ፈጥሮ እንደነበር አስታውሰዋል ።

በመጨረሻም፣ በ"ዘመቻ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" ጠላት የማድረግ አቅሙን አጥቶ ለሰላም ጊዜ በመስጠት ስም የያዛቸውን አካባቢዎች እንደለቀቀ፤ ለዚህም ውጤት መሳካት ሕዝቡ አካባቢውን በመጠበቅ፤ ለመከላከያ ስንቅ በማዘጋጀት እና የገንዘብ ድግፍ በማድረግ ከፍተኛ ሀገራዊ ሥራ የሠራበት እንደነበር፤ በአዲስ አበባ ላይ ሽብር ለመፍጠር የተዘጋጁትን የጁንታው አካላት ማክሰሙን ገልጸዋል። ሁሉም የመንግሥትም የግልም ሚዲያዎች፣ እንዲሁም ማህበራዊው ሚዲያ ጭምር በአንድነት ቆሞ ሀገሩን እንደተከላከለ አስታውሰዋል።

የውጭ ግንኙነት እና ዲፕሎማሲ

ሁለተኛው የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን ከውጭ ግንኙነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ሐሳባቸውን አካፍለዋል። ከህወሓት ጋር የተደረገው ጦርነት ምንም እንኳን የእኛ የውስጥ ጉዳይ ቢሆንም በኢትዮጵያ ላይ ልዩ ፍላጎታቸውን ለማራመድ የሚፈልጉ የውጭ ኃይሎች እጃቸውን አስገብተው በመንግሥት ላይ ዘርፈ ብዙ ዲፕሎማሲያዊ ጫና ማሳደራቸውን አንስተው፤ በዚህ ወቅትም ኢትዮጵያ ትክክለኛ ወዳጇቿንና ጠላቶቿን የለየችበት እንደነበር፤ ሕዝቡንም ያስተሳሰረ፤ በተለይ በማህበራዊ ሚዲያ መረጃ በማድረስ እና ሐሰተኛ ትርክቶችን በመከላከል ረገድ ከፍተኛ ተጋድሎ የተደረገበት እንደነበር ገልጸዋል። ግጭቱን ተገን አድርገው ፍላጎታቸውን ለማስፈጸም በኢትዮጵያን መንግሥት ላይ ጫና ሲያሳድሩ የነበሩ መንግሥታት ሚዲያዎች ይህን ፍላጎታቸውን የሚያስፈጽሙባቸው መሣሪያዎቻቸው እንደነበሩ አንስተዋል።

የተባበሩት መንግሥታትን ድርጅቶች ጨምሮ በሰብዓዊነት ስም የሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት በፊት በተለያዩ ሀገራት ይህን መሰል ወገንተኝነት አላቸው ተብለው ሲታሙ የሰማነው በራሳችን ደርሶ አይተነዋል። በዚህም ተቋማቱ የተወሰኑ ሀገራት እና መንግሥታት ፍላጎት ማስፈጸሚያ መሆናቸውንም ታዝበናል። በተቃራኒው፣ በተለያየ መድረክ ላይ ከኢትዮጵያ ጎን የቆሙ ወደጆቻችንም ለይተንበታል ብለዋል። በአጠቃላይ የነበረው ሁኔታ ኢትዮጵያውያን በአንድ እንዲቆሙ ያደረገ፤ በተለይ

ዲያስፖራው ያደረገው እና በማህበራዊ ሚዲያ ላይ የተከናወኑ ሥራዎች አፍሪካውያንን ያሰባሰቡ እንደነበሩ አንስተዋል።

በመጨረሻ፣ የውጭ ግንኙነት የውስጥ ጥንካሬ ነጸብራቅ መሆኑን አንስተው፤ በዲፕሎማሲው የበለጠ ጠንካራ ለመሆን የውስጥ አንድነታችንን ማጠናከር አለብን። የኢኮኖሚ አቅማችንንም ማሳደግ ይገባናል። በዚህ ወቅት ያየነው የሕዝብ ተሳትፎ በተለይ በዲያስፖራው በኩል ሲደረጉ የነበሩ እንቅስቃሴዎች እና የሚደርስብንን ጫና የመቋቋም ብቃታችን አቅማችን ምን ያህል ርቀት ሊወስደን እንደሚችል የታየበት እንደሆነ አስረድተው፤ አሁንም የውስጥ ሰላማችንን ማንም ጣልቃ ሳይገባበት በራሳችን መንገድ መልሰን ማስጠበቅ ይገባናል። ይህንንም በማድረግ ከተጽዕኖ ነጻ የሆነ ሰላም በማረጋገጥ ላይ ማተኮር እንደሚገባ አሳስበዋል ።

## የኢኮኖሚ ሁኔታዎች

የገንዘብ ሚኒስትሩ አቶ አሕመድ ሽዴ በኢኮኖሚው ዘርፍ የነበሩ ሁኔታዎችን እና የተወሰዱ ርምጃዎችን አስረድተዋል። ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት በነበሩት ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያ ሥራዎች የእድገት አማራጮችን ማስፈት፤ የፖለቲካ ምህዳሩን በማስፋት የሴቶችንም ተሳትፎ ማሳደግ እንደተቻለ አንስተዋል። መንግሥት በጦርነት ውስጥ እያለም የተሳካ ምርጫ አድርገናል። ኢኮኖሚው በጦርነቱ ሳቢያ ችግር የገጠመው ቢሆንም መቋቋም ተችሏል። ጦርነቱ ከፍተኛ ጫና ቢኖረውም ባለፈው ዓመት (2013 ዓ.ም) ኢኮኖሚው ስድስት በመቶ እንዳደገ ጠቁመዋል። በዘንድሮው ዓመትም (2014 ዓ.ም) የግጭቱ ስፋት በመጨመሩና ከሁለት ሚሊዮን ሕዝብ በላይ በመፈናቀሉ፤ ጦርነት በተካሄደባቸው ስፍራዎች ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ውድመት በመኖሩ፤ እንዲሁም በአካባቢው መሰብሰብ የሚገባው ገቢ ባለመሰብሰቡ ኢኮኖሚው ክፉኛ እንደተጎዳ ገልጸዋል። በጦርነቱ ለተጎዳው ሕዝብ የእለት ደራሽ አቅርቦት ለማድረስ አስከዐሥር ቢሊዮን ብር እንደወጣ፤ ከፍተኛ የገቢ መቀዛቀዝ እንዳለና በሥራ እድል ላይም ችግር እንደሚኖር አሳስበው፤ በውጭ ንግድ በኩል ግን ችግር እንደሌለ ግብርናውም በሌሎች ሰላማዊ ስፍራዎች በአግባቡ እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል።

በተጨማሪም፣ የጸጥታውም ኃይል ለማጠናከር በሚወጣው ወጭ ምክንያት የበጀት ሽግሽግ ማድረግ እንዳስገደደ፤ ያልተጀመሩ የልማት ፕሮጀክቶችም እንዲዘገዩ እንዳተደረጉ፤ በአጠቃለይ ጦርነቱ በእድገት አቅማችን ላይ ጫና እንዳደረሰ አስረድተዋል። በሌላ በኩል፣ የጦርነቱን ኢኮኖሚያዊ ችግሮች መቋቋም የሚችል የመንግሥት መዋቅር

መኖሩን እንደጥንካሬ አንስተው፤ ምርጫ መደረጉ፤ ከሰሜኑ የግጭት ቀጣና ውጭ በሌሎች አካባቢዎች ምርት፣ ንግድ እና መንግሥታዊ አገልግሎት ያለመቋረጡ ሌላው ጥንካሬ እንደሆነና ዲያስፖራው ያደርግ የነበረው ኢኮኖሚያዊ አስተዋጽዖም ከፍተኛ እንደነበር አንስተዋል። በግጭቱ የተጎዱትን አካባቢዎች መልሶ ለማቋቋም የመልሶ ግንባታ እቅድ እና በጀት የማስጸደቅ ሥራ እየተሠራ እንደሆነም አንስተው፤ ከልማት አጋሮች ጋር በመልሶ ማቋቋም ሥራ ላይ አብሮ ለመሥራት ስምምነት ተደርሶ ከሦስት እስከአምስት ዓመት የሚቆይ የመልሶ ግንባታ ሥራ ለመሥራት ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነ አስታውቀዋል። በቀጣይ በአብሮነት በሚያዘልቀው መንገድ ላይ ሰላምን የማረጋገጥ ሥራ አጠናክሮ በመቀጠል የተጀመረውን የብልጽግና ጉዞ ማጠናከር እና የኢትዮጵያውያን አብሮነት እና አንድነትም ሊጠናከር እንደሚገባ አሳስበው የውስጥ ችግራችንን ፈትተን ለቀጣናው የሰላም ምንጭ መሆን ይገባናል ብለዋል።

## ከባለሙያዎች የተሰጡ ሐሳቦች

የታሪክ ምሁሩ ዶ/ር ታምራት ከአድዋ ጦርነት ጀምሮ ከድል ማግስት በሚፈጠሩ ሁነቶች ነጻነቶቻችን ሁሉ የተሟሉ እንዳልነበሩ አንስተው ከታሪካችን ልንማር ይገባል ብለዋል። የሰላም እና የደኅንነት ትምህርት ባለሙያው ዶ/ር ዮናስ አዳዬ፣ ኢመደበኛ የጸጥታ ኃይሎችን አንድም በአካባቢ የሰላም ኮሚቴ ወይንም ከመከላከያው ጋር እንዲቀላቀሉ መደረግ እንደሚገባ፤ መከላከያውን እና ቤተሰቡን የሚደግፉ ሥራዎች መሠራት እንዳለባቸው፤ እንዲሁም ብሔራዊ አገልግሎት መጀመር እንዳለበት አሳስበዋል። ከሥነ ልቦና አኳያ በጦርነቱ ብዙ ጉዳት የደረሰ ቢሆንም፤ የሕዝብን ስሜት እና ወኔ ያነሳሱ ሥነልቦናዊ ጉዳዮች እንደነበሩ፤ በጦርነቱ በተጎዱ አካባቢዎች ላይ የሚደረግ የእርዳታ ተግባርም የሥነልቦናንም ድጋፍ ያካተተ መሆን እንደሚገባው ማሳሰቢያ ሰጥተዋል። ፕሮፌሰር አለማየሁ፣ የባለቤትነት ጉዳይ የአካባቢው እና የብሔራዊ መንግሥት መሆን እንደሚገባው፤ የኃብት ማሰባሰቢያና የመልሶ መገንባት ቦንድ ቢዘጋጅ የሚል ሐሳብ አቅርበዋል። አቶ ግርማ በኢኮኖሚው ድጋፍ ላይ በኢትዮጵያውያን የተደረገውን ርብርብ ተቋማዊ ማድረግ፤ የአደጋ ጊዜን ሥራ የተቀናጀና የታቀደ ማድረግ እደሚገባ ሐሳብ አቅርበዋል።

ከዚህ መሰል ሀገራዊ ችግር በኋላ በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መከላከያን የማዘመን ሥራ እንደተሠራ፤ አሁንም መከላከያ ማጠናከር እንደሚገባ፤ የዲፕሎማሲው ዘመቻ በዘላቂነት የሚመራ ባለመሆኑ የዲፕሎማቶች ምደባ እና ሥልጠና እንዲታሰብበት፤ አሁን ያለውን የሕዝብ መነቃቃት ለዘላቂ ሰላም እና ልማት ለማዋል እንዲሠራ፤ እንዲሁም ከፖለቲካ ችግር አዙሪት ለመውጣት አዳዲስ መንገድ መታየት

እንዳለበት፤ ከመከላከያው ግንባታ ጎን ለጎን ሕዝባዊ ኃይልም መገንባት አለበት። የጦርነቱ የሥነልቦና ጉዳት ከፍ ያለ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ጎልውናን ለማዝለቅ ሕግም ስለሚያስፈልግ ሕገ መንግስቱ "አንቀጽ 39"ን ይዞ የጎልውና ጉዳይ አሳሳቢ ስለሚሆን በሕገ መንግሥት ማሻሻል ላይ ምን ታስቧል? የሚሉ ሐሳቦች እና ጥያቄ ከተሳታፊዎች ተነስተዋል ።

የውይይቱ ሐሳብ አቅራቢዎች በሰጡት የማጠቃለያ ሐሳብ፤ አምባሳደር ሬድዋን የኢትዮጵያን የውጭ ግንኙነት ለማጠናከር ዲፕሎማቶች ሥራ እንዳላቸው አንስተው፤ ከዲፕሎማቱ በላይ ግን በየሀገሩ ያለው ዲያስፖራ "ለሀገሬ" ብሎ የሚያደርገው እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና እንደሚኖረው ጠቅሰዋል። ይህንን ቡድን የማሰባሰብ እና የማደራጀት ሥራ እንደሚያስፈልግ የእሥራኤልን ተጽዕኖ ፈጣሪነት በማሳያነት አንስተው አስረድተዋል። የውስጥ አንድነትን ማጠናከርም ለዲፖሎማሲው ከፍተኛ ጥንካሬ የሚሰጥ እንደሆነ በማንሳትም ከውስጥ መጋጨትን በማቆም እና "የችግሮች ምንጭ ሁሌም ሌሎች ናቸው" ከሚል እሳቤ ወጥተን "እኔም የችግሩ ባለቤት ነኝ" ወደሚል አስተሳሰብ መግባት እና ለመፍትሔ በጋራ መሥራት ይገባናል፤ ብለዋል። የውስጥ ሰላማችን በተበላሸ ቁጥር በአስማሚነት ስም በጀት መድበው ለሚመጡ አካላት ቦታ ሳንሰጥ ሰላማችንን በራሳችን መንገድ መፈለግ እንደሚገባም አንስተዋል። የብሔራዊ አገልግሎት ጉዳይም ለዘላቂ ሰላም ግንባታ አንዱ መንገድ ስለሚሆን ቢሠራበት ጥሩ ነው ብለዋል። በመጨረሻም፣ አንድነታችን ዘላቂ ሰላምን ለማረጋገጥም ጥቅም ላይ መዋል እንዳለበት እና በቀጣይ በሚደረገው አካታች የሀገራዊ ምክክር ብሔራዊ መግባባትን ለማምጣት ሁሉም ዜጋ በንቃትና በትኩረት መሳተፍ እንዳለበት አሳስበዋል ።

አቶ አሕመድ ሽዴም፣ ኢኮኖሚያችን ስናሳድግ እና ጠንካራ ሀገር ሲኖረን ድሎቻችንን ከዓለም ጫና ማላቀቅ እና ሀገረ መንግሥቱንም ማስቀጠል እንደሚቻል ገልጸዋል። በሌላ በኩል፣ ከመልሶ ማቋቋም ሥራ ጋር በተገናኘ ምንም እንኳን የልማት አጋሮች ድጋፍ የሚኖር ቢሆንም ሥራው የሚመራው በራስ አቅም እንደሆነና የትስስር እና የኃብት ማሰባሰብ ሥራ በሚኖረው የኃብት ማሰባሰቢያ ስትራቴጂ መሠረት የሚሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። ከልማት አጋሮች ጋር የሚኖር ግንኙነት የአጋርነት እንደሆነ፤ ይህም የሚመነጨው ኢትዮጵያ የብዙዎቹ የልማት ተቋማት መሥራች እንደመሆኗ የእኛም ግንኙነት በባለቤትነት መንፈስ የሚሠራ እንደሆነ አንስተዋል። በአጠቃለይ አሁን ያሉትን ተግዳሮቶች ለማለፍ ኢኮኖሚውን ማጠናከር እንደሚገባ አሳስበዋል።






# 4.4 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፤ የኑሮ ውድነት መንሥኤዎቹ እና የመፍትሔ ርምጃዎች

መጋቢት 29 ቀን 2014 ዓ.ም




በወርሃ መጋቢት 2014 ዓ.ም የአዲስ ወግ የውይይት መድረክ የተደረገ ሲሆን "የኑሮ ውድነት መንስኤዎቹ እና የመፍትሄ እርምጃዎች" በሚል ርዕስ ተካሂዷል። የኑሮ ውድነት እንዲከሰት የሚያደርጉ የተለያዩ ምክንያቶች አሉ። ዋናው መገለጫም የሸቀጦች ዋጋ መናር ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃ ከተከሰተው የኮቪድ-19 ወረርሽኝ በኋላ በተፈጠረው የምርታማት መቀነስ ሳቢያ የሸቀጦች ዋጋ መጨመር አሳይቶ የነበር ሲሆን፤ በአሁኑ ሰዓት በራሺያ እና ዩክሬን ጦርነት ምክንያት ደግሞ በተወሰኑ የምግብ፣ የማዳበሪያ እና የነዳጅ ምርቶች ላይ በዓለም አቀፍ ደረጃ የዋጋ ጭማሪ ተከስቷል። ይህም ኢትዮጵያን እየጎዳት እና የኑሮ ውድነቱን እያባባሰው ይገኛል። በዚህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም የኑሮ ውድነቱ ሀገራዊ እና ዓለም አቀፋዊ መንስኤዎች ምንድን ናቸው? መፍትሔውስ? በሚለው ላይ ሰፋ ያለ ውይይት ተደርጓል።

በመድረኩ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች፦

1. ዶ/ር ነመራ ገበየሁ፣ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር ዴኤታ።

2. ወ/ሮ ይርጋለም እንየው፣ በኅብረት ሥራ ኤጀንሲ የኅብረት ሥራ ግብይት ዳይሬክተር፤

3. አቶ መለስ ምናለ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ገዥ የማክሮ ኢኮኖሚ ከፍተኛ አማካሪ (የቀድሞ) ናቸው።

የውይይቱ ተሳታፊዎች ከጉዳዩ ጋር ቀጥታ ግንኙነት ያላቸው የመንግሥት ኃላፊዎች፣ ለምግብ ፍጆታ የሚሆኑ ሸቀጦችን ምርቶች አስመጪና ላኪዎች፣ አርሶ አደሩን ካቀፉ የኅብረት ሥራ ማህበራት እንዲሁም የሸማች ማህበራት የተወጣጡ ናቸው። ውይይቱን በአወያይነት የመራቸውም ጋዜጠኛ ሮዛ መኮንን ናት።

## የኑሮ ውድነት ( የሸቀጦች ዋጋ ንረት) ምንነት

የኑሮ ውድነት የሕዝቡን የመግዛት አቅም በየጊዜው እየሸረሸረ የሚያዳክም የመሠረታዊ ቁሳቁሶች ዋጋ ጭማሪ ነው። ጤናማ ከሆነው የዋጋ ጭማሪ የሚለየው ጭማሪው ከእለት እለት በፍጥነት የሚጨምርና የሕዝቡን የመግዛት አቅም የሚያዳክም በመሆኑ ነው፡ ፡ የዋጋ ጭማሪ ጤናማ የሚያስብለው አምራቾች ወይንም ነጋዴዎች በግብይትና በማምረት ሂደት ውስጥ ያሚያውጡትን ወጪ ለመሸፈንና ተመጣጣኝ ትርፍ ለማግኘት የሚጨመር እስከሆነ ድረስ እንደሆነ በውይይቱ ላይ ተገልጿል።

## የዋጋ ጭማሪ ዋና መንስኤዎች :-

• በኢኮኖሚው ውስጥ የምርት ፍላጎት እና አቅርቦት እድገት አቅም አለመጣጣም፤ (የአቅርቦት ፍላጎት የምርት አቅርቦት ከሚያድግበት በላይ መሆን)

• ምርቶች ከተመረቱ በኋላ ለተጠቃሚ በሚሠራጩበት ወቅት በሥርጭት ጉድለት ምክንያት፤

• ከዓለም አቀፍ የኢኮኖሚ ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሚመጣ የዋጋ ጭማሪ (በዓለም አቀፍ የገበያ ሁኔታ ዋጋቸው በሚወሰኑ የፍጆታ እቃዎች ዋጋ ጭማሪ ምክንያት)

• ከመንግሥት የገንዘብ ፖሊሲ ወይንም የፋይናንስ አስተዳደር ጋር ተያይዞ በሚመጡ ችግሮች ምክንያት ሊከሰት ይችላል።

አራቱ መንስኤዎች በተናጠል ወይንም በጋራ ሊከሰቱ ይችላሉ። የመንስኤዎቹ በጋራ መከሰትም ችግሩን ውስብስብ እና አስከፊ ያደርገዋል። በሀገራችን እየተስተዋለ ያለው ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ ከአራቱም መንስኤዎች ጋር ተያያዥነት ያለው ቢሆንም፤

የአቅርቦት እና የፍላጎት አለመመጣጠን ግን ከፍተኛውን ድርሻ ይወስዳል።

## ከግብይት ሰንሰለት ጋር ተያይዞ ያለው ችግር፦

በሀገራችን በምግብ እህሎች የግብይት ሰንሰለት ውስጥ ለዋጋ ጭማሪ መንስኤ የሚሆኑ ምንም ዓይነት እሴት የማይጨምሩ የግብይት ተዋንያን መኖራቸው እና የምርትን ዋጋ አምራቹ መወሰን አለመቻሉ በግብይቱ ሥርዓት ላይ ትልቅ ችግር ነው። ይህም የሆነው በሕገወጥ የግብይት ተዋንያን (ደላላዎች) ምክንያት ነው። እነዚህ በግብይቱ ሥርዓት ውስጥ ያሉ ደላላዎች በዋጋ ጭማሪው ከአምራቹ በላይ ጥቅም እያገኙ በመሆናቸው ትልቅ ችግር እንደሆኑ በውይይቱ ተነስቷል።

## የፍላጎት እና የአቅርቦት አለመጣጣም እንደምክንያት፦

በአሁኑ ወቅት በሀገር ውስጥ የዋጋ ጭማሪ ላይ ከፍተኛ ድርሻ ያላቸው ምግብ ነክ የግብርና ምርቶች ሲሆኑ፤ ለዚህም ዋነኛ ምክንያቶቹ የሕዝብ ቁጥር መጨመር፣ ላለፉት 20 (ሃያ) ዓመታት በኢትዮጵያ የተፈጠረው የኢኮኖሚ እድገት ከፍተኛ የምግብ እህል (በተለይም የስንዴ) እና የኢንዱስትሪ ምርቶች ፍላጎት እንዲጨምር ማድረጉ ነው። በአንጻሩ፣ የግብርና ምርታችን እና የሌሎች ሸቀጦች ምርት ግን በእነዚህ ዓመታት በፍላጎቱ ልክ አላደገም ነበር። ይህን አለመጣጣም ለማስታረቅ ምርቶችን ከውጭ በማስገባት የተወሰዱ ርምጃዎችም ከዓለም የምርት ዋጋ ጭማሪ ጋር ተዳምሮ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ እንዳመጡ በውይይቱ ላይ ቀርቧል።

## የገንዘብ ፖሊሲ ነክ መንስኤዎች፦

ከኢትዮጵያ የገንዘብ ፖሊሲ አንጻር ለዋጋ ጭማሪው ምክንያት የሆነው የአምራቹ ዘርፍ ከሚፈልገው በላይ ገንዘብ ወደኢኮኖሚው በመግባቱ ነው። በዚህም ምክንያት ምርት ከውጭ የማስገባት ፍላጎት ጨምሯል። ምርትን ከውጭ ለማስገባት ሲባል ደግሞ የዶላር ፍላጎት አብሮ ከፍ በማለቱ የብር የመግዛት አቅም እንዲቀንስ በማድረግ ከፍተኛ የዋጋ ጭማሪ አስከትሏል።

መንግሥት ኢኮኖሚውን ለማሳደግ ከብሔራዊ ባንክ በብድር ወደኢኮኖሚው ያስገባ የነበረው ገንዘብ ለዋጋ ጭማሪው ከፍተኛ ድርሻ የነበረው ሲሆን፤ ከለውጡ በኋላ መንግሥት አዳዲስ ኢንቨስትመንቶችን በማቆም የገንዘብ ምንጩን ኢኮኖሚው ውስጥ ካለው ገንዘብ፤ የግምጃ ቤት ሰነድ በመግዛት እና ከዓለም አቀፍ ለጋሾች በሚገኝ ገንዘብ ለማሻሻል ሞክሮ ውጤት እያሳየ ነበር። ነገር ግ፣ በኮቪድ 19፣ በድርቅ፣ በተደጋጋሚ የሰዎች መፈናቀል፣ በጦርነቱ እና በኢትዮጵያ ላይ በተከፈተው ዓለም አቀፋዊ

የኢኮኖሚ ጫና ምክንያት ለተከሰተውን የበጀት ጉድለት መንግሥት ከብሔራዊ ባንክ በብድር ለማሟላት ያደረገው ሙከራ የዋጋ ጭማሪውን ከፍ እንዲል እንዳደረገው በውይይቱ ተገልጿል።

## የመፍትሔ ሐሳቦች

ከላይ ያየናቸውን የበጀት ጫናዎች ለማስተካከል መንግሥት በገንዘብ ፖሊሲው ላይ ቁጥጥር በማድረግ ወደኢኮኖሚው የሚገባውን ተጨማሪ የገንዘብ መጠን በመቀነስ የዋጋ ጭማሪውን ማረጋጋት ስለሚችል አሁን ያሉት ዓለም አቀፍዊና የሀገር ውስጥ የበጀት ጫናዎች መሻሻል እስኪችሉ መታገስ አስፈላጊ እንደሆነ እና መንግሥት በወጪ ቅነሳ ላይ በትኩረት እንዲሠራ ምክረ ሐሳብ ቀርቧል።

የአቅርቦቱን ክፍተት ለመሙላት ግበርናውን ማዘመን እና የከተማ ግብርናን ማጠናከር፤ ምርታማነትን ለማሳደግ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፤ እንዲሁም ምርቶችን ገበያ መር ማድረግ እንደሚገባ፤ በግብርና ላይ በተለይ የእህል፣ የአትክልት እና የጥራጥሬ ምርት መጠን ማሳደግ፤ እንዲሁም የበጋ ግብርናን አጠናክሮ መቀጠል ይገባል ተብሏል። ባለፉት ሦስት ዓመታት መንግሥት በበጋ ግብርና ላይ የሠራው ሥራ ውጤት እያየን ነው። እዚህ ላይም አጠናክሮ መሥራት ይገባል። የግብርናውን ምርታማት ለማሳደግ ግብርናን በእውቀት መምራት፣ ለግብርናው ዘርፍ የፋይናንስ አቅርቦት ማሳደግ፤ (በዚህ ላይ በተለይ ልማት ባንክ እንዲሳተፍበት) የግብርናን ኤክስቴንሽን አቅርቦት ማሳደግ እና ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀምን ማስፋፋት ይገባል የሚሉ አስተያየቶች ተሰጥተዋል።

በግብይቱ ሥርዓት ላይ ያሉ ክፍተቶችን ለማስተካከል አምራቹን በቀጥታ ከተጠቃሚው ጋር ማገናኘት የሚችሉ ስልቶችን መፍጠር ያስፈልጋል። ለምሳሌ አምራቹ ምርቶቹን ለተጠቃሚው በቀጥታ ማድረስ የሚችልባቸውን የገበያ ስፍራዎች እና ባዛሮች ማዘጋጀት። በግብይቱ ሥርዓት ውስጥ የሚገኙ ግብዓት የማይጨምሩ ተዋንያንን ከሥርዓቱ ማስወጣት፤ እንዲሁም የኅብረት ሥራ ማህበራትን ውጤታማ እንዲሆኑ እና የግብይት ድርሻቸውን እንዲያሳድጉ ማገዝ፤ በተጨማሪም የአምራቹን እና የኢንዱስትሪውን ትስስር ማሻሻል ወይም በህብረት ሥራ ማህበራት በኩል አምራቾችን ከኢንዱስትሪው ጋር ማስተሳሰር ላይ እንዲሠራ የሚል ሐሳብ ቀርቧል።

የዋጋ ጭማሪው ያስከተለው ቀውስ ከሰላም መደፍረሱ ጋራ ተደማምሮ የፖለቲካ እና የኅልውና ጉዳይ እየሆነ በመምጣቱ በሰላም እና በደኅንነት ላይ ያሉትን ችግሮች ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት እንዲሠራ፤ በራሺያ-ዩክሬን ጦርነት ምክንያት ለተፈጠረው

የነዳጅ፣ የማዳበሪያ እና የስንዴ ዋጋ ጭማሪ ያለውን ቆጣቢ መጠቀም፤ አማራጭ ምርቶችን መጠቀም እና ከአግሮ ኢንዱስትሪ ጀምሮ ያሉትን የአምራች ኢንዱስትሪዎች አቅም በማሳደግ ከውጭ የምናስገባቸውን የኢንዱስትሪ ምርቶች በሀገር ውስጥ ምርት መተካት እንደሚገባ ተገልጿል። በአጠቃላይ የሕዝባችን የአመጋገብ ሥርዓት የሚሻሻልባቸውን ሥራዎች መሥራት ተገቢ ስለሆነ ሊታሰብበት ይገባል የሚሉ ምክረ ሐሳቦች ቀርበዋል።

## ማጠቃለያ

የኑሮ ውድነቱ በሸቀጦች ዋጋ መጨመር የተፈጠረ መሆኑን እና ለዚህም ዋና ዋና መንስኤዎቹ በአቅርቦት እና በፍላጎት ላይ ያለ አለመጣጣም፣ ምርቱን ለተጠቃሚ በማድረስ ሂደቱ መካከል ባሉ እሴት አልባ አካላት (ደላላዎች) እና ዓለም አቀፋዊ በሆኑ በኮቪድ 19 እና በራሺያ እና በዩክሬን ጦርነት ምክንያት በተፈጠረ ዓለም አቀፋዊ የሸቀጦች የዋጋ ጭማሪ እንደሆነ ማብራሪያ ተሰጥቷል። በገንዘብ ፖሊሲ ምክንያት እየተፈጠረ ያለውን ችግር ለማስወገድ የገንዘብ ቁጥጥሩን ማጠናከር፣ ምርታማነትን ማሳደግ፤ በተለይ በግብርናው ዘርፍ ምርትን ማሳደግ በተለያዩ ሁኔታ ከውጭ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርት መተካት፤ የመንግሥትን እና የሕዝቡን ወጪ መቀነስ፤ ቁጠባን ባህል ያደረገ አኗኗር መለማመድ፤ እንዲሁም በአምራቹ እና በተጠቃሚው መካከል ያሉትን አላግባብ ተጠቃሚ ደላሎች ከገበያ ማስወጣት እና አምራቹን ከተጠቃሚው ጋር በቀጥታ ማገናኘት የሚሉ ሐሳቦች በመፍትሔነት ቀርበዋል።









# 4.5 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ ሀገራዊ አምራችነት

ግንቦት 12 ቀን 2014 ዓ.ም




በዚህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም “ሀገራዊ ምርታማነት” በሚል ርዕስ በግንቦት 12፣ 2014 ዓ.ም ወርሃዊው የአዲስ ወግ ውይይት ተካሂዷል፡፡ ምርታማነት ሲባል ግብዓቶችን ተጠቅመን ምርትን የምናሳድግበት እና የአመራረት ሥርዓታችንን ጥራት የምናዘምንበት ነው፡፡ በሀገራችን ለምርታማነት ማነቆ የሆኑ የአስተሳሰብ፣ የክህሎት እና የሥርዓት ጉዳዮች ምንድን ናቸው? መፍትሔዎቻቸውስ? በሚሉ ነጥቦች ላይ ሐሳቦች ቀርበዋል፡፡ በመድረኩ የውይይት ሐሳብ አቅራቢዎች፣ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው እና ዶ/ር ታምራት ኃይሌ ናቸው፡፡ የውይይቱ ተሳታፊዎች ከተለያዩ ተቋማት የተወከሉ ባለሙያዎች ሲሆኑ፤ የፕሮግራሙ አወያይ ወ/ሮ ሰላማዊት ካሳ የመንግሥት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት ሚኒስትር ዴኤታ ናቸው፡፡

## በውይይቱ የተነሱ ዋና ዋና ሐሳቦች

በውይይቱ ዶ/ር ታምራት፣ በዓለማችን ውስጥ የሰዎች ትስስር እንዴት ውድድር እንዲፈጠር መንስኤ እንደሆነና ዓለማችን ካለፈችባቸው አስከፊ የምጣኔ ኃብት ውድቀቶች አንዱ የሆነው የኮቪድ 19 ወረርሽኝ ባስከተለው የኢኮኖሚ ቀውስ፤

እንዲሁም በዓለም አቀፋዊ ግጭቶች ምክንያት የዓለም ምርታማነት ተጽዕኖ ውስጥ ወድቋል። ይህም እንደኢትዮጵያ ላሉ በዓለም አቀፋዊ ትስስሩ ከፍተኛ የምርት ተቀባይ የሆኑ አዳጊ ሀገራት ላይ ጫናው ከፍተኛ ደረጃ መድረሱን አንስተዋል። ኢትዮጵያም ወደውጭ በምትልከው እና ከውጭ በምታስገባው ምርት ላይ ለዘመናት እየሰፋ የመጣው የሚዛን ጉድለት ሀገራችንን ከፍተኛ ጫና ውስጥ እንደከተታት በውይይቱ ተነስቷል። በመሆኑም፣ ተለዋዋጭ የሆነውን ዓለም አቀፋዊ ሁኔታ ተቋቁሞ ጠንካራ ሀገራዊ ምጣኔ ኃብት ለመገንባት ምርታማነትን ማሳደግ ወሳኝ አቅም እንደሆነ ተገልጿል።

ሁለተኛው የውይይቱ ሐሳብ አቅራቢ ፕሮፌሰር ዳንኤል ቅጣው፣ ምርታማት ማለት ጥራትን ማሳደግ፤ ብክነትን መቀነስ እና የምርትን መጠን ማሳደግ እንደሆነ አስረድተው፤ ምርታማትን ለማሳደግ በግብዓትነት ሊተገበሩ የሚገቡ ሦስት ጉዳዮች ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል። የመጀመሪያው እና ዋነኛው የልቦና ውቅር ለውጥ ማምጣት ነው። እንደሕዝብ ለሥራ እና ለጊዜ ያለንን አስተሳሰብ ወይም ምልከታ መቀየር ይገባናል። ሁለተኛ የሠራተኞችን ክህሎት ማሳደግ፤ ከመደበኛው ትምህርት እስከከፍተኛ ትምህረት ባለው ደረጃ ብቁ ክህሎት ያላቸውን ሠራተኞች ለመፍጠር ከህጻናት ጀምሮ መሥራት እንደሚገባ እና ፈጠራን የሚያበረታታ ባህል እና ሥርዓት የመገንባት ሥራ መሥራት እንደሚገባ አንስተዋል። የልቦናን ውቅር መለወጥ እጅግ አስፈላጊ የሚሆነው በኢትዮጵያ የሥራ ለዘብተኝነት በከፍተኛ ሁኔታ እንደሚታይ፤ እንደባሕልም እየተቆጠረ በመሆኑ ነው። ለልቦና ውቅር ለውጥ ከመንግሥት ይልቅ ዜጎች እንደግል ኃለፊነታቸው ወስደው የላቀ ለውጥ ለማምጣት የሚተገብሩት መሆን እንዳለበት አስረድተዋል።

ምርታማነትን በከፍተኛ ደረጅ ለማሳደግ የሰው ኃይል ዋነኛው ግብዓት እና አቅም እንደሆነ ተነስቷል። በዚህ ረገድ፣ ኢትዮጵያ ያላት ትልቁ ኃብት ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል ቢሆንም፤ ምርታማነቱ ግን አነስተኛ ነው። በኢንዱስትሪው ዘርፍ ያለው የምርማነት መጠን ለአብነት ቢታይ፤ ዘርፉ ከጎምሣ በመቶ ባነሰ የማምረት አቅሙ እያመረት እንዳለና ይህም ብዙ ብክነት እንዳለው ተጠቅሷል። ይሄንንም ለመቀየር ሠራተኞችን በክህሎት፣ በልምድ እና በአስተሳሰብ ማብቃት፤ የአሰሪውንና የሠራተኛውን የልቦና ውቅር መለወጥ፤ የሥራ መሣሪያዎችን አጠቃቀም ማሻሻል እንደሚገባና በአካባቢያችን የሚገኘውን ጸጋ በማወቅ ያሉንን ኃብቶች ምርታማነት መጨመር በሚያስችል መንገድ መጠቀም እንደሚገባ ምክረ ሐሳበ ቀርቧል። እንደማሳያም በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ተሠርቶ ውጤት እያሳየ ያለውን የጓሮ ግብርና ምሳሌ በማድረግ በየአካባቢያችን ልብ ያላልናቸው

ሀገራችንን እና ሕዝቦቿን ሊቀይሩ የሚችሉ ኃብቶች በማስተዋል እና በመለየት፤ ወደምርት በማስገባት ኢትዮጵያ ምርታማነቷን እንድታሳድግ መሰድረግ ተገቢ እንደሆነ ተገልጿል።

በአጠቃላይ፣ ምርታማነትን ለማሳደግ ዋነኛው ሊተኮርበት የሚገባው ጉዳይ የሰው ኃብትን አቅም ማሳደግ ነው። ኢትዮጵያም ከፍተኛ ቁጥር ያለው የሰው ኃይል ያላት ሀገር እንደመሆኗ ይህን ኃይል ምርታማ እንዲሆንና ምጣኔ ኃብታችንን ማሳደግ እንዲችል በመሥራት ረገድ መንግሥትና የግሉ ዘርፍ፣ ዜጎችም ጭምር ኃላፊነት እንዳለባቸው በውይይቱ ተነስቷል። እንደመንግሥት ብቁ ሠራተኛ ለማፍራት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በቴክኒክ እና ሙያ ትምህርት ማዕከላት ዜጎች የሥራ ገበያው የሚፈልገውን ክህሎት እና የሥነልቦና ዝግጁነት ይዘው እንዲወጡ በማድረግ ላይ በሰፊው መሠራት እንደሚገባ ተገልጿል። በሕግ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉትን ማነቆዎች በመቅረፍ ረገድ የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ተቋቁሞ ወደሥራ መግባቱ ክፍተቱን ለመሙላት ትኩረት እንደተሰጠው ያሳያል። ቀደም ሲል በሥራ ላይ የነበረው የአሰሪና ሠራተኛ አዋጅ ማስተካከያ ተደርጎበት መውጣቱ ምርታማነትን ለማሳደግ ትኩረት መሰጠቱን የሚያሳይ እንደሆነ በውይይቱ ላይ ተነስተዋል።

የሥራን ባህል ከመለወጥ አኳያም ከዘመቻ ይልቅ ዘላቂ የሆነ የንቅናቄ ሥራ የሚያስፈልገው ጉዳይ ነው። በመንግሥት በኩል ታላላቅ ፕሮጀክቶችን በራስ አቅም በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ሠርቶ ማጠናቀቅ እንደሚቻል በተለያዩ ሜጋ ፕሮጀክቶች ማሳየት መቻሉ እና በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ በዘመን መካከል ገዝፎ ይታይ የነበረውን በምግብ እህል እራስን የመቻልን ጉዳይ በየአካባቢው የሚገኝን የመስኖ አቅም በመጠቀም የበጋ ስንዴ በማምረት የተሠራው ሥራ ምርታማትን ለማሳደግ ከሚያስፈልጉ አንደኛው የአስተሳሰብ ባህልን ለመለወጥ የሚያስችል እና ትኩረት ተነፍጎት የነበረውን የግብርና ዘርፍ መነቃቃት የፈጠረ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ተብራርቷል።

## ማጠቃለያ

የሀገራችን ምርታማነት ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንዲደርስ ያደረጉ ሰፊ ምክንያቶች ሲዘረዘሩ፤ በዋነኛነት የሚነሳው የሰው ኃይል ችግር ነው። ችግሩም የሰው ኃይል እጥረት ሳይሆን ጥራት ያለው፤ በክህሎት እና በአስተሳሰብ የበለጸገ፤ ሠርቶ ሀገርን ለመለወጥ ዝግጁ የሆነ ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ የሰው ኃይል እጥረት እንደሆነ ተነስቶ፤ በክህሎትና በአስተሳሰብ የዳበረ ሠራተኛ ማፍራት በሁሉም ዘርፍ ምርታማነትን

ለማሳደግ አስፈላጊ እንደሆነ ተሰምሮበታል። ለግብርናው ዘርፍ፣ በተለይ ስንዴን ቆላማ በሆኑና ስንዴ አምርተው በማያውቁ አካባቢዎች በበጋ ወቅት የመስኖ ውኃ በመጠቀም እየተከናወነ ያለው የግብርና ሥራ ለገበሬውና በሌላም ዘርፍ ለተሰማራው ከተለመደው የአሠራር ሥርዓት እንዲወጣ እና በአዲስ አስተሳሰብ (የልቦና ውቅር) በመሥራት ምርትን ማሳደግ እንደሚገባ ያሳየ ተግባር እንደሆነ በውይይቱ ተገልጿል። ለዚህም ደግሞ መንግሥት የጀመረውን አቅጣጫ የማሳየት እና የመምራት ሥራ በአግባቡ በማስቀጠል ለውጡን ግለሰብ ተኮር ማድረግ እንደሚገባ ምክረ ሐሳብ ቀርቧል።

በዚህ ወቅት ኢትዮጵያ በፈተናዎች ውስጥ እንደመገኘቷ እነዚህን ፈተናዎች ለመሻገር በሀገር ውስጥ ያሉንን ኃብቶች በትኩረት ልንመረምር እንደሚገባ፤ በግለሰብ ደረጃም "በአካባቢያችን ያለ በቀላሉ ወደምርትነት ልንቀይረው ምንችለው ነገር ምንድነው?" የሚለውን ማጤን እንዳለብን፤ እንደሀገር በተለያዩ ምርቶች እራስን መቻልን እንደባህል ለማድረግ ያለንን ጸጋ መፈተሽ እንደሚገባም ተነስቷል። በስንዴ ምርት እራሳችንን ለመቻል የተጓዝነውን በሌሎች በለየናቸው ዘርፎችም ለማስፋት፤ አስፈላጊው ክህሎት ያለው እና ሀገሩን ለመለወጥ የቆረጠ የሰው ኃይል በመገንባት ሥራ ላይ በማተኮር ሊሠራ እንደሚገባ ሐሳብ ተሰጥቶበታል። በሌላ በኩል፤ ዓለማችን በከፍተኛ ለውጥ ውስጥ እንደመገኘቷ በሀገራችን ምርታማነትን ለማሳደግ እና ተወዳዳሪ ለመሆን በትብብር ከመሥራት በመነሳት ወደፋክክር ማሳደግ ይገባል። ትብብሩም ከግለሰብና ከተቋማት ደረጃ አልፎ በሀገር ደረጃ መሆን እንዳለበትና ምሥራቅ አፍሪካን የሚያስተሳስር ትልቅ የትብብር ገበያ መፍጠር እንደሚገባ በውይይቱ ተነስቷል።









# 4.6 የአዲስ ወግ አብይ ጉዳይ፣ ከጽንፎች መሐል ወርቃማውን አማካይ ፍለጋ

ሰኔ 20 ቀን 2014 ዓ.ም




ጽንፈኝነት በተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ዘንድ የተለያየ ግንዛቤ ያለው ሐሳብ ነው። የጽንፈኝነት እሳቤ እና ተግባራት ግን በተለያየ መጠን በሁላችንም ዘንድ ያለ ባሕሪይ እንደሆነ ይነገራል። በኢትዮጵያ በጽንፈኝነት አስተሳሰብ እና ጽንፈኛ በሆኑ ተግባራት ሳቢያ የሚደርስ ጉዳት ገፈት ቀማሽ ሆነናል። በዚህም፣ ሀገርን ጽንፈኛ ከሆነ "ከእኔ እና ለእኔ መሰሎች" ከሚሉ አስተሳሰቦች ለማውጣት፤ እንዲሁም በሀገራችን በተደጋጋሚ እየተሰሙ ካሉ አስከፊ የጽንፈኛ ጥቃቶች ድግግሞሽ ለመውጣት ታስቦ "በጽንፎች መካከል ወርቃማውን አማካይ ፍለጋ" በሚል ርእስ ውይይት ለማድረግ የተዘጋጀ የአዲስ ወግ የአብይ ጉዳይ ፕሮግራም ነው። ውይይቱ ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን በጽንፈኝነት እና በተያያዥ ሐሳቦች ዙሪያ የተነሱ የባለሙያዎች አስተያየቶችና ምክረ ሐሳቦችን እያንሸራሸረ በሰኔ 20- 21፣ 2014 ዓ.ም ተካሂዷል።

## 4.6.1 ክፍል አንድ

## የጽንፈኝነት ትርጉም፣ አውድ እና ታሪካዊ ምልከታ

የመጀመሪያው የውይይት ክፍል በጽንፈኝነት ትርጉም፣ አውድና ታሪካዊ ምልከታ ላይ በጥልቀት ትኩረቱን ያደረገ ነው። በዚህ የውይይት ክፍል ፕሮፌሰር ኃብታሙ ወንድሙ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ መምህር በሦስቱ ሐሳቦች ትርጓሜ (አክራሪነት፣ ጽንፈኝነት እና ሽብርተኝነት) ላይ ማብራሪያ ሰጥተዋል። በዚህም፦
አክራሪነት ፡ አክራሪነት የተወሰነ ሐሳብ፣ እምነት መቀየርን እና ርዕዮተ ዓለምን መቀየርን ወይንም ከመካከል መራቅን የሚያመለክት፤ በኅብረተሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን ሐሳቦች መቃወምን የሚገልጽ እንደሆነ አስረድተዋል። ወደጽንፈኝነት የሚቃረብ እንደሆነ፤ በአስተሳሰብና በተግባርም ለየት ብሎ መታየትን የሚያመለክትና የንቅናቄ ቡድን መፍጠርን ያሚያሳይ ሐሳብ እንደሆነ ገልጸዋል። አክራሪነት ከፍተኛ መሠረታዊ የፖለቲካና የማህበራዊ ለውጥ የመፈለግ ተግባር እንደሆነ፤ ሥርዓትን፣ ሕገ መንግሥትን ወይንም ፖሊሲን ለመቀየር ወይም ለመተካት እንቅስቃሴ ሲኖር አክራሪነት አለ እንደሚባል፤ በኅብረተሰብ ተቀባይነት ያላቸውን እሴቶች የመለወጥ ከፍተኛ ጥረት የሚደርግ እንደሆነና አብዛኛውን ጊዜ የዚህ መሰል ተግባር ተሳታፊዎች ወጣቶች እንደሆኑ አስረድተዋል።

ወጣቶች በተለያየ መንገድ በሚደረግባቸው ተጽዕኖ የቀደመ ባሕሪያቸውን እንደሚቀይሩና የቀኝ ወይም የግራ አክራሪ ሊሆኑ እንደሚችሉም አንስተዋል። የግራ አክራሪዎች ነጻነትን፣ እኩልነትን እና የመብት መስጠትን የሚያቀነቅኑ፤ ከዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ወደኮሚኒዝም እና ሲሻሊዝም የሥርዓት ለውጥ የሚያቀነቅኑ እንደሆኑ፤ የቀኝ አክራሪዎች ግን ፋሽዝምን፣ ናዚዝምንና መሰል የሥልጣን እና የብሔር የበላይነትን የሚያቀነቅኑ እንደሆኑ አስረድተዋል። ወጣቶች የአክራሪነት ወይንም የጽንፈኝነት ዝንባሌ ሲኖራቸው ሌሎችን የማዳመጥ ፍላጎት እና ፈቃደኝነት ያጣሉ። የተጨቋኝነት ስሜት ይሰማቸዋል። ድብቅ ባሕሪይ ያሳያሉ። በማህበራዊ ሚዲያ ላይ ረጅም ጊዜ ያጠፋሉ። የተለያየ ማንነቶችን በማህበራዊ ሚዲያም ሆነ በገሃዱ ዓለም መጠቀም ሲጀምሩም የአክራሪነት ዝንባሌው እንዳላቸው እንደሚያሳይ አስረድተዋል። በተጨማሪ ሰባት ምልክቶችንም ጠቅሰዋል።

1. በድንገት ከቤተሰብ እና ከጓደኛ መለየት፤
2. በድንገት ትምህርት ማቋረጥ እና ግጭት መፍጠር፤

3. በአመጋገብ፣ በአለባበስ እና በቋንቋ አጠቃቀም ሥርዓት ላይ ለውጥ ማድረግ፤
4. ፀረ መንግሥት፣ ፀረ አምልኮ እና ፀረ ሥርዓት መሆን፤
5. ከማህበረሰብ እራስን ማግለል፤
6. በማህበራዊ ሚዲያ መጠመድ፤
7. ጫፍ የረገጡ አመለካቶችን መደገፍ፤ የአክራሪነት ምልክቶች እንደሆኑ አንስተዋል።

ጽንፈኝነት፡- በፖለቲካ፣ በዘር እና በሃይማኖት ጉዳዮች ላይ በሕዝብ ከተለመደው፣ መንግሥት እና ሕጎች ከደነገጉት ውጭ ያለ አመለካከት እና ድርጊት ነው። በዚህም፣ ከመሀል የራቀ፤ ከሀገር ሕግ እና ደንብ ያፈነገጠ፣ መቻቻልን የማይቀበል፣ አሳታፊ እና ዴሞክራሲያዊ አስተዳደርን የማይቀበል፣ ሥርዓታዊ፣ ማህበራዊ ኑሮን እና ፖለቲካን የማይቀበል ክስተት እንደሆነ ወይም ገዢ ከሆነው የፖለቲካና እምነት ወጣ ያለ አመለካከት እና ድርጊት እንደሆነ የተለያዩ ትርጓሜዎችን በማጣቀስ ፕሮፌሰር ሃብታሙ አስረድተዋል። የአክራሪነት እና የጽኝፈኝነት ክስተቶች በየትኛውም ማህበረሰብ ዘንድ የሚገኙ እንደሆኑና ወደጥቃት አዘል ጽንፈኝነት ከማደጋቸው በፊት ሕዝብ እና መንግሥት ነቅተው ሊጠብቋቸው እንደሚገባ አሳስበዋል።

የጽንፈኝነት ባሕሪይ መገለጫዎች ብለው ካስቀመጧቸው ነጥቦች መካከል፤ በአንድ ማዕከል ጨቋኝ አገዛዝ ማመን፤ በአንድ እምነት፣ ርዕዬተ ዓለም እና አስተዳደር ብቻ እንጂ ልዩነትን የማይቀበሉ መሆናቸው፤ የመቻቻል ባሕሪይ እንደሌላቸው፤ ወደግባቸው ለመድረስ ማንኛውንም መንገድ የሚጠቀሙ መሆናቸው፤ የሚቃወሟቸውን እንደሚያጥላሉ፤ ከቻሉም የማስወገድ ፍላጎት አንዳላቸው፤ የውይይት እና የድርድር ሐሳብ እንደሚፈሩና የሰጥቶ መቀበልን እሳቤ እንደማይፈልጉ አብራርተዋል። በተጨማሪም ጽንፈኛ የሚያደርጉ ምክንያቶች በሚል፦

- ለራሳቸው ያላቸው ግምት ከፍተኛ ወይም ዝቅተኛ መሆን፤
- በሕይወታቸው ከፍተኛ ችግሮች የገጠሟቸው መሆናቸው፤
- በልጅነት ብዙ ስድብ፣ድብደባ እና ችግሮች የገጠሟቸው መሆናቸው፤
- ሌሎችን ለመምሰል የሚጥሩ ወይም ሌሎችን የሚከተሉ መሆናቸው፤
- በድንገት ለጽንፈኛ ፕሮፓጋንዳ መጋለጥ እና የቤተሰብ ክትትል ማነስ ወጣቶችን ወደጽንፈኛ አስተሳሰብ የሚመሩ ምክንያቶች ናቸው በሚል ገለጸዋል።

ሽብርተኝነት ፡- ሕገውጥ ሁከትን፣ ማስፈራራትን በመጠቀም ኅብረተሰብን በማሸበር፣ በማስደንገጥ የአንድን ቡድን የፖለቲካ እንዲሁም ሌሎች ዓላማዎች ለማሳካት የሚደረግ ሕገወጥ ድርጊት ነው። በኢትዮጵያ የጸረ ሽብር ሕግም "የፖለቲካ፣

የእምነት እና የርዕዮተ ዓለም ፍላጎትን ለማሳካት የሀገሪቱን መሠረታዊ ሕግ በማናጋት እገታ እና ጠለፋ የሚያደርጉ ድርጊቶች ናቸው" በማለት እንደሚያስቀምጣቸው ገልጸዋል። የፖለቲካ፣ የእምነት እና የርዕዮተ ዓለም ፍለጎትን ለማሳካት የሚደረግ የጥፋት ተግባር እንደሆነና በነባራዊው የኢትዮጵያ ሁኔታ የጎሳ ጉዳዮች ስሜታዊነት ያለባቸው በመሆናቸው ከአክርሪ/ጽንፈኛ ወደሽብር ጥቃት የማደግ እድል እንዳላቸው አሳስበው፤ ትኩረት ሊደረግባቸው እንደሚገባም ገልጸዋል።

## የጽንፈኝነት አውድ እና ታሪክ

ጽንፈኝነት እና አክራሪነት ሰዎች ሰላምና ደኅንነት እንዳይሰማቸው ያደርጋሉ። በኢትዮጵያ በተደረገ አንድ ጥናት አክራሪ እና ጽንፈኛ የሆኑ እሳቤዎች ወትሮም የነበሩ ቢሆንም፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የዜጎችን ሰላም እያወኩ እንደሚገኙ እንደተረጋገጠ እና የእምነት እና ዘውግ ተኮር ጽንፈኝነት በስፋት እንደተዛመተም ውጤቱ እንደሚያሳይ አንስተዋል። ለጽንፈኝነት ገፊ ምክንያቶች በሚልም የኢኮኖሚ እድል ማጣት፤ መገፋት እና መድሎ መኖር፤ ታሪካዊ ቁርሾ፤ የሕግ የበላይነት አለመከበር እና ሌሎችም ምክንያቶች እንደሆኑ ጠቅሰዋል። ወደጽንፈኝነት ሳቢ ምክንያቶች ደግሞ ማንነትን በአግባቡ አለመረዳት፤ ያልታወቀ የተሻለ ኑሮ ፍለጋ፤ የተሳሳተ የጎሳ እና የእምነት እሳቤ፤ የማህበራዊ ሚዲያ ተጽእኖ እና ልዩነትን ያለመቀበል አመለካከት እንደሚገኙበት አንስተው፤ የጽንፈኝነት እሳቤ ወደአሸባሪነት የመሸጋገሩ እድል ሰፊ እንደሆነም ገልጸዋል። ከላይ የጠቀሱትን የጥናት ውጤት ዋቢ በማድረግም በኢትዮጵያ በ2019 እ.ኤ.አ በማህበራዊ ሚዲያ ከተጋሩ ልጥፎች መካከል ከፍተኛውን ቁጥር የሚይዙት በሃይማኖት እና በጎሳ ጉዳዮች ላይ የተጻፉ እንደሆኑና የጥላቻ ንግግርንም በስፋት የያዙ እንደነበሩ፤ የእነዚህ ጸሑፎች ምንጭም መሆኑን አስረድተዋል።

በመጨረሻም፣ ፕሮፌሰር ኃብታሙ የአፍሪካ ኅብረትን መረጃ ዋቢ በማድረግ ለጽንፈኝነት እና ሽብርተኝነት አስተዋጽዖ ሚያደርጉ ዘጠኝ ነጥቦች እንደሚከተለው ዘርዝረዋል።

1. ዓለም አቀፍ የወንጀል ኃይሎች መኖር እና ድጋፍ ማግኘት፤
2. የጦር መሣሪያ በቀላሉ መዘዋወር፤
3. የውጭ ኃይሎች እና የውስጥ ባንዳዎች መተባበር፤
4. በተለያዩ የአፍሪካ ሀገራት ውስጥ የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ ያለመኖር፤
5. በየሀገራቱ የአስተዳደር በደል መኖር፤
6. የገቢ ማጣትና የድህነት መስፋፋት፤

7. በዜጎች መካከል እኩልነት ያለመኖር፤
8. የሃይማኖትን ትምህርቶች ሆን ብሎ ማንሻፈፍ፤
9. አቅመ ቢስ፣ ደካማ የሕግ አስከባሪ መኖር፤

ከፕሮፌሰር ኃብታሙ ገለጻ በተጨማሪ "ጽንፈኝነት ከደኅንነት፣ ከሥነጥበብ እና ከሚዲያ አኳያ" በሚል በሌሎች ባለሙያዎች ገለጻ ተደርጓል። በዚህም መሠረት ዶ/ር ቃልአብ ታደሰ የጽንፈኝነትን እና የአክራሪነትን ሐሳብ ከደኅንነት አኳያ ሲያስረዱ፤ እኛ በምንገኝበት ምሥራቅ አፍሪካ እና በሌላውም ዓለም ጽንፈኝነትን እና የአሸባሪነትን ከጅምሩ እስከፍሬው እንዳየነው አንስተው፤ አጥባቂነት ሦስት ዓይነት እንዳለው ገልጸዋል። የመጀመሪያው ለዘብተኛ (Passive) አጥባቂ የሚባለው እንደሆነ፤ ይህም ቡድን የራሱን ማንነት በመውደድ በስፋት የራሱን መገለጫዎች የሚጠቀም፤ ሁለተኛው "አሰርቲቭ" (Assertive) አጥባቂ እንደሆነና ይህም፣ የርሱን ሐሳብ ወይም ማንነት/አስተሳሰብ ሌሎች እንዲቀበሉት የሚፈልግ፤ ነገር ግን ይህን ፍላጎቱን በኃይል ማስፈጸም የማይፈልግ ቡድን ነው። ሦስተኛው ደግሞ ሌሎችን አስገድዶ መለወጥ የሚፈልግ ዓይነት አጥባቂነት እንደሆነ አስረድተዋል። አክራሪነት እና ሽብርተኝነት በጥቂት ሰዎች፣ በአጥፍቶ ጠፊዎች ወይንም በተዋጊዎች ብቻ የሚራመድ ሐሳብ እንዳልሆነ፤ ከእነዚህ ጥቂቶች ጀርባ ዓላማውን የሚደግፍ እና በተለያየ መንገድ የሚያበረታታ ሰፊ የማህበረሰብ መሠረት ያለው እንደሆነ አስረድተዋል። በተጨማሪም፣ ሽብርኝነት በሂደት የሚሰፋ ነገር እንደሆነና ሰዎችም በአንዴ የሚቀላቀሉት እንደልሆነ፤ ነገር ግን በግለሰቦች ላይ በሚፈጠሩ ድንገተኛ (catalysts) ክስተቶች ምክንያት የሚገቡበት እንደሆነ እና የደካማ መንግሥት መኖር ለሽብርተኝነት ምቹ አጋጣሚ መሆኑን፤ ይህንን ለመከላከልም ጠንካራ የደኅንነት ሥርዓት መገንባት እንደሚያስፈልግ አሳስበዋል።

ጽንፈኝነት ከሚዲያ አንጻር በሚል ሐሳብ የሰጡት ረዳት ፕሮፌሰር መኩሪያ መካሻ ደግሞ፣ ጽንፈኝነት የግጭት እና የጥላቻ ተግባር የሚከተል መሆኑን አንስተዋል። ለእነዚህ ክስተቶች በሚዲያው ላይ አጻፋዊ ትርክቶች ሊዘጋጁላቸው እንደሚገባም አሳስበዋል። በዚህና መሰል ሁኔታዎችም አንድ ዓይነት መንገድ የተግባቦት ስልት ከሚከተል ይልቅ በምክክር የሚዳብር (constructive communication through dialoge) የሚባለውን ዓይነት የተግባቦት ስልት መጠቀም እንደሚገባና በሂደቱም እራስን ማወቅ ጽንፈኞችን ማንነት እና ፍላጎት መረዳት/ማወቅ፤ እንዲሁም አውዱን በሚገባ በመረዳት ስትራቴጂ ነድፎ መሥራት ይገባል ብለዋል። ሚዲያው እራሱ ከጽንፈኛ እሳቤ እና ተግባር የጸዳ እንዲሆን መከታተል ያስፈልጋል። ለዚህም፣ የሚዲያ ፎረም ተቋቁሞ ጉዳዩን በዘላቂ መንገድ

መከላከል እና ለሕዝብም ማስተማር እንደሚገባው ገልጸዋል።

ሌላው ተናጋሪ ዶ/ር ጌታነህ መሐሪ፣ በሀገራችን ፖለቲካ ውስጥ የብሔርን ማንነት እንደመቀስቀሻ በመጠቀም የተጠቂነትና የብሶት ስሜት መጫሪያ ሆኖ ጥቅም ላይ እየዋለ እንደሆነ አንስተው፤ ማንነትን መሠረት ያደረጉ ፋክክሮች፣ ጥላቻ፣ አለመተማመን፣ ጥቃት መፈጸም፣ ማፈናቀልና የመሳሰሉ ድርጊቶች ስንመለከት፤ የብሔር ጽንፈኝነት እያቆጠቆጠ ነው ወደሚለው እሳቤ ውስጥ እንደሚገባ ገልጸዋል፡ ፡ እንደመፍትሔም ባለድርሻ አካላት የሚባሉት የባህል እና የቋንቋ ብዝሃነት እውነት እንደሆነ ሁሉ በባህሎች መካከል ያለውን መመሳሰል ማሳየት ይገባል። የሚያስተሳስሩንን እሴቶች ማጉላትም ተገቢ ነው። የፖለቲካ ልሂቃን የማንነት ፖለቲካን ከዴሞክራሲ ጋር ማስተሳሰር ይገባቸዋል። እንዲሁም ጭቆናንና ኢፍትሐዊነትን በማንኛውም ጊዜና ቦታ መቃወም ያስፈልጋል ብለዋል።

በመጨረሻም፣ ከተሳታፊዎች፣ በአጥባቂነት/ጽንፈኝነት መደቦች መካከል ከመጀመሪያው ወደሁለተኛው ዓይነት በሚደርግ ሽግግር ሚዲያ ጥቅም ላይ ይውላል። ለዚህም እንደኅብረተሰብ እራሳችን ወደሰዋዊነት፣ እንደመንግሥት ደግሞ ሚናውን ሕግ ማስከበር ላይ በመሥራት ወደትክክለኛው መንገድ መመለስ አለብን። ማህበረሰቡ በየትኛውም መንገድ የሚያያቸውን ጽንፈኛ ሐሳቦች ማውገዝ ይገባዋል። ፖለቲከኛውም ከመገፋፋት ፖለቲካ ወጥቶ ወደውይይት መግባት አለበት። ከኋላ ታሪካችን ልንወስደው ሚገባንን ነገር እድንለይ፣ ካለፈው 40ና 50 (ዐርባና ኀምሣ) ዓመታት የፖለቲካ ታሪክ ውስጥ ያገኘነው ትርፍ እና ኪሳራ እንዲታሰብበት፤ እንዲሁም፣ በትምህርት ውስጥ ትውልድ እንዴት ይገነባል? የሚለውንም ልናስብበት ይገባል። ቤተ እምነቶች እና የእምነት አባቶችም መሥራት በሚገባቸው ትውልድን በመቅረጽ ሥራ ላይ ማተኮር አለባቸው የሚሉ ሐሳቦች ተነስተዋል።
በመጨረሻም ፕሮፌሰር ኃብታሙ ሚዲያው ከፍተኛ ሚና እንዳለው አውቆ የሚገባውን እንዲሠራ፤ የማህበረሰብ ውይይት የሚባለውን የውይይት መንገድም ጽፈኝነትን ለመከለከል ልንጠቀምበት እንደሚገባ አሳስበዋል።


የጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት
Federal Democratic Republic of Ethiopia







# 4.6.2 ክፍል ሁለት
# የጽንፈኝነት መገለጫዎችና አሉታዊ ውጤቶች

በዚህኛው የውይይት ክፍል በ"ጽንፈኝነት መገለጫዎችና አሉታዊ ውጤቶች" በሚለው ርዕስ ላይ የመወያያ ሐሳብ ያቀረቡት ፕሮፌሰር ጀይላን ወልዩ ከሐሮማያ ዩኒቨርሲቲ፣ ዶ/ር ምሕረት ደበበ የአፍሪካ ልህቀት አካዳሚ ፕሬዚዳንት፣ እንዲሁም ዶ/ር ሰለሞን ተሾመ ከባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህር ናቸው። ውይይቱን የመራችው የኢትዮጵያ ብሮድካስት ኮርፖሬት ጋዜጠኛ ዓመት ራህማን አሕመድ ነች።

## የጽንፈኝነት ሥነልቦናዊ መገለጫዎች

በቅድሚያ ዶ/ር ምሕረት ደበበ ስለጽንፈኝነት ሥነልቦናዊ መገለጫዎች ገለጻ አድርገዋል። እርሳቸውም፤ ጽንፈኝት በሁላችንም አስተሳሰብ ውስጥ ያለ ጉዳይ እንደሆነ አንስተው፤ መንስኤዎቹም፣ ሰዎች ስለፖለቲካ፣ ስለቀለማቸው፣ ስለዘራቸው፣ ስለብሔራቸው ወይንም ስለሌሎች ከቤተሰብ የወረሷቸው ወይም መርጠው የራሳቸው ያደረጓቸው፤ ነገር ግን ለመቀየር የማይችሏቸው እሳቤዎች እንደሆኑ አስረድተዋል። ጽንፈኝነት ከሥነልቦና አንጻር በተፈጠሩ ሁኔታዎች ያለን እይታ ችግሩን እንደሚያባብሰው ወይንም ደግሞ ችግሩን ተረድተን የመፍትሔው አካል እንዳንሆን እንደሚያደርግም አስረድተዋል። ሰዎች በተለያየ አጋጣሚ ከላይ በተዘረዘሩት ጉዳዮች ላይ በሚፈጠርባቸው መዛነፍ ምክንያት ተበሳጭተው ጥግ ላይ ያለውን ክፉ ነገር ለማድረግ ያስቡና በኅብረተሰብ ላይ የሚደርሰውን መጥፎ ጥፋት ሲያስቡ ግን ወደትክክለኛው ልቦናቸው ተመልሰው ነገሩን የሚተውበት ሁኔታ እንዳለም ገለጸዋል።

ዓለም አንድ ሰው ለብቻው የሚኖርባት እንዳልሆነች መረዳት፤ ጽንፈኛ ከሆኑ፣ "ለእኔ ብቻ" ከሚሉ እሳቤዎች በመውጣት የሰው ልጅ መሠረታዊ ሕይወቱ የሆነውን ከሰዎች ጋር ትስስር የመፍጠር እና የመዋደድ ፍላጎቱን ተቀባይነት ባለው መንገድ ማስኬድ እንዳለበት አንስተው፤ ይህን ፍላጎት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይት ባለው መንገድ ማስኬድ አለመቻል ግን ጽንፈኛ የሚባሉት እሳቤዎች መገለጫ እንደሆነ ገልጸዋል። ጽንፈኝነት በጫካ ውስጥ ብቻ ሳይሆን በእኛ ሰብእና ውስጥም የሚኖር ነገር እንደሆነ

መረዳት ይገባል ብለዋል። ልዩነቱ ተገርቶ ከሌሎች ጋር አብረን እንድንኖር ማስቻሉ ወይንም አለመገራቱ እና ችግር ፈጣሪነቱ እንደሆነ አብራርተዋል።

በኢትዮጵያ ነባራዊ ሁኔታ ጽፈኝነትን በተመለከተ መካከለኛውን መንገድ የሚመርጡትን ሰዎች "መሃል ሰፋሪ" እና መሰል ስሞች በመስጠት በማጥቃት የግድ ወደአንዱ ጫፍ እንዲጠጉ የማድረግ ህብረተሰባዊ ልማድ እንዳለ፤ ይህም ጽንፈኛ የሆኑ ባሕሪይዎችንና እሳቤዎችን የሚያበረታታ እንደሆነ አንስተዋል። በሌላ በኩል፣ የጽንፈኝነት መገለጫዎች የሚባሉት ሰዎች ከሌሎች መሰሎቻቸው ጋር አብረው ለመኖር በሚያደርጓቸው ትስስሮች ውስጥ እንደሚታዩም አንስተው፣ ከስቃይ ለመውጣት የሚደረግ ጥረት፤ በሌሎች የተነገረን ደስታ፤ ገንዘብ ወይም መልካም ስም እና ዝና በሕይወት ዘመን ወይንም ከሞት በኋላ ለማግኘት ሲባል ወይንም ደግሞ በሙያ፣ በጾታ፣ በእምነት እና በሌሎች መሰል ተረኮች ብልሽት ምክንያትም ሊገባበት እንደሚቻል አስረድተዋል። ልጆች እና ወጣቶች ለዚህ ጉዳይ ከፍተኛ ተጋላጭነት እንዳላቸውም አሳስበዋል። ነገር ግን፣ ሁሉም ለእነዚህ ጉዳዮች የተጋለጠ ወጣት ሁሉ ጽንፈኛ ይሆናል ማለትም እንዳይደለ ገልጸዋል።

ዶ/ር ምሕረት፣ ጽንፈኝነት በልዩነት መብዛት ብቻ የሚመጣ ነገር አይደለም። ነገር ግን በሰዎች ግለሰባዊና ማህበረሰባዊ ፍላጎት ላይ ያተኮረ ነገር ነው ብለዋል። የበታችነት ስሜትም ዋነኛ መንስኤው እንደሆነ፤ "የበታችነት ስሜት" ያላቸው ሰዎች ይህን ስሜታቸውን ለመሸፈን "የበላይነት ስሜት" እንደሚፈጥሩና የሌላውን ማጣጣል እና እራስን የበላይ አድርጎ የመግለጽ ዝንባሌ እንደሚታይባቸው ገልጸዋል። ሰዎች በጽንፈኛ እሳቤ ውስጥ ሲገቡም "እኔ የተነጠቅሁት ነገር አለ" በሚል የተነጠቁትን ነገር ለማሳደግ ከመሥራት ወይም ከመሞከር ይልቅ "ሌሎች ብዙ አላቸው" ብለው ወይም ነጥቀውኛል ብለው የሚስቧቸውን ሰዎች ነገር ሁሉ ማጥፋትን እንደመፍትሔ እንደሚወስዱ ገልጸው፤ ብቸኝነት፣ ተቀባይነት ማጣት፣ የዝምድና እጦት እና መሰል ሁኔታዎች "ስለተገፋሁ የገፋኝን ሥርዓት አፈርሰዋለሁ" ወደሚል ጽንፈኛ አስተሳሰብ እንደሚያስገባ አስረድተዋል።

መፍትሔውም፣ ቅድሚያ የችግሩን ክብደት ማወቅ፤ በቀጣይም የጽንፈኝነቱን መሃንዲሶች፣ መሪዎች፣ መንጋዎች እና በመጨረሻ ላይ ያለውን ሕዝብ በመለየት ጉዳዩን ለመቀልበስ በሚያስችል መንገድ መሥራት ነው ብለዋል። በመሪ ደረጃ ሐሳቦች ሲፈጠሩ በጊዜ ለይቶ የግለሰቦችን ችግር መፍታት ወይም ከኋላቸው ያለውን አባባሽ ምክንያት ማከም እንደሚገባና መንጋውን፣ በአለማወቅ ታሪክ እና በሚዲያዎች

ምክንያት የሚገባውን በተለይ ወጣቱን ከመሪው መለየት እና ተጋላጭ እንዳይሆን ማድረግ ተገቢ ነው ሲሉ አሳሰበዋል።

## ጽንፈኝነት ከፖለቲካ አንጻር

በዚህ ርዕስ ዙሪያ ሐሳባቸውን ያጋሩት ፕሮፌሰር ጀይላን ወልዩ ናቸው። እርሳቸውም፣ ጽንፈኝነት ውስጠ ስሪቱ ፖለቲካ እንደሆነና ጽንፈኝነትን በመጠቀም የተለየ የፖለቲካ ወይም የኢኮኖሚ ፍላጎትን ለማሳካት የሚደረግ እንቅስቃሴም እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ ፖለቲካዊ ጽንፈኝነት አብዛኛው የማህረሰብ ክፍል የማያምነውን፤ የማይቀበለውን የቡድኖች ሐሳብ ጫና በመፍጠር፤ በማስፈራራት የማስፈጸም ሂደት እንደሆነ አስረድተዋል። ጥቃት አዘል ጽንፈኝነት (Violent Extremism) በፖለቲካ ጽንፈኝነት ውስጥ የሚንጸባረቅ እንደሆነ፤ ከምክንያታዊ ፖለቲካ ይልቅ በስሜታዊ ፖለቲካ ላይ በማተኮር እንደመቀስቀሻ እንደሚጠቀሙበት እና በተወሰኑ ጉዳዮች ላይ ብቻ ትኩረት እንደሚሰጥ፤ እነዚህም፣ የብሶት ስሜት፣ የእጦት ስሜት እና የተበዳይነት ስሜት ሲሆኑ እነዚህን በማሳደግ መቀስቀሻ መሣሪያ እንደሚያደርግ ገልጸዋል።

የፖለቲካ ጽንፈኝነት እንቅስቃሴ ውጤት የዴሞክራሲ እሴቶችን ያፈራርሳል። እንደኛ ሀገር ባሉ የሦስተኛው ዓለም ሀገራት ድኅነት፣ የታሪክ ሽሚያ እና አለመስማማት፣ እንዲሁም በማንነት እና በታሪክ ዙሪያ በሚፈጠሩ አወናባጅ ትርክቶች ምክንያት የብሔር ጽንፈኝነት ሊፈጠር እንደሚችል አስታውቀዋል። የብሶት ፖለቲካ፣ የስጋት ፖለቲካ እና የተሰፋ ፖለቲካ የብሔር ጽንፈኞች ለመቀስቀሻነት የሚጠቀሙባቸው ሐሳቦች እንደሆኑ ፕሮፌሰር ጀይላን አስረድተዋል። የጽንፈኝነት ፖለቲካ ልሂቃን የሚመሩት እንደሆነ፤ የብሔር ጽንፈኝነት በሂደት የማህበረሰብን የባህል ውቅሮች የሚያፈርስ እንደሆነና "የእኛ እና የእነርሱ" አሳቤን በመፍጠር "ሌሎች" በሚል የሚፈርጃቸውን ቡድኖች ጭራቅ አድርጎ በመሳል (Demonization,de-humanization) ለውድመት እና ለጥቃት እንደሚያመቻችም አስረድተዋል፡፡ የብሔር ፖለቲካ ሃይማኖትን እና የብሔር እሳቤን አጣምሮ የሚራምድ እንደሆነ ጠቅሰው፤ የፖለቲካ ጽንፈኝነትን ለመከላከል ውይይቶች ከላይ ጀምሮ እስከሕዝቡ ድረስ መደረግ እንደሚገባቸው እና (pragmatism, realism and Centerism) ማዕከላዊነትን የመሰሉ ሁሉንም ወደመሀል የሚያመጡ እሳቤዎች መከተል እንደሚገባ አሳስበዋል።

የሃይማኖት ጽንፈኝነት

ሌላኛው የውይይት ሐሳብ አቅራቢ ዶ/ር ሰለሞን ተሾመ "የሃይማኖት ጽንፈኝት በአብዛኛው ሃይማኖታዊ እሳቤ መሠረት  በማድረግ የራስን  ሐሳብ፣ ፍላጎት እና ትርጓሜ በሌላው ላይ በኃይል  ለመጫን እና በሕዝብ ዘንድ በስፋት ተቀባይነት ያገኘን የአስተሳሰብ ሥርዓት ለመታገል የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው" የሚል ትርጓሜ ትርጓሜ ሰጥተውታል። የሃይማኖት ጽንፈኝነት ሙሉ በሙሉ ሃይማኖታዊ ብቻ ሳይሆን፤ በፖለቲካ እና በማህበራዊ ጉዳዮች ተገፍተናል ወይም በደል ደርሶብናል የሚሉ ሰዎችን ለማሰባሰብ ኅብረት እና አንድነት ለመፍጠር ሃይማኖትን የሚጠቀሙበት እንደሆነ፣ የፖለቲካ ርዕዮት ዓለሞች ያለባቸውን ክፍተት በመረዳት ሃይማኖትን ትርጉም ያለው ትርክት ለመፍጠር ይጠቀሙበታል። የሃይማኖትን ሕግጋት በመውሰድም ለእነዚያ ሕግጋት ጠበቃ የቆመ በመምሰል ምክንያታዊነትን ለማግኘት፤ እንዲሁም የሃይማኖት ግጭቶችን በመፍጠርም ቀደም ሲል የነበረን ወይንም ወደፊት የሚገኝን ማህበራዊ፣ መንፈሳዊ እና የሰማያዊ ዓለም ክብር ለማግኘት እንደሚጠቀምበት አስረድተዋል።

የሃይማኖት ጽንፈኝነት፦ ሥነመለኮታዊነት፣ ከሃይማኖት መጻሕፍት የተገኙ ሐሳቦችን ወደሚፈልጉት ትርጓሜ በመውሰድ ለድርጊታቸው ራዕይ አዘል መንፈሳዊ ትረካዎችን በመፍጠር ሞራላዊና ምክንያታዊነት ለመያዝ መሞከር፤ ከእነርሱ ውጭ ያለውን ቡድን አይታገሱም፤ ልዩነትን አይቀበሉም፤ "ኢ-ሞራላዊ እና ስህተት" ያሉትን ለማጥፋት እና ሁሉም እንደእነሱ እንዲያስብ መሞከር፤ በቀጣት ያምናሉ፤ ቢችሉም ሌሎችን ያጠፋሉ፤ እራሳቸውን የፈጣሪ ተቆርቆሪ አድርገው ያስባሉ፤ ፈጣሪም የእነርሱን እርዳታ እንደሚሻ ማሰባቸው መገለጫ ባሕሪያት እንደሆኑ አብራርተዋል። ከሥርዓተ ከበራዊ (Ritual) ወይንም የጋራ አምልኳዊ እና የእርስ በርስ  ስሜቶች አንጻርም እነዚህ ሁነቶች በቀጥታ በፈጣሪ እንደሚመሩ ያምናሉ። ሥረዓተ ከበራዎቹ ከባህል፣ ከልምድ እና ከእድገት ጋር የማይቀላቀሉ ንጹህ እንደሆኑ አድርገው ያስበሉ። ከባህል እና ከልምድ ጋር የተቀላቀሉትን የሚፈጽሙትን "ኃጢያተኛ" እና "ከሀዲ" አድርገው እንደሚያሰቧቸው ገልጸዋል።

የሃይማኖት ጽንፈኞች እርስ በራሳቸው በሌሎች ላይ ያላቸውን የእውቀት፣ የመስዋዕትነት የበላይነት ለማሳየት እንደሚሞክሩ፣ ሌሎችን ለመፈረጅም ቅርብ እንደሆኑና በሃይማኖታቸው ውስጥ የሚነሱ አዳዲስ አሰተሳሰቦችን ሃይማኖታቸውን ለማፍረስ የታሰቡ አድርገው እንደሚወስዱ ገልጸዋል። ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ደግሞ ለመቀራረብ ፍላጎት የላቸውም። በፊት የነበራቸውን ማህበራዊ ሕይወት ሙሉ በሙሉ ያቋርጣሉ፤ ሌሎችን ሃይማኖቶች ይንቃሉ፤ ተከታዮችንም አያከብሩም፤

ለእነርሱ እምነት "ጥሩ አይደሉም" የሚሏቸውንም ነገሮች እንዳይከወኑ ይሞክራሉ ብለዋል። የሃይማኖት ጽንፈኞች ፖለቲካዊ መገለጫቸውም የሃይማኖት ሕግጋት ለፖለቲካ ሥርዓት መመሪያ እና መተዳደሪያ እንዲሆኑ መፈለጋቸው ነው። የፖለቲካን ሥርዓት በኃይል ለማፍረስ ይጥራሉ። የሃይማኖት ጽንፈኝነትም ድርጅታዊ እና መዋቅራዊ ቁመና እንዲኖረው ይታገላሉ። ሃይማኖትን ከሀገር፣ ከጎሳ፣ ከብሔር እና ከጾታ ጋር በማጣመር ለመቀስቀሻነት ይጠቀሙበታል። እንዲሁም፤ ግጭት አዘል ጽንፈኝነት በመፍጠር ግጭቱን ለሃይማኖታቸው የሚከፈል ተጋድሎ አድርጎ የመውሰድ ግንዘቤ እንዳላቸውም ዶ/ር ሰለሞን አስረድተዋል ።

የሃይማኖትን ጽንፈኝነት የሚያባብሱ ያሏቸውን ምክንያቶችም ሲጠቅሱ፤ ውስጣዊ አድሎ፣ መገለል፣ መገፋት፣ የበታችነት መንፈስ፣ የበላይ የመሆን ፍላጎት፣ የተጎጅነት መንፈስ እና ሃይማኖቱን በጥልቀት ያለማወቅ ውስጣዊ ምክንያቶች እንደሆኑ አስረድተዋል። ውጫዊ ምክንያቶች ደግሞ የሌሎች ቅስቀሳዎች፣ የገንዘብ እና የሞራል ድጋፍ፤ እና የሀገራት የፖለቲካ ሥርዓት እና ዓለም አቀፋዊ ሁኔታዎች ናቸው ብለዋል። የመንግሥት ደካማነት፣ የሕግ የበላይነት አለመከበር፣ የሙስና እና የወንጀል መስፋፋት ደግሞ አውዳዊ ምክንያቶች መሆናቸውን አስረድተዋል። መፍትሔ ይሆናሉ ያሏቸውን ሐሳቦችም አጋርተዋል። እነዚህም፦

• ጽንፈኝት በሁሉም ሃይማኖቶች እንደሚኖር መረዳት፤
• የቡድን/ግለሰብ መገለጫ በመሆኑ ከየትኛውም ሃይማኖት ጋር አለማገናኘት፤
• በሀይማኖት ጽንፈኝት ላይ የሚደረጉ ጥናቶችን እና ውይይቶችን ማበራከት፤
• በሃይማኖት ተቋማት መካካል ተግባራዊ የእርስ በርስ ግንኙነት መፍጠር፤
• ከብሔር ጽንፈኝነት ጋር ትስስር ስላለው ሁለቱንም የመከላከል ሥራ መሥራት፤
• በመከላከል ሥራ ላይ የሃይማኖት፣ የባህል መሪዎችን እና ሽምግሌዎችን ማሳተፍ፤ የባህላዊ እምነቶችን እና ወጣቶችንም አለመዘንጋት፤
• በጉዳዩ ዙሪያ እንዲመክት፤ አጸፋዊ ምላሽ እንዲሰጥ የባለሙያዎች ቡድን (ThinkThank) መመሥረት፤
• ፖለቲከኞች የሚሰጧቸው መግለጫዎች የሃይማኖት ቃላት እና ትዕምርቶች እንዳይኖራቸው ማድረግ እና በእምነቶች መካከል ያሉትን ትስስሮች በማጥናት የሚያስተሳስሩትን እሴቶች መለየት ነቸው።

በአጠቃላይ፣ ኢትዮጵያውያን ሁሉንም እምነቶች ስንቀበል በተለያየ መንገድ ከራሳችን ባህል እና ሌሎች ሁኔታዎች ጋር በማስተሳሰር ስለሆነ እነዚህን የእኛ የሆኑ ነገሮች በመለየት እና በጋራ ከሌሎች ሃይማኖቶች ጋር የምንጋራቸውን እሴቶች በመለየት

ጽንፈኝነትን ለመከላከል ልንጠቀምባቸው ይገባል ብለዋል።
ከዚህ በተጨማሪ ሦስት ባለሙያዎች ሐሳብ አቅርበዋል። አቶ ታደሰ መገርሳ የጥላቻ ንግግርን እና የቡድን ጽንፈኝነትን በተመለከተ፤ ቡድኖች በቡድኖች መካከል በሚደረግ ወይይት የቡድን ጽንፈኝነት (group polrizetion) እንዲሁም ግለሰቦች ተመሳሳይ እሳቤ እና ምልከታ (Value and belief) ኖሯቸው ውይይት ሲያደርጉ ከውይይታቸወ በፊት ከነበሩበት ሁኔታ በላይ ከውይይቱ በኋላ በጣም ጽንፈኛ የመሆን ምልክቶች ያሳያሉ ብለዋል። ይህም ሰዎች በሌሎች ለመወደድ ባላቸው ፍላጎት ምክንያት (Normative social influnces) ላለመነቀፍ በውይይቱ የተነሳውን ሐሳብ ስለሚቀበሉ ወይም ከውይይቱ በፊት ደብቀውት የነበረ ምልከታቸው በውይይቱ በሌሎች ሰዎች ሲነሳ ነጻነት ተሰምቷቸው በግልጽ የጽንፈኝነት አመለካከታቸውን እንደሚያራምዱ አስረድተዋል።

ሌላው ባለሙያ ዶ/ር አንተነህ ጸጋዬ ደግሞ ጠርዘረኝነት/ጽፈኝነት እንደኛ ባሉ ብዝሃ ባህል ባላቸው ሀገራት እንደሚኖርና ምክንያቱም ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ሊሆን እንደሚችል አንስተው፤ ዘረኝነት የሚመነጨው ባለመተዋወቅ እንደሆነ ተናግረዋል። ለዚህም ከአንዱ ባህል ወደሌላው ባህል ግንኙነት በይነ-ባህላዊ ትምህርት (intercfuture cultural learning) ባለመኖሩ እንደሆነና ይህም በሁለት ቡድኖች መካከል ጥራጣሬን፣ ጥላቻን፣ እና ጠርዘኝነትን ከፍ ሲልም ሽብርን ሊፈጥር እንደሚችል አስረድተዋል። ለዚህም አንድ ዜጋ ወደሌላ አካባቢ ሄዶ ተግባብቶ መኖር የሚያስችሉትን "መቻቻል"ን የመሰሉ ክህሎቶች እንዲያዳብር ማድረግ እና ቋንቋን ማስተማር እንደሚገባ፤ እንዲሁም ጠርዝ ላይ ያሉ ሐሳቦችን ለማጥፍት ከመሞከር ወደመሐል እንዲመጡ መሥራት እንደሚገባ አሳስበዋል።

ዶ/ር ኬረዲን ተዘራ በበኩላቸው፣ ጠርዘኝነት አሉታዊ ተጽዕኖዎቹ በሂደት ወደድርጊት በመሄድ ወደግጭቶችና ጥቃቶች እያደገ እንደሆነ አንስተው፤ ማህበራዊ መስተጋብሮችም በአካባቢያዊ ማንነት ላይ የተመረኮዙ እንደሆነ፤ ጽንፈኝነት ለውጥን እንደሚበላም ገልጸዋል። ሌላኛዋ ባለሙያ ዶ/ር መስከረም፣ ጽንፈኝነት በልማት ወደኋላ መቅረት ምክንያት የሚመጣ ነው። ለእነዚህ ድርጊቶች ከውጭ የሚገኘው የገንዘብ ማበረታቻ ብዙ በመሆኑም ተሳታፊዎች እየበዙ ይሄዳሉ። ከፍተኛ የሥራ አጥ ቁጥር መኖሩም አባባሽ ምክንያት እንደሆነ ገልጻዋል።

የውይይቱ ተሳታፊዎችም፣ በፊት የነበረው የሃይማኖት እና የብሔር ትስስር ተንኮል ተሠርቶበት እንዲሸረሸር እንደተደረገና ወደነበረበት ለመመለስ የሕዝቡን ማህበራዊ

ኑሮ፣ እሴቶች እና ባህላዊ እውቀቶች መጠቀም እንደሚገባ አስተያየት ሰጥተዋል። የፓኪስታኗ መሪ ቤናዚር ቡቶ “ጽንፈኝነትን ለመከላከል ሕዝቡን ወደሥራ ማምጣት፣ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ማምጣት እና የፓኪስታንን እሴቶችን ማስቀመጥ” እንዳሉት፤ ማህተመ ጋንዲም “ድኅነትን ለመቅረፍ በሥራ የተጠመደ ሕዝብ እና መደማመጥ የተጎናጸፈ ሕዝብ ጽንፈኝነት አይገባውም” ያሉትን ሐሳብ መጠቀም፤ እንዲሁም ጥሩ መምህራን እና ሽማግሌዎች የመሐሉን መንገድ ስለሚያሳዩ በእሱ ላይ መሥራት ይገባል፤ የሚል ሐሳብም ተነስቷል። “ወርቃማው መንገድ” ከእምነት አንጻር አምላክ የሰጠውን ሕግ ወይም ሕይወት መኖር ሲቻል እንደሆነና ሁሉም ሃይማኖቶች “በአንተ ላይ እንዲሆን የማትፈልገውን በሌሎች አታድርግ” የሚለውን መርህ ለብሔር እሳቤውም መጠቀም እንደሚቻል እና ትክክለኛውን የብሔር ማንነት፣ የኢትዮጵያዊነትም ሌሎችም ምን ማለት እንደሆኑ መለየት እንደሚገባ ሐሳብ ቀርቧል።

በመጨረሻም፣ ሐሳብ አቅራቢዎቹ በሰጡት ማጠቃለያ፤ ጽንፈኞች ሰፍረው ከሚሰጡን ማንነት ራሳችንን መከላከል ይገባል። ሰዎች ትክክለኛ ማንነታቸውን እንዲያገኙ መሥራትም ተገቢ ነው። የተጎዳውን የልዕልና ውቅር ማከምም ተገቢ እንደሆነ ሐሳብ ሰጥተው ለግጭት ነጋጃዎች በጥናት የተደገፈ መፍትሔ መስጠት ያስፈልጋል ብለዋል። ሃይማኖታዊም ሆነ ብሔር - ተኮር ጽንፈኝነት የሚንጸባርቅባቸው መንገዶች ብዙ እንደመሆናቸው እንደየሁኔታው ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል፤ ብለዋል። ዶ/ር ምሕረት ከሥነልቦና አኳያ ማንነቱ በጽንፈኛ አስተሳሰብ ለተጠቃበትና በመንጋው መሐል ላለ ሰው ሊደረግለት የሚገባው ነገር ጥያቄ መጠየቅ እንዲችል ማድረግ እንደሆነና ብዙ ጥያቄ መፍጠር ከቻልን የመሃንዲሱን ጉልበት መሪውን፤ የመሪውን ጉልበት ደግሞ መንጋውን ማሳጣት እንደሚቻል አስረድተዋል። ከውጭ የሚመጣውን ጫና በተመለከተም፤ እነዚህን መሰል ጫናዎች መመከት የግለሰብ ኃላፊነት ሳይሆን፤ “እንዴት መጣ? ምንድነው?” የሚለውን ከፍ ያለ ኃላፊነት ባላቸው የአዋቂዎች ቡድን ቢሠራ እንደሚመከር ሐሳብ ሰጥተዋል።

በማጠቃለያም፣ ዶ/ር ሰሚር የሱፍ በጽንፈኛነት እና አማካዩን ፍለጋ ላይ የተያያዙ ሁለት የተለመዱ፣ ልክ ያልሆኑ ሐሰቦች፤ ማለትም መካከለኛውን መንገድ የመፈለግ ጉዳይ የአቋም የለሽነት ወይንም ጥልቀት የሌለው እሳቤ እንደሆነ አድርጎ የመውሰድ እና ሞራላዊ ስሜቶች የማይነቃነቁ መሆን (moral indifference) ማለት እንዳልሆነም አንስተዋል። “ጠርዘኛነትን እና መካከለኛውን መንገድ መፈለግን” ለይቶ ማስቀመጥ እንደሚገባና ሞራላዊ ስሜት ያለው፤ በአስተሳሰብም ጥልቀት ያለው መካከለኛ መንገድ ፍለጋ ላይ በትኩረት ሊሠራ እንደሚገባ አሳስበዋል።









## 4.6.3 ክፍል ሦስት
## ጽንፈኝነትን የመከላከል ርምጃዎች

ከዚህ ቀደም የተካሄዱት ሁለት የውይይት መድረኮች በአክራሪነት እና በጽንፈኝነት መካከል ያለውን ልዩነት እና አንድነት፤ እንዲሁም በመገለጫዎቻቸው ላይ በባለሙያዎች እና በተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት የተደረገባቸው ናቸው። በዚህ በሦስተኛው ክፍል የአዲስ ወግ አብይ ጉዳይ ውይይት ፕሮግራም ደግሞ ጽንፈኝነትን ለመከላከል በመንግሥት ምን ምን ርምጃዎች እየተወሰዱ እንዳለ ውይይት ተደርጎበታል። በመደረኩ የመወያያ ሐሳብ ያቀረቡት፤ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ፣ የመንግሥት ተጠሪ ሚኒስትር፣ አቶ ብናልፍ አንዷለም፣ የሰላም ሚኒስትር እና አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደኅንነት አማካሪ ሲሆኑ፤ ውይይቱን የመራችው ደግሞ ሳልሳዊት ባይነሳኝ፣ የዋልታ ሚዲያ ጋዜጠኛ ነች።

### ጽንፈኝነትን ለመከላከል በመንግሥት እየተደረጉ ያሉ ተግባራት

በብልጽግና አስተዳደር በተጀመረው የለውጥ እንቅስቃሴ ውስጥ የለውጡ መሠረታዊ ምሰሶ ተደርጎ ሚወሰደው ለውጡን ሁሉን አቀፍ አድርጎ ማስፈጸም ነው። በዚህም መሠረት በማህበራዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ የአስተዳደርና የጸጥታ ዘርፎች ላይ በተመሳሳይ ለውጥ እየተደረገ እንደሚገኝ ያስረዱት የመጀመሪያው ተናጋሪ አቶ ተስፋዬ በልጅጌ ናቸው። በለውጡ ከዚህ ቀደም የነበሩ መልካም ጅምሮችን በማስቀጠል መሠረታዊ ለውጥ ለማምጣት እየተሠራ እንዳለ ገልጸዋል።

በፖለቲካው ዘርፍ እየተካሄዱ ያሉትን የለውጥ ሥራዎች ሲያስረዱም፤ በቅድሚያ በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል ውስጥ ዋና ዋና ችግሮችን፤ በተለይ ደግሞ ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ እያደጉ የመጡ መዋቅራዊ ስብራቶችን የመለየት ሥራ እንደተሠራና ከተለዩት ችግሮች መካከል የጽንፈኝነት አመለካከት እና ተግባር ቀዳሚው እንደሆነ አስረድተዋል። በተለይ በልሂቃን መካከል ጫፍ የረገጡ ሐሳቦች በመያዝ በግትርነት የመጓተት፣ ያለመደማመጥ፣ አብሮ ያለመሥራት በስፋት ይንጸባረቅ እንደነበር አንስተዋል። ከሐሳብ የበላይነት ይልቅ በአፈና እና በአፈሙዝ የበላይነት የማመን ልምድም በስፋት ተንሠራፍቶ እንደነበረ፤ የተለየ ሐሳብ የሚያሚያራምድን ቡድን

እንደጠላት በመቁጠር ለማጥፋትና ለማስወገድ ይደረጉ የነበሩ ደም መፋሰሶችም እንደዋነኛ የፖለቲካ ስብራት ተነስተዋል። የጽንፈኝነት አጀንዳ የሚቀረጸው በኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን የብሔር፣ የባህል እና የሃይማኖት ብዝሃነት መጠቀሚያ ለማድረግ እንደነበር አስታውሰው፤ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች ያሏቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች ወደስጋት እና የብሶት ስሜት በመውሰድ መቀስቀሻ መሣሪያ በማድረግ ግጭት እና መፈናቀል ሲጠምቁ እንደቆዩ፤ ሃይማኖትንም እንደብሔር መቀስቀሻ መሣሪያ ሲደረጉ እንደነበሩ አንስተው፤ የትኛውም ሃይማኖት ግን ጽንፈኛ እንዳልሆነ አስረድተዋል። ለዘመናት በጽንፈኞች ሲዘራ የነበረው የጥፋት ዘር አሁን ላይ ፍሬ አፍርቶ ብዙ ጥፋት እያደረሰ እንደሆነ አስተዳደራቸው የጀመራቸው የመከላከያ ሥራዎች እንዳሉም አንስተዋል።

ፖለቲካው ከጽንፍ እሳቤዎች ተላቅቆ ወደአማካይ፤ ወደወርቃማው መስመር እንዲመጣ የአስተሳሰብ ለውጥ በማምጣት ከፍረጃ እንዲወጣ እንደተደረገ፤ በብሔር ማንነት እና በሀገራዊ አንድነት መካካል ሚዛን የማስጠበቅ ሥራም እየተሠራ እንደሆነ፤ በሐሳብ ክርክር እና ውይይት ላይ ሚዛን የመጠበቅ ሥራም እየተሠራ እንዳለ አስረድተዋል። ተቋማትን መሠረት ያደረገ የዴሞክራሲ ባህል ግንባታ፤ ሀገራዊ መግባባትን በአካታች ሀገራዊ ምክክር የመገንባት ሥራ እና የወንድማማችነትን እሴት መሠረት ያደረገ ሀገራዊ ግንባታ በመተግበር ጥላቻን እና መጠላለፍን ለማስወገድ እየተሠራ እንደሚገኝም ገልጸዋል። "ከማን ምን ይጠበቃል?" በሚለው ሐሳብ ዙሪያም ኢትዮጵያ የሁላችንም እስከሆነች ድረስ ጽንፈኝነት ለኢትዮጵያ ስለማይጠቅም ወጣቱ፣ የሚዲያው ባለሙያ፣ ማህበራዊ አንቂው፣ ሁላችንም ልንከላከለው እንደሚገባ አሳስበዋል።

የሰላም ሚኒስትሩ አቶ ብናልፍ እንዷለምም፣ ፈታኝ የሆነ ለውጥ እየተደረገ እንዳለ፤ ነገር ግን ለውጡ ግዴታ እንደነበር በማንሳት፤ ከለውጡ በፊት ጽንፈኝነት ኢትዮጵያን ሊያፈርሳት ደርሶ እንደነበር ገልጸዋል። ለዚህም ዋነኛው ምክንያት ጽንፈኝነት መነሻው "ተበድያለሁ፤ ተገልያለሁ" የሚለው አስተሳሰብ ከግለሰቦችና ከብሔሮች ይነሳ ስለነበር እንደሆነ ገልጸዋል። ኢትዮጵያን ወደሰላም መመለስ የቅድሚያ ቅድሚያ ተሰጥቶት እየተሠራ እንደሆነም አንስተዋል። ለሰላም የተሠሩትን ሥራዎች ሲዘረዝሩም ከጎረቤት ሀገራት ጋር የነበሩትን ቁርሾች መፍታት፤ በተለይ ከኤርትራ ጋር፣ የታሠሩ ዜጎችን መፍታት፣ የፖለቲካ ምህዳሩን የማስፋት ሥራ፣ በሃይማኖቶች መካከል ያለውን ውጥረት ለማርገብ የድጋፍ ሥራዎች እንደተሠሩ ገልጸዋል። እንዲሁም፣ በመካከለኛው ምሥራቅ ለነበሩ ኢትዮጵያውያን መፍትሔ የመስጠት ሥራ መሠራቱን ጠቅሰው፤

አሁንም የኢትዮጵያ ሰላም በአስተማማኝ ሁኔታ መረጋገጥ አለመቻሉን፤ በየቦታው ግጭቶች እና ጦርነት መኖራቸውን በማንሳት ሰላም አለመረጋገጡን ገልጸዋል። ጽንፈኝነትን ለማስገድ እና ወደመሐል ለመምጣት መንግሥት ከጽንፈኝነት ምልክቶች ይልቅ በዋና መንስኤው ላይ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ እንደሆነ ጠቁመዋል። ለዚህም ብዝሃነትን በአግባቡ በማስተናገድ ጉዳይ፣ በታሪክ አተያይ፣ በጠቃሚ ታሪኮች ላይ በማተኮር፣ ሰብዓዊ መብትን ማክበር፣ ፍትህንና የሕግ የበላይነትን ማረጋገጥ፣ ልማት ማምጣት እንደሚገባ አስረድተዋል። የተቋማትን በተለይ የዴሞክራሲ ተቋማትን ሪፎርም በሕዝብ ተአማኒ በማድረግ ላይ፣ የሕግ አስከባሪ ተቋማትን በማጠናከር ላይ እና የውይይት ባህልን በማዳመር ላይ በአካታች የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን በኩል እየተሠራ እንዳለ አስረድተዋል።

ሦስተኛው ሐሳብ አቅራቢ አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን፣ ተቃርኖ የሰዎች ባሕሪይ እንደሆነና ጽንፈኝነት በአንዳንዶች የመጠቅለል ፍላጎት እና በአንዳንዶች የመነጠል፤ እራስን የማግለል ሂደት የሚወለድ ሁኔታ እንደሆነ አንስተው፤ በትናንት እና በዛሬ መካከል አጣጥሞ ነገን አሻግሮ ማየት ባለመቻል የሚከሰት እንደሆነ አስረድተዋል። በትናንት ችግር ብቻኛ ተወዳሽም ተወቃሽም እንደሌለ በመረዳት በትናንት ስህተቶች እና በዛሬ ሥራ ውስጥ ነገን አሻግረን ማየት እንደሚገባን አስታውቀዋል። በአካታችነትም በጋራ መቆሚያችን ላይ አንዱ "የእኔ" የሚለውን እንዲያሳውቅ እና "እኛ" በሚባለው ላይም ያዋጣውን ለማሳየት መጠቀም እንደሚገባ እንጂ፤ አንዱን ከፍ ሌላውን ዝቅ ማድረግ ትርፍ የሌለው ተግባር እንደሆነ አብራረተዋል። በእኛ የውስጥ መጓተት ምክንያት በሚፈጠር ስንጥቃት የሀገራችን ቋሚ ባላንጣዎች ሊጠቀሙበት እና ሀገራችን ጠንክራ እንዳትቆም ሊሠሩባት እንደሚችሉም ሊታሰብ ይገባል ሲሉ ጫፍ እና ጫፍ ሆኖ መጓተት በደኅንነት ላይ የሚኖረውን ችግር አሳይተዋል።

እንደሀገር የምንፈልገው ምንድን ነው? በማለት በምንሻው እና በምንችለው መካከል መነጋገር እንደሚገባን፤ በምንወስደው እና በምናበረክተው መካከል ያለውን ልዩነት ልንስታርቅ፤ በምጠይቀው እና በምንመልሰው መካከልም ልንሠራበት፤ በ"እኔ" እና በ"እኛ" እሳቤዎች መካከልም ልናስታርቅ፤ እንዲሁም በሚያምረን እና በሚያስፈልገን መካከል ያሉ ተቃርኖዎችን ልናስታርቅ እንደሚገባ ገልጸዋል። በዚህ የማስታረቅ ሂደትም መንግሥት ዋናውን ድርሻ እንደሚወስድ፤ ዜጎች በጥበብና በተለያየ መንገድ የሚጫወቱት ሚና እንደሚኖር፤ ሚዲያው የሀገርን ደኅንነት አደጋ ላይ ከመጣል ተቆጥቦ ሀገር የመገንባት ሚናውን እንዲወጣ፤ ልሂቃኑም ስጋትን ከመቀነስ አኳያ ማበርከት እንደሚገባቸው እና ሃማኖቶችም ከውስጥ አንድነታቸው አልፈው ከሌላው

እምነት ጋር ያላቸውን ትስስር ማጥበቅ እና ማስጠበቅ እንደሚገባቸው ገልጸዋል፡ ፡ በአጠቃለይ፣ ተቃርኖዎችን የማስታረቅ ሥራ የሁላችንም እንደሆነ መገንዘብ እንደሚገባ፤ እንደዚያ ሳይሆን ቀርቶ ከውስጥ እራሳችንን ሳናስማማ ከውጭ ይህን ክፍተት የሚፈልጉ ኃይሎች ከገቡበት ግን ሁሌም የምንፈልጋትን ዓይነት ሀገር መፍጠር እንደማይቻለን አሳስበዋል።

## የተሳታፊዎች አስተያየትና ጥያቄዎች

የውይይቱ ተሳታፊዎችም፤ ወደመሐል መምጣት እና የሕግ የበላይነትን ማስከበር ላይ መሥራት፤ የችግሩን መሠረታዊ መንስኤ ለማከም ሀገራዊ የሆነውን የነጻ አውጭ ትርክት ማስወገድ እና በአዲስ ሀገራዊ ትርክት መተካት እንደሚገባ፤ መንግሥታዊ ያልሆኑ እና ባህላዊ ተቋማትን ተጠቅሞ ሁነቱን ለመከላከል ተሳትፏቸውን ማስፋት እና አቅማቸውን ማሳደግ እንደሚገባ፤ ከመቻቻል ባሻገር አብሮ መኖር፤ አብሮ ማደግ፤ አብሮ ወደብልጽግና መሻገር ወደሚል እሳቤ ማደግ እንደሚገባና ዜጎች ከመንግሥት ጋር አብረው እንዲሠሩ መንግሥት ዜጎችን መደገፍ እንደሚገባው የሚያሳስቡ አስተያየቶች ተሰንዝረዋል። በተጨማሪም፣ ጽንፈኝነት የሚስፋፋው በማህበራዊ ሚዲያው እንደመሆኑ የዲጂታል ንቃተ ኅሊና ይህን ለመዋጋት ስለሚያስፈልግ በዚህ ላይ መንግሥት ሕዝብን የማንቃት ሥራ መሥራት ይጠበቅበታል።

የፍትህ ችግሮች የመጨረሻ የቅሬታ መፍቻ መንገድ በፌደሬሽን ምክር ቤት በኩል ከሚቀርብ በፓርላም የፍርድ ኮሚቴ ቢቋቋም እና በዚያ በኩል ለመፍታት ቢሞከር፤ መንግሥት ጽንፈኝነትን ለመከላከል "ሃርድ ፓወር" ተጠቅሞ የሕግ የበላይነትን በማስከበር "ሶፍት ፓውር" በመጠቀም ጥበቡን እና የትምህርት ፖሊሲውን በመጠቀም ስትራቴጂክ በሆነ መንገድ መሥራት እንደሚገባው፤ በሁለተኛው ውጤታማ ለመሆንም ዜጎች በራሳቸው ተነሳሽነት ሊከውኑት ስለማይችሉ መንግሥት በጉዳዩ ላይ ኢንቨስት እንዲያደርግ እና በሥነምግባር ጉዳይ ላይ ትልቅ ለውጥ ሊፈጥር የሚችለውን የብሔራዊ አገልግሎት ጉዳይም ታሳቢ እንዲያደርግ የሚሉ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል። በትርክት እና በአይዲዮሎጂ ደረጃ ላለፉት ዓመታት ጽንፈኛ ፍረጃዎችን፣ ለምሳሌ፦ "አሃዳዊ፣ በእኛ መቃብር ላይ ይገነባል" የሚሉ አደገኛ ንግግሮችን መንግሥት ራሱ ሲያራምድ እንደመቆየቱ፤ ትውልድ የመገንባት ኃላፊነት ደግሞ የመንግሥት እንደመሆኑ ይህን የማረም ሥራ ከውስጥ ቢጀመር፤ ከእምነት ተቋማት ጋር በኅብረት ይሠራ፤ የደኅንነት ተቋማትም ቅድመ መከላከል ላይ ጠንክረው ይሥሩ የሚሉ ምክረ ሐሳቦች ቀርበዋል።

በመጨረሻ በተሰጡ የማጠቃለያ ሐሳቦች፤ አቶ ብናልፍ አንዷለም ጽንፈኝነትን ለመከላከል አንደኛው ሕግ የሚያከብርና ጽንፈኝነትን የሚከላከል ኅብረተሰብ መገንባት ላይ መሥራት፤ ለዚህም የሕዝብን ተሳትፎ ማረጋገጥ እንደሚያስፈልግ፤ "በራስህ እንዲደረግ የማትፈልገውን በሌላው አታድርግ" የሚለው የመካከለኛው መስመር ወርቃማ ሕግ እንደሆነ ማስረጽ፤ ከዚህ ተላልፎ ወንጀል የሚፈጽመውን በሕግ መጠየቅን ማረጋገጥ እንደሚገባ አንስተዋል። ለዚህም ኅብረተሰቡ ሕግን ለማስከበር በሚሠራው ሥራ ተባባሪ መሆን ይጠበቅበታል ብለዋል። ከህጻናት ጀምሮ በሥነምግባር የማነጽ ሥራ መሥራት ጥሩ ሐሳብ እንደሆነና እየተሠሩበትም እንደሆነ ገልጸዋል። በብሔራዊ አገልግሎት ረገድ በሰላም ሚኒስቴር የወጣቶች በጎ ፍቃድ አገልግሎት ወጣቶች የሌላውን አካባቢ ማንነት እንዲያውቁ በማድረግ የግልን ማንነት ከኢትዮጵያዊ ማንነት ጋር አስተሳስሮ የማስኬድ ተግባር እየተሠራ ያለ ተጠናክሮም የሚቀጥል እንደሆነ ገልጸዋል።

አምባሳደር ሬድዋን በበኩላቸው፣ "መንግሥት ራሱ ጽንፈኝነትን ያራመደው ነበር" ከሚለው ጉዳይ ተሻግረን "አሁን እጃችን ላይ ያለውን ችግር እንዴት በዘላቂነት እንፍታው? ያለውን ስህተት እንዴት እንሻገረው?" በሚለው ላይ ማተኮር እንደሚገባ፤ "አንድ ዓይነት እንሁን" ከሚል እሳቤ እንዴት ብዝኃነታችንን ያከበረ ትብብር ውስጥ እንግባ?" በሚለው ላይ ማተኮር እንደሚገባ አሳስበዋል። "መቻቻል" የሚለው እሳቤ አንደኛው "ተቻይ" የሚል ስሜት ስለሚሰጥ ተዋድደን፤ ተጋግዘን እና ተፋቅረን የመኖርን አስፈላጊነት ማጉላት እንደሚገባ ሀሳባቸውን አጋርተዋል፡ ፡ በአጠቃላይ፣ ከነዚህ ሁሉ ችግሮች መውጫችን ከድኅነት መውጣታችን እንደሆነ መታመን አለበት። ከድኅነት መውጫ ጉዞ ላይ የሁሉንም ተሳትፎና ተጠቃሚነት ማረጋገጥም አለብን። ይሄ እንዲሆንም ግልጽነትንና ፍትህን ማስፈን እንዲሁም ብልሹ አሠራርን ማስወገድ እንደሚገባ አሳስበዋል።

አቶ ተስፋዬ ቤልጂጌም፣ ለጽንፈኝነት መፍትሔው ያለመደማመጥን ችግር መፍታት፤ በውይይት እና በድርድር ማመን፤ ሁላችንም የ"ሰጥቶ መቀበ"ን እሳቤ ማየት እና መተግበር ነው። በዚህ መሠረት በጋራ በመተባበር ለሀገራችን መሥራት ይገባናል ብለዋል።






## 4.7 የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፣ ፈተና፣ድል እና ተስፋ

ነሐሴ 30 ቀን 2014 ዓ.ም




ኢትዮጵያ እንደ ሀገር በ2014 ዓ.ም ያሳለፈችው ፈተና፤ የተቀዳጀችው ድል እና የወደፊት ተስፋዋ በዚህ የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ የውይይት መድረክ ቀርቧል። ያለፈው 2014 ዓ.ም ኢትዮጵያ ብዙ የተፈተነችበት፤ ድል የተቀዳጀችበት እና ብዙ ተስፋ የሚሰጡ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ እና የዲፕሎማሲ ሁነቶች ያስተናገደችበት ዓመት ነው። 6ኛው ሀገራዊ ምርጫ እና የመንግሥት ምስረታ፤ የህወሓት ወረራ እና ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በመሩት የ"ዘመቻ ለኅብረ ብሔራዊ አንድነት" የተሰኘው ዘመቻ ድል የተመዘገበበት፤ ዓለም አቀፍ ዲፕሎማሲያዊ/ኢኮኖሚያዊ ጫናው እና የትውልደ ኢትዮጵያውያን ትብብር፤ የጸጥታ ተቋማት ሪፎርም መሳካት፤ የግብርናው ስኬት፤ የዓመቱ የበጎ ፍቃድ ሥራዎች፤ ሦስተኛው የሕዳሴ ግድብ የውኃ ሙሌት መሳካት እና የሁለት ተርባይኖች ኃይል ማመንጨት የመጀመራቸው ስኬት፤ በሌላ በኩል፣ የህወሓት ሦስተኛ ዙር ወረራ በዋናነት በተሰናባቹ 2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ የተከሰቱ ትላልቅ ሁነቶች እንደነበሩ በውይይቱ ተጠቅሷል።

የዚህ አዲስ ወግ የውይይት መድረክ መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎች፦

- አምባሳደር ሬድዋን ሁሴን፣ የጠቅላይ ሚኒስትሩ የብሔራዊ ደኅንነት አማካሪ፤
- ዶ/ር ፍጹም አሰፋ፣ የፕላን እና ልማት ሚኒስቴር ሚኒስትር፤
- አቶ አደም ፋራህ፣ የብልጽግና ፓርቲ ምክትል ሊቀመንበር ናቸው ፤

መድረኩን በአወያይነት የመራችው ጋዜጠኛ ሮዛ መኮንን ናት።

የ2014 ዓ.ም የኢትዮጵያ ድሎች እና ፈተናዎች ምን ነበሩ?

ሰላም እና ደኅንነት፦ አምባሳደር ሬድዋንይህንን ዘርፍ በተመለከተ ባቀረቡት ሐሳብ 2014 ዓ.ም በሰላም እና ደኅንነት ረገድ በጸጥታ ተቋማት ላይ መሠረታዊ የሪፎርም ሥራ የተሠራበት እና ውጤቱንም የታየበት ነበር፤ ብለዋል። አያይዘውም፣ መከላከያ ከፓርቲ ጠባቂነት ወጥቶ የኢትዮጵያ ጠባቂ እንዲሆን እና በአደረጃጀቱም ኢትዮጵያን እንዲመስል ተደርጎ ተሠርቷል። በሥርዓቶች መካከል ጸንቶ መቆም የሚችል ቁመና እንዲኖረው ተደርጎም በአደረጃጀት፣ በእሳቤ እና በቴክኖሎጂ ተደራጅቷል። የደኅንነት መሥሪያ ቤትም በፊት በዜጎች የሚፈራ ከነበረበት ሥርዓት ወጥቶ መሠረታዊ ዓላማው ወደሆነው የዜጎችንና የሀገርን ደኅንነት ከውስጥ እና ከውጭ ጠላቶች የሚጠብቅ ሆኖ ተደራጅቷል። እራሱንም ለዜጎች ክፍት በማድረግ ምን እየሠራ እንዳለ እንዲታወቅ እና ዜጎች መረጃ/ሐሳብ ለመስጠት የማይፈሩት እንዲሆን የማድረግ ሥራ እየሠራና ተቋሙን በሰው ኃይል እና በቴክኖሎጂ በብቃት የማደራጀት ሥራ የተሠራበት ዓመት ነበር ሲሉ አስረድተዋል።

ፖሊስም ኅብረተሰብን ማገልገልን መሠረት ያደረገ የዶክትሪን ማሻሻያ ተደርጎለታል። ያሉት አምባሳደር ሬድዋን፣ በፖሊስ ሠራዊት መሠረታዊ እሳቤ ላይ የኅብረሰቡን እሴት እና ፍላጎት ያማከለ የማሻሻያ ሥራ፤ ከታች እስከላይ የአደረጃጀት ሥራዎች የተከናወኑበት መሆኑን አንስተው፤ በዘርፉ የተደረጉት ለውጦች የሀገራችንን ሰላም አስተማማኝ ለማድረግ፤ የዜጎችን ዋስትና ለማረጋገጥና የኢትዮጵያን ሉአላዊነት በበቂ ደረጃ ለመጠበቅ፤ ችግር ሲፈጠርም በቀላል ዋጋ ለመመከት የሚያስችል ሀገራዊ ቁመና ላይ መድረስ መቻሉን አስረድተዋል።

ህወሓት እና ታሪካዊ ጠላቶቻችን በጋራ በመሥራት የተለያዩ የውስጥ እና የውጭ ቡድኖችን በመላክ የሰላም እና የደኅንነት ፈተናዎች እንዲገጥሙን አድርገዋል። ህወሓት በመካላከያ ላይ ከባድ ጥቃት ማድረሱ እንዳለ ሆኖ፤ መከላከያ እየመከተ እና እያጠቃ እራሱን እያዘመነ አሁን የትኛውንም ስጋት ማጥፋት በሚችልበት አቅም

ላይ ይገኛል። ከህወሓት ጋር በነበረው ሕግ የማስከበር ዘመቻ መከላከያ መቀሌ ከገባ በኋላ ትግራይን ለቅቆ የወጣው እና ዳግም ከመግባትም የተቆጠበው የትግራይ ሕዝብ ፋታ እንዲያገኝ፤ ገበሬው እንዲያርስ እና እነዚህን የጥፋት ቡድኖችም "ከወገኔ ጋር አታጣሉኝ" የሚል ጥያቄ እንዲጠይቅ ነበር ሲሉም አስረድተዋል። አምባሳደር ሬድዋን ዓለም አቀፉን የዲፕሎማሲ ጫና በተመለከተም፤ የህወሓትን አቋም መሠረት ያደረገ ህወሓት ሲያጠቃ ዝም የሚል እና መንግሥት ርምጃ ሲወስድ ከፍተኛ የዲፕሎማሲ እና የሐሰተኛ መረጃ ጫና ሲደረግ እንደነበር አንስተዋል። በተቃራኒው ግን በራሳችን የዲፕሎማሲ ስህተት አበላሽተነው የነበረውን ከመካከለኛው ምሥራቅ ሀገራት ጋር የነበረንን ግንኙነት በማሻሻል ዓለም ፊቱን ባዞረብን ሰዓት በብዙ መንገድ አብረውን የቆሙ ሀገራት ጋር ግንኙነታችንን ማጠናከር ያስቻለ ሥራ በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ የተሠራበት ዓመት ነበር ሲሉ ገልጸዋል።

በማጠቃለያም ህወሓት በዚህ ወቅት መንግሥት ለሰላም የዘረጋውን እጅ ወደጎን በመግፋት ሦስተኛ ዙር ወረራ የጀመረበት ወቅት እንደመሆኑ፤ የመከላከያ እና የሌሎች የደኅንነት ተቋማት ከሪፎርሙ በኋላ በገነቡት አቅም ለሰላም የመጣን የትኛውንም ኃይል በሰላም የምንቀበል "አይ አሻፈረኝ" በማለት በሌላ መንገድ ለሚመጣ ደግሞ በዚሁ ምዕራፍ የመጨረሻ የሚቋጭበት ርምጃ የመውሰድ ብቃት ላይ እንደሚገኙ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ሊያውቅ ይገባል ብለዋል።

ከፖለቲካ አኳያ፦ በ2014 ዓ.ም በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ ዋነኛው ድል የነበረው የፌዴራል እና ክልል መንግሥታት ምሥረታ ነው። ይህም በነጻነቱና በፍትሐዊነቱ ኢትዮጵያ እስከዛሬ ካደረገቻቸው ምርጫዎች የላቀውና ዴሞክራሲያዊ የነበረው የስድስተኛውን ብሔራዊ ምርጫ ተከትሎ የብልጽግና ፓርቲ በማሸነፉ መንግሥት መሥርቷል። የመንግሥት ምሥረታው አካታችነት ለተፎካካሪ ፓርቲዎች ሥልጣን በማጋራት በኢትዮጵያ የፖለቲካ ባህል አዲስ ልምምድ ያስተዋወቀም ነበር። የብልጽግና ፓርቲ ጉባኤም ፓርቲው ለወደፊት የሚያራምዳቸውን ውሳኔዎች የወሰነባቸው፤ ፓርቲውን የሚመሩትን መሪዎች የመረጠበት እና ያሉበትን ክፍተቶች የገመገመበት እንደነበር አቶ አደም ፋራህ አብራርተዋል። በተጨማሪም የአካታች ሀገራዊ ምክክርን በኢትዮጵያ በማከናወን የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስንክሳሮች ለመፍታት የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የተቋቋመበት፤ ወጣቱን በሀገር አቀፍ ደረጃ በስፋት ያሳተፉ ሀገራዊ ጉባኤዎችን በስድስት ዙር እስከ2.2 (ሁለት ነጥብ ሁለት) ሚሊዮን የሚደርሱ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች በሀገራችን ጉዳዮች ላይ እንዲመከከሩ ያደረግንበትም ሌላው የፖለቲካ ክንውን ነበር ብለዋል።

በኢኮኖሚ ዘርፍ፦ ዶክተር ፍጹም አሰፋ ኢኮኖሚውን አስመልክተው፤ ባለፉት አራት ዓመታት የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በዓለም አቀፍ ተግዳሮቶች እና በማክሮ ኢኮኖሚ መዛነፍ ምክንያት በብዙ እንደተንገጫገጨ ጠቁመዋል። በ2014 ዓ.ም ግን የማክሮ ኢኮኖሚ አመላካቾች እንደሚያሳዩት ኢኮኖሚው በጦርነት ውስጥም ሆነን ብዙ ድሎች አስመዝግበንበታል። አጠቃላይ የውጭ ምንዛሬ ግኝታችን 22 (ሃያ ሁለት) ቢሊዮን ዶላር ነበር። ከዚህም ውስጥ የሸቀጥ ንግድ ገቢያችን ለመጀመሪያ ጊዜ ከአራት ቢሊዮን ዶላር በላይ ደርሷል። 3.31 (ሦስት ነጥብ ሦስት አንድ) ቢሊዮን ዶላር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመን በመሳብም ከአፍሪካ ቀዳሚ መሆን ችለናል። የፋይናንስ ተቋማትን አቅም ከማሳደግ አንጻር 1.7 (አንድ ነጥብ ሰባት) ትሪሊዮን ብር ቁጠባ፣ 427 (አራት መቶ ሃያ ሰባት) ቢሊዮን ብር የተፈቀደ ብድር እና 276 (ሁለት መቶ ሰባ ስድስት) ቢሊዮን ብር የተመለሰ ብድር የደረስንበት ዓመት እንደነበር አስታውቀዋል። እንዲሁም ለ2.38 (ሁለት ነጥብ ሦስት ስምንት) ሚሊዮን ሥራ ፈላጊዎች አዳዲስ ቋሚ የሥራ እድል ፈጥረናል ብለዋል።

በግብርናው ዘርፍም ትላልቅ ስኬቶች ተመዝግበዋል። በዚህም ከዋና ዋና ሰብሎች 336 (ሦስት መቶ ሠላሳ ስድስት) ሚሊዮን ኩንታል እህል ማምረት የተቻለበት እና በአትክልት እና ፍራፍሬ ዘርፍ 1.10 (አንድ ነጥብ አንድ) ሚሊዮን ቶን የተመረተበት፤ ይህም ከእቅዱ 94% (ዘጠና አራት በመቶ) የተሳካበት እንደነበር አንስተዋል። ሌላኛው እና ታላቅ ለውጥ የተመዘገበበት ደግሞ በስንዴ ምርት ነው። በበጋ ከ600 (ስድስት መቶ) ሺሕ ሄክታር መሬት 26 (ሃያ ስድስት) ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ ተሰብስቧል። የበጋን እና የክረምትን የስንዴ ምርት በአጠቃላይ የበልግን ሳይጨምር 90 (ዘጠና) ሚሊዮን ኩንታል የተመረተበት እና በ2015 ዓ.ም የስንዴ ምርታችን ከፍላጎታችን ተርፎ ወደውጭ ለመላክ ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝ አስረድተው፤ በግብርናው ዘርፍ የውስጥ መዋቅራዊ ለውጥ ለማምጣትም በእንስሳት ኃብት ልማት ላይ ከፍተኛ ሥራ እየተሠራ እንደሆነ ገልጸዋል። የአየር ንብረት ለውጥን ለመቋቋም እና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በአረንጓዴ አሻራ 400 (አራት መቶ) ሚሊዮን የፍራፍሬ ችግኞች የተተከሉበት እና ከዚሁም ዘርፍ 186 (አንድ መቶ ሰማንያ ስድስት) ቶን አቮካዶ ወደውጭ በመላክ የውጭ ምንዛሬ የተገኘበት ዓመት እንደነበር ዶ/ር ፍጹም አንስተዋል።

የአምራቹን ዘርፍ በተመለከተም፤ ዘርፉ መዋቅራዊ የአቅርቦት፣ የኢንዱስትሪ ባህል አለመዳበር እና የፋብሪካ ማኔጅመንት ችግሮች ያሉበት እደሆነ አንስተው፤ በተሠሩ የማሻሻያ ሥራዎች 500 (አምስት መቶ) ሚሊዮን ዶላር ገቢ ያስገኙ የተለያዩ

ምርቶች ማምረት የተቻለ ሲሆን፤ ሁለት ቢሊዮን ዶላር ያስወጡ የነበሩ ምርቶችም በሀገር ውስጥ ምርት መተካት መቻሉን አሳውቀዋል። በተጨማሪም በማእድን ዘርፍ የነበሩ የፖሊሲ ችግሮች በማስተካከል ከፍተኛ ገቢ ማስገኘት እንዲችል እየተሠራ እንደሆነና በዲጂታል ኢኮኖሚም ከመሠረተ ልማት ግንባታ ጀምሮ በዲጆታል ክፍያ ሥርዓት ታላላቅ ስኬት የተመዘገበበት ዓመት እንደነበር ገልጸዋል።

በአጠቃላይ በኢኮኖሚው መንግሥት በዘርፉ የነበሩትን ድርሻዎች ለግሉ ዘርፍ እየተው የወጣበት፤ በቴሌኮም እና በባንክ ዘርፍ የውጭ ድርጅቶች እንዲሳተፉ የተደረገበት፤ እንዲሁም በመንግሥት ሥር የነበሩ የልማት ድርጅቶች ወደግል ይዞታ የተላለፉበት፤ ለዜጎች ሰፊ የሥራ እድል የተፈጠረበት፤ ለግብርና ክፍለ ኢኮኖሚ ትልቅ ትኩረት የተሰጠበት፤ ለአርሶ አደሮች የብድር አቅርቦት እንዲኖር መዋቅራዊ ውሳኔዎች የተወሰኑበት፤ የኢኮኖሚው ቅልቅ ፈተና የነበረውን የዋጋ ግሽበት ለማቋቋምም የተለያዩ ተግባራት በመከናወን ግሽበቱ ላለፉት ሦስት ወራት ባለበት እንዲረጋጋ የተደረገበት፤ እና በድኅነት ቅነሳ የበጎ ፈቃድ ተግባራት ከፍተኛ ሥራ በፌዴራል እና በክልሎች የተከናወኑበት ዘመን መሆኑንም አስረድተዋል።

## ማጠቃለያ

በውይይቱ ማሳረጊያ ከተሳታፊዎች በተነሱ ሐሳቦች እና ጥያቄዎች ላይ የውይይት መነሻ ሐሳብ አቅራቢዎቹ በሰጡት ምላሽ፤ ሰላም እና ደኅንነትን በተመለከተ፤ አምባሳደር ሬድዋን ህወሓት እና ሌሎች ተላላኪዎች መንግሥትን በተለያየ አካባቢዎች በችግር እንዲወጠር እንዳደረጉ ገልጸዋል። ይህንንም የመከላከያ ሠራዊቱ እየመከተ እንደሆነ እና በአጠቃላይ ለኢትዮጵያ ሰላም ያለንን ነገር አውቀን፤ በራስ ለመቆም የሚያስችሉንን አቅሞች አሰባሰበን በጋራ ቆመን፤ ለኢትዮጵያ መከፈል ያለበትንም ዋጋ ከፍለን ሀገራችንን ማስቀጠል አለብን ብለዋል። የዲፕሎማሲውም መሠረት በራስ መቆም መቻል እና ከጎረቤት ጋር ሰላማዊ ግንኙነት መመሥረት እንደመሆኑ የገጠሙን የዲፕሎማሲ ችግሮች በአፍሪካ ኅብረት ጥላ ሥር በሠራናቸው ሥራዎች ውጤት እንዳስገኙ አስረድተዋል።

አቶ አደም ፋራህም፣ ሀገራዊ ምክክሩ ሁሉንም የሚያሳትፍ እንደመሆኑ ሁሉም ዜጋ እና የፖለቲካ አካል ተሳትፎ እንደሚደረግ ገልጸው፤ በሂደቱ ኮሚሽኑ ከሲቪክ ማህበራት ጋር የተለያዩ ሥራዎችን መሥራት የሚችልባቸው ቅደመ ሁኔታዎች እየተመቻቹ እንደሆነና መንግሥትም ሂደቱን በብርቱ እንደሚደግፍ አስታውቀዋል። ዶ/ር ፍጹም በበኩላቸው በዲጂታል ኢኮኖሚው ላይ ትላልቅ ሥራዎች


ነሐሴ 30, 2014 ዓ.ም.


ድል ተስፋ
ነሐሴ 30, 2014 ዓ.ም.




ነሐሴ 30, 2014 ዓ.ም.

እንደመሠራታቸው የሳይበር ደኅንነት ጉዳይ አንድም በሀገራዊ የደኅንነት ተቋማት ሪፎርም ላይ የተሠራበት እንደሆነ እና በተጨማሪም ዘርፉ ዘላቂ ለውጦችን የሚያስተናግድ እንደመሆኑ በየጊዜው አብሮ የማዘመን ሥራ እንደሚሠራ ጠቅሰው፤ በአፍሪካ የነጻ የንግድ ቀጣና ላይ ኢትዮጵያ ቀዳሚ ፈራሚ ሀገር እንደመሆኗ በትስስሩ “ምን ይዘን መቅረብ አለብን?” በሚለው ላይ ታሳቢ በማድረግ በአምራቹ ዘርፍ ላይ ብዙ የሚሠሩ ሥራዎች እንደሚኖሩ እና ነጻ የንግድ ቀጣናውን ዓላመ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችሉ ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ እንደሆም  አብራርተዋል።



# ክፍል አምስት፣
# የአዲስ ወግ መድረኮች
# 2015 ዓ.ም

# 5.1 አዲስ ወግ አንድ ጉዳይ ሕዝባችን ዐቅማችን፤

ጥር 2015 ዓ.ም




በዓለም ባንክ መረጃ መሠረት ሀገራችን ኢትዮጵያ በሕዝብ ቁጥሯ ከዓለም አገሮች በአሥራ ሁለተኛ ደረጃ ላይ ትገኛለች። የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ደግሞ አወንታዊ ጎኖች እንዳሉት ሁሉ አሉታዊ ጎኖችም ይኖሩታል፤ ይህ «የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ» ፕሮግራምም የሕዝብ ቁጥር ዕድገት < <አወንታዊ ጎኖችን እንዴት ጥቅም ላይ ልናውላቸው ይገባል? > > የሚለውን መሠረታዊ ሐሳብ መነሻ ያደርገ ነበር።

ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥርን እንዴት ወደ ዐቅም መቀየር እንደሚቻል፣ በሕዝብ ብዛት እና በአገልግሎት አሰጣጥ መካከል ያለው ቁርኝት ምን እንደሚመስልም ያሳያል፡ ፡ በዚህ ውይይት ላይ ሐሳብ አቅራቢዎች የፕላን ሚንስትር ዶ/ር ፍጹም አሰፋ ፣ የሥነ-ሕዝብ ባለሙያው ፕሮፌሰር ንጋቱ ገዳ እና ዶ/ር የሽጥላ ወንድሜነህ ነበሩ። በውይይቱ መጀመሪያ ላይ በፕሮፌሰር ንጋቱ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕድገት ታሪክ ምን እንደሚመስል ዝርዝር መረጃ እንደ መግቢያ ቀርቧል። ሀገራችን ከ1991ዓ.ም

ጀምሮ እየተከተለችው ባለው የቤተሰብ ምጣኔ አገልግሎት የማስፋት ሥራ ምክንያት ለውጥ እየታየ መሆኑም ተገልጿል። በዚህም ከአጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር ውስጥ 50 በመቶ የሚሆነው ከ 15 ዓመት እና 70 በመቶ የሚሆነው ደግሞ ከ30 ዓመት እድሜ በታች የሚገኝ የመሆኑ መረጃ ቀርቧል።ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቁጥር መብዛት ዋነኛው ምክንያትም የውልደት መጠን መጨመር እና የሞት መጠን በከፍተኛ ሁኔታ መቀነስ እንደሆነ ተነስቷል። በዚህም ከአምስት አመት በታች ያሉ ሕፃናት ሞትን ከ100 ሺህ ሕፃናት መካከል ከ165 ወደ 55 እና የእናቶችን ሞት ደግሞ ከ95 ወደ 50 እንዲወርድ አድርጎታል። የሥነ-ሕዝብ ትሩፋት ማለትም በከፍተኛ የሥነ- ሕዝብ ሽግግር የሚፈጠረውን የወጣት የሥራ ኃይልን መጠቀም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ዕድገት ማስመዝገብ መቻል መሆኑም ተብራርቷል።

የመጀመሪያውን የመወያያ ሐሳብ ያቀረቡት ደግሞ የፕላን ሚንስትር ዶ/ር ፍጹም አሰፋ ናቸው። ሚንስትሯ በንግግራቸው የሕዝብ ብዛት ዐቅም ሊሆን የሚችለው በመጀመሪያ ደረጃ ከብዙ የሕዝብ ቁጥር ውስጥ ብዙ ሠራተኛ ሕዝብ መኖር ሲችል እንደሆነ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሥነ- ሕዝብ ጥራት መኖር የሕዝብን ቁጥር ዐቅም ሊያጎለብተው እንደሚችል አንስተዋል። የሥነ-ሕዝብ ጥራት ሲባል በተለያዩ መለኪያዎች ሊታይ የሚቻል መሆኑንም ዶ/ር ፍጹም ገልጸዋል። የሥነ-ሕዝብ ስብጥር ጥራቱን የጠበቀ ትምህርትን ለሁሉም ተደራሽ በማድረግ በጥሩ ሥነ-ምግባር የታነጸ የሰው ኃይል መገንባት፣ በሽታን ከመከላከልና ከማከም ባለፈ ስርዓተ -ምግብን ማሻሻል እና ከሱስ የጸዳ ብቁ ዜጋን መፍጠር እንዲሁም የኅብረተሰቡን የገቢ ዐቅም ማሳደግ፣ በተዘዋዋሪ መንገድም የገበያ ዐቅም መሆን የሚችል ዜጋን የመፍጠር ሂደቶች የሥነ-ሕዝብ ጥራት መለኪያዎች ሊሆኑ እንደሚችሉ አስረድተዋል።

ዶ/ር ፍጹም በትምህርት ሥርዓቱ ላይ መንግሥት ረዘም ላሉ ዓመታት ከፍተኛውን በጀት መድቦ እየሠራ እንደሆነ፤ ሥራውም የሥነ-ሕዝብ ጥራትን ከሚወስኑት መሠረታዊ ጉዳዮች መካከል ዋነኛው ጉዳይ እንደሆነ አንስተዋል። የትምህርት ጥራተትን ለማስጠበቅ ሲባልም በትምህርት ቤት ምገባ ላይ እየተሠራ እንደሆነ፣ አዲስ ሥርዓተ ትምህርት ተቀርጾም ወደ ተግባር እንደተገባና የቅድመ መደበኛ ትምህርት 1 መጀመሩን አብራርተዋል።

በሌላ አንፃር እንደ ዶ/ር ፍጹም ገለጻ በጤና መድኅን ስርዓት አርባ ሰባት ሚሊዮን ሕዝብ ተጠቃሚ ሆኗል፤ ይህ ደግሞ ጤናውን የጠበቀ፣ በሥነ-ምግባር እና በክህሎት የላቀ የሰው ኃይል ለማፍራት የሚደረገው ጥረት አካል ነው። በተለይም በየዓመቱ

ከሁለት ሚሊዮን በላይ አዳዲስ ወጣቶች ወደ ሥራ ገበያው የሚገቡ ቢሆንም በሥራ ገበያው ላይ ብዙ ክፍተት ያለ መሆኑ በመታወቁ መንግሥት ጥራት ያለው የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሚያስችሉ ሥራዎችን እየሠራ እንደሚገኝ ሚንስትሯ አሳውቀዋል። በመቀጠል ሐሳባቸውን ያቀረቡት ፕሮፌሰር ንጋቱ ገዳ ነበሩ። ፕሮፌሰሩ ባደረጉት ንግግር የሕዝብ ቁጥር መጨመር ይዞት ሊመጣ የሚችለው መልካም ዕድል እንዳለው ሁሉ የተለያዩ ጫናዎችንም ይዞ ሊመጣ እንደሚችል አንስተዋል። እንደ ማሳያም በአገራችን በየዓመቱ 471 ሺህ አዳዲስ የመኖሪያ ቤቶች እንደሚያስፈልጉ አንስተው፤ በአንድ በኩል ይህን ያህል ቤት ለማቅረብ በበጀት ላይ ጫና ቢፈጥርም ከፍተኛ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር፣ ከዚያ ባለፈም ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት አስተዋጽዖ ያበረክታል ብለዋል።

ፕሮፌሰሩ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ጫናዎችን ለመመልከት የሚያግዙ ዐራት ነጥቦች ስለመኖራቸውም ሐሳባቸውን አካፍለዋል። የመጀመሪያው የሕዝብ ቁጥር ዕድገት በምግብ፣ በውኃ እና በሌሎች መሠረታዊ አቅርቦቶች ላይ እጥረት መፍጠሩ ነው፤ ሁለተኛው ነገር በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምክንያት የሚከሰተው የሕዝብ ጥግግት የጤና ችግር ይፈጥራል፤ ሌላው ደግሞ የሕዝብ ዕድገት ፍጥነቱ በአገሪቱ ኢኮኖሚ የመሸከም ዐቅም ላይ ጫና መፍጠሩ እና በሕዝብ ቁጥር ዕድገት ምክንያት የሰው ፍልሰት መከሰቱ ነው። በሀገራችን የተለመደው ፍሰት ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረግ ነው። የዚህ ፍሰት መነሻም የትልልቅ ከተሞች መፈጠር፣ ከዚህ ጋር ተያይዞም የተለያዩ ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት እና ጉዳዩም ከዓለምአቀፋዊ ሁኔታዎች ጋር እንደሚያያዝ አስምረውበታል።

ፍልሰት ለሀገር ኢኮኖሚ ዕድገት አስታዋጽዖ እንዳለው ያነሱት ፕሮፌሰር ንጋቱ የሀገራችን ከተሞች 38 በመቶ የሚሆነውን ሀገራዊ ምርት ከገጠር ወደከተማ በሚደረግ ፍልሰት እና በከተማ መስፋፋት የሚመነጭ እንደሆነ፣ ይህ የኢኮኖሚ ዕድገት ደግሞ ለሀገራችን ዋነኛው የዕድገት መሠረት ሊሆን እንደሚችል የግል ምልከታቸውን አጋርተዋል ። የፍልሰትን አውንታዊ ጎን ሲያስረዱም፣ ከገጠር ወደ ከተማ በሚደረግ ፍልሰት ምክንያት በገጠር ያለው የሕዝብ ጥግግት እንዲሚቀንስ፣ የከተማው ሕዝብ ቁጥር በማደጉ ምክንያት ደግሞ በገጠር ለሚመረቱ ምርቶች ከፍተኛ የገበያ ዕድል እንደሚፈጥር ፤ በተጨማሪም የከተሞችን ዕድገት በማፋጠን ብዙ የሥራ ዕድል እንደሚፈጥር እና ብዙ የኢንቨስትመንት ዘርፎች እንዲኖር ማስቻሉን አስረድተዋል። በመጨረሻም ፕሮፌሰር ንጋቱ ሀገራችን የሥነ-ሕዝብ ሽግግር ላይ በመሆኗ ከፍተኛ የውልደት እና የሞት ቁጥር መቀነስ መኖሩን አስረድተዋል። የሥነ-ሕዝብ ትሩፋትን መጠቀም ሲባል የወጣቱ ቁጥር ብዙ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ጥራት ያለው፣ በጥሩ

ትምህርት የተቀረጸ፣ ሀገሩን የሚወድ፣ ሥነ -ምግባር ያለው እና ራሱን አሻግሮ ሌሎችን ለማሻገር ፍላጎቱም ዐቅሙም ያለው መሆን እንደሚኖርበት አመላክተዋል።

በመቀጠል ሐሳባቸውን ያቀረቡት ዶ/ር የሺጥላ ወንድሜነህ ሲሆኑ የሕዝብ ቁጥር ከሕዝብ ሰላምና ደኅንነት ጋር ቀጥተኛ ቁርኝት ያለው መሆኑን ገልጸዋል። ይህም ማለት የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር የሰላም እና ደኅንነት ስጋቶችም እንደሚጨምሩ፣ በተቃራኒው አንዱ ሲቀንስ ሌላውም እንደሚቀንስ፤ ዝቅተኛ የሕዝብ ዕድገት ባለባቸው አገሮችም አነስተኛ የሰላም እና ደኅንነት ስጋት እንዳለባቸው ገልጸዋል። ከፍተኛ የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ባለባቸው 20 አገሮች በተደረገ ጥናት መሠረት የሕዝብ ቁጥር ዕድገቱን ተከትሎ ለፀጥታ ችግር፣ ለግጭት እና ለፖለቲካ አለማረጋጋት የተጋለጡ መሆናቸው ተረጋግጧል ብለዋል። የሕዝብ ቁጥር ሲጨምር በአገሮች ውስጥ ያሉ የተፈጥሮ ሐብቶች በአንጻራዊነት ስለሚያንሱ በተፈጥሮ ሐብት ክፍፍል ምክንያት ብሔር ተኮር ግጭቶች የመፈጠር ዕድላቸው እንደሚጨምር አብራርተዋል።

<<ከፍተኛ የሰው ፍልሰት በከተማ አካባቢ ሕገ-ወጥ ሰፈራዎች እንዲበራከቱ ስለሚያደርግ የደኅንነት ስጋት ይፈጥራል። መፍትሔ ሊሆን የሚችለው ደግሞ የፀጥታ መዋቅሩ ፈጣን እና ቴክኖሎጂን በአግባቡ መጠቀም የሚችል መሆን እና የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓት በሀገር አቀፍ ደረጃ መገንባት ነው። ሚዲያዎችም በሰላም ሥራ ላይ ትኩረት አድርገው በሰፊው በመሥራት ተቋማቸውን የሰላም ሚዲያ እስከሚመስል ሊሠሩበት ይገባል>> ሲሉ ዶ/ር የሺጥላ አሳስበዋል።

ከሕዝብ ቁጥር ዕድገት መጨመር ጋር የሚመጣውን የፀጥታ ችግር ለመፍታት ዋነኛው መንገድ የሰላም ባህልን ማሳደግ መሆኑን የሚያነሱት ዶ/ር የሺጥላ በየአካባቢው የሚገኙ የሰላም ተቋማትን ማጠናከር፣ የሰላም ትምህርትን በሥርዓተ- ትምህርት ውስጥ ማካተት፣ በትምህርት ተቋማት ውስጥ የሰላም ክበቦችን ማስፋፋት፣ የንግግር ፎረሞችን በመፍጠር የዲሞክራሲን ባህል ማሳደግ እና በሥነ-ምግባር የታነፀ ትውልድ በመገንባት ሥራ ላይ ጠንክሮ መሥራት እንደሚገባ ተናግረዋል። ይህን ታሳቢ ያደረገ የሲቪክስና ሥነ-ምግባር ትምህርት በትምህርት ቤቶች ሲሰጥ እንደነበር፣ ነገር ግን ትምህርቱ የተፈለገውን ያህል ውጤት ማምጣት እንዳልቻለ በማስረዳት ሌሎች መንገዶችን ማየት የሚያስፈልግበት ወቅት እንደሆነም ዶ/ር የሺጥላ አስገንዝበዋል።

ዶ/ር ፍፁምም የሕዝብ ቁጥር ብዛትን እና የኢኮኖሚ ዕድገትን እንዴት ማጣጣም እንደሚቻል ሲያስረዱ የሥነ-ሕዝብ ዕድገት የሀገር ዐቅም እንዲሆን ለማስቻል

የተለያዩ ተቋማት በጋራ መሥራት ይገባቸዋል ብለዋል። ለዚህ ሲባል በማኅበራዊ ዘርፍ በትምህርት እና በጤና ላይ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ እንደሚገኙ፣ በፖሊሲ ደረጃም ቢሆን የሚወጡ አዳዲስ ፖሊሲዎችን የማናበብ ሥራ (policy mapping and policy alignment) የአሠራር ስርዓት ተዘጋጅቶለት መተግባር እደተጀመረ፣ የጤና እና የትምህርት ፖሊሲዎችም ይህን መሠረት አድርገው ተግባራዊ ማድረግ እንደጀመሩ አስረድተዋል።

የሕዝብ ቁጥር መጨመር በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ እያስከተለ ያለውን መጨናነቅ በተመለከተ ሐሳባቸውን ያካፈሉት ፕሮፌሰር ንጋቱ በበኩላቸው በሥነ-ሕዝብ ሽግግር ላይ ያሉ አገሮች በሕዝብ ቁጥር መብዛት ምክንያት በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ ጉድለት ሊከሰት እንደሚችል ያምናሉ። በመሆኑም <<ችግሩን እንዴት እንለፈው?>> በሚለው ቁምነገር ላይ ማተኮር እንደሚገባቸው ቀዳሚ መፍትሔ ተደርጎ መወሰድ ያለበትም <<የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን ማሳደግ፣ በትምህርት ጥራት ላይ በመሥራት የሰው ኃይል በመገንባት ችግሩን መፍታት ይገባል>> በሚለው ላይም ያሰምሩበታል፤ የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ በመንግሥት የተሰጠው ትኩረት እንደሚበረታታም ሐሳባቸውን አካፍለዋል።

ከውይይቱ ተሳታፊዎች የተነሱ ሐሳቦች እና ጥያቄዎች፤

ከሕዝብ ቁጥር ብዛት ጋር የተያያዙ ሐሳቦች ትኩረት አግኝተው ውይይት እንዲካሄድባቸው በመደረጉ የውይይቱ ተሳታፊዎች ደስተኛ መሆናቸውን ገልጸዋል። በተጨማሪም 80 በመቶ የሚሆኑት በሥራ ገበያው ላይ የሚታዩ የሥራ አቅርቦቶች የሥራ ልምድ የሚጠይቁ እንደሆኑ፣ ይህም በየዓመቱ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው አዳዲስ ተማራቂ ተማሪዎች በሚወጡበት ወቅት በመሆኑ ከሥራ ገበያው ጋር እንደማይጣጣም፣ ለዚህ ሲባል ከአንደኛ ደረጃ ጀምሮ ለሥራ ገበያው የሚሆኑ ተግባራዊ ክህሎቶችን ተማሪዎች እንዲማሩ የሚደረግበትን መንገድ መፍጠር ይገባል የሚል ሐሳብ ሰንዝረዋል።

የትምህርት ሴክተር ከፍተኛ በጀት ተቀባይ በመሆኑ የሚመደብለት በጀት ቀላል አይደለም፤ ይሁን እንጂ የሀገሪቱ ከፍተኛ የሰው ኃይል የሚገኘው በአንደኛ ደረጃ የትምህርት ተቋማት ላይ በመሆኑ በበጀት ድልድሉ ትኩረት ማግኘት ቢችል ጥሩ ነው የሚል ሐሳብ አቅርበዋል።

በከተሞች ላይ እየመጣ ያለውን ጫና ለመቀነስ ሲባል ከአዲስ አበባ ከተማ በተጨማሪ በሌሎች የክልል ከተሞችም የፍልሰት ችግርን ለመቋቋም የሚከናወኑ

ተግባራትን እንዲጋሩ የሚሠሩ ሥራዎች፤ በተለይም በትምህርት ቤቶች የሚካሄደው የተማሪዎች የምገባ ፕሮግራም፣ ለትምህርት ጥራት እና የማቋረጥ ምጣኔን ለመቀነስ ከፍተኛ  አስተዋጽዖ በማበርከት ላይ የሚገኝ መሆኑ በበጎ ጎኑ እንደሚታይ በውይቱ ተሳታፊዎች ተገልጿል።

የቤተሰብ ምጣኔ ዕቅድ አገልግሎት በሥነ-ሕዝብ ጉዳይ ላይ ለሚሠሩ ተቋማት እንደቀዳሚ ሥራ የሚወሰድ ተግባር ነው። ይሁን እንጂ በኅብረተሰቡ እና በመንግሥት የሥራ ኃላፊዎች ዘንድ ያለው ግንዛቤ በጣም አነስተኛ ስለሆነ ይህንኑ አስመልክቶ ከፍተኛ ሥራ መሥራት እንደሚገባው ሐሳብ ቀርቧል። ከሥነ-ሕዝብ ፖለሲው በተጨማሪ የወጣቶች ፖሊሲም ትኩረት ሊደረግበት እንደሚገባ ተጠቁሟል።  በተጨማሪም የሰብእና ግንባታ ሥራ በመሥራት እና የብሔራዊ አገልግሎትን በማስጀመር ወጣቶች ስለሀገራቸው ያላቸውን የተሳሳተ ምልከታ እንዲለውጡ መሠራት የሚገባውን ተግባር ማጠናከር እንደሚገባ  ሐሳብ ተነስቷል።

በአሁኑ ወቅት የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ በዓለማቀፍ ደረጃ የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳይ ሆኗል፤ በሀገራችን ለውጥ ያለ ቢሆንም ለጉዳዩ እየተሰጠ ያለው ትኩረት አሁንም አነስተኛ ነስለሆነ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባልም ተብሏል።
በትምህርት ሥርዓት እና በሰው  ኃይል ማፍራት ሥራዎች ላይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ስኬታቸውን ተማሪዎችን በማስመረቅ ከመለካት ይልቅ <<ምን ያህል ሰው ወደ ሥራ አስገባን?>> ወደሚለው ቁምነገር ቢቀየር ተገቢ ሊሆን እንደሚችል ሐሳብ ቀርቧል። የሰላም ተቋማትን በተመለከተ የባህላዊ የሰላም ተቋማት መሠረታቸው እየተሸረሸረ በመሆኑ የሰላም ጉዳይን ከማስረጽ አንጻር የመሪዎች ቁርጠኝነት እና የተቋማት ዘላቂነት አስፈላጊ መሆናቸው ተነስቷል።

የተማሪዎች የማቋረጥ ምጣኔ በክህሎት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ እንደሚፈጥር፣ በተለይም ችግሩ በገጠር እና በሴት ተማሪዎች ላይ እንደሚከፋ አንስተው፤ በአዲሱ የትምህርት ፖሊሲ ችግሩን ለማቃለል ምን አይነት መፍትሔ እንደተዘጋጀ ግልጽ እንዲሆንላቸውም የውይይቱ ተሳታፊዎች ጠይቀዋል።

የኢትዮጵያ የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲ የወጣው ከሰላሣ ዓመት በፊት ነው፤ አሁን ካለው ነባራዊ ሁኔታ መቀያየር አንጻር እንዴት ይታያል? በተለይም ባለፉት ሦስት ስርዓታት እንደታየው የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲውን የሚያስፈጽመው ተቋም አደረጃጀቱ የተረጋጋ አልነበረም። ይህ ሁኔታ ደግሞ በተቋሙ ውጤታማነት ላይ የነበረው ተጽዕኖስ እንዴት

ተገምግሟል? በበጀት በኩልም የሥነ-ሕዝብ ሥራዎች አብዛኛውን ጊዜ ከለጋሽ ድርጅቶች በሚገኝ የበጀት ድጋፍ እንደሚሠሩ ይታወቃል። ወደፊት በራሱ በጀት ለመሥራት የመንግሥት ቁርጠኝነት ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎችም በውይይቱ ተሳታፊዎች ተነስተዋል።

ከሐሳብ አቅራቢዎች የቀረቡ የማጠቃለያ ሐሳቦች፤

ፕሮፌሰር ንጋቱ በሕዝብ ቁጥር ዕድገት የሚመጣን የአገልግሎት ጫና ቴክኖሎጂን በመጠቀም መፍታት እንደሚቻል፣ ፍልሰትን በተመለከተም ኢትዮጵያ ውስጥ በሚገኙ በሁሉም ከተሞች ትኩረት አድርጎ በመሥራት በትልልቅ ከተሞች ያለውን ጫና መቀነስ እንደሚገባ፣ ከተሞችም ፍልሰት በሰዎች መካከል ያለውን የአመለካከትና የአኗኗር ልዩነት የሚያጠብ በመሆኑ ጠቀሜታ ያለው አዲስ ባህል ሊገነቡ እንደሚችሉም ጭምር ማሰብ እንደሚያስፈልግ ገልጸዋል።

ዶ/ር የሺጥላ በበኩላቸው የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ የብሔራዊ ደኅንነት ጉዳይ መሆን እንደሚገባው አንስተው ባህላዊ የሰላም ተቋማት መዳከምን በተመለከተም ዘመናዊው የሰላም ስርዓት ተመራጭ ቢሆንም በጥናት ላይ ተመሥርቶ ሁለቱንም የሰላም መንገዶች አጣጥሞ ከጊዜው ጋር በሚሄድ መንገድ መጠቀም እንደሚሻል ሐሳብ አቅርበዋል። ዶ/ር ፍጹምም “የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲው በ1985ዓ.ም አካባቢ የወጣ እንደመሆኑ መጠን ክፍተት እንደነበረው፣ ከአደረጃጀት ጋር የነበረው ችግርም የሥነ-ሕዝብ ፖሊሲያችን እና ሥራዎች ዋነኛ ክፍተት መሆናቸው በመታወቁ ትኩረት ያገኘ ጉዳይ ነው፤ በመሆኑም የተለያዩ ጥናቶችን በማካሄድ አዲስ የፖሊሲ ረቂቅ እየተዘጋጀ ነው” ሲሉ አስተያየት ሰጥተዋል። በአሥር ዓመቱ ዕቅድ ከተለዩት ስድስት የትኩረት ነጥቦችም አንደኛው የሥነ-ሕዝብን ትሩፋት መጠቀምን ይሸፍናል። ተቋማዊ አደረጃጀቱን በሚመለከትም የሥነ-ሕዝብ ጉዳይ በብዙ ተቋማት የሚከወን ነበር፤ አሁን ግን በራሱ በተቋሙ እንዲወጣ ከማድረግ ይልቅ በአመራር ቁርጠኝነት እና በፖሊሲ ግልጽነት ላይ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሠራ እንደሚገኝ አስረድተዋል።

በመጨረሻም የሥነ-ሕዝብን ጉዳይ የሀገር ዐቅም ለማድረግ ትኩረት የተሰጠው በመሆኑ በአሥር ዓመቱ ዕቅድ ተገቢው ቦታ ተሰጥቶት እየተሠራ እንደሆነና በፖሊሲ ደረጃም ብዙ ለውጦች እየመጡ መሆኑን ዶ/ር ፍጹም ገልጸዋል። ለምሳሌ ያህልም በጤና ዘርፍ ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች ከፍተኛ የሞት ምንጭ እየሆኑ ከመምጣታቸው አንጻር ከመከላከል ወደ ማከም የትኩረት ለውጥ መኖሩን፣ በፋይናንስ ረገድም

የግሉን ዘርፍ በጤና ሥራዎች ላይ ተሳትፎውን ለማሳደግ እንደሚሠራ አሳስበው ውይይቱን አጠቃለውታል።









## 5.2 አዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፤ የመደመር ትውልድን መቅረጽ፤

ሚያዚያ 2015 ዓ.ም




ይህ የአዲስ ወግ ፕሮግራም ጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ ወደ ሥልጣን ከመጡ በኋላ «የመደመር ትውልድ» በሚል ርዕስ ባሳተሙት ሦስተኛ መጽሐፋቸው ላይ ባነሷቸው ሐሳቦች ዙሪያ የተካሄደ ውይይት ነው፡ ፡ መጽሐፉ የዘመናዊት ኢትዮጵያን ትውልዶች በአምስት ከፍሎ ተመልክቶታል። የመጨረሻውን አምስተኛውን ክፍል ትውልድ ደግሞ «የመደመር ትውልድ» የሚል ርእስ ሰጥቶ በትኩረት ይተነትነዋል። መጽሐፉ የትውልዱን ባህርይ፣ መለያውን እና ስሪቱን ይዳስሳል። በተጨማሪም የወደፊቷን የበለፀገች ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ይህ የመደመር ትውልድ ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንደሚኖረው ያስረዳል።

በትውልድ ቀረጻ ላይ አስተዋጽዖ የሚያደርጉ ብዙ አካላት እንዳሉ ይታወቃል። ከእነዚህ መካከል የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ከለያቸው ውስጥ < <የትምህርት ፖሊሲ፣ የትምህርት ተቋማት፣ ማኅበረሰብ እና ቤተሰብ ምን አይነት ሚና ይኖራቸዋል? > > በሚለው ላይ ያተኮረ የአዲስ ወግ ውይይት ነው።

ውይይቱን የመራው የፋና ብርድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋዜጠኛ የሆነው አላዛር ታደሰ ሲሆን የውይይቱ ሐሳብ አቅራቢዎች የትምህርት ሚኒስትር ፕሮፌሰር ብርሃኑ ነጋ፣ የለባዊ ዓለምአቀፍ አካዳሚ ሥራ አስኪያጅ ፕሮፌሰር ፓኖስ ሃዘንድሪያስ፣ የ12ኛ

ክፍል ተማሪ የሆነችው ተማሪ በአምላክሥራ ፋሲል እና የሥነ-ልቡና ባለሙያዋ ሰብለ ኃይሉ ናቸው።

ሀገር የምትሠራው በትውልድ ነው፤ በሀገር ደረጃ በተቀራረበ የዕድሜ ደረጃ ላይ የሚገኙ፣ በተመሳሳይ የታሪክ አጋጣሚዎች ውስጥ ያለፉ፣ በዘመን እሳቤ ማህቀፍ ውስጥ የተቀረጹ እና ተመሳሳይ ጠባይ የሚያንጸባርቁ የየዘመኑ የኅብረተሰብ ክፍሎች ትውልድ ተብለው እንደሚታሰቡ የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ያስቀምጣል።
የውይይቱ የመጀመሪያው ሐሳብ አቅራቢ የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ ሲሆኑ በንግግራቸው <<የትውልድ ቀረጻን ጉዳይ ትኩረት ሰጥተነው ሀገርን ለማሳደግ ምን አይነት ባህርይ ያለው ትውልድ ያስፈልገናል በሚለው ላይ ተወያይተን አለማወቃችን እንደ ሀገር ጉዳት አለው>> ብለዋል። ምን አይነት ባህርይ እና ተግባር ያለው ትውልድ ቢኖር ነው ሀገራችን ልትሆን ያልቻለችበትን ጉዳይ አርሞና አስተካክሎ የተሻለች ሀገር የሚያደርጋት የሚለውን ጉዳይ መጠየቅ እንደሚገባም አነስተዋል። እንድትኖረን የምንፈልጋት ሀገር ሰላሟ የተጠበቀ፣ በኢኮኖሚ ራሷን የቻለች እና ቢቻል ለሌሎች አገሮች የምትተርፍ እንድትሆን ነው።

ሀገራችን የሚያስፈልጋት የተማረ፣ እውቀቱን ለኢትዮጵያ በሚሆን መልኩ መጠቀም የሚችል እና ሀገሩ ወደ ኋላ ስትቀር <<ለምን>> በሚል በእልህ ለሀገሩ የሚሠራ፣ በውይይት የሚያምን፣ ለሐሳብ ቦታ የሚሰጥ እንዲሁም ከኅብረተሰብ ጋር እንዴት በሰላም መኖር የሚችል ትውልድ መፍጠር እንደሚቻል አብራርተዋ። ይህን የመሰለ ትውልድ የመገንባት ኃላፊነት ደግሞ የቤተሰብና የማኅበረሰቡ፣ የሃይማኖት ተቋማት እና የትምህርት ቤቶች እንደሆነ ፕሮፌሰሩ አስረድተዋል።

ቤተሰብ እና ማኅበረሰብ ልጆች እንደማኅበረሰብ እንዴት በጋራ መኖር እንደሚችሉ ያስተምራሉ፤ የሃይማኖት ተቋማት ቤተሰብን እና ልጆችን እንዴት በባሕርይ በመቅረጽ እንደሚቻል ፕሮፌሰሩ ያሰርዳሉ። የትምህርት ተቋማት ለተማሪዎች የዕውቀት ፍላጎትንና የሥራ ባህልን፣ ከሌሎች የማኅበረሰቡ አካላት ጋር መሥራትን በንድፈ ሐሳብ እና በተግባር እንደሚያስትምሩ አስረድተው፤ ትውልድን የመቅረጽ ኃላፊት ግን የእነዚህ ሦስት ተቋማት ድርሻ ብቻ እንዳልሆነ እና ሌሎችም <<በጉዳዩ ያገባናል>> የሚሉ ተቋማት ሁሉ በጋራ ተሰናስለው የሚሠሩት እንደሆነ አስገንዝበዋል።

ፕሮፌሰር ፓኖስ ከለባዊ አካዳሚ ልምድ ተነስተው ሐሳባቸውን ሲያጋሩም የተለያዩ የትምህርት ፍልስፍናዎችን እና የኢትዮጵያን ትምህርት እንዳጠኑት፣ በመጨረሻም

የሰው ልጅ ክቡር ነው፤ <ንቃተ ኅሊና ወይም ለባዊነት አለው> የሚለውን የዘርያዓቆብን ሐሳብ በመውሰድ የሰው ልጅ ከፈጣሪ በታች ያለ ክቡር የሆነ ፍጡር እንደሆነ ወደ ትምህርት ቤት ሲመጣ ባዶ እንዳልሆነ፣ ከቤተሰብ እና ከማኅበረሰቡ ያገኘው የራሱ የሆነ ለባዊነት እንዳለው በመረዳት በውስጡ ያለውን ማንነት እና ተስጥኦ በትምህርት ማውጣትና መተግበር እንዲችል በማድረግ ምክንያታዊ የሆነ ሕይወት እንዲኖር ለማድረግ እንደሚሠሩ አንስተዋል።

የመደመር ትውልድ መጽሐፍ ደግሞ አዲስ የትውልድ ቀረጻ መንገድን እንደሚያሳይ፣ ይህም መሪነትን እና ክህሎትን በልጆቻችን ላይ ማሳደግ እንሚኖርብን የሚያስተምር መሆኑን አስረድተዋል። ዕውቀትን ከአካባቢያችን ያለውን ነገር በመረዳት የምናገኘው ነገር እንደሆነ ልጆችን ማስተማር እንደሚገባ፣ ዕውቀት ሁሌም ከውጭ የምናመጣው ነገር እንዳልሆነ ልጆች መረዳት የሚችሉበትን ልዩ ልዩ ክህሎቶችን እንዲሁም ሥነ-ምግባርን የሚማሩበትን የትምህርት ስርዓት መገንባት ለትውልድ ግንባታ እንደሚጠቅም አብራርተዋል።

<<ትውልዱን ለመቅረጽ እየተሠራበት ያለው ዓውድ ምን ይመስላል?>> በሚለው ላይ አተኩራ ሐሳብ ያካፈለችው የሥነ-ልቡና ባለሙያዋ ሰብለ ኃይሉ ናት።
ቀጣዩን ትውልድ ለመሥራት እነሱን የሚያሳድገውን የአሁኑን ትውልድ መመልከት እንደሚገባና የአሁኑ ትውልድ ደግሞ በማኅበራዊ ምስቅልቅል፣ ባለመተማመን እና በጦርነት ውስጥ አልፎ ቁስለት ላይ እንደሆነ ተረድተን ቅድሚያ ይህን ማኅበረሰብ በማከም ላይ መሥራት እንደሚገባ አሳስባለች። ልጆች ሰብእናቸው እና ሥነ-ምግባራቸው በቤተሰብ እና በማኅበረሰብ እንደመገንባቱ ቤተሰብ ምን መምሰል አለበት፣ ማኅበረሰብስ ለልጆች ምን ማስተማር አለበት የሚለው ሊታሰብበት እንደሚገባ፤ የእምነት ተቋማት እንደማኅበረሰብ የገባንበትን መቃቃር እና አለመተማመን ለማከም ምን ማድረግ እንዳለባቸው አስበው ሊሠሩበት እንደሚገባም ምክረ ሐሳብ አቅርባለች።

ሌላዋ ሐሳብ አቅራቢ ተማሪ በአምላክሥራ ፋሲል ስትሆን ትውልድን ለመቅረጽ ዓለማቀፋዊ ሁኔታዎች፣ ቴክኖሎጂ እና ፖለቲካዊ ሁኔታዎች ድርሻ እንዳላቸው አስረድታለች። የትምህርት ስርዓታችንም በውጭ አገሮች አስተሳሰብ ተጽዕኖ ውስጥ የወደቀ በመሆኑ ትውልዱ ሌብነትን፣ ማጭበርበርን እና የምን-አገባኝ መንፈስን እንዲያሳድግ እንዳደረገው አንስታለች። ለዚህም መፍትሔ በሚያመጣ መልኩ የትምህርት ስርዓቱ መቀየር እንዳለበት ሐሳቧን አጋርታለች። የትምህርት ስርዓቱ ደረቅ ዕውቀትን ከማስጨበጥ ባለፈ ተማሪዎች ውይይትን እና የሐሳብ ትግልን የሚማሩበትን

ስርዓት የሚፈጥር እንዲሆን፣ ትውልድ የሚቀርጹ መምህራንም ቅድሚያ ራሳቸው ተገቢ ዕውቀት እና ሥነ-ምግባር ሊኖራቸው እንደሚገባ አሳስባለች። በአንጻሩ መምህራን መብት እና ጥቅማቸው የተከበረላቸው ሊሆኑ እንደሚገባ በማስገንዘብ የንባብ ባህልን በማሳደግ ላይ በመሥራትም ትውልዱ ያለፈውን የሀገራችንን ስህተት በውል እንዲያውቅ እና እንዳይደግመው መድረግ እንዳለበት ሐሳቧን አካፍላለች።

ፕሮፌሰር ብርሀኑ በበኩላቸው መጪው ጊዜ ለትውልድ ቀረጻ ምን አዲስ ነገር እንዳለው ሲያስረዱ ባለፉት ጊዜያት ሀገራችን ኢትዮጵያን ስንመለከትበት በነበረው የተለያየ አስተሳሰብ እና ርዕዮተ ዓለማዊ ምልከታዎች ችግር አሁን ላይ በግልጽ እየታዩ መጥተዋል። የመጠራጠር እና የአለመተማመን መንፈስ ማኅበረሰቡ እንደተጠናወተው አንስተው ቀጣዩ ዘመን ልባችንን ከፍተን ነገሮችን በቀናነት የምንመለከትበት፣ ተፈጥሮን፣ ውበትን እንዲሁም የሰዎችን ባሕርይ የምናደንቀበትን መንገድም መልመድ ይገባል ብለዋል። ለዚህም ጠቅላይ ሚኒስትር ደ/ር ዐቢይ የጀመሯቸውን የማስዋብ ሥራዎች የሰውን ልጆች ከሚለውጡ ነገሮች መካከል አንዱ መሆኑን አስበን በየትምህርት ቤቶች ለመሞከር እየተሠራ እንደሚገኝ አንስተዋል፡ ፡ ለመጪው ትውልድም ዕውቀትን ብቻ ከማስተማር ወጥተን እውነት በሚፈለግበት መንገድ ላይ ሊሠራበት እንደሚገባ፣ በዋናነት ትውልዱ ነገሮችን ቀስ በቀስ በትዕግስት መቀየርን መማር እንዳለበት ተናግረዋል።

ተቀራራቢ ሐሳብ ያነሱት ፕሮፌሰር ፓኖስ በበኩላቸው ትውልዱን ለመቅረጽ ሆኖ በመገኘት ማስተማር፣ ፈጠራን የሚያበረታታ ስርዓት መኖር እንደሚገባው እና ተማሪዎች እንዲሆኑ የምንፈልገውን ነገር መዋቅራዊ በሆነ መልኩ ተግብረን በማሳየት ትውልዱን በዚያ መንገድ መቅረጽ አስፈላጊ ስለመሆኑ ሐሳብ አካፍለዋል።
ኢትዮጵያ ሰፊ ሀገር እንደሆነች እና ሀገሪቱ በገባችባቸው ችግሮች ውስጥ ያሉትን የመጭው ትውልድ አባለት ያገናዘበ ሥራ በመሥራት የትውልድ ቀረጻ ተግባሩ ሁሉንም አካታች ማድረግ እንደሚገባ ሐሳብ ያነሳቹው የሥነ-ልቡና ባለሙያዋ ሰብለ ኃይሉ ናት። ሰብለ አያይዛም ለልጆቻችን ነጭ እና ጥቁር ከሆነ አስተሳሰብ በተለየ መኻል ላይ የሆነ አስተሳሰብ መኖሩን ማሳወቅ እንደሚገባም አንስታለች።

ተማሪ በአምላክም አዲሱ ትውልድ ቴክኖሎጂው የፈጠረውን አጋጣሚ ተጠቅሞ ዓለምአቀፋዊ እሳቤውን ማሳደግ እንደሚገባው አሳስባለች።
ከተሳታፊዎች የተነሱ ሐሳቦች እና ጥያቄዎች፤
በአስተያየት ደረጃ ሀገራችን ካለችበት ሁኔታ አንጻር ይህን ጉዳይ የምናስብበት እና

የምንወያይበት ጊዜ ነው ብሎ ማሰብ ይከብዳል፤ ትውልዱን በመገንባት ሥራ ላይ ሀገሩን እንዲወድ የሚያደርጉ ሥራዎች መካተት ቢችሉ ጥሩ ነው። ትውልዱን ከተዘፈቀበት ሱስኛነት ለማዳን መጠነ ሰፊ ሥራ መሥራትም ያስፈልጋል። በትምህርት ስርዓታችንም ሆነ በሌላ መንገድ ትውልዱን ለመቅረጽ ስናስብ ሦስት መሠረታዊ ነገሮችን እንደ መርሕ አድርገን ማስተማር ይገባል። እነሱም፡- በየትኛውም ማኅበረሰብ ውስጥ የሚገኘው የሰው ልጅ አንድ እና ተመሳሳይ እንደሆኑ ማሳወቅ፣ ፍትሕን እና የጾታ እኩልነትን ለሁሉም በአግባቡ ማስተማር መሆናቸው ተነስቷል።

ከተሳታፊዎች ከተነሱ ጥያቄዎች መካካልም የትምህርት ስርዓቱ በጣም እየተዳከመ ነው፤ የትምህርት ሚኒስቴር ምን ምን ነገሮችን ሊሠራ አስቧል? የሥነ-ጥበብ ትምህርት የተማሪዎችን የማወቅ ችሎታ የሚያሳድግና የሚያሰፋ ስለሆነ እንደ ተጨማሪ ተግባር ሳይሆን የካሪኩለሙ አንድ አካል ሆኖ ልጆች ሊማሩት አይገባም? የሚሉት ይገኙበታል።
ከሐሳብ አቅራቢዎች ከተሰጡ ምላሾችም የትውልድ ቀረጻ ጉዳይን ለማንሳት እና ለመወያየት ሁሌም ጊዜው እንደሆነና ምንም እንኳን ዛሬ ሀገር ችግር ላይ ብትሆንም ሀገር መቀጠል ስላለባት መወያየቱ የግድ መሆኑ ተብራርቷል። ከባህል ጋር በተያያዘም ጠቃሚ ባህሎችን ከትምህርት ስርዓቱ ጋር እያይዘን ማስቀጠል ይገባናል የሚል ሐሳብ ተሰጥቷል።

በትምህርት ስርዓቱ ላይ ያሉ ክፍተቶችን በተመለከተ ለተነሱ ጥያቄዎች ፕሮፌሰር ብርሃኑ ምላሽ ሲሰጡ የትምህርት ስርዓቱ በአጠቃላይ የኅብረተሰቡ ችግር የተጠናወተው በመሆኑ ይህን ለማሳየት እና ትምህርት ለፍተሕ ዕውቀት የምታገኝበት መሆኑን ለማሳየት አዳዲስ የፈተና ስርዓቶች ተግባራዊ በመደረግ ላይ መሆናቸውን እና የትምህርት ስርዓቱ ከፍተኛ የመሠረተ ልማት ችግር እንዳለበት ታውቆ እየተሠራበት እንደሚገኝ አስረድተዋል።

አጠቃላይ ያለውን ችግር ለመለወጥ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው እየተሠሩ ካሉ ሥራዎች መካከል ፈተናን በማዘመን ስርቆትን የማስቀረት ሥራ በተማሪውም ሆነ በማኅበረሰቡ ላይ መሠረታዊ የአሳቤ ለውጥ እያመጣ ስለመሆኑ ተናግረዋል። <<የትምህርት መሠረተ ልማት ችግሩን ለመፍታት ሲባልም ከዚህ በኋላ የሚሠሩ ትምህርት ቤቶችን <አዲሶቹ የኢትዮጵያ ትምህርት ቤቶች> የሚል ዲዛይን እንዲሠራላቸው መደረጉን እና ኅብረተሰቡም ትምህርት ቤቶቹን በራሱ እንዲያድስ የሚያደርግ ሥራ እየተሠራ ነው>> ብለዋል። ርዕሳነ- መምህራንን በተለየ መልኩ ሥልጠና እንዲያገኙ እና

ዘላቂ የማሠልጠኛ ተቋምም በመገንባት ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማትን ነጻ ሐሳብ አፍላቂዎች እንዲሆኑ ለማስቻል የራስ ገዝ ተቋማት መሆን በሚያስችላቸው ሂደት ላይ እየተሠራ መሆኑና የመጪዋን ኢትዮጵያ መሪዎች እና ሳይንቲስቶች ለመፍጠርም ከፍተኛ ውጤት ያላቸው የሀገሪቱ ተማሪዎች በፌደራል ደረጃ ተሰባስበው የሚማሩባቸውን አዳሪ ትምህርት ቤቶች ለማስጀመር እየተሠራ እንደሆነ ፕሮፌሰር ብርሀኑ አስረድተዋል።

በማጠቃለያቸውም ፕሮፌሰር ብርሀኑ ዛሬ ችግር ብቻ ስላለ ስለዛሬ ችግር ብቻ መነጋገር እንደማይጠበቅብን፣ ኢትዮጵያ 120 ሚሊዮን ሕዝብ ያላት ሀገር እንደመሆኗ መጠን ስለነገዋ ኢትዮጵያ በየትኛውም ጊዜ መነጋገር አስፈላጊ መሆኑን አሳስበው፣ ይህን መሰል ውይይትም በስፋት መቀጠል እንደሚገባ ሐሳባቸውን አጋርተው ውይይቱ ተጠናቋል።









## 5.3 አዲስ ወግ አንድ ጉዳይ፤ “የክረምት ትጋት የዓመት ልማት”

ነሐሴ 13፣ 2015 ዓ.ም




የዛሬው የአዲስ ወግ አንድ ጉዳይ ፕሮግራም ትኩረቱን የሚያደርገው ባለፉት ዓመታት  በክረምት ወቅት በሀገራችን ተግባራዊ እየተደረገ ባለው የክረምት የበጎፈቃድ ሥራዎች ላይ ነው። በዚህ በበጎ ፈቃድ አገልግሎት እየተከወኑ ካሉት ሥራዎች መካካል የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር፣ የደም ልገሳ፣ የአረጋውያን እና የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት፣ የትራፊክ እና የመንገድ ደኅንነት ማጠናከሪያ ትምህርቶች እንዲሁም የወሠን ተሻጋሪ  በጎ ፈቃድ አገልግሎት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡ ፡ በእነዚህ በጎ ፈቃድ ሥራዎችም ግለሰቦች፣ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና መንግስታዊ ተቋማት በጉልበት፣ በጊዜ እና በገንዘብ የሚተመን ከፍተኛ ተሳትፎ ያደርጋሉ። በአሁኑ ጊዜም እነዚህ ተግባራት የትውልዱ  የማህበራዊ ኃላፊነትን መወጫ መንገዶች እየሆኑ ይገኛሉ።

የዛሬው የአዲስ ወግ ውይይት ፕሮግራምም የክረምቱን ሥራ ከግብ ጋር በማስተሳሰር

የሀገራችንን የኢኮኖሚ ችግር በማሸነፍ፣ ተሞክሮዎችን ለማጋራት እና ሥራውን በማስፋት ዓላማ ላይ ትኩረት ያደረገ ነው።
በውይይቱ በሐሳብ አቅራቢነት የተሳተፉት ዓለምፀሐይ ጳውሎስ የጠቅላይ ሚኒስትር ጽ/ቤት ኃላፊ እና የካቢኔ ጉዳዮች ሚኒስትር፣ ዶ/ር አደፍርስ ወርቁ የአረንጓዴ አሻራ የቴክኒክ ኮሚቴ አስተባባሪ፣ አቶ ጀማል አህመድ የሚድሮክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና አቶ ሰለሞን ክቤ የደጃዝማች ወንድይራድ መጀመሪያ ደረጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር ናቸው። ውይይቱን የመራችው ደግሞ የኢ.ቢ.ሲ ጋዜጠኛዋ መቅደስ ጥላሁን ናት።

የውይይቱ የመጀመሪያው ሐሳብ አቅራቢ የነበሩት ዓለምፀሐይ ጳውሎስ ሲሆኑ <<በክረምቱ የበጎፈቃድ ሥራዎች ለዓመቱ ትጋት ያስቀመጡት መሠረት ምንድን ነው?>> በሚለው መሠረታዊ ጉዳይ ዙሪያ ሐሳባቸውን አካፍለዋል። የክረምት የበጎፈቃድ ተግባራት በፓኬጅ የሚከወኑ እንደሆነና ዋና ዋናዎቹ ተግባራትም ወጣቶችን በበጎፈቃድ ሥራ ላይ እንዲሰማሩ በማድረግ ከ20 ሚሊዮን በላይ ወጣተቶች በአካባቢ ጽዳት (በከተማ ውበት እና ጽዳት)፣ በትምህርት፣ በሰላም እና ሰብእና ግንባታ ላይ እንዲሳተፉ ተደርጓል፤ በተጨማሪም ከ53 ሺህ በላይ ወጣቶች በሰላም ግንባታ ዙሪያ ስልጠናዎችን አግኝተዋል።
የአቅመ ደካሞች ቤት እድሳት ፕሮግራምም በሀገር አቀፍ ደረጃ በግለሰቦች፣ በግል ድርጅቶች እና በመንግሥት ተቋማት አማካኝነት ባላፉት አራት ዓመታት ከ160 ሺህ በላይ ቤቶች፣ በዚህኛው ክረምት ደግሞ ከ70 ሺህ በላይ የአቅመ ደካሞችን ቤቶች ማደስ ተችሏል።

ሌላው ዓለምፀሐይ ጳውሎስ ያነሱት የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብርን ነው፤ በዚህም ባለፉት አራት ዓመታት 20 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ታቅዶ 25 ቢሊዮን ችግኝ መትከል እንደተቻለ ገልጸዋል። በዚህኛው ዓመትም 6.8 ቢሊዮን ችግኝ መተከሉን እና በተለይ ሁሉንም ኢትዮጵያዊ በማሳተፍ በአንድ ጀምበር 566 ሚሊዮን ችግኞችን መትከል መቻሉ በዓለማቀፍ ደረጃ ከፍተኛ እውቅናን ለሀገራችን ያስገኘ ተግባር መሆኑን አንስተው፣ የምግብነት ይዘት ያላቸው ችግኞችም በብዛት እየተተከሉ መሆናቸውን፤ ይህም የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የሚደረገው አንዱ ጥረት ማሳያ መሆኑን አስረድተዋል። በተጨማሪም በ2015ዓ.ም የመኸር ወቅት 16 ሚሊዮን ሄክታር መሬት መታረሱን እና ከዚህ ውስጥ 13.9 ሚሊዮን ሄክታር ያህሉ በዘር እንደተሸፈነ አብራርተዋል።

በትምህርት ለትውልድ ንቅናቄም ከ50 ሺህ በላይ ትምህርት ቤቶችን በበጎፈቃደኞች ለማደስ እና ለማሻሻል ታቅዶ በ26 ሺህ ትምህርት ቤቶች ላይ ንቅናቄውን ማስጀምር ተችሏል ብለዋል። ለዚህ ተግባር ከ1.4 ቢሊዮን ብር በላይ ገንዘብ ቃል እንደተገባ ከዚህ ውስጥም 833 ሚሊዮን ያክሉን ብር መሰብሰብ መቻሉን ገልጸዋል።
በጤና ዘርፉ በኩልም በደም ልገሳ 51 ሺህ ዩኒት ደም መሰብሰብ እንደተቻለ እና የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የጤና አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ መቻሉን አሳውቀዋል፤ በከተሞች በሌማት ትሩፋት ሥራዎች የእንስሳት ውጤቶችን፣ ዶሮ፣ የጓሮ አትክልትን እና የመሳሰሉትን ማምረት መቻሉን፤ ይህም በከተሞች የሚስተዋለውን የገበያ ዋጋ ንረት ለመከላከል እያገዘ እንደሚገኝ አብራርተዋል። በአጠቃላይ በክረምት የተሠሩት የበጎፈቃድ ሥራዎች በተለያየ ሙያ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የኅብረሰብ ክፍሎችን እንደሙያቸው ያሳተፈና ሁሉም አሻራውን ያሳረፈባቸው እንደሆኑ በማንሳት ተግባራቱም ተጠናክረው የሚቀጥሉ መሆናቸውን አስምረውበታል።

ተሞክሮን ከማስፋት አኳያም የአረንጓዴ አሻራን ልምድ በጎረቤት አገሮች ለማስፋት ሙከራዎች መደረጋቸውን እና የማስፋቱ ሥራም በጎረቤት አገሮች ተቀባይነትን አግኝቶ የችግኝ ተከላው ሥራ ጅምር መኖሩን አንስተዋል። ይህ ተግባርም የቀጠናውን የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የሚደረገውን ጥረት የሚያግዝ ተግባር ሆኖ እንደሚታይ አቅርበዋል። የክረምት በጎፈቃድ ሥራው መተባበር፣ መደጋገፍ፣ ወንድማማችነት እና እህትማማችነት በግልጽ የተስተዋለበት ሲሆን ለቀጣዩ የሀገራችን ብልጽግና መሠረት የተጣለበት እንደነበርም ዓለምፀሐይ ጳውሎስ አብራርተዋል።

ዶ/ር አደፍርስ ወርቁም አረንጓዴ አሻራ ለዘላቂ ልማት በሚኖረው አበርክቶ ዙሪያ ሐሳባቸውን አካፍለዋል። በንግግራቸውም በሀገራችን ከሕዝብ ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ በተፈጥሮ ሐብታችን ላይ ከፍተኛ ጉዳት እየደረሰ እንደሚገኝ፣ የኢትዮጵያ ግማሽ ያህሉ መሬትም በተለያየ ዓይነት ችግር ጉዳት እንደደረሰበት በጥናት መረጋገጡን ጠቅሰዋል። በጥናቱ መሠረትም በዓመት ከ92 ሺህ ሄክታር በላይ ደን እንደሚጨፈጨፍ፣ በመሬት መሸርሸር ምክንያት ሀገራችን በዓመት 4.3 ቢሊዮን ዶላር እንደምታጣ እና በተቃራኒው በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ የደን ምርቶችን በየዓመቱ ከውጭ እንደምትገዛ ገልጸዋል።

የደን ሽፋናችንም ከ20 በመቶ ያነሰ እንደሆነና ይህም ከዓለም በአማካይ 31 በመቶ ያንሳል ብለዋል። ይህ ሁሉ ችግር ተደማምሮ ሀገራችን ለአየር ንብረት ለውጥ በመጋለጥ ላይ እንደምትገኝ፣ በዚህ ምክንያት በተደጋጋሚ በድርቅ እየተመታች እንደምትገኝ

አንስተዋል። ለዚህ መሠረታዊ ችግር መፍትሔ እንዲሆን ታስቦ የተጀመረው የአረንጓዴ አሻራ መርሐግብር ሥራ ያለፉትን ዐራት ዓመታት ጨምሮ በቀጣዮቹ ተመሳሳይ ዓመታት፣ በአጠቃላይ 50 ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል መታቀዱን፣ ይህም በአየር ንብረት ለውጥ ላይ በጎ ተጽዕኖ በመፍጠር የሚገኘው ውጤት የሀገራችንን ዘላቂ ልማት የሚያፋጥን እንደሆነ አስረድተዋል።
በጎፈቃደኝነት በግሉ ዘርፍ እንዴት ባህል ሊሆን እንደሚገባ ሐሳባቸውን ያጋሩት ደግሞ የሚድሮክ ኢትዮጵያ ዋና ሥራ አስፈጻሚ የሆኑት አቶ ጀማል አህመድ ናቸው። አቶ ጀማል በንግግራቸው <<መንግሥት የሚሰበስበው ገቢ በሀገራችን የሚያስፈልገውን የልማት ሥራ ሁሉ መሥራት ስለማይችል የግሉ ዘርፍም ከሚያገኘው ገቢ የተወሰነውን እየቀነሰ ሀገርን ለማነጽ ማዋል አስፈላጊ ነገር ነው>> ብለዋል። በተለይም አንድ ግለሰብም ሆነ ድርጅት ድህነት በሰፊው በተንሠራፋበት ሀገር ውስጥ ብቻውን ለማደግ የሚያደርገው ጥረት ዋጋ እንደሌለው፣ የሚበላው እና የሚጠጣው የሌለውን ሕዝብ ይዞ አደግሁ ማለት ስለማይቻልም ካለው ማካፈል ግዴታው መሆኑን መገንዘብ እንደሚገባው አስረድተዋል።

ከአረንጓዴ አሻራ ሥራ አኳያም ድርጅቱ የእርሻ ሥራ በሚሠራባቸው በሀገሪቱ የተለያዩ ክልሎች ሲዘዋወሩ የአፈር ለምነት ከቀን ወደ ቀን እየቀነሰ መምጣቱን መታዘባቸውን አንስተው ይህን ችግር ለመከላከል የአረንጓዴ አሻራ ሥራዎች የግድ አስፈላጊ መሆናቸውን ገልጸዋል።
በተቋማቸው በኩል ከዓመታዊ ገቢያቸው እስከ 11 በመቶ ያህሉን ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን ለመወጣት እንደሚያውሉ ያሳወቁት ዋና ሥራ አስፈጻሚው የግል ባለሐብቱ ይህን ማድረግ የሚገባው ያገኘው እንዲበረክትለት እና የኅሊና ሰላም እንዲያገኝ እንደሚያደርገውም አስረድተዋል። በመጨረሻም ይህን መሰል በጎ ተግባራትን የሚሠሩ ድርጅቶችን ለማበረታትት ወጥ የሆነ አሠራር መኖር እንዳለበት፣ ለዚህም ወጥ የሆነ እውቅና የሚሰጥበት ስርዓት መዘርጋትና በዚህ መልክ ተሳታፊ የሆኑ ድርጅቶችም ያወጡት ወጪ እንደ ወጪ የሚያዝላቸውን ሁኔታ መፍጠር እንደሚገባ አሳስበዋል።

በሌማት ትሩፋት ዙሪያ ያላቸውን ልምድ ያካፈሉት ሌላው ሐሳብ አቅራቢ የወንድያራድ አንደኛ አደጃ ት/ቤት ርዕሰ መምህር አቶ ሰለሞን ክቤ ናቸው። የሌማት ትሩፋት ሥራዎች በትምህርት ቤታቸው ውስጥ ውጤት እዲያስመዘግቡ ያስቻላቸው መጀመሪያ ላይ ግልጽ ፖሊሲ አዘጋጅተው በግቢያቸው በሚገኝ 21 ሺህ ካሬ ሜትር መሬት ላይ ወደ ተግባር መግባት መቻላቸው እንደሆን አስረድተዋል። በግብርና ሥራዎች ላይ

ተማሪዎች እንዲሳተፉ መደረጉንና ተማሪዎች ሥራውን በቤታቸው ሳይቀር ተግባራዊ እንዲያደርጉት ማስቻላቸውን ተናግረዋል።
በተሠራው ሥራም 200 ተማሪዎች የከተማ ግብርናን በግቢያቸው መሥራት መቻላቸውን፣ ለትምህርት ቤት የምገባ ስርዓቱ ግብዓት የሚሆኑ ምርቶችንም ማምረት እንደቻሉ አንስተዋል። የጤና ችግር ላለባቸው ተማሪዎችም በሌማት ትሩፋት ሥራ በግቢው ከሚገኙ የወተት ላሞች እና ዶሮዎች ወተት እና እንቁላል ማቅረብ ችለዋል፡ ፡ ከህብረተሰቡ ጋር ጥሩ ትስስር በመፍጠርም ለ21 ወላጆች በከተማ ግብርና የሥራ ዕድል እንዲፈጠርላቸው ተደርጓል።

ትምህርት ቤታቸው በዚህ የከተማ ግብርና ሥራ ከሚያገኘው ገቢ 10 በመቶ ያህሉን አቅመ ደካሞችን ለመርዳት አውሎታል፤ ትምህርት ቤቱ ተማሪዎች ከቀለም ትምህርታቸው በተጨማሪ የሥራ ክህሎትን እና ባህልን የሚያዳብሩበት አጋጣሚ መሆኑንም አስረድተዋል። የሌማት ትሩፋት ሥራውን በአግባቡ መከወን በመቻላቸውም የተባበሩት መንግሥታት የአካባቢ ጥበቃ ድርጅት /UN Habitat/ ዕውቅና እንደሰጣቸው እና ለተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎችም ልምዳቸውን እያጋሩ እንደሚገኙ አቶ ሰለሞን ገልጸዋል።

ከተሳታፊዎች የተነሱ አስተያየቶች እና ጥያቄዎች፤

በውይይቱ ሐሳብ ከሰጡ ተሳታፊዎች መካከል አንዱ ዶ/ር ይተብቱ ሞገስ ናቸው። በአስተየታቸውም ሀገራችን በዓመት ለማብሰያ እና ለግንባታ አግልግሎት 70 ሚሊዮን ቶን የደን ውጤት እንደሚያስፈልጋት አንስተዋል። ይህን ጥሬ ሐብት ለማሟላት በግምሽ ቢሊዮን ዶላር ከውጭ ለግንባታ ተግባር ብቻ ሊውሉ የሚችሉ የደን ውጤቶች እንዲገቡ ይደረጋል። ይህን የውጪ ምንዛሪ አስቀርቶ በሀገራችን ምርት ለመተካት የአረንጓዴ አሻራ ሥራ ወርቃማ ጅምር እንደሆነ አንስተዋል።
ተግባሩን የበለጠ ውጤታማ ለማድረግም በተደራጀ መልኩ ውጤትን ታሳቢ ባደረገ መንገድ መሥራት እንደሚገባ፣ ‹ይህን ያህል ቢሊዮን ችግኝ› እያሉ ከማቀድ እና ከመትከል ይልቅ ‹በሄክታር ይህን ያህል መሬት በደን ተሸፈነ› በሚለው ላይ ማተኮር የሚሻል ስለመሆኑ ሐሳባቸውን አካፍለዋል። የደን መመናመን የሚያሳጣው ለም አፈርን ብቻ ሳይሆን በውድ የተገዛ ማዳበሪያም በውኃ ታጥቦ እንዲሄድ እንደሚያደርግ ዶ/ር ማንደፍሮ ንጉሴ አንስተው፣ ችግሩን ለመከላከል የግድ የደን ሥራው መጠናከር እንዳለበት እና የበጎ ፈቃድ ሥራዎች በመስኖ ሥራዎች ላይም ቢያተኩር ጥሩ እንደሚሆን አሳስበዋል።

ዶ/ር ደምስ ጫንያለው በበኩላቸው <<ግብርናን ለማዘመን ካፒታል የሚያስፈልገው ሥራ እንደመሆኑ መጠን ባንኮች በዘርፉ የገንዘብ አቅርቦት ላይ ትኩረት ሊሰጡት ይገባል>> ሐሳብ ሰጥተዋል።

በበጎ ፈቃድ ሥራዎች ላይ የወጣቱ ተሳትፎ እያደገ እንደመጣ ያሳወቁት የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዶኤታ ሙና አህመድ ሲሆኑ በተግባሩ ዙሪያ ወጥ አሠራር ቢኖር የተሻለ ሊሆን እንደሚችል ለተነሳው ሐሳብ የተዘጋጀ የብሔራዊ በጎፈቃድ ፖሊሲ መኖሩን አንስተው ወደፊት ፖሊሲው ሲጸድቅ የተነሱት ሐሳቦች መልስ ሊያገኙ እንደሚችሉ ገልጸዋል።

አቶ አብርሃም ታደሰ (ከአዲስ አበባ አስተዳደር) ደግሞ በአዲስ አበባ በ17 የምገባ ማዕከላት በየቀኑ እስከ 30 ሺህ ዜጎች በቀን አንዴ እንዲመገቡ ያስቻሉ ተቋማት በግሉ ዘርፍ ተሳትፎ እያደረጉ እንደሚገኙ እና የበጎፈቃድ ሥራውም ውጤት እያሳየ እንደሆነ አስረድተዋል። በተጨማሪም በውይይቱ የቤት እድሳት ተጠቃሚ የሆኑ፣ በከተማ ግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ የውይይቱ ተሳታፊዎችም የበጎፈቃድ ሥራዎች ብዙ ነገር እየቀየሩ እንዳሉ ሐሳባቸውን አካፍለዋል።

ከበላይነህ ክንዴ ግሩፕ የመጡ የውይይቱ ተሳታፊም በበጎፈቃድ ሥራው ላይ ወጥ ያልሆነ የአሠራር ችግር ስላለ መፍትሔ እንዲሰጠው፣ ባለሐብቱን የማቀናጀት ክፍተትም እንዲታረም እና ባለሐብቱን ከተለያየ ጫና ለመከላከል እንዲቻል የተለየ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸው ወሳኝ ሥራዎች ተለይተው እንዲሳተፉ የሚደረጉበት መንገድ ሊፈጠር ቢችል ጥሩ እንደሚሆን አስተያየታቸውን አቅርበዋል።

በመጨረሻም ዓለምፀሐይ ጳውሎስ ማጠቃለያቸውን ሲያቀርቡ፣ በጎነት የመደመር እሳቤ መገለጫ እንደሆነና የጎደለውን መሙላትም ከበጎነት የሚመነጭ መሆኑን፤ የአረንጓዴ አሻራ ሥራ የኢትዮጵያዊያንን ጽናት በትክክል ማሳየቱን ተናግረዋል። በበጎፈቃድ ሥራዎች ዙሪያ ወጥ የሆነ የአሠራር ማህቀፍ እንዲኖር የተነሱ ሐሳቦች ተገቢ በመሆናቸው እንደሚስተካከሉ፣ ከብድር አቅርቦት ጋር በተያያዘም ለግሉ ዘርፍ በሚቀርበው የብድር መጠን ላይ ማሻሻያ መደረጉን፣ ይህ ሁኔታም ሁሉንም ዘርፍ ግብርናውንም ሳይቀር ተጠቃሚ እንደሚያደርግ ገልጸዋል። የሌማት ትሩፋት ሥራም በግለሰብ ደረጃ ብዙ ለውጦችን የሚያሳይ ሥራ በመሆኑ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚኖርበት አሳስበዋል።

ዶ/ር አደፍርስ በበኩላቸው አረንጓዴ አሻራ የደን ሥራን የሁሉም ዜጋ ተግባር እና አጀንዳ እንዲሆን ማድረጉን አንስተው ለውጥን ለማየት ረዘም ያለ ጊዜ የሚያስፈልግ

መሆኑን በአግባቡ አውቀን መሥራት ይገባናል ብለዋል፡፡ የአረንጓዴ አሻራ መርሐ-ግብርም ትልቅ ፕሮግራም እንደሆነ ተገንዝበን ዓለምአቀፍ ማኅበረሰብም ይህን ተግባር በሚያግዝበትና በሚረዳበት መንገድ ላይ ትኩረት ሰጥቶ መሥራት አስፈላጊ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ጀማል በበኩላቸው ሥራዎችን ከማስጀመር አልፈን የማስቀጠል ሥራ ስንሠራ ውጤታማ መሆን እንደምንችል በጠቅላይ ሚኒስትር ዶ/ር ዐቢይ አሕመድ እና በከንቲባ አዳነች አቤቤ የተሠሩ የበጎአድራጎትና የሌማት ትሩፋት ሥራዎችን በምሳሌነት አቅርበዋል፡፡

አቶ ሰለሞን ክቤም በከተማ ውስጥ ጥቅም ላይ ያልዋሉ ክፍት ቦታዎችን በትክክል በመለየት፣ ዶሮ በማርባት እና የጓሮ አትክልቶችን በማልማት የሌማት ሥራዎችን ማገዝ እንደሚቻል፣ በዚህም የኅብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻል ስለሚቻል በስፋት ሊሠራበት እንደሚገባ አሳስበው ውይይቱ ተጠናቋል፡፡






የክረምት ትጋት
የዓመት ልማት


አዲስ ወግ
ነሐሴ 13፣2015 ዓ